በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የ2003/2004 ኦዲት ዓመት
የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት

አጠቃላይ ዘገባ

ጥራዝ 2

ሚያዝያ 2004
አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ

ገጽ

1. መግቢያ 1
   1.1 የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር 2
   1.2 የሪፖርቱ ዓላማ 3
2. የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት እና የ2003/2004 ኦዲት ዓመትና የሌሎች ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም 4
   2.1 ሥራ ላይ የዋለው በጀት 4
   2.2 የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ 5
   2.3 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን 5
   2.4 የሪፎርም ሥራን በተመለከተ 7
   2.5 የኦዲት ምርምርና ስርፀት እቅድ አፈጻፀም 8
   2.6 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፤ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሳቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት 8
   2.7 የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ... 9
   2.8 አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት 10
   2.9 የመንግሥት ዕዳ አስተዳደር የመረጃ ስርአትን ቁጥጥርን በተመለከተ................... 16
   2.10 .... ሴክተር ዘለል የሆኑ ሥራዎችን በተመለከተ 28

ክፍል ሁለት

3 .የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የመፍትሔ ሐሣቦች 30
  1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ ኦዲት.. 30
     1.1.የጥሬ ገንዘብ ጉድለት 30
     1.2 የጥሬ ግንዘብና የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመት የታየባቸው መ/ቤቶች 30
  2. ውዝፍ ትስብጻብሕ ሂጻብ.. 32
     2.1 በየመ/ቤቶቹ የተገኘ ተሰብሳቢ ሂሣብ 32
     2.2 በተሰብሳቢ ሂሣብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች 33

3. የገቢ ሂሣብ 35
3.1 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ ሕጎች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ 35
3.2 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሳብ 37
3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻ 37
3.4 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ 38
3.5 በበጀት ዓመቱ ያልተሰበሰበ የወጪ መጋራት ሂሳብ 39
3.6 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ስለተገኘው ሂሳብ 39
3.7 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች 40
4. የወጪ ሂሣብ 45
4.1 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ 45
4.2 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ 45
4.3 ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች 46
4.4 የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዢዎች 47
4.5 በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸሙ ክፍያዎች 47
4.6 የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ 48
4.7 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት 48
4.8 አላግባብ በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ 49
4.9 በብልጫ የተከፈለ ወጪ 49
4.10 የወጪ የሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች 50
4.11 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ 50
4.12 .... ወ
ጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ 51
5 የተከፋይ ሂሣብ 51
5.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ 51
5.2 በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ የአሰራር ድክመቶች 53
6 የበጀት አጠቃቀም 55
6.1 ከበጀት በላይ የወጣ 55
6.2 ያልተሠራበት በጀት 55
6.3 ስለበጀት አጠቃቀም የታዩ ሌሎች ድክመቶች 56
7 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ 57

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች 57
7.2 በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች......... 58
7.3 ተሽከርካሪ 63
7.4 የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀምበተመለከተ 63
8 ልዩ ልዩ 64
8.1 የቅጥር ደንብን ተከትሎ ያልተፈጸመ የሠራተኞች ቅጥር...64
8.2 የቅጥር መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመ የውጭ አገር ዜጐች ቅጥር............................65
8.3 የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የክፍያ መመሪያ መሠረት ያልተፈጸሙ 67
8.4 በተመሳሳይ ፊርማዎች ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ 67
8.5 ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ..............................68
9 የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብ... 71
9.1 የ2003/4 ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶችና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች 71
9.2 በ2003/4 የኦዲት ዘመን የታዩ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች................. 72
9.3 በ2003/4 የኦዲት ዘመን በተከናወኑ ተከታታይ ኦዲቶች ላይ የተሰጡ የውስጥ ቁጥጥር ኦዲት አስተያየቶች 73
9.4 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ፕሮጀክት የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት 74
10 የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች 74
10.1. በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጭ አገር ስለሚሠሩ ኢትዮጵያውያን የሥራ ሥምሪትና ደህንነት አጠባበቅ እና ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ 74
10.2. በሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ሚ/ር የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ ተካትቶ ተግባራዊ መደረጉን እና በሥርዓተ ጾታዙሪያ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር ውጤታማ ስለመሆኑ 79
10.3. በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን የዱር እንሰሳትልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም.. 84
10.4. በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የመስኖ ልማት አፈጻጸም በተመለከተ 90
10.5. በፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር የአርብቶ አደር አካባቢ የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት 96
10.6. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገድ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም 101
10.7. ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የህንፃና የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ደረጃና ቁጥጥር 121

10.8. በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የመንገድ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ................ 127
10.9. በውሃና ኢነርጂ ሚ/ር በውጭ ድጋፍ/እርዳታ እና በፌዴራል ደረጃ በማስተባበር የሚሰሩ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች አፈፃፀም............ 136
10.10.የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ለህብረት ሥራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የተዘረጋው የአሰራር ስርዓት አፈፃፀምና ውጤታማነት................................ 140
10.11 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድን በተመለከተ....................... 146
10.12 በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች አጠባበቅ 150
10.13 በትምህርት ሚኒስቴር በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የውጤት ተኮር ስልጠና እና የቴክኖሎጂ ሽግግርና ክምችት ስርአት ውጤታማነት 154
10.14 በምግብ፣ በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን የምግብና፤መድኃኒትና የጤና ቁጥጥርና ውጤታማነት................................ 157
10.15 በብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት የብዝሀ ሕይወት ሀብት አጠባበቅ እና አጠቃቀም 161
10.16 በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር የጥናትና ምርምር ስራዎች እና ኢንደስትሪ ትስስር 165
10.17 በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገዶች አጠባበቅ እና ጥገና........................ 167
11 ሌሎች ሥራዎች 172
11.1 የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትን በተመለከተ 172
11.2 የመ/ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና ሥልጠና...173
11.3 ለክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የተሰጠ የስልጠና ድጋፍ 174
11.4 በኢንፎርሜሽን ሰርቪስ የተሠሩ ዋና ዋና ሥራዎች 174
11.5 የእቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ 175
11.6 የሰው ሀብት ሥራ አመራር 176
12 ያጋጠሙ ችግሮች..178
13 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች 178
14 ማጠቃለያ 178

ክፍል ሶስት

1. መግቢያ 180
2. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2003 በጀት ዓመት እንቅስቃሴ ሪፖርት 180
2.1 የኮርፖሬሽኑ ዓላማ 180
2.2 የኦዲት ሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት 181
2.3 የሥራ ዕቅድና ክንውን 181
2.4 የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል ሁኔታ 182
2.5 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ 182
2.6 የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ 183
3. በ2003 በጀት ዓመት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች የተሰጡ ኦዲት አስተያየት 184
4. የኦዲት ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች 184
4.1 አቋም ሊወሰድበት የማይቻል የኦዲት አስተያየት የቀረበባቸው 185
4.2 ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት የሰጠባቸው 196
5. ስለድርጅቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ 200
5.1 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ 200
5.2 በመጋዘን ያሉ እቃዎች 201
5.3 ተሰብሳቢ ሂሳብ 201
5.4 በባንክና በካዝና ያለ ገንዘብ 202
5.5 ተከፋይ ሂሳቦች 203
5.6 ስለሂሳብና የሰነድ አያያዝ 203
6. የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሄያቸው 204
6.1 የችግሮቹ ምክንያቶች 204
6.2 ችግሮቹን ለማቃለል ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች 204

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በ2003/2004 የኦዲት ዓመት የተከናወኑ ኦዲቶች ሪፖርት እና እቅድ አፈጻጸም

/ከጥር 1/2003 - ታህሣስ 30-2004/

I. መግቢያ

የዋናው ኦዲተር መ/ቤት ቀደምትነት ካላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች አንዱ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ሀገሪቱ ከምትመራበት የፌዴራል ቅርጸ መንግሥትና ታዳጊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጋር ለማጣጣም በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 55/1 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራሉን መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስና የክዋኔ ኦዲት፣ የአከባቢ ጥበቃ፣የቁጥጥር ኦዲቶች፣ልዩ ኦዲቶች እና ሌሎች ኦዲቶች ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሣብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሣብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ /ስታንደርድ/ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

1.1 የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፤
- የፌዴራሉ መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- ፌዴራል መንግሥት ከብር 1 ሚሊዮን በላይ የሚጠይቅ ሥራ የግል ሥራ ተቋራጮች እንዲሰሩ በውል የሰጠ እንደሆነ ይህንኑ መንግሥት ነክ የሆነ የግል ሥራ ተቋራጮች ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የኘሮግራምና የአሠራር ቅልጥፍና ምርመራ ወይም ክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- ለፌዴራል መንግሥቱ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፡፡ የፌዴራሉ መንግሥት የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣

- ለግል ኦዲተሮችና የሂሣብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ የሂሣብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመሰማራት የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሠርዛል፣
- የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስለመንግሥት በጀት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ የሚያቀርበውን ዓመታዊ የሂሣብ ሪፖርት መርምሮ ሃሣብ ይሰጣል፣ ስለሁኔታውም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያቀርበው ዘገባ አስተያየቱን ይገልጻል፣

የሚሉት ናቸው::

1.2 የሪፖርቱ ዓላማ

ሪፖርቱ መ/ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 በአንቀጽ 13/1 እና 2 መሠረት በ2003/2004 የኦዲት ዓመት በአከናወናቸው ኦዲቶች የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች፣ ምክር ቤቱ ለ2003 በጀት ዓመት የፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘቱን ለማረጋገጥና በሪፖርቱ በቀረበው መረጃ መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችለው፤ መ/ቤታችን በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ለመወጣት እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴና የ2003/2004 የኦዲት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ለማመልከት ነው::

በሪፖርቱ ውስጥ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ፤ የክዋኔ ኦዲትና የዓለም ባንክ እና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪዎች የሚሰጡትን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ ኦዲት ለማስደረግ መንግሥት በገባው ውል መሠረት በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የወረዳ ፋይናንስና የከተማ መስተዳድር ጽ/ቤቶችን ኦዲት በማድረግ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1984 የተቋቋሙ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በሌሎች የሙያው ፈቃድ በተሰጣቸው የተፈቀደላቸው የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርገው የተገኘውን ውጤት ነው::

የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲቱ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ከመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ጋር በሚደረግ የመውጫ ስብሰባ ላይ የተነሱ ሃሳቦችን ያካተተ፣ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊና ተቆጣጣሪ መ/ቤት የኦዲት ሥራው እንዳለቀ እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው

የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው:: ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጀዎች ፤ አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸውን የመንግሥት ሂሣብ አያያዝ ስርዓት እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች፣ እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው::

መ/ቤታችን ባለው የሰው ኃይልና በተመደበለት በጀት በ2003/2004 የኦዲት ዓመት ያከናወናቸው ሥራዎች በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል:: የመጀመሪያው ክፍል የ2003/2004 የኦዲት ዓመት የመ/ቤቱ ዕቅድና አፈፃፀም፤በሁለተኛው ክፍል የ2003 በጀትዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች፤መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሣቦች እና ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶችን የሚመለከት ይሆናል::

የመ/ቤቱን የኦዲት ሥራ በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት የልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት፤የአካባቢ እና የክዋኔ ኦዲትን እንዲሁም መንግስት ከአለም ባንክ እና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪዎች ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (ፕብስ) ለክልል መንግሥታት የተሰጠውን ሂሳብ ተከታታይ ኦዲት ያጠቃልላል::

2. የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት እና የ2003/2004 ኦዲት ዓመት የሌሎች ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም

2.1 ሥራ ላይ የዋለው በጀት

በ2003/2004 የኦዲት ዓመት የተፈጸሙ ሥራዎችን ለማከናወን የተመደበውና ሥራ ላይ የዋለውን በጀት በተመለከተ በመ/ቤቱ አዲስ አሠራር መሠረት የመ/ቤቱ የኦዲት ሥራ ዓመት ከታህሣስ 1 - ጥር 30 ቢሆንም፣ የ2003 በጀት ዓመት ስራ ላይ የዋለው እንደሚከተለው ቀርቧል::

የ2003 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም

የወጪ አርዕስት	የበጀት ኮድ	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	አጠቃቀም በፐርሰንት
ሰብዓዊ ለሆኑ አገልግሎቶች	6100	9,389,595.47	9,363,920.24	99%
ለአላቂ እቃዎችና አገልግሎቶች	6200	6,216,103.44	4,959,271.53	80%
ለቋሚ ንብረቶችና ግንባታ	6300	589,836.35	267,633.51	45%
ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች መዋጮ	6400	151,431.00	125,878.17	83%
ድምር		16,346,966.26	14,716,703.45	90%

2.2 የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ

ለመ/ቤቱ በተፈቀደው መዋቅር የተያዘው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 384 እና ለድጋፍ ሰጪ 226 በድምሩ 610 ሲሆን፤ በኦዲት ዓመቱ 30 የኦዲት ባለሙያዎችና 7 የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 37 ሰራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን፣ 2የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉና 30 ኦዲተሮችና 7 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ የለቀቁ፣ በድምሩ 39 ሠራተኞች መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የነበሩ የኦዲት ባለሙያዎች 153 ወንዶችና 83 ሴቶች በድምሩ 236፤ የድጋፍ ሰጪ 69 ወንዶችና 69 ሴቶች በድምሩ 138 ሠራተኞች ሲሆኑ፤ በአጠቃላይ 374 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን፤236 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡

2.3 የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን

መ/ቤቱ በአዲሱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ በአራት ዳይሬክቶሬቶች እና የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት በየሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፤ ከጥር1/2003 እስከ ታህሣስ 30/2004፤ የ130 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የመደበኛ ኦዲት ለማድረግ

በእቅድ በተያዛው መሠረት የ131 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ ይህም በዕቅዱ መሠረት በኦዲት በዓመቱ የተከናወነው ሥራ 103% ነው፡፡

የመሠታዊ የአገልግሎቶች ማስከበር ኘሮጀክት ተከታተይ ኦዲትን በተመለከተም ለወረዳዎች ከተሰጠው የድጋፍ ሂሣብ ውስጥ የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ በ248 ወረዳዎች ሂሣቡን ለማስተዳደር የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ብቃት ያለውና አጥጋቢ መሆን ወይም አለመሆኑን ኦዲት ለማድረግ የታቀደ ሲሆን፣በ2003/4 የኦዲት ዓመትየ262 ወረዳዎች ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ተልኳል፡፡ይህም ክንውን ከበጀት ዓመቱ እቅድ ጋር ሲነጻፀር 106% ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን 131 በሚሆኑ የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና በ262 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ በሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር የተሰጡት የኦዲት አስተያየት ከ2002 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ ቁ.	መግለጫ	በፌዴራል መንግሥት ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲት		አጠቃላይ	
		2002	2003	2002	2003	2002	2003
1	አጥጋቢ ሆነው በመኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው(Clean opinion)	49	57	4	6	53	63
2	ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion)	50	52	266	255	316	307
3	አቋም ለመውሰድ እንደማይቻልበመግለጽ አስተያየትየተሰጠባቸው	8	7	3	1	11	8

	(Disclaimer of Opinion)						
4	**የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው** (Adverse Opinion)	**14**	**13**	**3**	**-**	**17**	**13**
5	**ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለመዝጋታቸው አስተያየት ያልተሰጠባቸው**	**8**	**2**	**-**	**-**	**8**	**2**
	ድምር	**129**	**131**	**276**	**262**	**405**	**393**

2.4 <u>የሪፎርም ሥራን በተመለከተ</u>

በመ/ቤታችን የተካሄደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ተጠናቅቆ፣በሁሉም የዋናና ድጋፍ ሰጭ የሥራ ሂደቶች እየተተገበረ ሲሆን በተለያዩ ደረጃ ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡

የሪፎርሙ አካል የሆነው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናቱን ተከትሎ ለም/ቤቱ ቀርቦ የነበረው የመ/ቤታችን መዋቅርና የደመወዝ ስኬል የተፈቀደው ከመ/ቤታችን ልዩ ባህርይና ባለሙያዎቹ በገበያ ላይ ካላቸው ከፍተኛ ተፈላጊነት አንፃር ችግሩን የሚያቃልል ሆኖ ስላልተገኘ፣ እንደገና እንዲታይልን ባቀረብነው መሠረት፣በም/ቤቱ በኩል ለሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር ቀርቦ በባለሙያ ተጠንቶና በም/ቤቱ ጸድቆ በቀረበው መሰረት የሠራተኛ ምደባ ተከናውኗል፡፡ ቀሪ ክፍት መደቦችም በውስጥ ዕድገትና በቅጥር ለመሙላት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል፡፡

በመ/ቤታችን የውጤት ተኮር የምዘና ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ጥናቱ የተጀመረ ሲሆን በቅርቡ እንደሚጠናቀቅና ከ2005 በጀት ዓመት መጀመሪያ አንስቶ ተግባራዊ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

ከሪፎርሙ ተከትሎ የተተገበሩ አዳዲስ አሰራሮችን በመረጃ ቴክኖሎጂ ለማስደገፍ የተጀመረው ጥረት የመረጃ ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ግዥ ከመጠን በላይ በመዘግየቱ በዕቅዱ መሰረት በፍጥነት ሊተገበር አልቻለም፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት ሂደቱን ለማፋጠን ጥረት በመደረግ ላይ ነው፡፡

የሰው ሀብት ልማት ሥራውም የሰው ሀብት ልማት ስትራቴጂውን ተከትሎ በመከናወን ላይ ሲሆን ትልቁ ፈተና የሰው ሀብት ልማትና መደበኛ ሥራን ማጣጣምና አቅሙ የተገነባውን ሠራተኛ ማቆየት የመቻሉ ጉዳይ በመሆኑ ም/ቤቱ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

2.5 የኦዲት ምርምርና ስርፀት አቅድ አፈጻፀም

ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በ4 መ/ቤቶች የኦዲት ጥራት ማረጋገጫ ፍተሻ ማካሄድ፣ በየደረጃው ላሉ ኦዲተሮች የስልጠና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ የኦዲት ደረጃዎችና መመሪያዎች በአግባቡ በሥራ መተርጐማቸውን መከታተል፣ በኦዲት ሪፖርት የተሰጡ የማሻሻያ ሀሣቦች ምን ያህል ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑን ለመገምገም በእቅድ ይዟል፡፡

በዚህም መሠረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለኦዲቱ ሥራ የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ አዋጆች ደንቦችና መመሪያናዎች ለኦዲተሮቹ እንዲደርሱ አድርጓል፡፡ በ9 መ/ቤቶች የኦዲት ጥራት ሥራ ላይ ግምገማ ተደርጓል፡፡ የኦዲት ግኝቶችን መንስኤ ለመተንተን የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት በ4 መ/ቤቶች ላይ ጥናት ተካሂዷል፡፡ የክዋኔ ኦዲትንለማድረግ የሚቻልባቸውን የኦዲት አካባቢዎችን በመምረጥ ለማኔጅመንት በማቅረብ በመረጃ ሥርዓት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ የኦዲት የሥራ ወረቀቶች ለሥራው በሚያመች መልክ ተስተካክለው እንዲቀረፁ ተደርጓል፡፡ ለመ/ቤቱ ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች እና ከመ/ቤቱ ውጭ ለሆኑ ሠራተኞች በየጊዜው የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መሠረት በማድረግ የሙያ እገዛና ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ለውስጥ ኦዲተሮች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ደረጃዎች በሚሰጠው ኮሚቴ ውስጥ በአባልነት ተሣትፎ አድርጓል፡፡

2.6 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሳቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና በውጭ እርዳታ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ሂሣብ በሙሉ ኦዲት ለማድረግ የመ/ቤቱ አቅም ውሱን በመሆኑ ላለፉት ጊዜያት የነዚህ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ሂሣብ የኦዲት ሙያ ፈቃድ ከመ/ቤቱ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶችና በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እየተደረገ

በተገኙት የኦዲት ግኝቶች ላይ ኦዲት ተደራጊው ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ መ/ቤቱ ክትትል ከማድረጉም በላይ የግል ኦዲት ድርጅቶችም ሆኑ የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ተፈላጊውን የሙያ ሥነ ምግባር ሳያጓድሉ ሥራውን እንዲያከናውኑ በተወሰነ አቅም ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት በ2003 በጀት በዓመት በመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ የልማት ድርጅቶች 99፣ ፕሮጀክቶች እና የዕርዳታ ሂሳቦች በግል ኦዲት ድርጅቶች 146 ኦዲቶች በድምሩ 245 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ ሂሳብ ኦዲት የተደረገውን የቅርቡ እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር የተወሰደ ነው) የተለያዩ በጀት ዓመት ሂሣቦች የተከናወኑ ሲሆን፣ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑትን ኦዲቶች በተመለከተ በተለይም አቋም መውሰድ ያልተቻለበትና የጎላ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተቀባይነት የሚይሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው የልማት ድርጅቶችን ዋና ዋና ግኝቶች በዚሁ ጥራዝ በክፍል 3 ቀርቧል፡፡

2.7 <u>የክዋኔ ኦዲት በተመለከተ</u>

በመንግሥት የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መወጣታቸውን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ የክዋኔ ኦዲት ያከናውናል፡፡ ይህን ዓለማ ለማሳካት የክዋኔ ኦዲት የሥራ ክፍል ከየካቲት 2002 ጀምሮ በአዲስ አደረጃጀት በሁለት ዳይሬክቶሬቶች የተደራጀ ሲሆን በ2003-2004 የኦዲት ሥራ ዘመን (Audit Calendar) በሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች ከጥር 2003 በፊት ተጀምረው የዝርዝር ኦዲት ስራቸው ወደዚህኛው የኦዲት አመት የዞሩ 5 ኦዲቶች እና ከጥር 2003 በኋላ ተጀምረው እስከ ታህሣስ 30/2004 የሚጠናቀቁ 12፤ እንዲሁም ከሰኔ 2003 በኋላ ተጀምረው የዳሰሣ እና ቅኝት ሥራቸውን በማጠናቀቅ ወደሚቀጥለው የኦዲት ዓመት የሚዛሩ 5 ኦዲቶች በድምሩ 22 የክዋኔ ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ ተይዞ ነበር፡፡

በዚሁ መሠረት የእቅድ ዘመኑ የክዋኔ ኦዲት ኘሮጀክቶች አፈጻፀም ሲታይ ካለፈው ዓመት የዞሩትን 5 ኦዲቶች ጨምሮ በዚህ የእቅድ ዘመን ወጪ መደረግ ከሚገባቸው 17 ኦዲቶች ውስጥ የ17ቱ ሥራ ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው የተላከ ሲሆን፤ የ5 ኦዲቶች ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ተጀምረው ወደ ቀጣዩ ዓመት ተላልፏል፡፡

ይህም ከአጠቃላይ እቅድ አንጻር ሲታይ 100% በስኬት መጠናቀቁን ያሣያል፡፡

/የተጠናቀቁት ክዋኔ ኦዲቶች ግኝትና የማሻሻያ ሃሳቦች በዚሁ ጥራዝ ተራ ቁጥር 10 ላይ በዝርዝር ቀርቧል/

በዕቅዱ መሠረት ወደ 2004/2005 የኦዲት ዓመት የዞሩ የክዋኔ ኦዲቶች፤

1. በማሪታይም ጉዳዮች ባለስልጣን የገቢና ወጪ ዕቃዎች ትራንዚት አገልግሎት አሰጣጥ፤
2. በደቡብ ኢትዮጵያ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ማጥፊያ ፕሮጀክት የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ማጥፊያ ዕደት
3. በግብርና ሚ/ር የደን ሀብት ልማትና ጥበቃ
4. በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት
5. በንግድ ሚ/ር የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ናቸው፡፡

2.8 <u>አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት</u>

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቀን 17/05/2004 በተላከው የ2003 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

በዚሁ መሠረት የፌዴራል መንግስት የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2.8.1 <u>የገቢ ሂሣብ ያልተሰበሰበ የመልሶ ማበደር ሂሣብን በተመለከተ</u>

መንግስት ከውጭ ሀገር ተበድሮ በመልሶ ማበደር ስምምነት ለልማት ድርጅቶች መንግስት ያበደረውን ገንዘብ ተበዳሪዎች በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ተመላሽ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከ 9 ብድሮች /አምስት መ/ቤቶች/ በድምሩ ብር 100,920,131.52 እስከ ሰኔ 30, 2003 ዓ.ም ድረስ ያልተሰበሰበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ዝርዝሩም እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

የመ/ቤቱ ስም	ዋና ገንዘብ	ወለድ	ቅጣት	ጠቅላላ ድምር
የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	17,344,225.85	22,462,377.04	-	39,806,602.89
ኢትዮ- ጅቡቲ ምድር ባቡር	10,670,413.84	2,905,669.57	604,386.89	14,180,470.30
ወንጂ ስኳር ፋብሪካ	-	14,717,051.07	338,603.89	15,055,654.96
ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ	-	31,125,427.34	620,964.07	31,746,391.41
ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ	-	-	131,011.96	131,011.96
ጠቅላላ ድምር	28,014,639.69	71,210,525.02	1,694,966.81	100,920,131.52

በመሆኑም መንግስት ያወጣውን እቅድ ለማሳካት የሚያደርገውን ጥረት ገቢው በወቅቱ ባለመሰብሰቡ እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል ከላይ የተመለከተው ያልተሰበሰበ የመልሶ ማበደር ሂሳብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ ክትትል በማድረግ እና ገንዘቡ የሚሰበሰብበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

2.8.2 <u>የቀረጥ ተመላሽንና ለቀረጥ ተመላሽ በሂሳብ መደብ 6412 በጀት የሚያዝ መሆኑ</u>

በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በተለያየ ምክንያት(በዋጋ ወይም በታሪፍ አመዳደብ ወዘተ) በስህተት የተሰበሰበ ቀረጥ ግብር ከፋዩ በስህተት የከፈለ ለመሆኑ ሲታወቅና በኮሚቴ ሲረጋገጥ በስህተት የተከፈለው ቀረጥ ለግብር ከፋዩ ተመላሽ የሚደረግለት ሲሆን ተመላሽ የተደረገው የቀረጥ መጠን ግን በገቢ ሪፖርት ተመዝግቦ ለሚኒስቴሩ እየቀረበ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ይህንኑ ሂሳብ እያጠቃለለ ይገኛል፡፡ይህ አሰራር ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚያቀርበውን

የገቢ ሪፖርት ከፍ (overstated) የሚያደርገው በመሆኑ የተጠቃለለው የገቢ ሪፖርትም በዚያው መጠን ሚዛኑ ከፍ(overstated) እንዲል እየተደረገ ለመሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በ2003 በጀት አመት ለቀረጥ ተመላሽ ብር 109,622,001.95 የከፈሉ ቢሆንም የተመለሰው ቀረጥ ግን በገቢ ሪፖርት ላይ የተካተተ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪ ለቀረጥ ተመላሹ በጀት የሚያዘው በሂሳብ መደብ 6412 መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርአት ማንዋል /ግንቦት 1999/ መሰረት ደግሞ ሂሳብ መደብ 6412 ለተቋሞች እና ድርጅቶች ለሚደረግ ድጋፍና ድጎማ የሚመዘገብበት ሂሳብ መደብ መሆኑን ይገልጻል፡፡ነገር ግን በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በተለያየ ምክንያት በስህተት ለተሰበሰበ ቀረጥ ተመላሽ ለሚሆን ሂሳብ በጀት የሚያዘው በሂሳብ መደብ 6412 መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ይህም በስህተት የተሰበሰበ ሂሳብ ለባለቤቱ ተመላሽ ሲሆን ድጋፍና ድጎማ እንደተደረገለት የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ ሂሳብ መደብ የሚታየው ባላንስ ትክክለኛውን ሁኔታ አያሳይም፡፡

በመሆኑም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በጋራ በመሆን በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በበጀት አመቱ ውስጥ በስህተት ተሰብስቦ ነገር ግን ለግብር ከፋዩ ተመላሽ የሚደረግ ሂሳብ በበጀት አመቱ የገቢ ሪፖርት ውስጥ እንዳያካትቱ አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡

በተለያየ ምክንያት በስህተት ቀረጥ ከተሰበሰበ ለባለቤቱ ተመላሽ ለማድረግ በሂሳብ መደብ 6412 በጀት መያዙ ለተቋሞች እና ድርጅቶች ድጋፍና ድጎማ ሳይደረግ ድጋፍና ደጎማ እንደተደረገ የሚያሳይ በመሆኑ ለወደፊቱ ጉዳዩን ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመነጋገር ለቀረጥ ተመላሽ በጀት የሚያዝበት ሂሳብ መደብ ላይ አስፈላጊው ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.8.3 <u>የውጭ አገር ብድርን በተመለከተ</u>

በ2003 በጀት ዓመት ወደ አገር ውስጥ የገቡ የውጭ አገር ብድሮች በትክክልና ሙሉ ለሙሉ በሂሳብ መግለጫ ላይ መካተታቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት በ2003 በጀት አመት በመንግስት ሂሳብ አስተዳደር ሂሳብ መግለጫና በብድር አስተዳደር ምዝገባ መካከል የውጭ አገር ብድር ልዩነት ያለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::

ተጠቃሚው መ/ቤት	የሂሳብ መደብ	የገንዘቡ መጠን		ልዩነት በመብለጥ /በማነስ/	መግለጫ
		በመንግስት ሂሳብ	በዕዳ አስተዳደር		
የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን	3002	490,328,887.03	484,399,038.63	5,929,848.40	
የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን	3003	78,500,989.20	78,297,957.88	203,031.32	
GEQIP	3014	238,936,404.30	236,688,699.60	2,247,704.70	በቫውቸር ቀጥር 007 እና 1000 ተመዝግቦ የተገኘ.
ድምር		838,408,542.71	799,385,696.11	8,280,584.42	

በመሆኑም በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከተው የውጭ አገር ብድር ገቢ በብድር የሂሳብ መደቦች 3002፣ 3003፣ እና 3014 በዕዳ አስተዳደር ተመዝግቦ ከተያዘው በብር 8,280,584.42 የሚበልጥ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይህም የሂሣብ መግለጫው ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም የስህተት መንስኤው የምንዛሬ ለውጥ ነው ቢባልም ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላም ችግር ሊሆን ስለሚችል ከብድር አስተዳደርና ከሂሳብ አቅራቢ መስሪያ ቤት ጋር በመሆን ልዩነቱ ሊጣራ ይገባል፡፡

2.8.4 ከብድር አስተዳደር በተገኘ መረጃ ብቻ ገንዘቡ ለተጠቃሚው አካል እንደደረሰ በመቁጠር ተመዝግቦ የተገኘ የውጭ አገር ብድር

በ2003 በጀት ዓመት ከብድር ፋይናንስ የተገኘ ገንዘብ በዓመታዊ ገቢና ወጪ የሂሳብ መግለጫ ላይ መካተቱንና በበቂ መረጃ መደገፉን ለማረጋገጥ ኦዲት በሚደረግበት ወቅት ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል እና አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት በድጋፍ መልክ ከብድር ፋይናንስ ላገኙት ገንዘብ ከተጠቃሚ መስሪያ ቤቶቹ ገንዘቡ ለመድረሱ መረጃ ሳይኖር ከብድር አስተዳደር በተገኘ መረጃ ብቻ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የተጠቃሚው መ/ቤት ስም	የሂሳብ መደብ	የቫዉቸር ቁጥር	የገንዘቡ መጠን
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	3002	001	234,069,557.08
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	3003	001	19,495,519.04
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	3014	001	319,924,490.75
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	3022	001	13,757057.19
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	3289	001	18,592,107.61
የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት	3014	002	158,688,411.60
ጠቅላላ ድምር			764,527,143.27

ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤቶች የውጪ ምንዛሬው በባንክ አካውንታቸው በገባበት ቀን ባለው የመግዣ ዋጋ መሰረት መዝግበው ሪፖርት የሚያደርጉ ሲሆን በብድር አስተዳደር ግን የውጪ ምንዛሬው በእለቱ ባለው የመሸጫ ዋጋ መሰረት የሚመዘግብ ስለሆነ ከብድር አስተዳደር በተገኘ መረጃ ብቻ መመዝገቡ የሂሳብ አመዘጋገብ ስርአቱ ወጥነት (consistency) *እንዳይኖረው የሚያደርገው ከመሆኑም በላይ ተጠቃሚ መስሪያ ቤቱ ገንዘቡ ለመድረሱ መረጃ ባላቀረበበት ሁኔታ ከብድር አስተዳደር በተገኘ መረጃ ብቻ ምዝገባ ማከናወኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡*

በመሆኑም የሂሳብ ምዝገባው ለተጠቃሚው አካል መድረሱን ሊያረጋግጥ የሚችል መረጃና ከተጠቃሚው በኩል በሚገኝ ዶክመንት በመደገፍ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

2.8.5 *በሂሳብ መደብ 4210 ተመዝግቦ ስለተገኘው ሂሳብ*

በተጠቃለለው የ 2003 *የመንግስት ሂሳብ ሚዛን ማጠቃለያ ላይ በሂሳብ መደብ* 4210 (*በመንግስት መስሪቤቶች መካከል ሌሎች ቅድሚያ ክፍያች*) *መካከል ብር* 47,438,375.56 *ማስረጃ ሳይኖረውና ሁኔታው ሳይጣራ ተካቶ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የሂሳብ ሚዛኑ ከ*1995 *በጀት አመት ጀምሮ* IBEX *ላይ በ*4418 *የሚታይ መሆኑን በአደረግነው ማጣራት ለማወቅ ተችሏል፡፡*

በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርአት ማንዋል /ግንቦት 1999/ *መሰረት ሂሳብ መደብ* 4418 *አላቂ እቃ/ የሚመዘገብበት አርእስት መሆኑን ይገልጻል፡፡አሁን ባለው ሁኔታ አላቂም ሆነ ቋሚ እቃ በሂሳብ መግለጫ ውስጥ የሚካተትበት ስርአት የሌለ በመሆኑ ያለምንም ማስረጃ ወደ ሂሳብ መደብ* 4210 *የተጠቃለለው ሂሳብ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡*

ይህም የተዘጋጀው የሂሣብ ሪፖርት ትክክለኛውን የፋይናንስ እንቅስቃሴ እንዳያሣይ ያደርገዋል፡፡

ሥራ አመራሩ በ4418 ሂሳብ መደብ የተመዘገበው ገንዘብ ኤልሲ (L/C) መሆኑንና ከውጪ የሚገባ እቃ በመሆኑ በጉዞ ያለ እቃ (Goods in transit) ነው በሚል በ4418 የአላቂ እቃ ውስጥ ተመዝግቦ የነበር እንደሆነና አሁን ግን ሲጣራ ገንዘቡ በባንክ ውስጥ ስላለ እና እስከሚከፈል በቅድሚያ ክፍያ (Advance payment) እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ድጋሚ በተደረገ ማጣራት ሂሳቡ በኤልሲ (L/c) ባንክ አካውንት ቁጥር 01601/012850/00 ከ1995 በጀት አመት ጀምሮ የሚታይ ሲሆን በዚህ ገንዘብ ከውጪ የሚገዛ እቃ ለመኖሩ መረጃ እንዲቀርብ ጥያቄ ቢቀርብምም ምንም አይነት መረጃ ሊቀርብልን አልቻለም፡፡

በተጨማሪ በሂሳብ መግለጫው ማብራሪያ ኖት (Disclosure notes) እና በባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ (bank statement) መሰረት በኤሊሲ (L/c) ባንክ አካውንት ቁጥር 01601/012850/00 የሚገኘው ገንዘብ ባላንሱ ብር 57,007,790.39 መሆኑን ይገልጻል፡፡ስለዚህ ማጣራት በማድረግ በገንዘቡ የተገባ ግዴታ ከሌለ ገንዘቡ ስራ ላይ የሚውልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡

2.8.6 <u>የሂሳብ ምዝገባ መነሻን በተመለከተ</u>

በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 13 መሰረት ተገቢው ማዘዣ ሳይሞላ ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊደረግ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡እንዲሁም በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ማናቸውም የሂሣብ እንቅስቃሴ በገቢ ደረሰኝ ወይም ከወጪ ማስመስከሪያ ወይም ከሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ ወይም እነዚህን ሊተኩ፣ ከሚችሉ፣ በሚኒስቴሩ እውቅና በተሰጣቸው ሰነዶች መነሣት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንጻር ስራዎች የሚሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከትሬጀሪ አካውንት ክፍያ ለመፈጸሙም ሆነ ወደትሬጀሪ አካውንት ገንዘብ ለመግባቱ መረጃ ሲደርሰው ተገቢው ማዘዣ ሳይሞላ በባንክ አድቫይስ ላይ ብቻ ኢንትሪውን በማሳለፍ የሚመዘገብ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በፋይናንስ ደንቡና መመሪያው መሰረት ማንኛውም የፋይናንስ እንቅስቃሴ በታተመ ተከታታይ ቁጥር ባለው ወጪ ማስመስከሪያ ወይም ሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ ላይ አለመመዝገቡ የተለያዩ ክፍተቶችን የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ለአንድ የፋይናንስ እንቅስቃሴ ማለፍ ያለበት የሂሳብ ምዝገባ ያለፈ ለመሆኑ ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል ፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ ደንቡና በመመሪያው መሰረት ለእያንዳንዱ የሂሳብ እንቅስቃሴ የምዝገባ ማዘጃ እየተዘጋጀ ለትክክለኛነቱም በሚመለከተው አካል እየተረጋገጠ ስራው መሰራት ይኖርበታል፡፡

2.9 <u>የመንግሥት ዕዳ አስተዳደር የመረጃ ስርአትና ቁጥጥርን በተመለከተ</u>

Ministry of Finance and Economic Development

Public Debt Management Information System& Control

Audit Report

I. BACKGROUND

In the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Regulation the office of the Federal Auditor General is required to conduct audit of consolidate accounts of the Federal Government. Among the component in the financial statement, public debt has substantial amount.

The Debt Management Directorate in the Ministry of Finance and Economic Development uses the Debt Management and Financial Accounting system (DMFAS) developed by UNCTAD to manage the recording, mobilization of funds, debt service operations, statistics and reportingof public debt information.

To provide reasonable assurance about the achievement of the public debt management objectives with regard to reliability of financial reporting, effectiveness and efficiency of operations and compliance with applicable law and regulations, internal controls should be designed and implemented by management. In this regard our objective is to check the adequacy of the internal control specifically the information systems controls and provide assurance to the auditee management and the parliament about the reliability of the report generated from the public debt information system.

Therefore, the purpose of this audit is to undertake information systems audit on the Debt Management and Financial Accounting System (DMFAS), to be able to provide assurance regarding the adequacy to the general and application controls.

The matters mentioned in this letter are therefore those that were identified through tests considered necessary for the purpose of the audit and it is possible that there might be other matters and/or weaknesses that were not identified.

II. OBJECTIVE

Our objective were to ascertain whether the public debt information system has adequate General and application IT controls and the controls are properly implemented.

It focus on examining and evaluating the adequacy of the operating and administrative procedures, practices and policies to obtain reasonable assurance that sufficient controls exist over DMFAS to protect the application and database from unauthorised access; to provide for continuation of computer processing capability and to ensure that the input, processing and output of data is accurate and complete.

III. SCOPE AND METHODOLOGY

The audit was conducted in accordance with the International Standards of Supreme Audit Institutions (ISSAIs). These standards require that the audit is planned and performed so as to obtain reasonable assurance that, in all material respects, controls are designed and implemented to provide reliable information.

Our audit focused on the daily operation of Debt Management Directorate and the responsibility of each employee regarding DMFAS. This report includes the evaluation of the controls over the public debt management information system from January 1, 2011 to June 30, 2011.

Our audit procedures included interviewing key personnel in Debt Management and Information Technology Directorate, reviewing draft security policy and procedures, DMFAS user guide, identifying and assessing the adequacy of general and application controls, and testing the relevant controls.

IV.FINDINGS AND RECOMMENDATIONS

Our findings and recommendations are structured as general control, application control and governance issue. General Controls comprise the processing environment including management of computer resource, file access, business continuity and recovery planning and backup of critical files; application controls are specific to an application and ensure only authorised data is processed, processing is complete and accurate and output is reliable and governance issues are related with a number of responsibilities concerning financial and risk management and internal control.

Effective general controls form the foundation for effective application controls.

1. General Control

1.1. Security policy and procedure are not approved and implemented

Ministry of Finance and Economic development have the responsibility of to employ prudent information security policies, standards and practices to minimise the risk to the integrity, confidentiality, and availability of the debt management information.

There was no approved security policy and procedure. Although a security policy has been drafted by the Ministry Information Technology Directorate, it is not approved and implemented.

As a result, it will not be possible to make accountable unauthorised users, and even it could lead to exposure of organisation's information; and Systems and data are prone to virus attacks.

Recommendation

The draft security policy should be approved, communicated to all users and implemented in all the systems including DMFAS to minimize the risk of integrity, confidentiality and availability of the

information system and make accountable those unauthorised users. The recommendation is accepted,by the IT Directorate and agreed to provide the draft policy and procedure for approval and it will start implementation by the end of year 2011

Management Response

The recommendation is accepted, and as a result, the IT Directorate agreed to provide the draft policy and procedure for approval and it will start implementation by the end of year 2011.

1.2. The database and DMFAS administration is made by line staff

Sound information system controls dictate that proper segregation of functions should be maintained between database and DMFAS administration, with line duties.

The debt management Directorate was found to have one individual who manage the database, the application (DMFAS) and also responsible for line duties in the public debt management operation.

Segregation of functions is not achieved if application administrator has ability to provide unlimited access for himself. And as a result, malicious or unintentional damage to system or non-compliance with policies will remain undetected.

Recommendation

We recommend that aseparate individual who doesn't have involvement in the day to day operation of debt management should be assigned to manage the DMFAS and the database.

The Debt Management Directorate explained that the duty is not separated because they have only one debt management expert who has been trained in DBA and DMFAS. However, the debt management application and database can be managed by the IT Directorate and the debt management expert can focus on the day

to day function of the debt management and as a result segregation of duty can be maintained

Management Response

The Information System Administration center currently has adequate and qualified staff members to fully administer the technical portion of the DEMFAS system. Hence, as recommended the technical administration part of the system will be separated from the daily operational activities.

1.3. DMFAS users passwords were weak to protect unauthorised access

Passwords are a final layer of security protecting resources. A password's strength is the key factor in determining how difficult it may be to gain unauthorised access to a resource. To enforce the implementation of strong password management development of password policy is essential.

Our examination identified the following deficiencies for the system and database accounts.

- We found no password policy;
- The password length is not determined;
- The password combination was not determined and as a result users are free to use alphabet, numbers, special characters, etc.
- The expiry date for users password were found to one year
- No record of password history and as a result one password can be used for more than a year.

As a result, unauthorised users could potentially gain access and control of critical service, servers and database leading to a compromise of the information systems' availability, integrity and confidentiality.

Recommendation

The Debt Management Directorate should design and implement appropriate password policy to rectify the above weakness. The recommendation is accepted by the Debt Management Directorate, and during the audit we confirm that expiry date of password is reduced to six month.

Management Response

The recommendation is accepted, Even though the system could support password complexity policy, it was not set to force. Hence it will be ensured that this will be implemented. In addition, UNCTAD would be consulted regarding this issue as it is the owner of the application.

1.4. Business continuity and recovery plan not developed

The objective of business continuity planning is to ensure that key business activities are restored and maintained as quickly as possible following any major disaster or failure that affects essential services or facilities.

Business continuity and recovery plan is not developed for the debt management information system, except backup taking and keeping it in the same site.

As a result, any major disaster can destroy the backup and the system at the same time and it may not be easy to recover appropriately from disaster.

Recommendation

We recommend developing the business continuity and recovery plan and implementing the plan to prevent the risk of failure to recover from disaster. The recommendation is accepted by the IT Directorate, to establish disaster recovery site, budget is already allocated and the recommendation will be implemented in 2011. They also agreed on the importance of having the business

continuity plan. Currently the IT Directorate is taking back up every day.

Management response

To establish disaster recovery site, budget is already allocated and the recommendation will be implemented in 2011. They also agreed on the importance of having the business continuity plan. Currently the IT Directorate is taking back up every day.

2.0 APPLICATION CONTROLS

2.1. Audit logs are not maintained

In order to place reliance on the integrity of data generated by an application a complete audit trail of transactions processed should be maintained in form of an application log. The log will include the date, time and user identification of input and record of any changes made to the data

The operators log needs to be monitored and followed by the security administrator to take corrective action promptly on the incident of security breach.

The DMFAS 5.3 does not have an auditing functionality to routinely generate, store, and analyse system log.

Consequently, Debt Management Directorate may not be able to identify major security incidents, policy violations, fraudulent activity, or significant operational problems, all of which can greatly compromise their availability, integrity, and confidentiality of the DMFAS and the financial data.

Recommendation

We recommend that the database administrator should be trained on how to use Oracle RDBMS' audit functionality and improve the security monitoring, detection, response, recovery, to minimize the level of risk and threat to the public debt data. Or alternatively to

upgrade the current version to version 6 so that, the control can be implemented easily.

The recommendation is accepted by Debt Management Directorate, but building an audit log in DMFAS and implementing this recommendation is considered to be expensive.

However:

- without spending extra money to build the audit log in DMFAS it is possible to setup and configure this control on the database (ORACLE) by training staffs on ORACLE database management system or
- DMFAS 6 has this control; management can also consider upgrading the current version to DMFAS 6.

Management Response

The recommendation is accepted, currently this functionality is not set in the system. However, it is possible to set this functionality and have an audit log within the system even before the new version (DEMFAS 6.0) is installed.

2.2. Duplicate Entries

An increase in the number of transactions that need to be processed increases the risk that duplicate transactions will occur and remain undetected. To address this risk, applications must be able to detect and flag duplicate transactions.

We noted 29 disbursements transactions from the same creditor, with the same amount and reference number are recorded and processed without being rejected or flagged by the DMFAS system.

Recommendation

Disbursement input data validation was found weak to prevent recording of duplicate data, and as a result to reduce the risk of duplicate data entry, management should establish a system of

checking recorded data by individual who is not involved in the recording activity. Debt Management Directorate accepted the recommendation and the issue will be communicated to UNCTAD, they decide to design compensating control to reduce the risk.

Management Response:

Checking for duplication of transaction and/or inaccurate disbursement data entry is done manually by staffs not involved in the recording activity. However, as this problem inherent in the system (DMFAS), the issue will be communicated to UNCTAD.

2.3. Luck of Resource sharing

One of the advantages of IT is to avoid data decentralisation and enhance sharing of resource, and as a result it would increase efficiency and reduce cost of maintaining duplicate data. In this regard domestic debt management function is shared by Ministry of Finance and Economic Development and National Bank of Ethiopia, however the two institutions maintain their own data and sharing is only manual, creating duplication of resources. The current version of the DMFAS cannot support web enabled architecture to enhance sharing of resources.

Recommendation

DMFAS 6 is a web enabled architecture which can help to sharing resource between Ministry of Finance and Economic Development and National Bank of Ethiopia from the same database. Therefore, to utilize resource efficiently and avoid data redundancy management should look for upgrading the current version to DMFAS 6. Debt management directorate accepted the recommendation. However, as the two organisations use the data for different purpose; they need to look the issue further if DMFAS 6 meets the needs of the two organisations.

Management Response:

When DMFAS 6.0 is installed, the National Bank of Ethiopia will be approached if it is willing to share MoFED's database.

2.4. Data Validation

Data validation contributes for better indebtedness decision; risk management through more reliable indicators and debt statistics and analytical work.

During the audit we understand that the Debt management staffs were trained in data validation and developed the data validation procedure with the help of UNCTAD. However we found no evidence on the implementation of data validation procedure. During the audit we observed that:

- No evidence of formal request for reconciliation of data with creditors
- Delay of debt repayment not properly explained,
- Repayments showing waiting status due to recording errors which were not detected timely,
- Repayments delayed due to incomplete documentation from creditors were not followed up to make timely payment.
- The reason for loans which should have been disbursed, but still have undisbursed balance were not explained properly.

Recommendation

In order to have confidence on the quality of the data entered in the database and on the quality of the report produced from the data base the Debt Management Directorate needs to design a system of data validation with domestic (information from the same institution and other domestic institution) and external (external creditor) primary source of information in addition to checking the completeness, accuracy and consistency of the debt data in the

database. The Debt Management Directorate explained that they have implemented the data validation procedure partially and based on the recommendation then Directorate agreed to implement the procedure fully and conduct data validation in a continuous base.

Management response

Debt Management Directorate has already prepared a Data Validation Calendar. However, due to the exiting shortage of manpower, it is not being fully executed. As the indicators for completeness, consistency and accuracy checks are already in place, implementation will be at full scale when vacant posts are filled.

2.5. Lack of monitoring to Reference files and other standing data

Standing Data File controls are important to ensure the integrity and accuracy of reference files and loan agreements to protect information stored in the reference file and general loan agreement. This information's are critical to the processing and reporting of financial and operational data. Weak control in the system maintenance of standing file may lead to unauthorised and uncontrolled amendments to the standing data as well as poor documentation of the amendment procedures, etc.

During the audit we found out that one employee is assigned to collect and record reference file information like exchange rate, however we noted that, there is no system of checking by another individual for correct and complete recording of these information's. In addition to this incorrectly recorded data can be corrected by the individual making the mistake without the knowledge and authorisation of the Public Debt Director or responsible body.

Recommendation

To ensure the integrity and accuracy of the standing data Debt Management Directorate should establish:

- Procedure of checking records by individual not involved in recording the data and
- A system of authorisation for the amendments of the standing data as well as documentation of the amendment procedures.

Debt Management Directorate explained that DMFAS 5.3 do not have a constraint which allow to prevent an employee who have accesses right to encode exchange rate from not correcting errors without authorisation. The directorate agreed to establish compensation control as per the recommendation and also to inform UNCTAD if it is possible to prevent such activity.

Management Response

Data for daily exchange rates entered in to the system is checked as much as possible by other staff when reports are produced. The current version of DMFAS does not contain a user from making changes/collections. However, this issue would be addressed in DMFAS 6.0, and the problem would be resolved when the system is upgraded.

3.0 IT GOVERNANCE

3.1. Lack of Monitoring DMFAS Internal Control by Internal Audit Directorate

Internal audit plays a crucially important role in an organisation by reviewing and monitoring internal controls on a regular basis. It is also the first line of defence against fraud. In an IT environment, the internal auditors should be entrusted with the responsibility of periodically reviewing the IT security, general and application controls for the purpose of preventing fraud and other irregularities.

Discussions with Debt Management Directorate and the Internal Audit Directorate revealed that no internal audit was conducted on DMFAS system before as part of review and monitoring internal controls on a regular basis.

Recommendations

Without an effective internal audit function, it becomes difficult to monitor and enforce system controls. Therefore management should ensure that the Internal Audit function is instituted and accorded a responsibility on the system for the day to day monitoring of risks and internal controls on DMFAS System.

Management Response:

The recommendation is accepted, Internal Audit in the ministry is working in the review and monitoring activities, mainly of financial and property administration. Basically strengthening the internal control system in the organization contributes a lot towards economical utilization and better efficiency. By appreciating the recommendation, we continue to increase the skill of staffs through necessary trainings to capacitate them to monitor the system.

2.10 <u>ሴክተር ዘለል የሆኑ ሥራዎችን በተመለከተ</u>

በሥርዓተ ጾታ፤ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና የአከባቢ ጥበቃ ዙሪያ ከተከናወኑት ተግባራት፤

- በስርዓተ ጾታ ተወካይና በመ/ቤቱ የሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ አስተባባርነት በተደረገ እንቅስቃሴ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለሶስተኛ ጊዜ በመ/ቤታችን የማርች 8 ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን እንዲከበርና በተጋባዥ የሴቶች ጉዳይ ባለሙያ በቀረበ የሥርዓተ ፆታ ትምህርት ሠራተኛው ግንዛቤ እንዲያገኝ አድርጓል፡፡

- ለ34 የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የ Gender Mainstreaming በሥርዓተ-ጾታና ልማት፤ የሴቶች ተሳትፎና የማብቃት ስትራቴጂዎች በሚሉ አርእስቶች ዙሪያ የ1 ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ከቡድን መሪ ጀምሮ በአመራር ደረጃ ለሚገኙ የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች "Women in Leadership Position Challenges & Prospects" በሚል ርዕስ በዘርፉ ልምድ ባላቸው ባለሙያ የ 2 ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- የዓመቱ የአለም የኤድስ ቀን መሪ ቃል "አንድም ሰው በኤች.አይ.ቪ. እንዳይያዝ ኃላፊነታችንን እንወጣ!!!" የሚል መልእክት በማስተላለፍና ሠራተኛው የቀይ ሪቫን በደረት ላይ በማድረግ የዓመቱ የዓለም የኤድስ ቀን መሪ ቃል መልዕክት ላይ እርስ በእርስ እንዲወያዩ ተደርጓል፣
- መታቀብ፣ ካልሆነም አንድ ለአንድ መወሰን እንደሚቻል በመመርመር እራስን በማወቅ ጤንነታችንን ለመጠበቅ የሚያስችል ጽሑፍና ሌሎች ብዛት ያላቸው ብሮሸሮችና በራሪ ወረቀቶች በላይብረሪ እንዲቀመጥና በመ/ቤቱ ህንፃዎች ላይ እንዲለጠፉ ተደርገዋል፣
- በሶሻልና ኢንቫሮሜንት ኮሚቴ አስተባባርነት የመ/ቤቱ ሰራተኛ በሙሉ የተሳተፈበት የ2003 የችግኝ ተከላ ፕሮግራም በኦሮሚያ ክልል ገላን ከተማና በድሬ ግድብ አከባቢ ተከናውኗል፡፡
- በኦዲቱ ስራም በተለይም በክዋኔና አካባቢ ኦዲት በዕቅድ ዘመኑ በሥርዓተ-ጾታና አካባቢ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረጉ የተለያዩ አርዕስቶች ተከናውኖ ሪፖርታቸው ቀርበል፡፡

II. የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የመፍትሔ ሃሣቦች

በዚህ ክፍል የሚነሱ አብዛኞቹ ግኝቶች ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችን ደጋግመን ያቀረብናቸው ቢሆንም፣በርካታ ጉድለት የታየባቸው መሥሪያ ቤቶችና የሚመለከታቸው አካላት አጥጋቢ እርምጃ ወስደው ባለመገኘታቸው አሁንም ደግመን ለማቅረብ አስፈላጊና ግዴታ ሆኖ በመገኘቱ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

መ/ቤታችን በ2003/2004 የኦዲት ዓመት በ131 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች መደበኛ የፋይናንስና ህጋዊ ኦዲት፣ በክልል መንግሥታት ደግሞ በ262 የወረዳና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲት ያከናወነ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት የታዩ ጉልህ የአሠራር ስህተቶችና ግድፈቶች ከመፍትሄ ሃሣቦች ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1 የጥሬ ንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

1.1. የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት አያያዝና አጠባበቅ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የውስጥ ኦዲተሮች ባደረጉት ምርመራ በ4መ/ቤቶች ብር 1,066,524.68 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 6ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፣ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ29 መ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡/የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ- 8 ተመልክቷል/

ከታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያየዝ ጉድለቶች፤

- የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር የማይመሳከር መሆኑ፤
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉ /የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አድርገናል ቢሉም ማስረጃ ያላቀረቡ/ መሆኑ፤
- የዋና ገንዘብ ያዥ የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠርያ መዝገብ አለማዘጋጀት፤
- በባንክ ሂሣብ ገቢ ለሆኑ ሂሣቦች፣ የገቢ ደረሰኝ አለማዘጋጀትና አለመመዝገብ፤
- የተሰበሰበውን ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ አለማድረግ፤
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ መሆኑ፤
- ለልዩ ልዩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ያለማስፈቀድ እና ከተፈቀደውም በላይ በሳጥን ማስቀመጥ፤
- በግዥ ሠራተኞች እጅ በርካታ የጥሬ ገንዘብ እንዲያዝ መደረጉ፤

  በውጭ ምንዛሪ ባንክ ያለ ገንዘብ /4102/ ተብሎ ሪፖርት የተደረገውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የባንክ ሂሣብ መግለጫ ያልቀረበለት መገኘቱ፤

  የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል ልዩነት በ10 መ/ቤቶች ብር 1,555,007.88 በማነስ የሚታይና በሀገር መከላከያ ሚ/ር የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 291,928.19 ለዓመታት ያልተተካ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-7 ተመልክቷል/

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፤ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ፤በማነስ የታየው ልዩነትም ተጣርቶ እንዲተካ፤እንዲሁም የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ አሳስበናል፡፡

2 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 በየመ/ቤቶቹ የተገኘ ተሰብሳቢ ሂሳብ

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ59 መ/ቤቶች ብር 1,275,970,326.90 የሰነድ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-9 ተመልክቷል/

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የትምህርት ሚኒስቴር ብር 723.77 ሚሊዮን፤ የመከላከያ ሚ/ር ብር 133.78 ሚሊዮን፣ ግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ብር 115.02 ሚሊዮን፤ጤና ጥበቃ ሚ/ር ብር 48.05፤ በግብርና ሚ/ር 38.55 ሚሊዮን፤ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 35.16 ሚሊዮን፤ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ብር 31.79 ሚሊዮን፤ውጭ መልዕክተኞች ብር 29.97 ሚሊዮን እና በፌዴራል ፖሊስ 23.99 ሚሊዮን ይገኙበታል፡፡

ስለተሰብሳቢው ሂሳቦች ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ከሰጡት ምላሽ በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ለሥራ አመራር ሪፖርት በሰጠው መልስ ብር 18,500,490.05 በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ማለት በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ብር 11,593,098.46 እና በሌሎች 8 ክፍሎች ብር 6,907,391.59 የወደመ፣ የጠፋና የተሰረቀ መሆኑን እና በፋይናንስ ሕግ መሠረት ከመዝገብ ለማስረዝ ኮሚቴ መቋቋሙን፣ ለብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽንና ለብራና ማተሚያ ቤት ከተከፋይ የሠራዊት ደመወዝ በብድር ከተሰጠው ብር 55,000,000.00 ብር 4,000,000.00 ከብራና ማተሚያ ቤት የሚፈለግ የሚቀር መሆኑንና ሌላብር 51,000,000.00 በዚህ ዓመት ተመላሽ መደረጉን፣ ብር 17,830,739.30 ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ በሰነድ ወጪ መደረጉን እየተወራረደ መሆኑን፣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በላከው መልስ እስከ 2004 በጀት ዓመት አጋማሽ በርካታ ሂሣብ እንዲወራረድ መደረጉን፤ትምህርት ሚኒስቴር ለየዩኒቨርስቲዎች ግንባታ የተሰጠውን በርካታ ገንዘብ እንዲወራረድ ጥረት በማድረግ ላይ

መሆኑንና ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል።

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቡ በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ /ሳይወራረዱ/ የቆዩት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል።

2.2 በተሰብሳብ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

- በአንዳንድ መ/ቤቶች /ድርጅቶች/ እና ግለሰቦች ስም ያሉ ክፍያዎች በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች የሂሳብ መደብ የተያዘ ቢሆንም ሂሳቡ ከማን እንደሚፈለግና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ የማይታወቅ መሆኑ፤
- ለእቃ ግዥ ሰራተኞችና ሌሎች ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በተደጋጋሚ የሚሰጥ በመሆኑና በእያንዳንዱ የእቃ ግዥ ሰራተኛ ተቀጽላ ሌጀር ባለመኖሩ ማስረጃ ቀርቦለት ያልተወራረደና ከሰራተኛው የሚፈለግ ቀሪ እዳ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥና ለይቶ ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ፤
- ለበርካታ ዓመታት ሳይወራረዱ የቆዩና ያለበቂ ማስረጃ በተሰበሳብ ሂሳቦች ስለሚያዙ ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ መኖሩ፤
- የወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 1,953,500.00 በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድመ ክፍያዎች ብር 21,205.30 በልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ እና ብር 20,849.64 በአቅራቢዎች ቅድመ ክፍያ መያዝ ሲገባው፤ በጥቅሉ ብር 1,995,554.94 በግዥ ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መደብ ተይዞ መገኘቱ፤ በተጨማሪም በዚሁ ዩኒቨርስቲ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 66,145.03 በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች የሂሳብ መደብ የተያዘ ቢሆንም ሂሳቡ ከማን እንደሚፈለግና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ የማይታወቅ መሆኑ፤
- በጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 448,095.38 ተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ የተያዘ ቢሆንም ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ የሠነድ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፡-

- በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 74,313.27 በተቋሙ ሠራተኞች ላይ የሚፈለግ ዕዳ እንደሆነ ቢገለጽም በእያንዳንዱ በላዕዳ ስም ተቀጽላ የሂሳብ ሌጀር በመክፈት የሚፈለግበት ሂሣብ ፤የተከፈለው ገንዘብና ቀሪ ዕዳ እየተቀናነሰ የማይመዘገብ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከሁለት የተቋሙ ሠራተኞች ደመወዝ ላይ በየወሩ 1/3 እየተቀነሰ ለጉራፈርዳ ወረዳ የገንዘብና ኢ/ል/ጽ/ቤት ገቢ እንዲደረግ የተወሰነው ገንዘብ ብር 37,814.66 አላግባብ በተቋሙ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱ፣
- በባህርዳር ዩኒቨርስቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለሥራ አመራሩ በተዘጋጀው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት መሠረት ብር 20,105,034.19 ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ የተገለጸ ቢሆንም በዝርዝር ለማየት ተሞክሮ ትክክለኛ ገጽታውን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- በትምህርት ሚኒስቴር ከተመለከተው ተሰብሣቢ ሂሣብ ውስጥ የካፒታል ሂሳብ (የሂሳብ መደብ 4274) ብር 37,883,977.02 ከሰኔ 1994 ዓ.ም ጀምሮ ያለና በ1999 በጀት ዓመት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በቀረበው ሪፖርት ላይ የተመለከተ/ያልተወራረደ/ ሲሆን፤ የመደበኛ ሂሳብ (የሂሳብ መደብ 4201፣ 4202 እና 4253) ብር 5,478,706.92 ከ1995 ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ የተሰብሳቢ ሂሣብ ነው፡
- በትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 11,004,054.87 ማስረጃ የሌለው የተሰብሳቢ ሂሳብ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሔራዊ ጽ/ቤት ብር 2,482,145.92 ለቃሊቲ ማእከል ግንባታ ቅድሚያ ክፍያ ከተከፈለው ሂሳብ ማስረጃው ያልቀረበ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት ማስረጃዎቹ ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የኢትዮጵያ የሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የታየው የተሰብሳቢ ሂሳብ በትክክል በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ መያዙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ብር 84,878.90 በሂሳብ ሪፖርት ያልተገለጸ መሆኑ ታውቋል፡፡

- በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በተቀጽላ የሂሳብ ሌጀሮች በድምሩ ብር 420,850.71 በክሬዲት አቅጣጫ ተመዝግቦ ተገኝቷል::
- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሂሣብ መደብ 4203 በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት የተደረገው ሂሣብ በተቀጽላ ሌጀሮች ድምር ከታየው በብር 1,289,269.38 አንሶ መገኘቱንና ይህ ባለፉት ኦዲቶችም የታየ ልዩነት ያልተስተካከለ መሆኑ፤
- በኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ብር 141,686.45 የተሰብሳቢ ሂሣብ ከማን እንደሚፈለግ እና የየትኛው በጀት ዓመት ሂሣብ እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ የሌለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም በቅድሚያ ክፍያ የተሰጡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ፤ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ተጣርቶ አስፈላጊው ማስረጃ እንዲቀርብና ማስተካከያ እንዲደራግላቸው፤በተሰበሳብ ሂሳቡች ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3 <u>የገቢ ሂሳብ</u>

3.1 <u>በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ ሕጎች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች፤ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ15 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 952,938,239.61 በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሰበሰብ ተገኝቷል። /ዝርዝሩም በአባሪ- 11 ተመልክቷል።/

በአዋጁ በመሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ብር 638.14 ሚሊዮን፤ ምስራቅ አዲስ አበባ ብር 132.56 ሚሊዮን፤ ውሃና ኢናርጂ ሚ/ር ብር 120.63 ሚሊዮንና ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 10.58 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ ካልተሰበሰበው ገቢ ውስጥ የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 50,929.88 እንደሰበሰበ፣ ሌሎችም እንዲከፍሉ ደብዳቤ መጻፉን፣የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 238,651.95 መሰብሰቡን በድምሩ ብር 289,581.86 መሰብሰቡን ፣እንዲሁም የጅንአድ በተመለከተ በውሉ መሰረት በ45 ቀናት ውስጥ ገቢ እንዲያደርግ ክትትል እተደረገ መሆኑና ሌሎችም ውዝፍ ገቢውን ለመሰበሰብ የተለያየ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ለስራ አመራር ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Coustom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሳበሳበ የንግድ ትርፍ ግብር እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ከዚህ ሂሳብ ውስጥ በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 125,182.90 እና በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 35,571.28 በድምሩ ብር 160,754.18 መሰብሰቡን የገለጹ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ እየታዩ ያሉ እንደሆነና ሌሎችም ገቢውን ለመሰብሰብ እንቅስቃሴ እንደጀመሩ ለስራ አመራር ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.2 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሳብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ ሰባት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፣ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 272,148,506.59 እና በሌሎች 4 መ/ቤቶች ብር 14,623,028.28 በድምሩ ብር 286,771,534.84 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ተረጋግጠል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-10 ተመልክቷል/

ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች የገቢዎችና ጉምሩክ ዋና መ/ቤት ብር 120.43 ሚሊዮን፣ በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 94.59 ሚሊዮን፣ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 26.12 ሚሊዮንና በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ብር 10.53 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ያልተሰበሰበውም ገቢ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት የተወረሱና የተተው ዕቃዎችን ለሸቀጦችና ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት ለመሸጥ በገባው ውል መሰረት ያለጨረታ በዱቤ ከተሸጠው ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ውዝፍ ያልተሰበሰበ ገቢ ሲሆን ፣ ሌሎቹም ከግብር ከፋዮች ሊሰበሰብ ከሚገበው የንግድ ግብር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ከዚሁ ጋር የተያያዘ ወለድና ቅጣት እንዲሁም፣የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ከደንበኞቹ ለ16 ዓመታት ያልሰበሰበው ውዝፍ ገቢ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶትተገቢ እርምጃ በመውሰድ የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለየመ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ ሶሰት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች ሶስት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 225,587,797.44 የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ ከማን እንደተሰበሰበ ሳይገለጽ በኮድ

በመሰብሰቡ የተሰበሰበው ገቢ መሰብሰብ በሚገባው ልክ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለመቻሉ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል። /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ- 12 ተመልክቷል፡፡/

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙ ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

3.4 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ 18መ/ቤቶች የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር 138,594,989.18 ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ- 13 ተመልክቷል፡፡/

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱት አብዛኞች የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፣ በተጨማሪም በ9 መ/ቤቶች /ዝርዝራቸው በአባሪ-15 ተመልክቷል/ በአዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10/2 መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባሳተመው ወይም እንዲታተም በፈቀደው ደረሰኝ ገቢ መሰበሰብ ሲገባቸው የሚኒስቴሩን ፈቃድ ሳያገኙ የጥሬ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በስማቸው በማሳተም ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ገንዘብ የሚሰበስቡና ሪፖርትም የማያደርጉ መሆኑ ታውቋል።

ይህ አሰራር በመ/ቤቶቹ የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ገቢ ሕገዊ በሆነ መንገድ በታተሙ ደረሰኞች ብቻ በመጠቀም እንዲሰበስቡና በሂሳብ መግለጫዎችም በመካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 በበጀት ዓመቱ ያልተሰበሰበ የወጪ መጋራት ሂሳብ

የወጪ መጋራት አሰባሰብ መመሪያ ቁጥር 26/2001 ክፍል 5.2/ሀ መሰረት የተቀጣሪዎች የእፎይታ ጊዜ እንደተጠናቀቀ ከጥቅል የወር ደመወዝ ላይ 10% በአሰሪው እየተቀነሰ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈሰስ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የእፎይታ ጊዜያቸውን ከጨረሱ 31 ሠራተኞች ሊሰበሰብ የሚገባው ብር 37,879.20 እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 78219.55 ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

በተጨማሪም 3 መ/ቤቶች- የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም፤ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ሂሳብ የማይሰበስቡ መሆኑ ታውቋል።

መሰብሰብ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ሊዘገይ ከመቻሉም በላይ ሳይሰበሰብ ሊቀር የሚችልበትም አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል።

በመሆኑም የወጪ መጋራት ሂሳብ በመመሪያው በተቀመጠው ቀነ ገደብ መሰረት እንዲሰበሰብ ተገቢውን ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና ያልተሰበሰበውም ሂሳብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

3.6 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ስለተገኘው ሂሳብ

የተመዘገበው ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:-

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋናው መ/ቤትከ10 ቅ/ጽ/ቤቶች የተላከው የሂሳብ ሪፖርት በትክክል ባለመመዝገቡ በተለያዩ በሂሳብ መደብ በድምሩ ብር 70,321,371.23 በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-14 ተመልክቷል/

የገቢ ሂሳብ በተገቢው የሂሳብ መደብ ካልተመዘገበ የሂሣብ ሪፖርት እና የአፈጻጸም ሪፖርት ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አወቃቀር መሰረት ትክክለኛውን የሂሳብ መደብ ተከትሎ ሊመዘገብ እና የሂሳብ መግለጫውም ትክክለኛውን የገቢ አፈጻጸም በገቢው አይነቱ እንዲያሳይ ለማድረግ የግብር ከፋይ ምዝገባ ሲከናወን ግብር ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን የታክስ አይነት በመለየት ትክክለኛ ምዝገባ ሊከናወን የሚገባ ሲሆን፤ ከቅ/ጽ/ቤት የሚቀርበው ሪፖርት ከሂሳብ መግለጫ ጋር እየተገናዘበ አስቀድሞ የተመዘገበው የግብር መረጃ ሊስተካከል ይገባል፡፡

3.7 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

3.7.1 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የኤክሳይዝ ታክስ በወቅቱ ስለማሣወቃቸው ማስረጃ ያልቀረበለት፤

በኤክሳይዝ ታክስ በአዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 2ሀ (2) መሰረት ታክስ በወቅቱ እና በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤

- በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ሶስት ግብር ከፋዮች ሂሳባቸውን በአዋጁ መሰረት ስለማሳወቃቸው የቀረበ ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም በላይ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ አለመወሰዱ፤ እንዲሁም በምስራቅ አዲስአበባ ቅ/ጽ/ቤት ስድስት የኤክሣይስ ግብር ከፋዮች በየወሩ ማሣወቃቸው ለማረጋገጥ ሲሞከር ሪፖርት ስለማድረጋቸው በፋይሎቻቸው ውስጥ ማስረጃ የሌለ መሆኑ፤
- በምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት 21 ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በአዋጁ መሰረት ያላሳወቁ ቢሆንም፣ በነዚህ ግብር ከፋዮች ላይ በህጉ መሰረት እርምጃ ስለመወሰዱ የሚገልጽ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት አለመቅረቡ፤

- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ዘጠኝ ግብር ከፋዮች የ2002 የግብር ዘመን ገቢያቸውን በወቅቱ ያላሳወቁ መሆኑ ፤
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በዲክላራሲዮን ቁጥር C-868/11 ለተሰበሰበው ብር 106,532.83 የተሟላ የዋጋ ሰነድ ሳይቀርብ ቀረጥና ታክሱ መሰብሰቡን፣ እንዲሁም በዲክላራሲዮን ቁጥር C-4977/10 ለተሰበሰበው ብር 1,626,359.74 በእቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ (packing list) ላይ ዝርዝር የእቃው አይነት የተገለጸ ቢሆንም፣ በዋጋ ሰነዱ ላይ ግን የእያንዳንዱ እቃ ዋጋ ያልተገለጸ በመሆኑ ምክንያት እያንዳንዱ እቃ በትክክለኛው የታሪፍ ምጣኔ መሰረት ቀረጡ ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር c-121/11 ለገባው እቃ በዶክመንቱ መሰረት የመኪናው ዓይነት Isuzu NPR እንደሆነ የመንገድ ትራንስፖርት ፈቃድ በሰጠበት ደብዳቤ፣ የባንክ ፈቃድ፣ ትራክ ዌይ ቢል፣ ፓኪንግ ሊስት፣ ኮመርሽያል ኢንቮይስ፣ ዲክላሬሽን ኦፍ ፋክት እና የቶጎ ውጫሌ የፍተሻ ደብዳቤ ላይ የተገለጸ ሲሆን፤ በድሬዳዋ መቅረጫ ጣቢያ በተደረገ ፍተሻ መኪናው Isuzu NPR Chasis መሆኑን በመግለጽ እና የልዩነቱ መንስኤ እንዲጣራ ሳይደረግ ቀረጥና ታክስ በፍተሻው ውጤት መሰረት መሰላቱ፤
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የዋጋ ሰነዱ በአንዳንድ በዲክላራሲዮኞች ላይ የእቃዎቹን ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን ገላጭ ባልሆነበትና በፍተሻ እና በፍሬ ነገር መግለጫ (declaration of fact) ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ባልቀረበበት ሁኔታ አነስተኛ ዋጋን በመውሰድ ቀረጥና ታክስ የተሰበሰበ መሆኑ፤

<u>በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት</u>

- ለአንዳንድ ሰነዶች የፍሬ ነገር መግለጫ የማይሞላ ሲሆን ለአንዳንዶቹ የፍሬ ነገር መግለጫ ቢያያዝም እያንዳንዱ እቃ የተመደበበትን ታሪፍ ቁጥር የማይጠቅስ መሆኑ፣

- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በዲክላራሲዮን ቁጥር c-4923/2011 ዲክሌር ከተደረጉት እቃዎች ውስጥ Bush (spare part) እቃው የላስቲክ እቃ (Rubber) ከሆነ የጉምሩክ ቀረጥ (import tax rate) 30% ሲሆን Rubber ካልሆነ ግን የጉምሩክ ቀረጥ (import tax rate) 20% ይሆናል:: ነገር ግን እቃው የላስቲክ እቃ (Rubber) መሆን አለመሆኑ በዋጋ ሰነዱ፣ በፍተሻ ወይንም በፍሬ ነገር መግለጫ ላይ ሳይገለጽ አነስተኛ የታሪፍ ምጣኔውን በመውሰድ ቀረጡ የተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በአራት በዲክላራሲዮኖች ላይ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን በማስረጃ ላይ የተመለከተው ሞዴል እና ቀረጥ ለማስከፈል የተጠቀሙበት ሞዴል የሚለያይ እና የመጫን አቅማቸውም ሳይታወቅ መስተንግዶ የተሰጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ከቀረጥ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች ወደ ግለሰቦች በሽያጭ ሲዘዋወሩ በጉምሩክ አዋጁ ቁጥር 622/01 ምዕራፍ 2 አንቀጽ 94(1) እና 98 መሰረት ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በመንገድ ትራንስፖርት መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቱ ለመንግስት የተሰጡ መብቶች ማስፈጸሚያ የስራ ሂደት እና በኢንተለጀንስ ቡድን መካከል የመረጃ ልውውጥ ደካማ መሆን ምክንያት የተጭበረበረ ሰነድ በመጠቀም ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ከቀረጥ ነጻ የገቡ ተሽከርካሪዎች ወደ ህጋዊነት እየዞሩ መሆኑን የቅ/ጽ/ቤቱ የኢንተለጀንስ ቡድን በመግለጽ ወንጀሉን ለመከላከል እንዲቻል ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር እንደሚገባው ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች እና የስራ ክፍሎች የላከውን ደብዳቤ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም በዚሁ መሰረት የተስተካከለ አሰራር አለመኖሩ ፤

3.7.2 የወጪ ንግድ (Export) ቀረጥና ታክስን በተመለከተ

- በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች በአዋጅ ቁጥር 543/1999 አንቀፅ 11(7) መሰረት ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ አራት ድርጅቶች ጥሬ ዕቃ ያስገቡ እና ጥሬ እቃው ስራ ላይ ውሎ ምርቱን ወደ ውጭ መላክ ያለባቸው ቢሆንም፣ ምርቱ ሳይላክ ከአንድ አመት በላይ የቆየና የፈቃድ ማራዘሚያም ያልተደረገ መሆኑ፣ ይህም በማበረታቻ መልክ ቀረጥ ሳይከፈልበት ወደ አገር ውስጥ የገባ ጥሬ እቃ ለተባለው ዓላማ ሳይውል በሀገር ውስጥ ገበያ ሊሸጥና መንግስት ሊያገኝ የሚገባው የውጭ ምንዛሬ ሊያሳጣ እና ሊሰበሰብ የሚገባው ቀረጥና ታክስም ላይሰበሰብ ይችላል፡፡
- ሳባ ሃር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወደ ውጪ የላካቸው እቃዎች ዋጋ ሲታይ በአንድ የዋጋ ደረሰኝ ላይ የተገለጹ አንድ አይነት የዕቃ ሞዴል ያላቸው እቃዎች በተመሳሳይ ቀን እና ዲክላራሲዎን ቁጥር አማካኝነት የተላኩ እቃዎች የተለያየ ዋጋ ተሰጥቷቸው አንዳንዶቹን በዝቅተኛ የነጠላ ዋጋ በማስላት መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን የውጭ ምንዘሬ አነስተኛ እንዲሆን መደረጉ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ መንግስት ሊያገኝ የሚገባው የውጭ ምንዛሬ በUSD 1034.00 አንሶ ተገኝቷል፡

3.7.3 የሌሎች መ/ቤቶች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

በቤተ-መንግስት አስተዳደር፣

- በቤተ መንግስቱ ቅርንጫፎች ከልዩ ልዩ የአትክልትና የአዝዕርት ምርት ሽያጮች ገቢ የሚሰበሰብ ቢሆንም፣ የተመረቱት ምርቶች ከማሣ ወደ ንብረት (ሽያጭ) ክፍል ገቢ ከተደረጉ በኋላ በገቢም ሆነ በወጪ የማይመዘገቡ መሆኑ፣የዋጋ ትመና ውሳኔ የሚያሳይ ማስረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ የዋጋ ትመናው ሂደት ግልጽነት የጎደለው መሆኑ፣

- ከዋናው መ/ቤት የመጡ ደረሰኞች በሞዴል 19 ወይም በመዝገብ የማይመዘገቡና በአመቱ መጨረሻ የደረሰኞች ቆጠራ ተከናውኖ የማያውቅ መሆኑ፣
- በሁለቱም ቅርንጫፎች ቀድመው የነበሩት ሠራተኞች ከቦታቸው ሲነሱ የተሰራባቸውንም ሆነ ያልተሰራባቸውን የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ርክክብ የማይደረግ መሆኑ፤
- የፌደራል ስፖርት ኮሚሽን በስታዲዮም ዙሪያ ከሚያከራያቸው የንግድ ቤቶች የሚሰበስበው የኪራይ ገቢ ከ15 ዓመታት በፊት በተተመነ ዋጋ መሰረት መሆኑና አንዳንድ መ/ቤቶችም ምንም ባልተጠናና በሚመለከተው አካል ባልተፈቀደ የዋጋ ታሪፍ ገቢ የሚሰበስቡ መሆኑ ፤
- በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ብር 98,277.62 የያዙ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለተቀነሰ ገንዘብ የሚሰጥ ደረሰኝ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡
- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቁጥር አውግ-54/ በቀን 9 ነሐሴ 2000 በተላለፈ መመሪያ መሰረት ለቤት አበል የሚፈጸም ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት የተመለከተ ቢሆንም የጅማ ዩኒቨርስቲ ግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ፣የጅማ ዩኒቨርስቲ፣የጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ፣ የመዳወላቡ ዩኒቨርስቲ፣የጎንደር ዩኒቨርስቲና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ በተላለፈው መመሪያ መሰረት ለቤት አበል የተፈጸመው ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ የሥራ ግብር እንደማይቀነስ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ጎንደር ዩኒቨርስቲ ለትምህርት ወደ ውጭ አገርና ወደ ተለያዩ የትምህርት ተቋማት ለሄዱ መምህራን የመኖሪያ ቤት አበል እንደሚከፍልና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ለአስተዳደር ሰራተኞች የመኖሪያ ቤት አበል ክፍያ የሚፈፀም መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙና ተቋማቱ በመንግሥት የሚወጡ አዋጆችንና ደንቦችን በመከተል ደረሠኝ ከማሣተማቸው በፊት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማስፈቀድ እንዳለባቸው በተጨማሪም ከክፍያዎች የሚቀነሱ ገቢዎች ደንቡንና መመሪያውን ተከትሎ መፈፀም እንዳለበት በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

4 የወጪ ሂሳብ

4.1 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶች ብር 79,529,842.89 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-17 ተመልክቷል/

ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ለመ/ቤቱ የበላይ ሀላፊ ለውጭ ጉዞ ለመኝታና ቁርስ ለከፈለው የአሜሪካን ዶላር 3,450.00 እና ለእጅ ኳስ ፌደሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ ለመጠባበቂያ ለከፈለው ዩሮ 70.00፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለውጭ ጉዞ ለተከፈለው የአሜሪካን ዶላር 621.39 ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንድቀርብለት አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ አሳስበናል፡፡

4.2 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ12 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 38,666,777.07 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 16 ተመልክቷል፡፡/

ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር መረጃ ሳይደገፍ፤ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጎላ ያሉት ናቸው::

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽገልጸዋል::

4.3 <u>ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ26 መ/ቤቶች ብር 237,164,457.41 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ- 19 ተመልክቷል/

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ ክፍያዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ 119.53 ሚሊዮን፤መቀሌ ዩኒቨርሲቲ 79.29 ሚሊዮንና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ 34.52 ሚሊዮን ሲሆን፤ምክንያቶቹም የምህንድስና ክፍል የቁጥጥርና የማማከር ፈቃድ ሳይኖረው የተከፈለ፤ለማበረታቻና ለሽልማት በቦርድ ሳይጸድቅ የተከፈለ ፤ በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ዕቃዎች(materials on site) ተብሎ የተከፈለና ሌሎችም የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈጸም፤ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት መመሪያ የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተፈከለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል::

4.4 የግዥ አዋጅ ፣ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዢዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ33 መ/ቤቶች ብር 313,263,670.05 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -18 ተመልክቷል፡፡/

ከደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፤መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 224.22 ሚሊዮን ፤ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 41.38 ሚሊዮን የኢንፎረሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 7.56 ሚሊዮንና የመቀሌ ጤና ሳይንስና አይደር ሪፈራል ሆስፒታል ብር 3.06ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ካልተከተሏቸውየግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን ግዥ ውድድር ሳይደረግ በመፈጸም እና በአቅራቢነት ካልተመዘገቡ ድርጅቶች ግዥ ማከናወን የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዦ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፤መ/ቤቶቹም አስተያየቱን ተቀብለውታል፡፡

4.5 በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት በተገቢው ባለሥልጣን እየተፈቀዱ መከናወናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,623,791.53 ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ ሳይታዘዝ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -22 ተመልክቷል፡፡/

ከዚህም ዋነኛው በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 2.62 ሚሊዮን በኃላፊ ሣይፀድቅ በወጪ የተመዘገበው ነው፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ወጪ በሚመለከተው ባለሥልጣን እየተፈቀደ መከፈል እንዳለበትና የተጠቀሰውም ወጪ ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ እንዲረጋገጥ አሳስበናል፡፡

4.6 <u>የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ</u>

በበጀት ዓመቱ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶች በተለያየ ምክንያት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ ብር 2,032,423,012.07 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 12 ተመልክቷል/

የወጪውን ሂሣብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለበቸው ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሠራዊት ደመወዝ፣ ወጪ ያደረገው ብር 1.87 ቢሊዮን፤ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት 54.25 ሚሊዮን፤ እንዲሁም የውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ ብር 33.34 ሚሊዮን እና የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ብር 49.99 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሶስቱ የደህንነት መ/ቤቶች ለደመወዝ ለነዳጅና ለስልክ ወዘተ… ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ለማረጋገጥ በኮድ የተከፈለውን ደመወዝ የሠራተኞቹ ኮድ፤ የመኪኖች ታርጋና የስልክ ዝርዝሮች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር በላክው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰዉ የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ሚስጥራዊ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

4.7 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆረጠለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች በብር 83,991,211.71 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 21 ተመልክቷል/፡፡

ከዚህም ውስጥትምህርት ሚ/ር ብር 75.26 ሚሊዮን ፤ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 4.02 ሚሊዮን እና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ብር 3.9 ሚሊዮን ለተገዛው ዕቃና ንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር ለንብረት ብክነት ስለሚያጋልጥ አሠራሩ ተገቢ ሆኖ ባለመገኘቱ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊደረግና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ንብረቶች ለየመ/ቤቶቹ አገልግሎት ለመዋላቸው በማስረጃ እንዲረጋገጥ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.8 አላግባብ በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 981,864,470.70 በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 20 ተመልክቷል/

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ትምህርት ሚ/ር ብር 539.69 ሚሊዮን፤ ጂማ ዩንቨርሲቲ ብር 168.43 ሚሊዮን፤ ውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 155.84 ሚሊዮን እና፣አርባ ምንጭ ዩንቨርሲቲ ብር 68.16 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.9 በብልጫ የተከፈለ ወጪ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡ በ 7 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግዢዎች ብር 423,674.61 እና ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በ 12 መ/ቤቶች ብር 1,204,408.33 በጠቅላላው ብር 1,628,082.94 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 24 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ዕደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤በድገሚ ወጪ በማድረግ

ወይም ከተገበው ውል ውጭ በመክፈልና ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል፤ እንዲሁም በውጭ ጉዞ በዕለቱ ከነበረው የሚንዛሪ መጠን በላይ በመክፈል የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የግዢ ስርዓቱን ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.10 <u>የወጪ የሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች</u>

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ21 መ/ቤቶች ብር 20,200,592.08 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -26 ተመልክቷል/

የወጪ ሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል ትምህርት ሚ/ርብር 3.77 ሚሊዮን እና ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ብር 1.75 ሚሊዮን እና በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 1.15 ሚሊዮን ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.11 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ</u>

በወጭ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤በ12 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 20,970,915.91 የበጀት

ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2003 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -25 ተመልክቷል/

ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪውም በዚያው በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.12 ወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ8 መ/ቤቶች ብር 55,270,057.50 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያላደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዘሩ በአባሪ-23 ተመልክቷል/

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስት አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫን የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5 የተከፋይ ሂሣብ

5.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ36 መ/ቤቶች ብር 247,976,021.92 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ -27 ተመልክቷል/

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 144.43 ሚሊዮን ፤ውጭ መልዕክተኞች ብር 19.33 ሚሊዮን ፤ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 49.58 ሚሊዮን፤አዲስ አበባ ንግድ ስራ ት/ቤት ብር 9.68 ሚሉዮን ፤በወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 5.03 ሚሊዮን ፤ አርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ብር 3.85 እና ጤና ጥበቃ ሚ/ር ብር 3.15 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ፤በሌሎች መ/ቤቶችም የተከፋይ ሂሳቡ የሠራተኞች የጡረታ መዋጮንም ይጨምራል፡፡

- የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2003 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 144.43 ሚሊዮን የሠራዊቱ አባላት በተለያየ ጊዜ ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና ሂሣቡም በወጪ የተመዘገበ መሆኑንና ገንዘቡ በመከላከያ ሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ የባንክ ሂሣብ እንደሚገኝ ገንዘቡን ሙሉ በሙሉ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመለስ እንደማይቻል ሆኖም ገንዘቡ እንዳይከማች ደረጃ በደረጃ ወደ ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ የሚደረግበት አሠራር መቀየሱንና በዕቅድ መያዙን በላከው መልስ ገልጿል፡፡
- የውጭ መልዕክተኞች በላከው መልስ የተከፋይ ሂሣብ እንደተሰብሳቢ ሂሣብ ለረጅም ዓመታት ሲንከባለል የቆየ መሆኑንና የተከፋይ ሂሣብ ዝርዝር መግለጫ ከሞላ ጐደል መዘጋጀቱን ጠቅሶ ቀሪ ማስረጃዎችን የማሰባሰብና ለሌሎች መ/ቤቶች የሚከፈሉ ሂሣቦችን በማጣራት ላይ መሆኑን በላከው መልስ ገልጿል፡፡

ሆኖም የሀገር መከላከያ ሚ/ር አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት፤ ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር እየተጠየቀ እንዲከፈልና ሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ የአሰራር ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የመ/ቤቱ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከቅ/ጽ/ቤት የተላኩ ሂሳቦች በትክክለኛ የሂሳብ ሚዛናቸውን ጠብቀው ሪፖርት መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በቅ/ጽ/ቤቶችና የሂሳብ መደቦች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን የማያሳዩ በዋናው መ/ቤት እና በአምስት ቅርንጫፎች የተከፋይ ሂሳብ ብር 1,883,172.42 በዴቢት፣ ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 122.53 በክሬዲት እንዲሁም በአንድ ቅርንጫፍ የወጪ ሂሳብ ብር 13,123.80 በክሬዲት የሚታይ መሆኑ እና ይህም ተገቢው ማጣራት እና ማስተካከያ ሳይደረግ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫ ላይ ተካቶ ተገኝቷል።/ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ-32 ቀርቧል።/
- በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ብር 7,150.81፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሔራዊ ጽ/ቤት ብር 4,403.65 (ሁለት የተለያዩ ሂሳቦች) መነሻ ሰነድ የሌላቸው መሆኑ፤ኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን ብር 4,693.33፤ እንዲሁም በማዕከላዊ ስታስቲክስ ብር 700,860.51፤ በድምሩ ብር 717,108.30 ማስረጃው ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማጣራት አልተቻለም።
- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ:
- የጡረታ መዋጮ ብር 125,146.77;
- የደመወዝ የተጣራ ተከፋይ ሂሣብ ብር 23,000,357.47
- በድምሩ ብር 23,125,504.24 ሰኔ 30/2003 በተከፋይ ሂሣብ መግለጫ ውስጥ ተካተው ሪፖርት ለተደረገው ሂሣብ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- የውጭ መልዕክተኞች በተለያዩ የተከፋይ የሂሣብ መደቦች ባልተለመደ የሂሣብ መደብ (Abnormal Balance) የዴቢት ሚዛን ብር 112,770.06 የሚያሳይ፤

- በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 79,416.94 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን / Abnormal Debit balance/ በመያዙ የ2003 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሣብ ሚዛን በብር 79,416.94 አላግባብ ዝቅ ተደርጎ የተያዘ መሆኑ፤

- በሃዋሳ ዩኒቨርስቲ-የወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮለጅ የተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች በድምሩ ብር 55,713.75 ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን /Abnormal Debit balance/ የሚያሣዩ በመሆኑ የ2003 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሣብ ሚዛን በብር 55,713.75 ዝቅ እንዲል አድርጓል ፡፡

- የጅማ ዩኒቨርስቲ ግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ ብር 4,648.52 ተከፋይ ዕዳ መኖሩ የተመለከተ ቢሆንም ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ ባለመኖሩ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፤

- በሚዛን -ቴፒ ዩኒቨርስቲ የ2003 በጀት ዓመት የተከፋይ ሂሳብ መግለጫ መሰረት ለዩኒቨርስቲው ሠራተኞች ያልተከፈለ ደመወዝ ብር 342,021.17 መኖሩ የተመለከተ ቢሆንም ዝርዝር ሁኔታውን የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ ሂሣብ ውስጥ ብር 191,810.66 ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ ሂሣብ እንደሆነና በጉዳዩ ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በተደጋጋሚ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፤

- በባህርዳር ዩኒቨርስቲ ብር 5,758,577.00 እና በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ብር 7,546,129.63 በድምሩ ብር 13,304,706.63ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ የተገለጸ ቢሆንም በዝርዝር ለማየት ተሞክሮ ትክክለኛ ገጽታውን የሚያሳይ ማስረጃሊቀርብ አልቻለም፡፡

በመሆኑም ከላይ ለተዘረዘሩት የተከፋይ ሂሳቦቹን አያያዝ ድክመቶችተገቢ የማስተካከያዕርምጃ እንዲወሳድ በሪፖርታችን ባሳሰብነው መሰረት፤ አብዛኛዎቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የተቀበሉት መሆኑን በሰጡት ምላሽ አስታውቀዋል፡፡

6 የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 ከበጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ29 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 288,580,617.52 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-28 ተመልክቷል፡፡/

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 102.40 ሚሊዮን፤ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 67.40 ሚሊዮን ፤ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 47.44 ሚሊዮን ፤ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 24.07 ሚሊዮን እና ጥቁር አንበሳ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 20.82 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱም መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙም የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2 ያልተሠራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣በ92 መ/ቤቶች ብር 3,054,108,751.58 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-28 ተመልክቷል፡፡/

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት የተገኘ ሲሆን፤ በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም በመንግስት ተፈቅዶላቸው ሌሎች መ/ቤቶች

ሊጠቀሙበት የሚችሉትን በጀት እንዳይጠቀሙ ከማድረጉም በላይ የብቃት ማነስን (inefficiency) የሚያመለክት በመሆኑ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.3 ስለበጀት አጠቃቀም የታዩ ሌሎች ድክመቶች

- በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ሆኖም በድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,942,149.92፣ በደብራማርቆስ ዩኒቨርስቲ ብር 8,959,340.44 በድምሩ ብር 10,901,490.36 የውስጥ ገቢያቸውን በደንቡ መሰረት ሳያስፈቅዱ ስራ ላይ አውለው ተገኝቷል፡፡
- የደቡብ ኢትዮጵያ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ብሄራዊ ጽ/ቤት በመንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ ሀ-መ መሰረት በ2003 በጀት ዓመት የተፈቀደለትን በጀት አጠቃቀም በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችል የበጀት መቆጣጠሪያ ቋት(ሌጀር) ያላዘጋጀ መሆኑ፣
- ከሁለት የተለያዩ የሂሳብ መደቦች ማለትም ከሂሳብ መደብ 6212 ብር 25,000.00 እና ከሂሳብ መደብ 6313 ብር 10,000.00 ወደ ሂሳብ መደብ 6259 ዝውውር የተከናወነ ስለመሆኑ በዘገባ መዝገብ ላይ ማየት የተቻለ ቢሆንም፣ በድምሩ ብር 35,000.00 የበጀት ዝውውሩ የተፈቀደበት ቅጽ በማ/1 ለኦዲት ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648 አንቀፅ 10(3) መሰረት የተሰበሰበው የመንግስት ገንዘብ ወደ ተጠቃለለው ፈንድ ገቢ ማድረጉንና ሂሳቡንም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በየወሩ ሪፖርት ማድረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ወሊጋ ዩኒቨርሲቲ ከሰበሰበው ከውስጥ ገቢ ብር 9,803,084.23 ውስጥ ብር 3,017,000.00 እንዲጠቀም የተፈቀደለት ሲሆን ቀሪው ብር 6,786,084.23 እና ቀደም ካሉት አመታት የዞረው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ በአዋጁ መሰረት ፈሰስ ያለመደረጉ፣ አሰራሩ በአዋጁ መሰረት እንዲስተካከል በ2002 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት ላይ የተገለፀ ቢሆንም ምንም አይነት እርምጃ አልተወሰደም፡፡

- ከውስጥ ገቢ ወጪ ለማድረግ ከተፈቀደው በጀት በላይ ጥቅም ላይ የዋለ፤
- ጎንደር ዩኒቨርስቲ - ብር 2,419,084.20
- ባህርዳርዩኒቨርስቲ - ብር 66,247,352.36 መገኘቱ፤

ይህም ያልተጠየቀና ያልተፈቀ የበጀት ዝውውር ሊመዘገብና ሥራ ላይ ሊውል ይችላል፡፡ ከተፈቀደው በጀት በላይ ስራ ላይ ቢውል በወቅቱ ላይደረስበት ይችላል፡፡የውሰጥ ገቢን በጀት ሳያስፈቅዱ ስራ ላይ ማዋል የህግ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁን መሰረት አድርገው እንዲሰሩ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች ተገኝተል፡፡

- ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ 26 መ/ቤቶች
- ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ 15 መ/ቤቶች
- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ 22 መ/ቤቶች
- ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ 22 መ/ቤቶች
- አገልግሎት ላይ ያልዋሉ ንብረቶች የተገኙባቸው 8 መ/ቤቶች
- አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶችን በመንግስት መመሪያ መሰረት ሳያስወገዱ የተገኘባቸው 33 መ/ቤቶች
- ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው 7 መ/ቤቶች

እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ- 29 ተመልክቷል፡፡/

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፣አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንም በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.2 በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች

የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች

- በመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት፣

- በተደራራቢ ግዥ በመፈፀሙ ምክንያት በመጋዘን ውስጥ ዕቃዎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- በመጋዘን ውስጥ ያለ አገልግሎት ለብዙ አመታት የተቀመጡ የተለያዩ ዕቃዎች መገኘታቸው፣

- በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የቋሚ ዕቃ መጋዘን ውስጥ ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት ከ1999 ጀምሮ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ 10 ፕሮጀክተሮች ወደፊት ሊጠቅሙ ይችላሉ በሚል ለረዥም ጊዜ ያለስራ እንዲቀመጡ መደረጉ፣ ለብልሽት እንዲዳረጉ የሚዳርግ በመሆኑ በሽያጭ ወይም በስጦታ ሊወገዱ የሚችሉበት መንገድ መፈለግ እንደሚኖርበት
- በማእከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2003 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት መሰረት ከአየርላንድ ኢምባሲ በእርዳታ ከተሰጡት እቃዎች ውስጥ ብዛታቸው 15 የሆኑ ያገለገሉ ቋሚ ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ አለመደረጋቸው እና እቃዎቹንም የተረከበው ግለሰብ ስራው የማይመለከተው መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች</u>

በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ :

- ከግብርና ሚ/ር የመጡ የተለያዩ አሮጌ ንብረቶችን የንብረት ክፍል ሠራተኛ ያልተረከቧቸው መሆኑ፤
- የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ ከመከናወኑም በላይ ሥራው የሚከናወነው በኤጀንሲው የመልዕክት ሰራተኛ በተደራቢነት መሆኑ፣

በብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል :

- በአብዛኛው በእንስሳት እና በአንዳንድ ቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ሪፖርት ላይ የንብረቶቹ ዋጋ ያልተጠቀሰ መሆኑ ፣

በምግብክምችትአስተዳደር:

- በዋናው መሥሪያ ቤት፣ በናዝሬትና በሽንሌ መጋዘን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በእቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ በማዘጋጀት እቃዎችን የመረከብና የመጠበቅ፤ እንዲሁም የንብረት ወጪ ደረሰኝ በማዘጋጀት እቃዎችን ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰው የሚሰራ መሆኑ ፣
- በናዝሬት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በእቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ እቃዎች ከሚወገዱ እቃዎች ጋር ተቀላቅለው ተቀምጠው የሚገኙና የተለያዩ ኬሚካሎች በወለል ላይ ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ የተቀምጡ መሆኑ ፣
- በናዝሬት መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወደ መጋዘን የሚገቡ እህሎች በከፊል እንጂ በሙሉ የማይመዘኑ ሲሆን፤ በሽንሌ መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ደግሞ በጊቢው ውስጥ የሚገኙ የምድር ውስጥ ሚዛንና ሌሎች ተንቀሳቃሽ ሚዛኖች የተበላሹና ጥቅም የማይሰጡ በመሆኑ ወደ መጋዘኖቹ የሚገቡና የሚወጡ እህሎች የማይመዘኑ መሆኑ ፣

➢ የሸንሌ መጋዘን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የእሳት አደጋ መከላከያ የሌለው፤ እንዲሁም በውስጡ ያለው የተለያዩ እህሎች የታሸጉበት ማዳበሪያ በመቀደዱ በመጋዘኖቹ ወለል ላይ ስንዴ በብዛት ፈሶ የተገኘ መሆኑ ፣

በብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል :

➢ ለምርምር የተገዙት የቀንድ ከብቶች ማለትም ፍየሎችና በጎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጣቸዉ መሆኑ ፤

➢ በኢትዮጵያ የምግብ፤መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን፤ ለተሽከርካሪዎች ነዳጅ ለመቅዳት የሚጠቀሙበት አቢሲንያ ካርድ በሾፌሮች እጅ የሚቀመጥና የሚደረግ ቁጥጥር አናሳ መሆኑ፤

➢ በብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ንብረቶች እንዲሁም በስፖርት ኮሚሽን በዕርዳታ የሚገቡ የስፖርት ትጥቆች ፣ ቱታዎች ፣ ማልያዎች በመዝገብ ተመዝግበው ያልተያዙ መሆኑ ፣

➢ በቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል አንድ የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ የተረከቡትን የቡና መቁያ ማሽኖች፣ የቡና ሳንፕል ሚዛን፣ የኤሌክትሪክ ምድጃዎች ኮምፒዩተር ከነፕሪንተሩ እና የተለያዩ ቋሚ አቃዎች ያላስረከቡ መሆኑ፣

በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካልሰርቬይ፤

➢ 173 ሰራተኞች ብር 1,594,818.71 የሚገመት ንብረት እና የገንዘብ ዕዳ እያለባቸው መ/ቤቱን የለቀቁ መሆኑ፣

➢ መካኒሳ በሚገኘው መጋዘን ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸው በርካታ ኬሚካሎች ሳይወገዱ በሰራተኞቹ ላይ የጤና ጉዳት እያደረሱ መሆኑ፣

በግብርና ሚኒስቴር :

- ለረጅም ዓመታት ግምጃ ቤት ገቢ የተደረጉ፣ እና በተለይም በ1996 የተለያዩ መ/ቤቶች ሲዋሐዱ ተመላሽ የተደረጉ ንብረቶች በዓይነትና

አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡት ሳይለዩ ለቁጥጥር በሚያስቸግር ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ ፣

- መሥሪያ ቤቱ ለተመላሽ ንብረቶች ማከማቻ እንዲሆን የሚጠቀምበት 9 መጋዘኖች ሲኖረው ንብረቱን የሚረከበው እና ወጪ የሚያደርገው አንድ የግምጃ ቤት ሰራተኛ ብቻ ከመሆኑም በተጨማሪ ንብረቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል ቢን ካርድ ወይም ሌላ የመቆጣጠሪያ ስልት የሌለው፤የተሟላ መረጃ ያልያዘና ለቁጥጥር የማያመች መሆኑ፤
- በመሥሪያ ቤቱ ለረጅም ጊዜ የንብረት ማስወገድ ስራ ባለመስራቱ ምክንያት ብዛት ያለው ንብረት፤ የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸው ከሚካሎች፣ የእንስሳት መድሃኒቶች እና ሰብሎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- የተመላሽ ንብረት ቆጠራ እና የመዝገብ ማስታረቂያ ወይም ኦዲት ተደረጎ ለመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣
- በቃሊቲ በሚገኘው የመሥሪያ ቤቱ መጋዘን በክልሎች ስም የመጡ የተለያዩ ብዛት ያላቸው የግብርና መሳሪያዎች፤ እንዲሁም በዕርዳታ የተገኙ ዘመናዊ ለግብርና ሥራ የሚያገለግሉ፣ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ ፣

በአላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ፡

- በበጀት አመቱ የንብረት ቆጠራ ቢከናወንም በቆጠራ ሪፖርት ላይ በአብዛኛው የንብረቶች ዋጋ የማይጠቀስ መሆኑ፣
- በቆጠራ ሪፖርት መሰረት 10934 ሊትር ነዳጅ ጉድለት የሚያሳይ መሆኑ፣

➢ በአጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ፡

- በንብረት ቆጠራ ሪፖርት ውስጥ የዕቃዎች ዋጋ የማይሞላ (የማይገለፅ) መሆኑ፣
- የተገዛው የነዳጅ መጠን መቆጣጠሪያ (Dip stick) በትክክል ለመስራቱ በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን ያልተረጋገጠ መሆኑ ፣

- በአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ፡

  - የመንግሥትን ንብረት ሳያስረክቡ ከኮሌጁ የለቀቁሰራተኞች እንዳነበሩና የመንግሥትን ንብረት አጥፍተው በስራ ላይ በሚገኙ ሰራተኞች ላይም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ፣

- በአሳሳና አርዳይታ ኮሌጅ ግቢ ውስጥ የሚገኙት የነዳጅ ማደያ ቆጣሪዎች የተበላሹ ሲሆን፤ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

<u>የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች</u>

- በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ በብር 123,280.00 ከተገዙት 400 /Flash Disk 4 GB/ ውስጥ ብር 121,122.00 ዋጋ ያላቸው በቁጥር 393 ፍላሾች የተበላሹና አገልግሎት ላይ ሊውሉ የማይችሉ ሲሆን፣በአቅራቢው ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- በጅማ ዩኒቨርስቲ ለማትኮን ኮንስትራክሽን ድርጅት በብድር የተሰጠ ብዛት *100* እና ለኮሚኒቲ ት/ቤት ብዛት 200 ኩንታል ሲሚንቶ እንዲሁም ለጅማ ግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ በብድር የተሠጠ ቴራዞ የመሬት ምንጣፍ በቁጥር 1550 ተመላሽ አልተደረገም፡፡ በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው ለሚከናወኑ ጅምር ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚሆን ብዛት 64,400 ኩንታል ሲሚንቶ በተቋሙ መገዛቱንና ለስራ ተቋራጮች በዱቤ የተከፋፈለ መሆኑን ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ የወሰደው ሲሚንቶ ብዛትና ዋጋ እንዲሁም ተቋራጩ ተመላሽ ያደረገው ወይም የከፈለው ገንዘብና የሲሚንቶው ብዛት መከታተያና መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርድ/መዝገብ *በማቋቋም* ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች</u>

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት መጋዘን ኬሚካሎች የጐማ የውስጥ ላስቲኮች /ከመነዳሪያ/ ሌሎችም ለረጅም ዓመታት እንውገዱ እርምጃ ሳይወሰድ መገኘቱን፣
- በብረታ ብረት ልማት ኢንስቲተዩት የወርክ ሾፑ የንብረት ክፍል ኃላፊ እና የንብረት አስተዳደር ሠራተኛ በሆኑት አንድ ሰረተኛ የንበረት ገቢና ወጪ

ደረሰኝ የማዘጋጀት፣ ንብረት የመመዝገብ እና የዕቃ ግምጃ ቤት ጠበቂ በመሆን ሁሉንም ሥራዎች ስለሚያከናውኑ ቁጥጥሩ የላላ ከመሆኑም በላይ የሥራ ክፍፍል ባለመኖሩ የንብረት መባከን ሊያስከትል ይችላል።

የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል እና እንዲፈፀም መሥሪያ ቤቶቹ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል።

7.3 ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

- ሊብሬ ያልቀረበላቸው፣ በ15 መ/ቤቶች 221 ተሽከርካሪዎች፣
- በብልሽት ምክንያት የቆሙ በ19 መ/ቤቶች 219 ተሽከርካሪዎች፣
- በሊብሬውየተገለጸው ቁጥር በሞተር ላይ ካለው የተለያየ በ1 መ/ቤት 1 ተሽከርካሪ

መኖራቸውታውቋል።/ዝርዝሩም በአባሪ -30 ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፣ሊብሬ/የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ ያሌላቸው እንዲወጣለቸውና በሊብሬው ላይ የተገለጸው ቁጥር በሞተር ላይ ካለው የተለያየው ጉዳዩ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል።

7.4 የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀምበተመለከተ

- በኢትዮጵያ የምግብ፣መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን፣ ለተሽከርካሪዎች ነዳጅ ለመቅዳት የሚጠቀሙበት አቢሲንያ ካርድ በሾፌሮች እጅ የሚቀመጥና የሚደረግ ቁጥጥር አናሳ መሆኑ፣

በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

- ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ነዳጅ መሙለት ኩፖኖችን ወደ ፋክቱር መቀየር ቀሪ ኩፖኖችንና ነዳጅ የተቀዳባቸውን ፋክቱሮች የመጠበቅ ስራ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፣

ለወጪና ለገቢ ኩኖች መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑና ከወጪ ቀሪው የማይገናዘብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በተጨማሪም የተሽከርካሪዎች የነዳጅ እና የኪሎ ሜትር ቁጥጥር ሁኔታ ሲጣራ በማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ተሽከርካሪዎች ጋራዥ ከገቡ በኋላ ተጠግነው ሲወጡ ለፍተሻ በሚል ምክንያት ከ100 ኪ.ሜ በላይ የሚነዱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም ውስጥ አምስት ተሽከርካሪዎች ከ300 እሰከ 584 ኪሎሜትር የተነዱ መሆኑ ፤

በማዕከላዊ ስታስቲክስ የሰሌዳ ቁጥር 4-03084 ቶዮታ ኮሮላ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-00637 ሱዙኪ መኪናዎች በብልሽት ምክንያት በእርሻ መሣሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት ጋራዥ ጥገና ሳይደረግላቸው ከሁለት ዓመት በላይ መቆየቱ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ለነዳጅና ቅባቶች ግዥና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ምዝገባ እንዲከናወንና ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

8. <u>ልዩ ልዩ</u>

8.1 <u>የቅጥር ደንብን ተከትሎ ያልተፈጸመ የሠራተኞች ቅጥር</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሰራተኛ ቅጥር የሚፈፅመው በፌዴራል ስቪል ሰርቪስሚኒስቴር የሰራተኛ ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :

- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ :

  በሕግ ጉዳዮች ላይ የሙያ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት እንዲሰጡ የቀጠራቸው የሕግ ባለሙያ የኮንትራት ቅጥር አፈጻጸም ሁኔታ ሲገመገም :

- የኮንትራት ቅጥር የተፈጸመው በሙያው ብቃት ያላቸው ሌሎች ተወዳዳሪዎች እንዲወዳደሩ ሳይደረግ መሆኑን፣

- ግለሰቡ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀጥረው የሚሰሩ መሆኑን ካቀረቡት የሥራ ልምድ ማስረጃ ለመገንዘብ ተችሏል።በመሆኑም በታክስ አዋጁና ደንቡ መሰረት የሥራ ግብሩ ተቀናሽ መደረግ ያለበት በሌላ መንግሥት መሥሪያ ቤት ከሚያገኙት ደመወዝ ጋር ተዳምሮ በትርፍ ጊዜያቸው ካገኙት ገቢ ላይ መክፈል ያለባቸው ሥራ ግብር እንዲሰላ ማደረግ ሲገባው ግብሩ የተቀነሰው በኤጀንሲው ከሚከፈላቸው ደመወዝ ላይ ብቻ መሆኑን፣

- የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ነሐሴ 4 ቀን 2003 ዓ.ም እና ጥቅምት 28 ቀን 2003 ዓ.ም የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ከፍተኛ ኦፊሰር I በቋሚነት ለመቅጠር ባወጣው ማስታወቂ ያመሰረት ክፍት የሥራ መደቡ በፐሣ6 ደረጃ ሰባት ዓመት የሥራ ልምድ ይጠይቃል። ይሁን እንጂ ለወጣው ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ አግባብነት ያሌለው አንድ ዓመት የሥራ ልምድ ብቻ ያላቸው ግለሰብ እንዲመዘገቡ ተደረጎ በዜሮ የሰራ ልምድ በሚጠይቅ ቦታ ላይ ማስታወቂያ ሳይወጣ እንዲቀጠሩ የተደረ ገ መሆኑን፣
- በአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጁ አንድ የህግ ባለሙያ በኮንትራት እንደቀጠረ ታዉቋል፡፡ ይሁን እንጂ ቅጥሩ ማስታወቂያ ሳይወጣ እና ያለውድድር የተፈጸመ መሆኑን፣

ለመገንዘብ ተችሏል።

ከላይ በየመሥሪያ ቤቶቹ የተፈጸሙት የቅጥር አፈጻጸሞች ለጥፋት መንገድ የሚከፍቱ ከመሆኑም በላይ የሌሎች ዜጎችን ተወዳድሮ የመቀጠር መብት የሚገድቡ በመሆኑ መሥሪያ ቤቶቹ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር (የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ) ያወጣውን የቅጥር አፈጻጸም መመሪያ ተከትለው ቅጥር መፈጸም እንዳለባቸው ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ።

8.2 የቅጥር መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመ የውጭ አገር ዜጐች ቅጥር

በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 22/2/ መሰረት አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከፍተኛ ባለሙያ ለሚጠይቅ ማናቸውም ክፍት

የሥራ መደብ በደረጃ፣ በዕድገት፣ በዝውውር ወይም በቅጥር ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ለማግኘት አለመቻሉን በማረጋገጥ፣ የውጭ አገር ዜጎችን በአገር ውስጥ በኮንትራት መቅጠር አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ፣

- በመንግሥት የተፈቀደ በጀት መኖሩ፡
- ተቀጣሪዎቹ በኮንትራት የሚቀጠሩበትን የሥራ መደብ የሚገልፅ የሥራ ዝርዝር መኖሩ ፡
- የትምህርት ማስረጃው በሚመለከተው አካል አቻ ግምት የተሰጠው መሆኑ፣
- የሙያና የሥራ ልምድ ማስረጃው በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ መሆኑ፣
- ከሥራ ዝርዝሩና ከስምምነቱ አንጻ እንዲከፈላቸው የታሰበው ደመወዝ ልክ የሚያሣይ መግለጫ መኖሩ፣
- የኮንትራት ውል መኖሩ ፣

መረጋገጥ ይኖርበታል። በዚሁ መሰረት የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ በ2002 እና በ2003 በጀት ዓመት ለ15 የቻይና እና ለ2 የኬንያ ዜጎች ለሁሉም በጠቅላላው በየወሩ 17,900.00 የአሜሪካን ዶላር በመክፈል ቅጥሩን የፈጸመው ከላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች ከተሟሉ በኋላ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ቅጥሩ እንዲፈጸም በባለሥልጣን የተፈቀደ ለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም።
- ቅጥሩ የተፈጸመው ያለውድድር መሆኑ ታውቋል።
- በቻይና ቋንቋ የተጻፈ የትምህርት ማስረጃ ቢቀርብም፣ የትምህርት ማስረጃው እንዲተረጎም እንዲሁም በሚመለከተው አካል አቻ ግምት እንዲሰጠው አልተደረገም።
- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 ክፍል አንድ አንቀጽ 5 ቡዋሪስርተራቁጥር 1 እና 2 መሰረት ተቀጣሪዎቹ ታክስ እንዲከፍሉ አልተደረገም።

ይሁን እንጂ ቅጥሩ የቅጥር አፈጻጸም መመሪያን ተከትሎ አለመፈጸሙ፤ በግብር አዋጁ

መሰረትም ተገቢው ግብር እንዲከፍሉ አለመደረጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም።እንዲህ ዓይነቱ ከደንብ ውጪ የሆነ አሰራር የሌሎች ዜጎችን ተወዳድሮ የመቀጠር መብት ከመገደቡም በላይ የቅጥሩን አካሄድና አፈጻጸም ተዓማኒነት ያሳጣዋል ። መሥሪያ ቤቱም ከአገልግሎቱ ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ወጪ ሊያወጣ ይችላል።

በመሆኑም ማንኛውም ቅጥር የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ያወጣውን የቅጥር መመሪያ ተከትሎ እንዲፈጸም እንዲሁም በግብር አዋጁ መሰረት ተገቢው ታክስ እንዲቀነስ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል ።

8.3 የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የክፍያ መመሪያ መሠረት ያልተፈጸሙ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው የክፍያ መመሪያ ቁጥር 4 ከብር 50,000.00 በላይ መ/ቤቶች የሚፈጽሙት ክፍያ በቀጥታ አቅራቢው ወይም ተጠቃሚው የባንክ ሂሣብ እንዲገባ የሚያዘውን በመተላለፉ፤

- የውጭ መልዕክተኞች ብር 4129,735.31
- የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር 121,775.00

የውጭ መልዕክተኞ ለሰነአ የትብብር ፎረም በቼክ የሀገር መከላያ ሚ/ር የኢትዮጵያ አየር ኃይል በጥሬ ገንዘብ ከፍለው መገኘታቸውን በመግለጽ በመመሪያው መሠረት ክፍያዎች አለመፈጸሙ በርካታ ገንዘብ ግለሰቦች እጅ ሊገባና ለብክነት ሊጋለጥ እንደሚችል በመግልጽ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

መ/ቤቶቹ በላኩት መልስ ለወደፊቱ በመመሪያው መሠረት እንደሚፈጽሙ ተገልጿል፡፡

8.4 በተመሳሳይ ፊርማዎች ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት በቅድሚያ ለምርጫ በሰነድ ተሰጥቶ የተወራረዱ ተሰብሳቢ ሂሣቦችኦዲት ሲደረግ ብር 183,950.00 ከ32-772 ሰዎች ክፍያ በተመሳሳይ ፊርማ ተፈጽሞ ሠነድ የወሰዱት ሰዎች አወራርደው ካቀረቡት ማስረጃ መረዳት መቻሉን በመግለጽ፣ ወጪዎች ሲወራረድ የማስረጃዎች አግባብነት መጣራት እንደሚገባ በናሙና ታይቶ ከላይ የተገለጸው ሁኔታ እንዲጣራ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

8.5 ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች

በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

- ✓ በዋናው መ/ቤት የችሮታ ጊዜ ተከፋይ ሂሳብ ብር 3,864,313.29 ሁኔታው ተጣርቶ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ፤እንዲሁም የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ሂሳብ በጀት በሂሳብ መደብ 6412 መጠየቅ እንደሌለበት የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠ ቢሆንም በማሻሻያ ሀሳቡ መሰረት ተፈጽሞ አልተገኘም፡፡
- ✓ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ለአላቂና ቋሚ እቃ የንብረት መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑና የቆጠራ ውጤት ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር የሚገናዘብበት ስርአት የሌለ በመሆኑ እንዲስተካከል የማሻሻያ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም አለመስተካከሉ፣ ለበከልቻ ትራንስፖርት አ/ማህበር በነጻ የተላለፈው የቅ/ጽ/ቤቱ ፎርክሊፍት እንዲመለስ ወይም በሽያጭ እንዲተላለፍ የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አልተወሰደም፣ የጉምሩክ ስነስርአት ሳይፈጸምባቸው ከተከፈቱ ከአመት በላይ የሆናቸው 15 ዲክላራሲዎኖች ቀጣይ የጉምሩክ ስነስርአት ያልተፈጸመባቸው በመሆኑ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ የማሻሻያ ሀሳብ ቢሰጥም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- ✓ በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት ከአንድ ድርጅት ብር 255,617.74 ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ በመሆኑ ቅ/ጽ/ቤቱ ከሚመለከተው ድርጅት ቀሪ ሂሳቡን እንዲሰበስብ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ቀሪ ሂሳቡን ለመሰብሰብ የተወሰደ ምንም አይነት እርምጃ አለመኖሩ፤

በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት 27 የቫውቸር ተጠቃሚዎች በወቅቱ ሂሳባቸውን ያላወራረዱ በመሆኑ፣ የተወሰነላቸውን የጊዜ ገደብ ጠብቀው ባለመጓጓዛቸው ከተቀጡ 5 ድርጅቶች እና ወኪሎቻቸው ሊሰበሰብ የሚገባው ቅጣት ባለመሰብሰቡ፣ ለመንግሥት ገቢ ሳይደረግ የተገኘ የዋስትና ጊዜያቸው ያለፈበት የ457 ዲክላራሲዎን የቦንድ ሂሳብ የተገኘ በመሆኑ በአዋጁ መሰረት እርምጃ

አለመወሰዱ እና ለኦዲት ሥራ ያልቀረቡ 15 ድክላራሲዮኖች ተፈልገው በነዚህ ዲክላራሲዮኖች የተሰበሰበው ገቢ ትክክለኛነት እንዲጣራ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የእርምት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

<u>በንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች</u>

<u>የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር</u>

በ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ውጤት ብር 1,275,750.00 ለአሰልጣኝ፣ ለቱቶር እና ለወታደራዊ አሠልጣኞች ከውል ውጭ በብልጫ የተከፈለው ያልተተካ መሆኑን፤

<u>የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት</u>

በ1994 ዓ.ም ለትምህርት መሣሪያዎች አቅራቢ ድርጅት ለተከፈለው ብር 279,101.07 ንብረቱ ለጽ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ /ሞዴል/19/ ያልቀረበለት መሆኑ፣

- በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት እና በተቀጽላ ሌጀር ልዩነት መኖሩ፣
- ከጽ/ቤቱ ሠራተኞች ለረጅም ዓመት ያልተወራረደ ብር 183,482.74 መኖሩ፣
- በጽ/ቤቱ ኦዲት መምሪያ በሰኔ 2 ቀን 2002 በተጻፈ ደብዳቤ ብር 1,574,134.88 በሁለት ክፍሎች ጉድለት መገኘቱን እንደተገለጸ በመጥቀስ አስፈላጊው ማጣራት ተደርጐ እርምጃ እንዲወሰድ በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ያሳሰብን ቢሆንም፤ተገቢ እርምጃ አለመወሰዱ፤

<u>በልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች</u>

- ➢ በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሁለት ሠራተኞች ወደ ውጪ ሀገር ሲሄዱ ያለ አግባብ በብልጫ 320 የአሜሪካን ዶላር የተከፈላቸው ላይ ምንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

- ➢ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በአንድ ትልቅ መጋዘን፣ ጊዜ ያለፈባቸው ብዛት ያላቸው ፀረ ተባይ ኬሚካልና ዲዲቲ በመኖራቸው ፤ በዕቃ ግምጃ ቤት ባለበት አካባቢ መጥፎ ሽታ የፈጠረ ከመሆኑም በተጨማሪ ግምጃ ቤቱ በእርጅና ምክንያት በመፍረስ ላይ የሚገኝመሆኑ፣

- በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር:
    - በግንባታ የሥራ ክፍያ ወቅት ብር 23,440,193.83 የተጨማሪ እሴት ታክስ አሁንም ያልተሰበሰበ መሆኑ ፣
    - የቅድመ ክፍያንና የመያዣ ሂሣብ ሳይቀነስ ለተቋራጩ ብር 132,710,589.58 የተከፈለ መሆኑ ፣
    - በወጪ ተመዝግቦ ለተገኘው የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ ብር 113,692,327.25 ማስተካከያ ሳይሠራለት የተገኘ መሆኑ ፣
- በምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ለብር 310,240.46 የተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች የተሰሩበት ምክንያት አይታወቅም። በተጨማሪም ማስተካከያ ሊሰራላቸው ለሚገቡ ሂሳቦችም የተሰራው ማስተካከያም ቢሆን በትክክለኛው የገንዘብ መጠን ካለመሆኑም በላይ ሂሳቡ እንዲገጥም ለማድረግ ብቻ የተሰራ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በ2002 በጀት ዓመት በናዝሬት መልካሳ ላይ ባለ 2 ክፍል ቢሮና ባለ 3 ክፍል ማሰልጠኛ የፋይበር ተንቀሳቃሽ ቤት ለማሰራት ከደጀን አቬሽን ኢንጅነሪንግ ኮምፕሌክስ ጋር በብር 1,109,380.00 ዉል ገብቶ የውሉን 50% ክፍያ ብር 554,690.22 በመፈጸሙ ፣የግንባታውን ቀጣይ ሂደት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተከስተዋል። ይኸውም :
    - ኤጀንሲው ሚያዚያ 8,2002 ዓ.ም ግንባታውን ከሚያከናውነው ከደጀን አቬሽን ኢንጅነሪንግ ኮምፕሌክስ ጋር በፈጸመው ውል ላይ ቀሪው 50% ብር 554,690.22 ርክክቡ እንደተፈጸመ በሶስት ቀናት ውስጥ የሚከፈል ለመሆኑ የተመለከተ ቢሆንም : ኤጀንሲው ግንባታው በተገቢው መንገድ ለመጠናቀቁ በቅድሚያ ባባለሙያ ሳያረጋገጥና ርክክቡ ሳይፈጸም የችሮታ ጊዜ ክፍያ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጠይቆ ቀሪውን ክፍያ በሙሉ ለደጀን አቬሽን ኢንጅነሪንግ ኮምፕሌክስ ፈጽሞ ተገኝቷል።
    - በዉሉ አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 6.1 መሰረት ዉሉ በተፈረመ በስድስት ሳምንት ጊዜ ዉስጥ ድርጅቱ ስራዉን አጠናቆ እንደሚያስረክብ

ሥምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም ስራዉ ከተጀመረ ከአስራ ሰባት ወራት በላይ በኋላም ርክክብ ያልተፈጸመ መሆኑ ታውቋል ።

- ሐምሌ 1997 በወጣው የግዥ መመሪያ አንቀጽ 11 ተራ ቁጥር 11.14 መሰረት ደጀን አቬሽን ኢንጂነሪንግ 10% የውል ማስከበሪያ ብር 110,938.00 እንዲያሲዝ ያልተደረገ መሆኑ ተገልጾ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በ2002 በጀት አመት ሂሳብ ሪፖርት ላይ የተገለጸ ቢሆንም፤ ይህ ሳይፈጸም ሙሉ ክፍያው እንዲፈጸም ተደርጓል። አሰራሩ የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ሆኖ ተገኝቷል።

ከላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች በ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም የማስተካከያ እርምጃ ሣይወሰድባቸው ተገኝተዋል፡፡

ይሁን እንጂ በተሰው የኦዲት የማሻሻያ ሃሳብ መሠረት እርምጃ አለመውሰድ አግባብ አለመሆኑን ገልፀን የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት አስተያየቶች መሠረት እርምጃ መወሰዱን በቅርብ ክትትል እንዲያደርጉ አስገንዝበናል፡፡

9. <u>የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብ</u>

9.1 <u>የ2003/4 ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶችና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች</u>

በአሁኑ ወቅት የሚያከናውነው ኦዲት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት ሲሆን፣ ይህም ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

ስለሆነም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሁለተኛ ዙር (PBS II) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲት ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ በመሆኑ፣ በየሩብ ዓመቱ እየተጠቃለለ የሚላከው የተከታታይ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን፣ በዓይነት ላይ (Qualitative) በመሆኑ፣ ዋና ዋና ግኝቶች የሚባሉት በዓይነት እንጂ በመጠን አለመሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

በመሆኑም በ2003/4 የኦዲት ዘመን ለተከናወኑት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የኦዲት አስተያየቶችና በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያላቸው በመሆኑ፣ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶቹ በአንድ ላይ ተጠቃለው በሚከተለው ሁኔታ ቀርበዋል፡፡

እንዲሁም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጀክት የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ ቀርቧል፡፡

9.2 በ2003/4 የኦዲት ዘመን የታዩ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች

በአሁኑ ወቅት የተወሰነ መሻሻል ቢታይም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በበርካታ የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ውስጥ በመታየት ላይ ናቸው፡፡ እነሱም;-

- በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ አልፎ አልፎ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች አልፎ አልፎ በወቅቱ አለመወራረዳቸው፣
- የተወሰኑ ክፍያዎች በበቂና አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች አለመደገፋቸው፣
- የሂሣብ እንቅስቃሴዎች(Transactions) አልፎ አልፎ በወቅቱ አለመመዝገባቸው፣
- ወርሃዊ የሂሣብ መግለጫዎች አልፎ አልፎ በወቅቱ እየተዘጋጁ ለሚመለከተው ክፍል አለመላካቸው፣
- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአብዛኛው መ/ቤት አለመቋቋም፣

- ቋሚ ዕቃዎች በአብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ የማይወገዱ መሆኑ፣
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በአብዛኛው የማይመዛዘኑ መሆኑ እና
- ባለፈው ኦዲት ወቅት በታዩ ድክመቶች ላይ በአብዛኛው የማሻሻያ እርምጃ አለመወሰዱ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ የሚከተለውን ይመስላሉ፡-

- ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣
- ከፍተኛ የሥራ ጫና መኖር፣ እና
- የግንዛቤ ማነስ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

9.3 በ2003/4 የኦዲትዘመንበተከናወኑተከታታይኦዲቶችላይ የተሰጡ የውስጥ ቁጥጥር ኦዲት አስተያየቶች

በ2003/4 የኦዲት ዘመን (ከጥር/2003 እስከ ታህሣሥ/2004) 262 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሁለተኛ ዙር (PBS II) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች የተከናወኑ ሲሆን፣ በተከታታይ ኦዲቱ ወቅት በወስጥ ቁጥጥር ድክመቶች ላይ የተሰጡት የኦዲት አስተያየቶች (Audit Opinions) እንደሚከተለው ተጠቃሎ

ተ.ቁ	የተሰጠው የኦዲት አሰትተያየት	ብዛት በቁጥር	በመቶኛ (%)
1	ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified) የኦዲት አስተያየት	6	2.3
2	ነቀፌታ ያለበት (Except for) የኦዲት አስተያየት	255	97.3
3	ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse) የኦዲት አስተያየት	-	-
4	አቋም የማይወስድ (Disclaimer) የኦዲት አስተያየት	1	0.4
ድምር		262	100

በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-33 (Annex I) በሚል ተመልክቷል/

9.4 <u>የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ፕሮጀክት የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት</u>

የመሠረታዊ አገልግሎቶች 'PBS II' ፕሮጀክት የ2003 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ (PFS) የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን በመከተል፤ በስምምነቱ በተቀመጠው (TOR) መሠረት ኦዲት ተደርጎል፡፡ የኦዲት ስራው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ደረጃ በተዘጋጀው የተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የተከናወነ ዓመታዊ ኦዲት ሲሆን የተሰጠው የኦዲት አስተያየት "ነቀፌታ የሌለበት" (Unqualified) ነው፡፡

10. <u>የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች</u>

የክዋኔ ኦዲት መሠረታዊ ተልዕኮ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች የተመደበላቸውን የሰው ኃይል፣ ገንዘብና ቁሳቁስ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በመጠቀም እንቅስቃሴአቸውን በብቃት በማከናወን የተሰጣቸውን የሥራ ኘሮግራም ከግብ በማድረስ የሚጠበቀውን ውጤት ማስገኘታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት አካሂዶ የታዩ ድክመቶች እንዲስተካከሉ ለሥራ አመራሩ ተገቢውን የማሻሻያ ሃሣብ ማቅረብና ተፈፃሚነታቸውንም በመከታተል ስኬታማ ውጤት እንዲገኝ መርዳት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ነው::

የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀዷቸውን ሥራዎች በተመደበላቸው በጀት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እና በቅልጥፍና ማከናወናቸውን እንዲሁም የሥራ ኘሮግራሞቻቸው ስኬታማ መሆናቸውን የፌዴራል ዋናው ኦዲተር አጣርቶ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 በተሰጠው ስልጣንመሠረት በተለያዩ መ/ቤቶች/ፕሮጀክቶች 17 የክዋኔ ኦዲቶች አድርጎ፣ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የታዩ ጉልህ የሆኑ ግኝቶች ጠቅለል ባለ መልኩ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

10.1 <u>በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጭ አገር ስለሚሠሩ ኢትዮጵያውያን የሥራ ሥምሪትና ደህንነት አጠባበቅ እና ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተቀጥረው ስለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ</u>

- በናሙና ከታዩት ወደ ኩዌት፣ ሳውድ አረቢያ እና የተባበሩት አረብ ኢምሬት (ዱባይ) ለመሄድ የተዘጋጁ ሠራተኞች የሥራ ውል ውስጥ ወደ ሳውዲ አረቢያ የሚሄዱ ሠራተኞች የሥራ ውል በቀጣሪው የማይፈረም፣ ሳውዲ አረቢያ

ባለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ቀርቦ ውሉ እንደማይጸድቅና የሥራ ውሉ የሚሞላውም ሆነ የቀጣሪው ፊርማ ቦታ ላይ የሚፈረመው በኤጀንሲዎች ሲሆን በቀጣሪው ያልተፈረመ እና በኢትዮጵያ ኤምባሲ/ ቆንስላ ያልተረጋገጠ ውል በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጸድቅ መሆኑ፤

- የተወሰኑ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ሠራተኞቹን ወደላኩበት አገር ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት የላኳቸውን ሠራተኞ ዝርዝር ብቻ ሪፖርት የሚያቀርቡ ቢሆንም የሥራ ፈቃድ ስለማግኘታቸው ግን በአዋጁ በተጠቀሰው መሰረት በ15 ቀን ውስጥ የማያሳውቁ መሆኑ፤
- የተወሰኑት የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ደግሞ የላኳቸውን ሠራተኞች ዝርዝርም ሆነ የሥራ ፈቃድ ማግኘታቸውን በአቅራቢያው ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ ፤
- በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው 15 ኤጀንሲዎች ውስጥ ከሁለት ዓመት በላይ የላኳቸውን ሠራተኞች ዝርዝር ሠራተኞቹን በላኩበት አገር ለሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት ያላሳወቁ መኖራቸው ፤
- ወደ ኩዌት እና ሳውዲ አረቢያ ለሥራ የሄዱ ዜጎች የሥራ ውላቸው ሲታደስ እና ሲሻሻል በአቅራቢያው ወደሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት ቀርቦ የማይጸድቅና የሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር መ/ቤት እንዲያውቀው ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክትትል ያገኛቸውን ጉድለቶች እና ግድፈቶች እንዲያስተካክሉ ለኤጀንሲዎቹ የሚያሳውቅ ቢሆንም፤ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት በስተቀር የእርምት እርምጃ በማይወስዱት ላይ ፈቃዳቸውን የማገድ ብሎም የመሰረዝ እረምጃ አለመወሰዱ፤
- በናሙና ከተመረጡት 15 የሥራ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የአቤቱታ ፋይል ለመረዳት እንደተቻለው ከውጭ አገር ሥራ ሥምሪት ጋር በተያያዘ ለኢትዮጵያ ኤምባሲ/ቆንስላ ጽ/ቤት እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የቀረቡ ለ181 አቤቱታዎች መልስ ለማግኘታቸው መረጃው ለኦዲት አለመቅረቡ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡ 15 ኤጀንሲዎች የጠቅላላ ጉዳይ ፋይል ለመረዳት እንደተቻለው ኤጀንሲዎቹ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት ማሟላት ከሚገባቸው መስፈርቶች ውስጥ ሳያሟሉ ፈቃድ የሚሰጣቸው መሆኑ፤

- በውጭ አገር የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ቅርንጫፍ ቢሮዎችን ለመክፈት ሚኒስቴር መ/ቤቱን ሲጠይቁ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ኤጀንሲው በክልሉ ውስጥ ቅርንጫፍ ለመክፈት እንዲችል ትብብር እንዲደረግለት ደብዳቤ ከመጻፍ ውጪ በየትኛው ከተማ ወይም ሥፍራ እንደሚከፍቱ ሳያረጋግጥ የሚጽፍ ሲሆን ኤጀንሲዎቹም ሆነ ክልሎቹ ቅርንጫፍ ቢሮዎች በትክክል በየትኛው ስፍራ እንደተከፈቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማያሳውቁ ወይም ሪፖርት የማያደርጉመሆኑ፤
- በአዋጅ ቁጥር 632/2001 መሰረት በአሰሪው መሸፈን የሚገባውን የመግቢያ ቪዛ ክፍያን ሠራተኞቹ እንዲከፍሉ እየተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ ከቀረበላቸው 72 ወደ ውጭ ለሥራ ለመሄድ ከተዘጋጁ ሠራተኞች እንደተገለጸው ያለአግባብ እንዲከፍሉ የተደረገውን የመግቢያ ቪዛ ክፍያን ሳይጨምር ከብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር) እስከ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) የሚደርስ በድምሩ ብር 315,808.00 (ሦስት መቶ አስራ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር) ለኤጀንሲዎቹ በብልጫ መክፈላቸው መገለጹ፤
- በናሙና የታዩት 15 የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ከውጭ አገር ያገኙትን የውጭ ምንዛሪ በአገር ውስጥ ባንክ ገቢ ለማድረጋቸው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ያደረጉበት ማስረጃ አለመገኘቱ/አለመቅረቡ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ውጭ ለሥራ የሄዱ ሠራተኞች ከሄዱ በኋላ የሚሠሩት ሥራ በትክክል ውሉ ላይ የተመለከተው መሆኑን የሚያረጋግጥበት እና የሚገኙበትን ሁኔታ ለመከታተል የሚያስችል የክትትል ስርዓት አለመዘርጋቱ፤ ሠራተኞች የሚገኙበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ የሚደረግ ክትትል የሌለ ሲሆን ክትትልና ቁጥጥር የሚደረገው ከሠራተኛዋ ቤተሰብ ወይም ከራሷ ከሠራተኛዋ አቤቱታ ሲቀርብ ብቻ እንደሆነ መገለጹ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ እስከ ጥቅምት 2004 በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ለተሰማሩ የውጭ ሀገር ዜጎች የሥራ ፍቃድ ሲሰጥም ሆነ ሲያድስ ለክልሉ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ አለማሳወቁ፤
- ባለፉት ሦስት በጀት ዓመታት(ከ2001-2003) በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ለሥራ ለተሰማሩ 14,773 (በአዲስ አበባ 12,015፤ ኦሮሚያ 1,903፣ ትግራይ 414፣

ድሬዳዋ 302፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል 83) የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የተሰጠ ቢሆንም የሠራተኞቹ መረጃ ለየክልሎቹ አለመተላለፉ፤

- ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ሲጠየቅ ሥራው በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ሊሸፈን አለመቻሉ፣ በመስኩ ኢትዮጵያዊ ባለሙያ የሌለ ወይም እጥረት መኖሩ፣ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ፈቃድ የሚጠይቁት ድርጅቶች /አሠሪዎች እንዲያረጋግጡ አለመደረጉ፤

➢ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ከተሰጣቸው የሥራ መስኮች መካከል 132 ሰራተኞች በሂሳብ አያያዝ (accountant)፣ 223 በአናጢነት (Carpenter)፣ 12 በጸሀፊ (Secretaries)፣ 30 በስፌትና ተመሳሳይ ስራዎች ('TEXTILE, GARMENT AND RELATED TRADES WORKERS)፣ 43 ፋይናንስ ማናጀር፣ 63 ምግብ አብሳይ፣ 15 ሾፌር፣ 13 ገንዘብ ያዥ፣ 254 አሰተማሪዎች፣ 20 ቀለም ቀቢ፣ 11 እንጨት ሠራተኛ ይገኙበታል፡፡ይሁን እንጂ በአገር ውስጥ ባለሙያ የሚሸፈን ሥራ በውጭ ዜጎች እንዲሸፈን መደረጉ የሥራ አጥ ቁጥርን ከመጨመሩም በላይ በሙያው ብቃት ያላቸው ዜጎች ያላቸው የሥራ ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ ጉዳዩ ጠንክሮ ሊሠራበት የሚገባ መሆኑ መገለጹ፤

- ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ለመስጠት መመሪያ የተዘጋጀና መስፈርት የወጣ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 23 የሥራ ፈቃድ ከተሰጣቸው የውጭ ዜጎች ፋይል ውስጥ የ10 ሠራተኞች የትምህርት ማስረጃ በሠራተኛው ማህደር ውስጥ ተያይዞ አልተገኘም፤ በኦዲቱ ወቅትም እንዲቀርብ ተጠይቆ አለመቅረቡ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱን በመወከል የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጄንሲ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለወሰዱ የውጭ አገር ዜጎች ፈቃድ ሲሰጥ ለተጠየቀው የሥራ መስክ አስፈላጊው የትምህርት ማስረጃና የሥራ ልምድ መኖሩን ሳያረጋግጥ ፈቃድ እንደሚሰጥ፣ እንዲሁም በየአመቱ ለፈቃድ እድሳት ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲመጡ የጎደለውን የትምርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲያሟሉ የማይደረግ መሆኑ፤

- የውጭ ሀገር ዜጎች በተቀጠሩበት ድርጅት ውስጥ ተተኪ ኢትዮጵያውያን እንዲሰለጥኑና የክህሎት ሽግግር እያደረጉ መሆኑን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት እያቀረቡ ስለመሆኑ ማስረጃ አለመቅረቡ፤ የሥራ ፈቃድ ሲታደስም ተተኪ ባለሙያ ለማፍራት ያልተቻለበት ምክንያት ሳይቀርብ ፈቃዱ የሚታደስ መሆኑ፤ እንደዚሁም ኢትዮጵያውያን ሠራተኞችን ለማብቃት የእውቀትና የክህሎት ሽግግር እየተከናወነ መሆኑን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

  በኦዲቱ ወቅት ተውቋል፡፡

በመሆኑም ወደ ውጭ አገር ለስራ የሚሰማሩ ሠራተኞችን በተመለከተ የስራ ውሎች ተገቢውን ስነስርዓት ማሟላታቸውና አግባብ ላለው አካል ቀርበው መጽደቃቸው፤ ለስራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በአዋጁና በመ/ቤቱ የወጡትን መመዘኛዎች ስለማሟላታቸው፤ ለስራ ወደውጭ አገር የተላኩ ዜጎች በሄዱ በ15 ቀናት ውስጥ ስራ ማግኘታቸውን፤ ለሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ለአገናኝ ኤጀንሲዎች የሚቀርቡ አቤቱታዎች አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ፤ ኤጀንሲዎች ለስራ ወደ ውጭ የሚልኳቸው ዜጎች ስራውን ለመስራት የሚያስችል እውቀትና ክህሎት ያላቸው ወይም እንዲያገኙ የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

በተጨማሪም ሰራተኞቹ የሚገኙበት ሁኔታ ለማውቅ የሚያስችል ክትትል ማድረግ፤የመግቢያ ቪዛን ጨምሮ በአሰሪው መሸፈን ያለባቸውን ክፍያዎች ሰራተኞቹ እንዳይከፍሉ መደረጉን ማረጋገጥ፤በሃገሪቱ ያለውን የስራ ገበያ መረጃ አጠናቅሮ ለመያዝ እና ወቅታዊ ለማደረግ፤ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የስራ ፈቃድ የሚጠይቁ የውጭ አገር ዜጎች ተፈላጊው የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ያላቸው መሆኑና ስራው በኢትዮጲያዊያን ሊሸፈን የማይችል ስለመሆኑ አስቀድሞ እንዲጣራ፤ የውጭ ዜጎች የስራ ፈቃድ ከመታደሱ በፊት የእውቀትና ክህሎት ሽግግር ስለመኖሩ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

10.2 <u>በሴቶች፤ሕጻናትናወጣቶች ሚ/ር የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ ተካትቶ ተግባራዊ መደረጉን እና በሥርዓተ ጾታዙሪያ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር ውጤታማ ስለመሆኑ</u>

- የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የስርዓተ ፆታ ማካተቻ መመሪያ (National Gender Mainstreaming Guide line) በእንግሊዘኛ ቋንቋ በማዘጋጀት ከፌዴራል እና ከክልል ለተወጣጡ በሥርዓተ ፆታ ላይ ለሚሠሩ ሥልጠና የሰጠ ቢሆንም የማስፈጸሚያ ሰነዱ በሥልጠናው ላይ ከተሳተፉ ግለሰቦች፤በተጨማሪ ለሴክተር መ/ቤቶች፣ ለክልሎች፣ ለዞኖችና ወረዳዎች እንዲደርሳቸው ባለመደረጉ በናሙና በተመለከትናቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ መ/ቤቶች ሰነዱ የማይገኝ መሆኑ፤
- በናሙና ከተመረጡ የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው የሥርዓተ ጾታ ማስፈጸሚያ ሰነድ እንዳልደረሳቸው፣ ነገር ግን ሴክተር ተኮር የሆነ የሥርዓተ ጾታ የማስፈጸሚያ ማንዋል (Sector specifc main streaming manual) በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ስልጠና የሰጡ ሲሆን፣ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣንና የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው ሰነድ እንዳልደረሳቸው እና በራሳቸውም ያላዘጋጁ መሆኑ ፤
- የሰነዱን ተግባራዊነት በተመለከተ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በሥራቸው በሚገኙ መ/ቤቶች በየስራ ዘርፉ ለመካተቱ ክትትል የሚያደርጉ ሲሆን፣ በሌሎቹ የክትትል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ ፤
- በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፤ በዞኑ ሥር ያሉ የሴክተር መ/ቤቶች ውስጥ የሥርዓተ ጾታን ጉዳይ የሚከታተል አካል በአምስቱ መ/ቤቶች ብቻ በመዋቅር ደረጃ የተቋቋመ ሲሆን፣ በሌሎቹ ግን በተጠሪ (focal person) እንደተጨማሪ ሥራ የሚሠሩ መሆኑን፣ በጎማ ወረዳ ለ10 ሴክተር ጽ/ቤቶች መዋቅሩ ያላቸው ቢሆንም፣ ከግብርና ጽ/ቤት እና ትምህርት ጽ/ቤት በስተቀር ሌሎቹ መደበኛ

ሥራቸው ሌላ በሆኑ ሠራተኞች በተጠሪነት እንደተጨማሪ ሥራ የሚሠሩ ሲሆን፣ በአጋሮ ከተማ ደግሞ በሁሉም የሴክተር መ/ቤቶች የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ የሚሠራው በተጠሪዎች መሆኑ፤

- በጋምቤላ ህዝቦች ክልል፤ በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ቢሮዎች የሴቶች ዩኒት መቋቋሙን፣ በጋምቤላ ከተማ መስተዳደር ካሉ 17 ጽ/ቤቶች ውስጥ በ8ቱ በዩኒት ደረጃ መቋቋሙን በሌሎቹ ግን እንዳልተቋቋመ፣ በአበቦ ወረዳ በ6 የሴክተር ጽ/ቤቶች የሴቶች ዩኒትን የሚከታተሉ በሹመት የተመደቡ ቢሆንም እነሱን የሚያግዝ ባለሙያ ግን ያልተመደበላቸው መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥርዓተ ጾታ ጉዳዮች በፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተገቢው መልኩ መተንተናቸውንና በየስራው ዘርፍ መካተታቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፤
- በናሙና ከተመረጡ 8የፌደራል መ/ቤቶች የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲና ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱና ተግባራዊነቱን ከዕቅድ እስከ አፈፃፀም የክትትልና የግምገማ ስርዓት የሌላቸው መሆኑ፤
- ሴቶችን አስመልክቶ የወጡና ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው ኮንቬንሽኖች አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተደራጅተው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመያዛቸው በኦዲቱ ወቅት መረጃው አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም ኮንቬንሽኖቹ/ ስምምነቶቹ መጀመሪያ በተዘጋጁበት በእንግሊዘኛ ቋንቋ የቀረቡና በፌደራሉ የሥራ ቋንቋ ወደ በአማርኛ ብሎም ወደ ተለያዩ የክልል ቋንቋዎች እንዲተረጎሙ አለመደረጉ፤
- በናሙና ከተመረጡ የፌደራል መ/ቤቶች፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲና የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን ተለይተው ስምምነቶቹ ተለይተው ያለመያዛቸው እና በስምምነቶቹ ዙሪያ ስልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

- በናሙና በተመረጡት በጋምቤላ ሕዝቦች ክልል፤ የክልሉ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ፣ የአበቦ ወረዳ የሴቶች፣ ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት የጋምቤላ ከተማ መስተዳድር የሴቶች፣ ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን፤ የዞኑ የሴቶች ሕጻናት እና ወጣቶች ጽ/ቤት፣ የአጋሮ ከተማ የሴቶች፣ ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና በጎማ ወረዳ የሴቶች፣ ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ስምምነቶቹ የሌሉና ተለይተው ያልተያዙ መሆናቸውን እና በስምምነቶቹ ዙሪያ ስልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- ከሴቶች ጋር በተያያዘ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ያለውን አመለካከትና ልማድ፤በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችና ኋላ ቀር አስተሳሰቦች የስርዓታ ጾታ ጉዳይ ቢሮዎች(ጽ/ቤቶች) ያሉባቸውን የአቅም ክፍተቶች አስመልክቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጠኑ ጥናቶች ቢኖሩም፤ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የቀረቡና የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ ወደሆነው አማርኛ እና እንደአስፈላጊነቱ ወደ የክልሉ የስራ ቋንቋዎች አለመተረጎማቸው፤ በእነዚህ ጥናቶች መሰረት እርምጃዎች የተወሰዱ ስለመሆኑ መረጃ አለመቅረቡ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የጋምቤላ እና የኦሮሚያ ክልሎች ዞኖችና ወረዳዎች የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ (ጽ/ቤት) ጋር ስምምነት ለመፈራረም ሲንቀሳቀሱ የክልሎችንም ሆነ የዞንና የወረዳ የሴት ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች እንዲያውቁት የማይደረግ መሆኑ፤
- ከዚህ ቀደም በሴቶች ልማት ፈንድ አማካኝነት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በጋምቤላ ከተማ የተቋቋሙ 10 የሴቶች ማህበራት ብር 307,349.50 (ሦስት መቶ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ወስደው ሥራ የጀመሩ ቢሆንም በአሁን ሰዓት ግን ስራ ላይ የሚገኘው አንድ ማህበር ብቻ መሆኑ፤
- በሴቶች ልማት ፈንድ አማካኝነት የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው የተለያዩ አካላት የልማት ፈንዱ ሥልጣንና ኃላፊነት ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተላለፈ በኃላ ያሉበትን የፋይናንስ ሁኔታም ሆነ ፈንዱን ለወሰዱበት ዓላማ

ስለማዋላቸው ለማወቅ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ ስለመሆኑ መረጃ አልቀረበም፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በተለያየ መልክ የሚገቡ ፈንዶች ምንጫቸውና ለምን ዓላማ እንደተሰጡና የጊዜ ገደባቸውን ጭምር በሚገልጽ መንገድ ተለይተው ለመመዝገባቸውና ለመያዛቸው፣ ፈንዶቹ ለታለመላቸው ዓላማና ተግባር መዋላቸው በክትትል የሚረጋገጥበት እና የሚገመገምበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ መረጃ አለመቅረቡ፤

- በናሙና በተመረጡ የፌደራል መ/ቤቶች ውስጥ በሴቶች ዙሪያ በሚወጡ ህጎች እና ፖሊሲዎች ላይ የቤተሰብ ህጉን ጨምሮ የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጠ ቢሆንም ስልጠናው ተፈላጊውን ለውጥ ስለማምጣቱ ግምገማ አለመደረጉ፤
- በጋምቤላ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖሩ ሴቶች በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ለማድረግ ብድር የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ በክልሉ አነስተኛ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ተቋም (Micro finance) ተቋቁሞ በተወሰኑ ወረዳዎች ላይ ፅ/ቤት የከፈተ ቢሆንም የሚያበድረው ለግለሰቦች ብቻ በመሆኑ ለተደራጁ የሴቶች ማህበራት የብድር አገልግሎት ባለመኖሩ ሴቶች ተጠቃሚ አለመሆናቸው፤
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከበጎ አድርጎት ኤጀንሲና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት የፈቃድ አሰጣጥ፣ የክትትል እና የግምገማ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 621 አንቀጽ 67 የተደነገገ ቢሆንም እንቅስቃሴያቸውን ለመከታተልም ሆነ ለመገምገም የሚያስችል ስርዓት አለመዘርጋቱ፤
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራል ደረጃ ባሉ ዋና ዋና አስፈጻሚ መ/ቤቶች እና ክልሎች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት፤ የምክክር መድረክ ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ ቢሆንም ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ የተለያዩ በሴቶች ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት ስርዓት አለመኖሩ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የፌዴራል አስፈጻሚ መ/ቤቶች፣ በኦሮሚያ እና በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች ውስጥ ከሥርዓተ ጾታ ጋር የተያያዙ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ላይ የአያያዝ ችግር መኖሩ፣ በሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ፣ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚካሄዱ የተለያዩ ፕሮግራሞችና

ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሁኔታንና ለተጠቃሚዎች ያስገኙትን ፋይዳ በተመለከተ መረጃዎች ተደራጅተው ያልተቀመጡ መሆኑ፤

- በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን በተመለከተ የችግራቸውን አይነት፣ ስፋትና ጥልቀት በትክክል የሚያሳይና የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድ የሚረዳ መረጃ ከቀበሌና ከወረዳ ጀምሮ በየደረጃው እየተጠናቀረ በማእከል የሚያዝበት ስርዓት የሌለ መሆኑ፤
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጠውን ሃላፊነት ለመወጣት በሴቶች ሁለንተናዊ ደህንነት ዙሪያ አስፈላጊ መረጃዎች ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀትና ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የመረጃ ፍሰት ስርዓት ስለመዘርጋቱና ተግባራዊ ስለመደረጉ፤ ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ሥርዓተ- ጾታን የሚመለከቱ መረጃዎችን አሰባስቦና አደራጅቶ በግብአትነት ለመጠቀም ወይም መረጃውን በግብዓትነት የሚፈልጉ ሌሎች አካላት በቀላሉ የሚያገኙበትን የመረጃ አያያዝና አቅርቦት ሥርዓት ስለመዘርጋቱ መረጃ አለመቅረቡ፤
- ከተለያዩ ክልሎችና ከፌዴራል አስፈፃሚ አካላት የሚሰበሰቡ ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የልምድ ልውውጦች እና በመስክ ጉብኝት የሚገኙ መረጃዎች የሚጠናቀሩበት፣ የሚተነተኑበትና እርምጃ የሚወሰድበት ሥርዓት አለመኖሩ፤በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሴቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በመረጃ መረብ (web site) ለማሰራጨት የሚያግዝ የመረጃ መረብ አለመዘርጋቱ፤
- ሥርዓተ ፆታን ሜይንስትሪም ያደረጉ የፌደራል መ/ቤቶች፣ ድርጅቶች እና ክልሎች በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ በየሩብ አመቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት እንደሚያደረጉ ቢገለፅም ከ2000-2003 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከክልሎች የተላኩ ሪፖርቶች እንዲያቀርቡ ተጠይቆ፣ መረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ አለመቅረቡ፤

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በዚህም መሰረት የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት በፌደራል እና በክልሎች ከሚገኙ ዋናዋና በለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የስርዓተ ጾታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ ለማካተት እንዲቻል፤ የተጋዘጋጁት

የማስፈፀሚያ ሰነዶች (Gender Mainstreaming Guideline) በየደረጃው ላሉ ለፌደራል እና የክልል መንግስታት አስፈጻሚ አካላት የሚደርሱበትን፤ የስርዓተ ጾታ ጉዳዮች በፖሊሲዎች ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ተተንትነው በየስራ ዘርፉ የሚካተቱበትን፤ባህላዊ የሆኑ ሴቶችን የበታችነት የሚያንጸባርቁ አመለካከቶች እና ጎጂ ልማዳዊ ድረጊቶች በማስቀረት የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚደረጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ያስገኙትውጤት የሚገመገምበት፤ በስርዓተ ጾታ ዙሪ የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተው እና ተጠናቅረው የሚያዙበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

10.3 <u>በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን የዱር እንስሳት ልማት፤ጥበቃ እና አጠቃቀም</u>

- በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የዱር እንስሳት ብዛትና ስርጭትን ለማወቅ እንዲቻል አጠቃላይ ቆጠራ በመሬትና በአየር ለማድረግ የሚያስችል የበጀትና የማቴርያል ድጋፍ የሚያስገኝ ሰነድ በ2000 በጀት አመት ለማዘጋጀትና ፈንድ ለማሰባበስብ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፤ በዕቅዱ መሰረት ሰነዱ አለመዘጋጀቱና በአገሪቱ የሚገኙ የዱር እንስሳት አይነት፤ ብዛት እና ስርጭት ጥናትም አለመከናወኑ፤
- በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሥር የሚተዳደሩ 11 ብሔራዊ ፓርኮች እና 2 የዱር እንስሳት መጠለያ ጣቢያዎች በድምሩ 13 የጥበቃ ቦታዎች ያሉ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ ተከልለው ህጋዊ ሰውነት ያገኙት 3ቱ (የአዋሽ ብ/ፓርክ በአዋጅ ቁጥር 54/1961)፤ የሰሜን ተራሮች ብ/ፓርክ (በአዋጅ ቁጥር 59/1969) እና የአላጥሽ ብ/ፓርክ (በአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 38/1998)) ብቻ መሆናቸው፤
- ቀሪዎቹ 10 የጥበቃ ቦታዎች ህጋዊ ሰውነት የሌላቸው ሲሆን ሕጋዊ ሰውነት ያገኘው የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ የአዋሽ ከተማ በፓርኩ ይዞታ ክልል ውስጥ እየተስፋፋና ሕገወጥ የቤት ግንባታና የመሬት ምሪት እየተካሄደ በመሆኑ በዱር እንስሳቱና በመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ ተጽዕኖ እየፈጠረ መሆኑ፤

- በቀድሞው የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር በ1998-2002 ዓ.ም. በተዘጋጀው የአምስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ መሰረት እንዲሁም መ/ቤቱ ለብቻው እንደ ባለሥልጣን ከተቋቋመ በኃላ ባለው ከ2000-2002 ዓ.ም. ቀሪ የስራቴጂክ እቅድ አመታት ውስጥ ለ10 የጥበቃ ቦታዎች የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ለማዘጋጀት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በባለስልጣኑ ከሚተዳደሩት 13 የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የሰሜን ተራሮች ብ/ፓርክ በ2002 ዓ.ም.፣ የባሌ ተራሮች ብ/ፓርክ በ2000 ዓ.ም. እና የአዋሽ ብ/ፓርክ በ1984 ዓ.ም. እና በድጋሚ በ1996 ዓ.ም የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ እንደተሰራላቸው፣ አላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ በረቂቅ ደረጃ መጠናቀቁ እና የባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ ሙሉ ስራው ተጠናቆ መፅደቅ የሚቀረው መሆኑ፣ ለቀሩት የጥበቃ ቦታዎች የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ አለመሰራቱ፣
- የፓርክ ማኔጅመንት ዕቅድ ከተሰራላቸው የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ የአዋሽ ብ/ፓርክ በ1996 ዓ.ም የተዘጋጀ የፓርክ ማኔጅመንት እቅድ ቢኖረውም እየተሰራ ያለው በ1984 ዓ.ም. በተዘጋጀው እቅድ መሆኑን፣ የባሌ ተራሮች ብ/ፓርክ ደግሞ በተዘጋጀው የፓርክ ማኔጅመንት እቅድ መሰረት መተግበርን ያቆመ መሆኑ፣
- በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ስር በሚተዳደሩ የጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ህገ-ወጥ ሰፈራ (በቋሚነት እና በጊዜያዊነት) ፣ የእርሻ ስራና ግጦሽ፣ እንዲሁም ህገ-ወጥ የዱር እንስሳት አደን በኦሞ፣ በአብጃታ-ሻላ ሐይቆች ፣ በአዋሽ ፣ በባሌ ተራሮች እና በጋምቤላ ብሄራዊ ፓርኮች፣ በሰንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያ እና በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ የሚከናወን መሆኑ፣
- በዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውስጥና አካባቢ የልማት እንቅስቃሴ ከመካሄዱ አስቀድሞ የአካባቢ ተፅዕኖ ቅኝት (environment impact assessment) ከጥበቃ ቦታዎቹ የማኔጅመንት ዞን ዕቅድ (management zone plan) ወይም የልማት ፅንሰ ሀሳብ እቅድ (development concept plan) አንፃር እየተገመገመ በዱር እንስሳቱ እና አካባቢያቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር አለመሆኑ እየተረጋገጠ ስለመጽደቁ መረጃ አለመቅረቡ፣

- በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ በሦስተኛ ወገን የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎች ልማቱ ከመፈቀዱ በፊት በጥበቃ ቦታው ላይ ወይም በዱር እንስሳቱ ላይ ሊያሳድር ስለሚችለው ተፅዕኖ ልማቱ በታቀደበት ቦታ የሚገኙ የጥበቃ ቦታ ፅ/ቤቶች እና የባለሥልጣን መ/ቤቱ አስተያየት በጥናቱ ውስጥ እንዲካተት ወይም እንዲያውቁት አለመደረጉ፤

- በአሁኑ ወቅት የግንባታ ስራቸው የተጠናቀቁ እና በሂደት ላይ ያሉ በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ ከሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በአብጃታ ሻላ ብ/ፓርክ የሶዳ-አሽ ፋብሪካና የእንጉዳይና አልጌ ምርት፣ በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ የፍሎራ ኢኮ-ፓወር ፕሮጀክት በጥበቃ ቦታዎች ላይ ሊያስከትሉ ስለሚችሉት አሉታዊ ተፅዕኖ በተመለከተ ጥናት ስለመከናወኑ መረጃ አለመቅረቡ፤

- በሀገራችን ብቻ የሚገኙ (endemic) የዱር እንስሳት ዓይነት፣ ዝርያ፣ ብዛት፣ ሥርጭትና የአኗኗር ሁኔታ በተመለከተ በተወሰኑት ላይ ጥናት የተደረገ ቢሆንም ጥናቱ ሁሉንም ያካተተ አለመሆኑ፤

- በእልቂት ስጋት ላይ ለሚገኙ (endangerd) የዱር እንስሳት ዝርያዎች ጥበቃ በማድረግ ረገድ ለቀይ ቀበሮ "በኢትዮጵያ ቀይ ቀበሮ ጥበቃ ፕሮጀክት" አማከኝነት በባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ፤ ለስዋይን ቆርኬዎች በሰንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያ ተቋቁሞ ጥበቃና እንክብካቤ እየተደረግላቸው ቢሆንም፤ ለተቀሩት ለእልቂት ስጋት የተጋለጡ ብርቅዬ የዱር እንስሳትን በተመለከተ መረጃ አለመገኘቱ፤

- ከዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ውጭ ያሉት የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸው የሚተዳደሩበት ደንብና መመሪያ የሌለ መሆኑ፤

- በዱር እንስሳት ላይ የሚደርሱ የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ አደጋዎችን እና በሽታዎችን አስቀድሞ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አለመዘርጋቱ፤

- ባለሥልጣኑ የዱር እንስሳቱን ከበሽታ ለመከላከል የግብርና ሚኒስቴርን ሀገራዊ የእንስሳት በሽታ መከላከያ ሥርዓትን እንደሚጠቀሙ ቢገለጽም በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ እና በአዋሽ ብ/ፓርክ ከሚገኙት 2 የዱር እንስሳት የጤና

ባለሙያዎች በስተቀር በተቀሩት የጥበቃ ቦታዎች የዱር እንስሳት ጤና ባለሙያ አለመኖሩ፤

- በባሌ ተራሮች ብ/ፓርክ ከ2000-2003 ዓ.ም. 223 ቀይ ቀበሮ በራቢስ እና ካናይን ደስቴምበር በሚባሉ በሽታ መሞታቸውን፣ በአብጃታ-ሻላ ብ/ፓርክ ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ትንሹ ቆልማሚት የሚባል አእዋፍ ዝርያ በአልጌ መመረዝ ምክንያት እንደሞቱ፣ በሰንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያ የስዋይን ቆርኬ በአንትራክስ በሽታ መሞቱን ከየጥበቃ ቦታዎቹ ኃላፊዎች መገለጹ፤
- የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው በአብጃታ ሻላ፣ በአዋሽ፣ በነጭ ሳር፣ በባሌ ተራሮች ብ/ፓርኮች እንዲሁም በሰንቀሌ የቆርኬዎች እና በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያዎች የቤት እንስሳት ከዱር እንስሳቱ ጋር ተቀላቅለው የሚግጡ ሲሆን በሰንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው መሬት በህገ-ወጥ መንገድ በእሳት ተቃጥሎ መገኘቱ፤
- በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ የውሃ እጥረት በመኖሩ አርብቶ አደሮቹ ለራሳቸውና ለከብቶቻቸው ያከማቹትን ውሃ ዝሆኖች ስለሚጠጡባቸውና ሰብላቸውንም ስለሚያበላሹባቸው፤ በአዋሽ እና በአብጃታ-ሻላ ሐይቆች ብ/ፓርኮች፤ በስንቅሌ የቆርኬዎች መጠለያ እንደ ከርከሮና የመሳሰሉት የአርሶ አደሩን ሰብል የሚበሉና የሚያበላሹ በመሆኑ፤ እንደ አንበሳና ነብር የመሳሰሉት ደግሞ ከብቶቻቸውን ስለሚበሉባቸው በእንስሳቱ እና በአካባቢው ህብረተሰብ መካከል ግጭት እንደሚፈጠር፤ በዚህም ምክንያት ራሰቸውን፣ ከብቶቻቸውንና ሰብላቸውን ለመከላከል ሲሉ የአካባቢው ነዋሪዎች የዱር እንስሳትን የሚገደሉ መሆኑን፤
- በአብጃታ-ሻላ ሀይቆች ብ/ፓርክ ባለፉት አምስት አመታት አካባቢው ለሰጎኖቹ ለመታቀፍ አመቺ ባለመሆኑ ሊፈለፈሉ ያልቻሉ ከ600 በላይ የሚሆኑ የሰጎን እንቁላሎች በጥበቃ ቦታው መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በጥበቃ ቦታው ከዚህ ቀደም ከ 70 በላይ የነበረው የሰጎኖች ቁጥር በአሁኑ ጊዜ ሰባት የታቀፉ እንቁላሎችን ሳይጨምር ወደ 18 ሰጎኖች ዝቅ ማለቱ፤
- የአብጃታ ሀይቅን መሰረት አድርጎ በ1976 ዓ.ም. የተቋቋመው የሶዳ አሽ ፋብሪካ ሲቋቋም ከተተከለው የውሃ መሳቢያ ፓምፕ ውሃው ከ3 ኪ.ሜ. በላይ

በመቀነሱና ከፓምፑ በመራቁ፣ ፋብሪካውም ውሃውን ለመሳብ የሚጠቀምባቸው የውሃ መሳቢያ ፓምፖችና የማስተላለፊያ ፉካዎች ውሃውን በመከተል ወደ ውስጥ እየተስፋፋ መሆኑ፤

- በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ለውስጥ የተሰሩ መንገዶች ከጥበቃ ቦታዎቹ ስፋት አንፃር በቂ ካለመሆናቸው በተጨማሪ ለተሽከርካሪ አስቸጋሪና የማይመቹና የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ጥገናም የሚደረገው በሰው ሀይል ብቻ መሆኑ፤
- በ4 የጥበቃ ቦታዎች ከሚገኙት የሎጅ አገልግሎቶች ውጭ፤ በቀሪዎቹ ቦታዎች የቱሪስት አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሌሉ መሆኑ፤
- በአብጃታ-ሻላ ብ/ፓርክ ክልል ውስጥ በሻላ ሀይቅ ዳርቻ ላይ የጥበቃ ቦታው በኦሮሚያ ክልል ይተዳደር በነበረበት ወቅት በአንድ ባለሀብት ተጀምሮ የነበረ የሎጅ ግንባታ መቋረጡ፤
- በአብጃታ-ሻላ ሀይቆች ብ/ፓርክ በፓርኩ ሠራተኞች ከሚደረግ ገለፃና ከሚሰጠው የአቅጣጫ ምሪት ውጭ የትኛው መንገድ ወዴት እንደሚወስድ፣ በዚያ አካባቢ ምን አይነት መስህብ እንዳለ የሚያሳዩ አቅጣጫ ጠቋሚ ፤ ለቱሪስት ማረፊያነት የተፈቀዱ ቦታዎች እና በጥበቃ ቦታ ውስጥ የተከለከሉ ተግባራትን ማስገንዘቢያ እና አቅጣጫ ጠቋሚ ገላጭ ምልክቶች የሌሉ መሆኑ፤
- የሰንቀሌ የቆርኬዎች መጠለያ የሚገኝበት ሥፍራ ከዋናው መንገድ 10 ኪሎ ሜትር ወደ ውስጥ ገባ ያለ በመሆኑ ወደ ጥበቃ ቦታው የሚወስደው መንገድ ላይ አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች በተወሰነ እርቀት ላይ የተተከሉ ቢሆንም የመጠለያው የመግቢያ በር እና የትኬት መቁረጫ ቢሮው የጥበቃ ቦታው ክልል ስለመሆናቸው፤ በባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ እንዲሁም በጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ የጎብኚዎች ማስተናገጃ ሥፍራ የመግቢያ በር እና የትኬት መቁረጫ ቢሮ የጥበቃ ቦታው ክልል ስለመሆናቸው ማስገንዘቢያ ምልክት የሌላቸው መሆኑ፤
- በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ ግለሰቦችና ተቋማት (ሆቴሎችና የንግድ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች)

ከሚመለከታቸው አካላት ፈቃድ ሳይሰጣቸው የዱር እንስሳትን ከጥበቃ ቦታዎች ውጭ በህይወት ይዘው የሚገኙ መሆኑ፤

- የዱር እንስሳት የመያዝና የማዘዋወር ፍቃድ የተሰጣቸውም ቢሆኑ የዱር አንስሳቱን ለማቆየት የሚጠቀሙባቸው ስፍራዎች አገሪቱ የገባቻቸውን አለም አቀፍ የዱር እንስሳት ደህንነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ስለመሆኑ የሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር አለመኖሩ፤
- ከ15 በላይ ክፍሎች ባሉት የባለስልጣኑ የዱር እንስሳት ውጤቶች እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ 5287.5 ኪሎ ግራም የዝሆን ጥርስና ከዝሆን ጥርስ የተሰሩ ጌጣጌጦችን ጨምሮ ከህገወጦች የተወረሱ ብዛታቸው በቁጥር 29,899 የሆኑ 320 አይነት የዱር እንስሳት ውጤቶች በ12 ክፍሎች ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- የዱር እንስሳት ውጤቶች የሚጠበቁበት ግምጃ ቤት ከወጣት ወንዶች ክርስትያን ማህበር ጋር በአንድ ቅጥር ገቢ ውስጥ በመሆኑ ለጥበቃ አስቸጋሪ መሆኑ፤
- ባለስልጣኑ የዱር እንስሳት ውጤቶችን በአግባቡ ለማስወገድ የሚያስችል አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መመሪያ ቢኖረውም በመመሪያው መሰረት ውጤቶቹ በወቅቱና በአግባቡ እንዲወገዱ ባለመደረጉ በየመጋዘኑ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተከማቹት የዱር እንስሳት ውጤቶች በተለይም የዱር እንስሳት ቆዳዎችና በታክሲደርሚ መልክ (ህይወት ያላቸው አስመስሎ ቅርጻቸውን ጠብቆ ለማቆየት) የተሰሩት ለብልሽትና ለጉድለት የተጋለጡ መሆናቸው ፤
- በአገሪቱ 23 የጥበቃ ቦታዎች(20 ፓርኮች እና 3 የመጠለያ ጣቢያዎች)፤ 17 የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች፣ ከ 10 በላይ ክፍት የሆኑ የማደኛ ቦታዎች፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች እና የማህበረሰብ ጥበቃ ቦታዎች የሚገኙ ሲሆን የሁሉንም የጥበቃ ቦታዎች ተፈጥሮዊ፤ ባህላዊ እና ታሪካዊ ገጽታ በጥበቃ ቦታዎቹ ውስጥ ስለሚገኙ የዱር እንስሳትና አካባቢያቸው የተከናወኑ የተለያዩ ጥናቶች በተጠቃሚዎች አይነትና ፍላጎት መሰረት የተደራጀ ዝርዝር መረጃ በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የመረጃ ማዕከል የሌለና በብሔራዊ ደረጃም የተጠነቀረ የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ አለመኖሩ፤

- የአገሪቱ የዱር እንስሳት ሀብትና የጥበቃ ቦታዎችን ማራኪ ገፅታ በቴሌቪዥን፣ በሬድዮ (በኢትዮጵያ ሬድዮና በተለያየ ኤፍ. ኤም ጣቢያዎች)፣ በሶኒክ እስክሪን፣ በቢልቦርዶች በትምህርት ሚኒስቴር የፕላዝማ ፕሮግራም፣ በአውቶብስ ማቆሚያዎች ወዘተ... የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የሚሰራ፣ በበራሪ ፁሁፎች /ብሮሸሮች/፣ መፅሄቶችና ፖስተሮች እንዲሁም በባለስልጣኑ መ/ቤት ድህረ ገፅ የማስታወቅ ስራ የሚካሄድ ቢሆንም፣ያንጉዲራሳ፣ አብያታ ሻላ እና ኦሞ ብሔራዊ ፓርኮችን በተመለከተ በድህረ ገፁ ላይ የተቀመጡት መረጃዎች የጥበቃ ቦታዎቹን አሉታዊ ገጽታ ያካተቱ ሲሆን የገራይሌ ብሔራዊ ፓርክን በተመለከተ ምንም አይነት መረጃ አለመካተቱ፣

  በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን በተመለከተ በየደረጃው ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የዱር እንስሳቱ ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ የሚያገኙበት፣በዱር እንስሳቱና በአካባቢው ነዋሪዎች መካከል ግጭትን የሚያስነሱ ጉዳዮችን በመለየት በጋራ መፍትሄ የሚፈለግበት፣ የሁሉንም የጥበቃ ቦታዎች ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ ገጽታ በጥበቃ ቦታዎቹ ውስጥ ስለሚገኙ የዱር እንስሳትና አካባቢያቸው የተከናወኑ የተለያዩ ጥናቶች በተጠቃሚዎች አይነትና ፍላጎት መሰረት የተደራጀ ዝርዝር መረጃ በብሔራዊ ደረጃ ተጠነቅሮ በመረጃ መረብ እንዲያዝና በየጥበቃ ቦታዎች የመሰረተ ልማት አውታሮችን በማስፋፋት ለጎብኚዎች የተመቻቸ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደረግ እንደሚገባ በሪፖረታችን በሰጠናቸው የማሻሻያ ነጥቦች አሳስበናል፡፡

10.4 <u>በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የመስኖ ልማት አፈጻጸም በተመለከተ</u>

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የፕሮጀክቶች አዘገጃጀት መመርያ መሰረት የፕሮጀክቶች ጥናት ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች የፕሮጀክት ዑደትን የተከተሉ መሆን ሲገባ፣ በቆቦ ጊራና የከርሰ-ምድር መስኖ ፕሮጀክት በ 700 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈው የነባሩ ዲዛይን (Semi-Pressurized Irrigaiton System) ላይ የተወሰኑ ማሻሻያዎች ሂደቱን ሳይጠብቁ መደረጋቸዉ ፣

➤ ለኦፕሬሽን በንጽጽር አስቸጋሪ መሆናቸዉ፤ የማንሆል መክፈቻና መዝጊያ በሮች በቀላሉ መክፈትና መዝጋት አለመቻሉ እና ፍትሃዊ የዉሃ ስርጭት አለመኖር መታየቱ፤

➤ በማንሆሎች አፍ ከፍተኛ ደለል መግባትና በዚህም ሳቢያ ዉስጥ ለዉስጥ የተቀበሩ ቧንቧዎች የመደፈን ዕድላቸዉ ሰፊ መሆኑና ከፍተኛ የሆነ ደለል የማስወገድ ስራ ስለሚጠይቅ፤

➤ ማንሆሎች መዝጊያ ስለሌላቸው ህጻናትና ሌሎች አዉሬዎች በቀላሉ ሊገቡና ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችል መሆኑ፤

➤ በነባሩ ዲዛይን ያለዉን ሲስተም ወደ ጠብታ (Drip) እና የርጭት (Sprinkler) መስኖ ለመቀየር ቢፈለግ ቧንቧዎቹ የዉሃ ግፊት የመቋቋም ብቃታቸዉ አነስተኛ በመሆኑ፤ የዲዛይን ለዉጥ ማስፈለጉና፤የዲዛይን ማሻሻያ በመደረጉ ለግንባታ የተጠቀሙባቸው አንዳንድ ቁሳቁሶች በሃገር ዉስጥ በቀላሉ የማይገኙ መሆናቸዉ የአዲሱ ዲዛይን ችግሮች እንደሆኑ በፕሮጀክቱ አማካሪ መሃንዲስ መገለጹ፤

➤ በዉሃ እና ኢነርጂ ሚ/ር ባለቤትነት በፌዴራል የዉሃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት አማካሪነት እና በፌዴራል ዉሃ ስራዎች ግንባታና ቁጥጥር ድርጅት ተቋራጭነት የግንባታ ስራው እየተካሄደ ያለው የርብ መስኖና ግድብ ፕሮጀክት ጥልቅ የሆነ የደሰሳ እና የአዋጭነት ጥናት (Pre-feasibility and Feasibility Study) ሳይሰራ ወደ ግንባታ በመገባቱ የዲዛይን ለውጥ ማስከተሉ፤

➤ የደሰሳ ጥናት ፣ የአዋጭነት ጥናት ፣ ዲዛይንና የኮንስትራክሽን ስራ ጎን ለጎን ተይዞ ስለተገባ በግንባታ ወቅት ነባራዊዉ የጂኦሎጂካል ዉጤት ዲዛይን ከተደረገዉ የጂኦሎጂካል ጥናት ዉጤት ጋር ባለመጣጣሙ (ሳይት ላይ ያለዉ ማቴሪያል ከጥናቱ መስፈርት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ) የዲዛይን ለዉጥ ማስከተሉ፤

➤ በ 1,336,274,358.08 ብር ወጪ ይጠናቀቃል ተብሎ የታቀደው የርብ ግድብ ፕሮጀክት ግንባታ ግድቡ ያርፍበታል ተብሎ የታሰበበት ቦታ ላይ

ከፍተኛ የሆነ ጥልቅ የመሰረት ቁፋሮ (Excavation for Cut-off Trench) በማስፈለጉ ይቆፈራል ተብሎ ከታሰበው 125,054 ሜትር ኪዩብ አፈር በላይ የ 210,217.22 ሜትር ኪዩብ አፈር ተጨማሪ ቁፋሮ በማስከተሉ በመሰረት ቁፋሮ ላይ ይወጣል ተብሎ የታሰበውን ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲንር ስለሚያደርገው የግድቡ ግንባታ ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ የሚችል መሆኑ፤

- ከዚህ ጋር ተያይዞ በ Intake tower ላይ የተደረገው መሠረታዊ የዲዛይን ለውጥ እና የተለያዩ የስትራክቸር ማሻሻያዎች በዋጋ በኩል ያመጡት ተፅዕኖ ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚታይ መሆኑ፤
- በቆጋ መስኖና ተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት ያልተጠበቀ የአፈር ዓይነት በመገኘቱ በዲዛይን ጊዜ በተተመነው የዋጋ ዝርዝር ለዋናው ግድብ ተይዞ ከነበረው ብር 27,972,720.78 ላይ የብር 301,939.71 እና ለኋላ ፍሰት መከላከያው ተይዞ ከነበረው ብር 6,893,021.10 ላይ የብር 1,206,558.71 በድምሩ ከተያዘለት ወጪ በላይ የብር 1,508,498.42 ተጨማሪ ወጪ ማስከተሉና በፕሮጀክቱ የግንባታ የሥራ ላይ መዘግየት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ ማድረጉ፤
- በውሃና ኢነርጂ ሚ/ር የሚከናወኑ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በቅድመ ትግበራ ግምገማ ሂደት እንዲያልፉ ባለመደረጉ ለመስኖ ልማት በሚዘጋጁ ረቂቅ የፕሮጀክት ጥናት ሰነዶች የሚደረስባቸው ውጤቶች ሳይመዘኑና ሊስተካከሉ የሚገቡ ግድፈቶች የማሻሻያ ሃሳብ ሳይሰጣቸው ወደ ትግበራ እንዲገቡ መደረጉ፤
- በውሃና ኢነርጂ ሚ/ር የሚቀረጹ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በተፈቀደላቸው ወጪና በታቀደላቸው ጊዜ ሊጠናቀቁ ሲገባ የቆጋ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በአጠቃላይ በብር 405.2 ሚሊዮን ይጠናቀቃል ተብሎ በብር 715.62 ሚሊዮን በመጠናቀቁ 310.42 ሚሊዮን ብር ወይም 76.6% ተጨማሪ ወጪ ማስከተሉ፤

- እንደዚሁም ፕሮጀክቱ በጥናቱ መሰረት፣ በ 2002 ተጀምሮ በ 2008 እ.ኤ.አ መጠናቀቅ ሲገባው፣ ከታቀደው ጊዜ በሶስት ዓመታት ዘግይቶ በ2011 መጠናቀቁ፤
- የጊዳቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ስራ በ 2004 ይጠናቀቃል ተብሎ ቢታቀድም፣ እስከ ሰኔ 30/2003 ዓ.ም የተጠናቀቀው በተከታታይ የሥራ ክንውን 18.5% ብቻ መሆኑ፤
  - በየርብ መስኖ ግድብ ፕሮጀክት፣ በቆጋ መስኖና ተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት፣በቆቦ ጊራና የከርስ ምድር መስኖ ፕሮጀክት፣በጊዳቦ እና በዝዋይ መስኖ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ቢደረግም፣የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊ ለማድረግና ለማስፈጸም የጥናት ሰነዱ(ዶክመንቱ) በአማካሪዎችና ተቋራጮች እንዲሁም በአስፈጻሚ አካላቶች እጅ አለመኖሩ፤
- በዚህም ምክንያት የወረዳ ግብርና ቢሮዎችና ባለድርሻ አካላት የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት አስተያየት በእጃቸው ባለመኖሩ በውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ባለቤትነት በሚሠሩ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ በቂ የሆነ የአካባቢ ደህንነት አጠባበቅ ሥራዎችን በጥናቱ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ አለመቻላቸው፤
- የቆቦ ጊራና የከርሰ-ምድር መስኖ ፕሮጀክት የግፊት መስኖ አውታር (Piped Surface Irrigation) ዝርጋታው የመስክ ቦይ (Field canal) እስኪደርስ ሙሉ በሙሉ በቱቦ ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ ከጠብታ ወይም ከርጭት መስኖ ጋር ሲወዳደር በማሳ ውስጥ አንፃራዊ የውሃ ብክነት ያለው መሆኑ፤
- በሦስት መቶ ሄክታር ላይ የሙከራ ሰብል ምርት መመረቱን መሰረት በማድረግ የውሃ ብክነትን የሚገልፅ የተጠና ጥናት ወይም መረጃ አለመኖሩ፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሰሩ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የሚገመገምበትና ወቅታዊ ብቃታቸው የሚለካበት የምርምርና ስርፀት ፕሮግራም አለመኖሩ፤
- የግድብ ፕሮጀክቶችን ጥራት ለመጠበቅ የሚያግዝ በከፍተኛ ሁኔታ የተደራጀ ለቦራቶሪ ባለመኖሩ ከፍተኛና ለአንድ ጊዜ ብቻ የናሙና ምርመራ የሚያስፈልጋቸው ስራዎች ከሳይት ውጪ ተልከው የሚሰሩ መሆኑ፤

- የቆጋ መስኖ ተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት ዘመናዊ የመስኖ ፕሮጀክት ሲሆን ግንባታው ተጠናቆ ግልጋሎት መስጠት የጀመረ ቢሆንም ግድቡና የመስኖ አውታሩ የሚፈቅደዉ ዘመናዊ የዉሃ አጠቃቀምን መረጃ የሚሰጡ የዉሃ መጠን መለኪያዎች (Gauges) በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ እየተጠቀሙበት አለመሆኑ፤
- በክረምት መጨረሻ ላይ የተከማቸ የውሃ መጠን (Live Storage) ከአይን ዕይታ (Physical Observation) ውጭ በየጊዜው ልኬት (Measurement) እየተወሰደ የሚቀመጥ ዳታም ሆነ ጥናቶች አለመኖራቸው፤
- ከዲዛይን ጥናት ውጭ በመስኖ አውታሮች ላይ የክዋኔ ብቃት ምዘና (Performance Evaluation) የሚገልፅ መረጃዎች(ዳታዎች) አለመኖራቸው፤
- አርሶ አደሩ ለሁለት ዙር ምርት ሲያገኝ የግብርናው ምርታማነት የኑሮ ደረጃውን መሻሻሉን የሚገልፅ ተጨባጭ መረጃዎች በተደራጀ መልክ አለመኖራቸው፤
- በግምገማ/Appraisal report/ ላይ ፕሮጀክቱ አካባቢ በ22,000 ሄክታር መሬት ላይ የተፋሰስ ልማት ስራዎች እንደሚሰሩ ቢታቀድም የተሰሩ የተፋሰስ ልማቶችን የሚገልፁ ጥቅል መረጃዎች ማግኘት አለመቻሉ፤
- በዳሰሳ ጥናት ላይ ከተሰራ የውሃ ጥራት ደረጃ በስተቀር ምርት ማምረት ከተጀመረ በኋላ የተሰራ የውሃ ጥራት ናሙና አለመኖሩ፤
- የመስኖ አውታሩ ዘመናዊ በሆነ መልክ ይገንባ እንጂ ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች ባለመኖራቸው የመስኖ ቴክኖሎጂው አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ከፍተኛ ክፍተቶችንና ምርታማነት ላይ የሚኖራቸውን ተጽእኖ ለመረዳት አለማስቻሉ፤
- በአማራ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ተቋራጭነት እና በአማራ ውሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ተቆጣጣሪነት በመሰራት ላይ ያለው የቆቦ ጊራናን የከርሰ ምድር የግፊት መስኖ ፕሮጀክት የሥራ ክንውን አፈጻጸም ሪፖርት የሚቀርበው ፕሮጀክቱ ሲያልቅ ብቻ እንደሆነ መገለጹ፤

- በርብ የመስኖና ግድብ ፕሮጀክት የግንባታ ክትትል ሪፖርቶችን በተመለከተ ከተቋራጩ ወቅታዊ የስራ ሂደቱ ሪፖርት (Work Progress Report) ለውሃና ኢነርጂ ሚ/ር የሚቀርብ ቢሆንም፤ የዲዛይን ሥራው አልቆ ሥራው እየተሰራ እያለ የግንባታ አማካሪው የፌዴራል ውሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር እና የፕሮጀክቱ ባለቤት የሆነዉ የውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ተወካዮች (Consultant & Client) ብዙ ጊዜ በስብሰባ ላይ የማይገኙ መሆኑ፤

- በተጨማሪም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚላኩት ባለሙያዎች አብዛኛውን ጊዜ በግድቡ ዙሪያ በሚነሱ ማህበራዊ ችግሮች፤ ለምሳሌ የካሣ ክፍያ ችግሮች የመሳሰሉትን ለመቅረፍ የሚመጡ እንጂ በግንባታው ሂደት ያጋጠሙ ሙያዊ ችግሮች ለመፍታት የሚችሉ የቴክኒክ ሰዎች ባለመሆናቸው ለፕሮጀክቱ ግንባታ ስኬት የሚረዱ ሥራዎች አለመሰራቱ፤ በቂ ክትትልና ቁጥጥርም እየተደረገ አለመሆኑ፤

- በእያንዳንዱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ሊሳተፉ የሚገባቸው ባለድርሻ አካላት ተግባርና ሃላፊነት በዝርዝር ተለይቶ እንዲታወቅ ባለመደረጉ በናሙና በታዩ ፕሮጀክቶች ላይ ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት አለመቻላቸው፤

- በመላ አገሪቱ በተለያየ ደረጃ (በከፍተኛ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ) ለመስኖ ልማት ሊውሉ የሚገባቸው ስፍራዎች እና የለሙ መሬቶች ቢለዩም የተሟላ መረጃ በሚሰጥ መልክ በመረጃነት ተደራጅቶ አለመቀመጡ፤

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በመስኖና ድሬይኔጅ ዳይሬክቶሬት ጥናታቸው የተጠናቀቁ የመስኖ ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያገኙ ልማትን ለሚያካሂዱ ባለሃብቶች በተለያዩ ዘዴዎች የማስተዋወቅ፤ በህጉ መሰረት ማትጊያ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን የማመቻቸትና የማስፈጸም ተግባር በዕቅድ ቢያዝም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሥራ አለመከናወኑ፤

- በዚህም ምክንያት ለመስኖ ልማት ዘርፍ የሚያስፈልገውን ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ከባለሃብቶች በኢንስትመንት መልክ ተጨማሪ የፋይናንስ ድጋፍ እንዳይገኝ ማድረጉ፤

- በርብ የመስኖና ግድብ ኘሮጀክት የግንባታ ክትትል ሪፖርቶችን በተመለከተ ከተቋራጩ ወቅታዊ የስራ ሂደቱ ሪፖርት (Work Progress Report) ለውሃና ኢነርጂ ሚ/ር የሚቀርብ ቢሆንም፤ የዲዛይን ሥራው አልቆ ሥራው እየተሰራ እያለ የግንባታ አማካሪው የፌዴራል ውሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር እና የፕሮጀክቱ ባለቤት የሆነዉ የውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ተወካዮች (Consultant & Client) ብዙ ጊዜ በስብሰባ ላይ የማይገኙ መሆኑ፤

- በተጨማሪም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚላኩት ባለሙያዎች አብዛኛውን ጊዜ በግድቡ ዙሪያ በሚነሱ ማህበራዊ ችግሮች፤ ለምሳሌ የካሣ ክፍያ ችግሮች የመሳሰሉትን ለመቅረፍ የሚመጡ እንጂ በግንባታው ሂደት ያጋጠሙ ሙያዊ ችግሮች ለመፍታት የሚችሉ የቴክኒክ ሰዎች ባለመሆናቸው ለፕሮጀክቱ ግንባታ ስኬት የሚረዱ ሥራዎች አለመሰራቱ፤ በቂ ክትትልና ቁጥጥርም እየተደረገ አለመሆኑ፤

- በእያንዳንዱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ሊሳተፉ የሚገባቸው ባለድርሻ አካላት ተግባርና ሃላፊነት በዝርዝር ተለይቶ እንዲታወቅ ባለመደረጉ በናሙና በታዩ ፕሮጀክቶች ላይ ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት አለመቻላቸው፤

- በመላ አገሪቱ በተለያየ ደረጃ (በከፍተኛ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ) ለመስኖ ልማት ሊውሉ የሚገባቸው ስፍራዎች እና የለሙ መሬቶች ቢለዩም የተሟላ መረጃ በሚሰጥ መልክ በመረጃነት ተደራጅቶ አለመቀመጡ፤

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በመስኖና ድሬይኔጅ ዳይሬክቶሬት ጥናታቸው የተጠናቀቁ የመስኖ ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያገኙ ልማትን ለሚያካሂዱ ባለሃብቶች በተለያዩ ዘዴዎች የማስተዋወቅ፤ በህጉ መሰረት ማትጊያ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን የማመቻቸትና የማስፈጸም ተግባር በዕቅድ ቢያዝም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሥራ አለመከናወኑ፤

- በዚህም ምክንያት ለመስኖ ልማት ዘርፍ የሚያስፈልገውን ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ከባለሃብቶች በኢንስትመንት መልክ ተጨማሪ የፋይናንስ ድጋፍ እንዳይገኝ ማድረጉ፤

➢ ባለሃብቶች በመስኖ ልማት ዙሪያ ለመሳተፍ እና ኢንቨስት ለማድረግ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ በዘርፉ ያለውን ዕድል እንዳይጠቀሙ ማድረጉ፤

በመሆኑም የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በበቂ የደሰሳና ቅኝት ጥናቶች ላይ ተመስርተውበተዘጋጁ የዲዛይንና ግንባታ ዕቅድ መሰረት ሊሰሩ እንደሚገባ፤የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ ስራዎች በተያዘላቸው በጀትና የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ከቅድመ ግንባታ ጥናት ጀምሮ በጥቅም ላይ እስከሚውሉ ድረስ የሚታዩ ችግሮችን በማስወገድ ውጤታማ ስራ ለመስራት የሚያግዙ የአሰራር ሰርዓቶችን በስራ ላይ እንዲያውሉ፤ የዘገዩ ፕሮጀክቶች በፍጥነት ለማጠናቀቅ የሚያስችሉ የአጭር ጊዜ እቅዶች ማዘጋጀት እንደሚገባ በኦዲት ሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

10.5 በፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር የአርብቶ አደር አከባቢ የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት

የአርብቶ አደሩ የዳልጋ ከብት አመጋገብ ለማሻሻል የመኖ አዘገጃጀትና አቅርቦት የሚያድግበት ሁኔታ ሊመቻችና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተለይም አርብቶአደሩ ዓመቱን ሙሉ በአካባቢው ሊገኙ የሚችሉ የመኖ አይነቶችን ለይቶ በማወቅ ያለውን መኖ አመጣጥኖ ለመመገብ እንዲችል ግንዛቤ የሚያገኝበት ሥርዓት እንዲዘረጋ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የግብርና ሚኒስቴርን በማስተባበርና ስለ ተፈፃሚነቱም ክትትል ሊያደርግ የሚገባ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፤

➢ በናሙና ጉብኝት በተደረገባቸው የኦሮሚያና የሶማሌ ክልል አርብቶ አደር ወረዳዎች የሰብል ተረፈ ምርቶች፤ የተሻሻሉ የመኖ ዘሮችን ዘርቶ በማምረት፤ ሞላሰስና የግጦሽ ሳርን ለከብቶቻቸው በመኖነት የሚጠቀሙ ሲሆን በአንዳንድ ወረዳዎች ያለው የከብት ብዛትና የመኖ ሁኔታ/አቅርቦት የማይጣጣም በመሆኑ በአካባቢው በበጋ ወቅት ከፍተኛ የሆነ የመኖ እጥረት መኖሩ፤

➢ በኦሮሚያ ክልል ፊንቻሌና ሚኤሶ ወረዳ፤ በሱማሌ ክልል ጅጅጋ፣ ቀብሪበያ፣ ጉርሱም እና አቡበሬ ወረዳዎች፤ በአፋር ክልል ገዋኔ፣ ሚሌ፣እና አፋምቦ ወረዳዎች የሚገኘው የመኖ መጠን በወረዳው ካሉት የከብቶች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ጉብኝት ከተደረገባቸው 11 ወረዳዎች ውስጥ በ9ኙ /82 ከመቶ/የመኖ እጥረት ያለባቸው መሆኑ፤

➢ አካባቢው በተደጋጋሚ በዝናብ እጥረትና በድርቅ የሚመታ በመሆኑና፤ በፊት ከነበረው የግጦሽ መሬት ለእርሻና ለሌሎች አገልግሎቶች እንዲውል

መደረጉ፤በፊት የግጦሽ መሬት ከነበረው 50ሺ. የሚሆነው በአላስፈላጊና ለመኖነት በማያገለግሉ አረሞች መወረሩ ለመኖነት የሚውሉ ግብዓቶች አቅርቦት በወረዳው ካለው የከብት ብዛት ጋር የሚጣጣም አለመሆኑ፤

- አርብቶ አደሩ የከብቶች መኖ ችግር በሚከሰትበት ጊዜ ምግባቸውን ወደ ሚያገኙበት ራቅ ያለ አካባቢ እንዲሄዱ ስለሚገደዱ ለከብቶቹ መክሳትና መሞት ምክኒያት ከመሆኑ በተጨማሪ ለገበያ አቅርቦት ሳቢ እንዳይሆኑ እና ቆዳቸውም ሳይቀር በገበያ ተፈላጊ እንዳይሆን በማድረግ እንስሳቱ መስጠት የሚገባቸውን ውጤት ሊያስገኙ አለመቻላቸው፤
- በአርብቶ አደሩ አካባቢ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ ሲከሰት ከብቶችን ለመመገብና አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የመኖ ክምችት ሊኖርና መኖዎችንም ለማከማቸት የሚያገለግሉ የመኖ ባንኮች በየወረዳው ሊቋቋሙ የሚገባ ሲሆን፤
- በኦሮሚያና በሱማሌ ክልል አርብቶአደር ወረዳዎች የመኖ ባንኮች የሌሉ መሆኑንና በሁሉም በዕቅድ ደረጃ እንኳን ለማቋቋም የታሰበ አለመሆኑ፤
- በአፋር ክልል በገዋኔ፤ አሳይታ እና በዱብቲ ወረዳዎች የመኖ ባንክ የተቋቋመ ሲሆን፤በአፋምቦ ወረዳ አንድ የመኖ ባንክ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ግን አገልግሎት መስጠት ማቆሙን፤
- በሱማሌ ክልል በጅጅጋ፤ በጉርሱም እና በአቡበሬ ወረዳዎች የመኖ ባንክ ያልተቋቋመ ሲሆን በቀብሪበያ የመኖ ባንክ ቢቋቋምም ሥራ አለመጀመሩ፤
- በኦሮሚያ ክልል በሚኤሶ እና በፈንታሌ ወረዳዎች የመኖ ባንክ አለቋቋሙ፤
- አርብቶአደሩ የልቅ ግጦሽ ዘዴን የሚጠቀም በመሆኑ፤ የግጦሽ መሬት ከጊዜ ወደ ጊዜ የተመናመነ በመምጣቱ፣ ያለው የግጦሽ መሬትና የእንስሳት ብዛት የማይጣጣምና ከልክ በላይ ከብቶች የሚሰማሩበት መሆኑ፤
- በኦሮሚያ እና በአፋር ክልል በፊት ለግጦሽ ይውል ከነበረው መሬት ሃምሳ በመቶ/50%/ በአላስፈላጊ አረሞች መወረሩ፤መታረስ የሌለባቸው የግጦሽ መሬቶች እየታረሱ መሆኑ፣ የእንስሳት ቁጥር እየጨመረ መምጣቱና አረሞች ከመጠን በላይ በግጦሽ መሬቶች ላይ የሚታዩ መሆኑ፣ የግጦሽ መሬት አስተዳደርም ስለሌለና ባህላዊው/የጋራ/ ዘዴ በሥራ ላይ መዋሉ፤

- በኦሮሚያ ክልል የፈንታሌና የመኤሶ ወረዳዎች በአፋር ክልል በአብዛኛው ወረዳዎች ኘሮሶፒስ (Prosopis) በመባል የሚታወቀው የአረም አይነት በከፍተኛ ደረጃ በመስፋፋቱና ከወረዳዎቹ ቁጥጥር ውጪ መሆኑ፤
- በግጦሽ መሬቶች ላይ አላስፈላጊ አረሞች በስፋት መታየታቸውና ችግሩንም ለማስወገድ የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦች በመዘግየታቸው በአርብቶ አደሩ አካባቢ ላሉ የዳልጋ ከብቶች የሚሆነውን የግጦሽ መሬት እንዲያንስ እና የመኖ እጥረት እንዲከሰት ከማድረጉም በተጨማሪ ለዳልጋ ከብቶች መክሳትና መሞት ምክንያት መሆኑ፤
- በኦሮሚያ ክልል በፈንታሌ ወረዳ ኢላላ ቀረሪ ቀበሌ ለዳልጋ ከብቶች የሚሆን ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የሌለ ሲሆን፤ የኩሬውም ውሃ የደረቀ መሆኑ፣
- በሶማሌ ክልል ጅጅጋ ወረዳ በአርብቶ አደር ማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክት የተገነባው የኩሬ ውሃ /ማጠራቀሚያ ገንዳ/ የደረቀ በመሆኑ ከብቶች ብዙ ኪሎ ሜትር ውሃ ለመጠጣት ሲጓዙ እየሚውሉ መሆኑ፤
- አርብቶ አደሮቹም የከብቶቻቸውንም ሆነ የራሳቸውን ዕድሜ ለማራዘም ከሌላ ቦታ በከፍተኛ ዋጋ በቦቴ በመግዛትና በማስመጣት ወደ ጉድጓዱ በመገልበጥ ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት የሚያደርጉ ታመሆኑ፤
- በቀብሪበያ ወረዳ አርትሼክ ቀበሌ ቮካ በሚባል ድርጅት ለተሰራ የእንስሳት የገበያ ማዕከል እንዲያገለግል የተገዛ 1000 ሊትር ውሃ ለመያዝ የሚችል የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር /ሮቶ/ ያለአገልግሎት መቀመጡ ፤
- የውሃ አቅርቦቱ ባለመሟላቱ ከብቶች ውሃ ለማግኘት ሲጓዙ እየሚውሉ ሲሆን ከጠጡም በኋላ ከሁለት ቀናት በፊት እየማይመለሱ በመሆኑ ለክሳትና ለሞት መዳረጋቸው፤
- በናሙና ጉብኝት በተደረገባቸው በኦሮሚያ፤ በሱማሌ እና በአፋር ክልል በተመረጡ ወረዳዎች የተሻለ ዝርያ ያላቸውን የዳልጋ ከብቶችን የማራባትና የመጠቀሙ ሁኔታ ብዙ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ፤
- የከብቶችን ቁጥር ሳይጨምር የተሻሻለ ዝርያ ያላቸውን የዳልጋ ከብቶች በመጠቀም ውጤታማ የሆነ የአረባብ ዘዴን በመከተል የተሻለ ጥቅም ማግኘት ይቻላል የሚለው ሀሳብ በአርብቶአደሩ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ የተሰራው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ አነስተኛ መሆኑ፤

- በናሙና ከተመረጡት በኦሮሚያ ክልል በሚኤሶ ወረዳ 9 ክሊኒኮች ያሉ ቢሆንም የሚያስፈልገው ግን 46 መሆኑና አንድ የእንስሳት ክሊኒክ ተገንብቶ ያለ አገልግሎት ከአንድ ዓመት በላይ የተቀመጠ መሆኑ፣
- በሱማሌ ክልል ቀብሪበያ ወረዳ ክሊኒክ የሌለ ሲሆን አንድ የጤና ኬላ አሰራሩ ደረጃውን ያልጠበቀና ፈራርሶ በዝናብ ወቅት ውሃ የሚያስገባ መሆኑ፤
- በአፋር ክልል ገዋኔ ወረዳ የጤና ኬላ፣ በሚሌ ወረዳ ክሊኒክ የሌለ ሲሆን በሚሌ ከሚገኙት አምስት የጤና ኬላዎች አገልግሎት የሚሰጠው አንዱ ብቻ መሆኑ፣
- በአፋምቦ ወረዳ 1 ክሊኒክና 5 የጤና ኬላዎች በግንባታ ላይ የሚገኙ መሆኑ፤ በአሳኢታ ወረዳ 1 ክሊኒክና 2 ጤና ኬላዎች ያሉ ቢሆንም፤4 ክሊኒክና 7 ጤና ኬላዎች የሚያስፈልጉት መሆኑና ያሉት ክሊኒኮች በሰው ኃይልም ሆነ በመድኃኒት አቅርቦት ያልተሟሉ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ ክልል በሚኤሶ ወረዳ፤ ሱማሌ ክልል ጅጅጋ፣ ጉርሱም፣ አቡበሬና ቀብሪበያ ወረዳዎችና በአፋር ክልል በሚሌና አሳኢታ ወረዳዎች የመድሃኒት አቅርቦት ውስንነት መኖሩ፣ በኦሮሚያ ክልል በሚኤሶ ወረዳ፣ በአፋር ክልል አፋምቦና በአሳኢታ ወረዳዎች የክትባት አቅርቦት ውስንነት መኖሩ፣ ሱማሌ ክልል ጉርሱም፣ አቡበሬና ቀብሪበያ ወረዳዎች እና በአፋር ክልል አሳኢታ ወረዳ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ያልተማሉ መሆኑ፤
- በፈንታሌ ወረዳ እንዳሉ ተለይተው ለታወቁ የበሽታ አይነቶች አላስፈላጊ መድሃኒቶች ተገዝተው የሚመጡ ከመሆኑም በላይ ለብልሽት የተጋለጡና የአገልግሎት ጊዜያቸው እያለፈባቸው መድሃነቶች መደብሮችን አጣብበው መገኘታቸው፤
- በሚኤሶ ወረዳ ክሊኒኮች ተገንብተው ካለቁ በኋላ ወደ ስራ የማይገቡት በዝናብ እና ኮንትራክተሮች ባለማስረከባቸው ምክንያት መሆኑን፤ የእንስሳት ባለሙያዎች እጥረት የተከሰተው አካባቢው ወጣ ያለ በመሆኑ ባለሙያዎች ሥራ በመልቀቃቸውና ወደ ሌላ የተሻለ ቦታ የሚዘዋወሩ በመሆኑ፤ የከብቶች ብዛትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ በወረዳው ያሉት ክሊኒኮች ላሉት የዳልጋ ከብቶች በቂ እንዳማይሆኑ መገለጹ፤

- በናሙና በተመረጡት በሱማሌ፣ በኦሮሚያና በአፋር ክልል ወረዳዎች የተገኙ መረጃዎች እንደ አፍተግር /FM/፣ አባሰንጋ፣ ጎሮርሳ፣ የሳምባ ምች፣ አባጎርባና ቦቫይን ፓስትሪሎሲስ /Bovaine pastrioulosis/ ያሉ የተለያዩ የበሽታ አይነቶች በስፋት የሚገኙ መሆኑ፤
- የክትባት እና የመድሃኒት አቅርቦትና ስርጭት ውሱንነት፣ የባለሙያዎች እጥረት፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች አለመኖር እና የክሊኒኮች በተሟላ ሁኔታ አገልግሎት አለመስጠት በአካባቢው በዛ ያሉ በሽታዎች ተንሰራፍተው እንዲገኙ ከማድረጉም በላይ የዳልጋ ከብት ጤና ሽፋን አነስተኛ እእንዲሆን ማድረጉ፤
- ለባለሞያዎችም ሆነ ለአርብቶአደሩ ስልጠናዎች በአግባቡና ወጥነት ባለው መንገድ ባለመሰጠቱ ባለሞያዎች ወቅታዊ በሆነ ዕውቀት እንዳይሰሩ፤አርብቶ አደሮችም ዘመናዊ የግጦሽ መሬት አጠቃቀም እንዳይከተሉ፣ የተሻሻሉ የመኖ ዘሮችን በስፋት እንዳይጠቀሙና በከብት ብዛት ላይ እንጂ በጥራት ላይ የተመሰረ የአረባብ ዘዴ እንዳይከተሉ ማድረጉ፤
- በኦዲቱ ከተካተቱት የሱማሌ የአፋር እና የኦሮሚያ ክልሎች አርብቶ አደር አካባቢዎች ያለው የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ወጥነት የሌለው አሊያም የመረጃ ስርዓት የሌለ መሆኑ፤
- በሱማሌ በክልል ደረጃ ያሉትን የዳልጋ ከብቶች ብዛት፣ በአካባቢው ላለው ከብት ምን ያህል መኖ እንደሚያስፈልግና እጥረቱ የሚታወቅበት፣ ለአርብቶ አደሩ በየጊዜው የተሰራጩ የመኖ ዘሮች (የመኖ ዕፅዋት ቁርጥራጮችን ጨምሮ) መጠን በኪሎም ሆነ በቁጥር ለማወቅ የሚያስችል ስርዓት አለመኖሩ፤ በተጨማሪም በአካባቢው ያለውን የዳልጋ ከብት የሞት መጠንና የሞቱ ምክንያት እየተመዘገበና እየተተነተነ የሚጠናቀርበት ሥርዓት አለመኖሩ፤
- ለአርብቶአደሩ የሚያደርገው የልዩ ድጋፍ ሥራ ከእንስሳት ሃብት ልማት ጋር በተያያዘ የአርብቶ አደሩን የፍላጐት እና የአቅርቦት የአቅም ክፍተትን ጨምሮ በቅድሚያ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ እንዲለዩ ሊደረግና በጥናት የተለዩትን ክፍተቶች ለመሙላት የሚያስችሉ የተለያዩ ፓኬጆችን በማዘጋጀት በሥራ ላይ ማዋል የሚገባ ቢሆንም፤ለአርብቶአደሩ የሚደረገው የልዩ ድጋፍና የልማት

ትብብሩ የእስካሁን ሂደት የአርብቶአደሩን መሰረታዊ ፍላጐትና የአቅም ክፍተትን መሰረት ያላደረገ መሆኑ፤

- በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አማካኝነት የተለያዩ የዳሰሳ ጥናቶች የተጠኑ ቢሆንም የአርብቶ አደሩን ፍላጐት በተለይም በውሃ አቅርቦት ላይ የሚታየውክፍተት አለመቀረፉን በጅጅጋ ዙሪያ ወረዳ በሚገኙ አርብቶ አደሮች መገለጹ፤

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የአርብቶ አደሩን ከዳልጋ ከብት ምርት ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በመኖ፡ የግጦሽ መሬት፡ የውሃ፤ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እና በህክምና አገልግሎች አቅርቦቶች ዙሪያ ለተነሱት ችግሮች አግባብ ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድ በኦዲት ሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

10.6 የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገድ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም

- የመንገዶች ግንባታ፣ ማጠናከሪያ እና ማሻሻያ ፕሮጀክቶችን የመምረጫ መስፈርት (መመዘኛ) በዋነኛነት ለእድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱትን የኢኮኖሚ ዘርፎች (ግብርና፣ ማእድን፣ ቱሪዝም፣ ኢንዱስትሪ) በመለየት ቅድሚያ ትኩረት መሰጠት ያለበት ሲሆን፤ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡት ፕሮጀክቶች ውስጥ፤ ለኮምቦልቻ-ወልዲያ፣ ዛሪማ - ማይጸምሪ፣ መካነ ሰላም -ግንደወይን፣ ዱር ቤቴ - ሻሁራ፣ ጎንደር - ደባርቅ፣ ሃረር - ጂጂጋ፣ ማይጸብሪ - ሺሬ፣ ማይጸምሪ - ዲማ፣ ሞጆ- አረርቲ፣ ቡታጂራ- ጉብሬ፣ ሁምቦ- አርባ ምንጭ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች በመንገድ ሴክተር ዴቨሎፕመንት ፕሮግራም በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት ተገምግመው የተመረጡ/የተመለመሉ ስለመሆኑ፤የተመረጡበት መመዘኛ መስፈርት እና የተሰጣቸው ነጥብ በተመለከተ ማስረጃ አለመቅረቡ፤
- ለመንገድ ስራ ግንባታ ፕሮጀችቶች የአዋጭነት ጥናት፣ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተጽእኖ ጥናት (Resettlement action plan)፣ እና የምህንድስና ዲዛይን ጥናት /Detail Design study/ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ እያለ

ከዱር ቤቴ ሻሁራ- ጎለጎ መንገድ የፊዚቢሊቲ እና የዲዛይን ጥናት አለመደረጉ ፤ እንዲሁም ከሁምቦ-አርባ ምንጭ ፕሮጀክት የአዋጪነት በለመደረጉ ጥናቱ የዲዛይን ጥናቱ አካል ሆኖ የተሰራ መሆኑን ቢገለጽም የጥናት ሰነዶቹ ባለመቅረባቸው ማረጋገጥ አለመቻሉ፤

ሐረር -ጂጂጋ መንገድ ስራ ፕሮጀክት 50 023 942.48 ተጨማሪ ወጪ ማስከተሉ

- የመንገድ ለውጥ (Realignment) በመደረጉ በፕሮጀክት ዋጋ ላይ የ 2,026,081.49 ብር ተጨማሪ ወጪ (ቫሪዬሽን) ማስከተሉ፣
- የድልድዮችን የተፋሰስ አቅም (hydrolic capacity) ያላገናዘበ በመሆኑ ብር 1,223,669.82 ቫርዬሽን (ጭማሪ) ያስከተለ መሆኑ፣
- በዲዛይን ጥናት ወቅት ከጅጅጋ ከተማ ማስተር ፕላን ጋር የተጣጣመ የከተማ መንገድ ባለመካተቱ በተጨማሪ ብር 38,279,336.34 ቫሪዬሽን ያስከተለ መሆኑ፣
- በዲዛይን ዶክመንት ላይ ጋርድሬይል (የብረት መከላከያዎች) የሚያስፈልግበትን ቦታ ባለመጠቀሱ ተጨማሪ የጋርድሬይል ሥራዎች ለማከናወን ብር 3,833,064.94 ቫሪዬሽን ያስከተለ መሆኑ፣
- በኮንትራት ውሉ ተጨማሪ ድልድዮች ባለመካተታቸው ከቫት በፊት ብር 4,661,789.89 ጭማሪ ያስከተለ መሆኑ፣ ከቫርዬሽን ኦርደር ሊታወቅ መቻሉ፤

ሁምቦ - አርባምንጭ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት በዲዛይን ችግሮች ምክኒያት ብር90 341 161.84 ተጨማሪ ወጪ ማስከተሉ

- ረግረጋማ (Marshy Area) ቦታዎች ላይ በኢንባንክመንት ከፍ ተደርጎ መሠራት ሲኖርበት በአነስተኛ ኢንባንክመንት እንዲሠራ የተደረገ መሆኑ፣
- በዲዛይን ወቅት የሃይድሮሎጂ ጥናት በጥልቀት ባለመካሄዱ አንዳንድ የድሬኔጅ ስትራክቸርስ በውለታው ባለመካተቱ በተጨማሪ የብር 24,932,790.68 ቫሪዬሽን ያስከተለ መሆኑ፣

- የድሬኔጅ ሥራ በአግባቡ ተጠንቶ ባለመካተቱ የብር 65,408,371.16 ጭማሪ ያተስከተለ መሆኑን ከቫርዬሽን ኦርደር ለማወቅ መቻሉ፤፡

ጎንደር -ደባርቅመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ብር 52 352 158.13 ተጨማሪ ወጪ ማስከተሉ፤

- ከባለስልጣኑ በታዘዘው የ3 ከተሞች (የአምባ ጊዮርጊስ፣ ዳባት እና ደባርቅ) የቫርዬሽን ኦርደር ምክንያት የኮንትራት ዋጋ ከብር 690,779,965.26 ወደ ብር 743,132,123.39 ማደጉ የብር 52 352 158.13 ተጨማሪ ወጪ ማስከተሉ እና የፕሮጀክቱን ማጠናቀቂያ ጊዜ በ120 ቀናት እንዲጨመር ማደረጉ፣

- ባልተጠበቀ የመሬት መስመጥ እና መንሸራተት ምክንያት ከመጀመሪያው ዲዛይን አዲስ የመስመር ለውጥ የተደረገ መሆኑ፣

- ለዛሪማ - ማይጸምሪ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ከዲዛይን ጋር በተያያዘ ችግር ከአዲአርቃይ ከተማ መግቢያ ላይ መንገዱ በመቃብር ቦታ ላይ እንዲያልፍ፤ እንዲሁም በገደል ውስጥ (በኪ.ሜ. 29 + 500 አካባቢ) እንዲያልፍ የተደረገ መሆኑ፣

- ለማይጸምሪ - ሽሬ በመጀመሪያ ከተዘጋጀው የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት የዲዛይን ጥናት ላይ 5 አዳዲስ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች የተጨመሩ ሲሆን ከ40 በላይ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች (ከልቨርትስ) ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ ዲዛይናቸው የተቀየረ መሆኑ፣

- የመጀመሪያው ግንደወይን-መካነ ሰላም ፕሮጀክት የዲዛይን ጥናት ዶኩመንት በመንገዱ የጎርጅ አካል (በሁለቱ ትላልቅ ወንዞች በጥቁር አባይ እና በዲፋርሳ ወንዞች በሚገነቡ ድልድዮች መካከል) ያለውን የጂኦሎጂካል እና የሃይድሮሎጂካል መረጃዎችን ያላካተተ መሆኑ፣

<u>ሞጆ-አረርቲ የመንገድ ፕሮጀክት</u>

- ለሞጆ - አረርቲ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት አጠቃላይ ስፋት 64.5 ኪ.ሜትር ውስጥ 4 ኪ.ሜትር የሚሆን ቦታ የአፈር ስራዉና የሳብቤዝ ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ በጥቁር አፈር ምክንያት በአንዳንድ የመንገዱ ክፍሎች ላይ

በተፈጠረው የመሰንጠቅ ችግር የዲዛይን ማሻሻያ ተደርጎበት እንደ አዲስ እንዲሰራ መደረጉ፣

- በመንግስት የፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያ መሠረት በማንኛውም የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ሰነድ ላይ በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ቴክኒካዊና ከወጪ ረገድ ያሉ ቁልፍ መረጃዎች ትክክል ስለመሆናቸው እንዲሁም ሥራውን ከሚያካሂደው ተቋም (ባለቤት) አቅም ጋር በተያያዘ ተቀባይነት ያላቸው ለመሆናቸው ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ቢገለጽም፤
    - ሆኖም ለዛሪማ - ማይጸምሪ፣ መካነ ሰላም - ግንደወይን፣ ዱር ቤቴ - ሻሁራ፣ ጎንደር - ደባርቅ፣ ሐረር - ጂጂጋ፣ ዛሪማ - ማይጸምሪ፣ መካነ ሰላም - ግንደወይን፣ ማይጸብሪ - ሺሬ፣ ሞጆ - አረርቲ፣ ቡታጂራ - ጉብሬ፣ ሁምቦ አርባ -ምንጭ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች በአማካሪ ድርጅቶች የተከናወኑ የአዋጪነት ጥናት ሰነዶች በባለስልጣኑ ባለሙያዎች የተገመገሙ ስለመሆኑ (የተሰጠ አስተያየት) ማስረጃ አለመቅረቡ፤
    - እንዲሁም ለጎንደር - ደባርቅ፣ ሐረር - ጂጂጋ፣ ኮምቦልቻ - ወልዲያ፣ ዛሪማ - ማይጸምሪ፣ ማይጸብሪ - ሽሬ፣ ቡታጂራ - ጉብሬ፣ ሁምቦ አርባ - ምንጭ መንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች በአማካሪ መሃንዲሶች የተከናወነውን የዲዛይን ጥናት በባለስልጣኑ ባለሙያዎች ግምገማ የተከናወነበት (comments) ስለመሆኑ ማስረጃ አለመቅረቡ፤
- በአስፈጻሚ አካላት የሚዘጋጁ ረቂቅ የፕሮጀክት ጥናት ሰነዶች (draft project proposal and design) (ምዘና) በመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያ በተገለጸው መሠረት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ቀርበው የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሊደረግባቸው ሲገባ፤ የኮምቦልቻ - ወልዲያ፣ ዛሪማ - ማይጸምሪ፣ መካነ ሰላም - ግንደወይን፣ ዱር ቤቴ - ሻሁራ፣ ጎንደር - ደባርቅ፣ ሃረር - ጂጂጋ፣ ዛሪማ - ማይጸምሪ፣ መካነ ሰላም - ግንደወይን፣ ማይጸብሪ - ሽሬ፣ ማይጸምሪ - ዲማ፣ ሞጆ - አረርቲ፣

ቡታጂራ -ጉብሬ፣ ሁምቦ - አርባምንጭ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሳይደረግባቸው ወደ ትግበራ የተገባ መሆኑ፤

- ማንኛውም የዲዛይን ኮንሰልታንት የዲዛይን ጥናት ሲያከናውን በሚጠናው ዲዛይን አማካኝነት ሊሰሩ የታሰቡ ሥራዎችን ሙያው በሚጠይቀው ደረጃ መሰረት የአዋጭነት ጥናት፣ የሃይድሮሎጂና የጂኦሞርፎሎጂ ጥናት በጥልቀት ማካሄድ፣አስፈላጊ ሥራዎችን መለየትና በፕሮጀክቱ ውስጥ ማካተት፣ ዲዛይን ማከናወን፣ ትክክለኛ የሥራ መጠን ግምት መስራት፣ ዲዛይን ድሮዊንግና የቅየሳ መረጃዎችን ማዘጋጀት፣ የፕሮጀክቱን ዋጋ ግምት በትክክል ማከናወን ያለበት ቢሆንም፤
- የመጀመሪያ የዲዛይን ጥናት በትክክል ባለመሠራቱ ምክንያት በተደረገ ክለሳ የሥራ ለውጥ፣ የኮንትራት ዋጋ ጭማሪ እና የጊዜ መራዘሞች የሚከሰቱ በመሆኑ፤
- የሐረር - ጅጅጋ ፕሮጀክት የዲዛይን ጥናት በትክክል ባለመሠራቱ ክለሳ (ለውጥ) በመደረጉ ምክንያት የተከሰቱ የሥራ ለውጥ፣ የኮንትራት ዋጋ ጭማሪ እና በጊዜ መራዘም ምክንያት የግንባታ ማቴሪያልስ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ በመናሩ ብር 112,563,279.20 የዋጋ ማስተካከያ (Price Adjustment) ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
- ከፕሮጀክቱ የቀድሞ አማካሪ መሃንዲስ (Roughton & Partners International LTD) ለተቋራጩ ከአራት መቶ በላይ የሥራ ትዕዛዝ (Engineer's Instruction) የተላለፈ መሆኑ ከቫርዬሽን ኦርደር እና ከዲዛይን ዶኩመንት ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የትዕዛዞችን አይነት በተመለከተ ዝርዝር ማስረጃዎች በተቆጣጣሪ መሃንዲስ እጅ ናቸው በሚል አለመቅረቡ፤
- በቀድሞ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ የተሰጡ የሥራ ትዕዛዛት ዝርዝር ማስረጃ ለኦዲት ባለመቅረቡ አጠቃላይ የገንዘብ መጠኑን ለማወቅ ባይቻልም የፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ጊዜ ከ3 ዓመታት በላይ በመራዘሙ (ከ10/01/2009 ወደ 10/3/2012) የግንባታ ማቴሪያልስ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ በመናሩ ምክንያት የዋጋ ማስተካከያ ክፍያ መፈጸሙን ለመገንዘብ መቻሉ፤

- በራስ ሀይል ለተከናወነው የኮምቦልቻ- ወልዲያ ፕሮጀክት የመንገድ ንጣፍ (Pavement) ማሻሻል፣ ለተቀየሩ የመንገድ መስመሮች አዲስ ግንባታ ማከናወን፣ ስድስት ድልድዮችን በአዲስ መተካት እንዲሁም የማይነር ድሬይኔጅ ስትራክቸሮች ጥገና ስራዎችን ለማከናወን የታቀደ ሲሆን የፕሮጀክቱ ይዘት በመቀየሩ ምክኒያት በተካተቱ አዳዲስ ሥራዎች የፕሮጀክቱ የውለታ ዋጋከ ብር 360,639,363.55 ወደ ብር 932,921,141.70 በማደጉ ከፍተኛ ጭማሪ (259%) ማሳየቱ፣
- በመንገድ ሥራፕሮጀክቱ ከተካተቱት አስር ቫሪዬሽን ውለታዎች ስምንቱ ከፍተኛ ጭማሪ ያስከተሉ ማሆናቸው፣
- v.o 01.(ከቫርዬሽን ኦርደር)የግንባታ ሥራው በመስፋፋቱ የጥራት ቁጥጥር ስራን ለማቀላጠፍ የስድስት መኪኖችና የራዲኦ መሳሪያ ግዢ ለመፈፀም ብር4,541,008.0 ወጪ መሆኑ፣
- v.o 02 በመጀመሪያ ውለታ ያልተካተቱ ሥራዎች በመካተታቸውና የሥራዎቹ ነጠላ ዋጋ በመሻሻሉ ብር 368,437,055.00 ጭማሪ መከሰቱ፣
- v.o 03 በቀድሞ ዲዛይን 15 ሜትር ስፋት የነበረውን የኮምቦልቻ ከተማ መንገድ ስፋት ወደ 19 ሜትር በመቀየሩ ብር 13,987,201.82 ጭማሪ የታየ መሆኑ፣
- v.o 04 በደሴ የከተማ መንገድ ከ15 ሜትር ወደ 19 ሜትር በመስፋቱ ጋር በተያያዘ ብር 69,093,462.10 ጭማሪ መታየቱ፣
- v.o 05 በወልዲያ የከተማ መንገድ መስመር ቅያሪ (Realignment) ሳቢያ ብር 55,823,959.03 ጭማሪ የታየ መሆኑ፣
- v.o 06 ሦስት ድልድዮችን (B-62,B-64&B-65) በአዲስ ለመተካት ብር 5,043,762.63 ጭማሪ የታየ መሆኑ፣
- v.o 07 የውጫሌ፣ መርሳና ስሪንቃ የከተማ መንገድ ቦይ (paved ditches) ለመገንባት በጠቅላላው ብር 15,831,516.10 በውለታው ላይ ጭማሪ ማስከተሉ፣

- v.o 08 ፓይፕ ከልቨርቶችን በኮንክሪት ከልቨርት ለመተካት ብር 39,986,021.28 ወጪ መደረጉ፣
- የልዩነቱ ከፍተኛ መሆን በዲዛይን ወቅት በጥንቃቄ ጥናት ካለማድረግ የተከሰተ መሆኑን ለመገንዘብ መቻሉ፤
- ለማንኛውም የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት የዲዛይን ጥናት ሰነድ ዝርዝር ላይ የእቅድ አፈጻጸም መርሃ ግብር ሊኖረው እና በመርሃ ግብሩ ሠነድ ላይ የወጪ ግምት፣ የተመደበ ሀብት፣ (የሰው ሀይልና ማቴሪያል) የቁጥጥር ስርዐት እና የፕሮጀክቱ ሥራ የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት ቀን መገለጽ ያለበት ቢሆንም፤
- ለማይጸምሪ - ዲማ መንገድ ሥራፕሮጀክት፣ የመጀመሪያውን የጨረታ ዶኩመንት ባዘጋጀው መሀንዲስ የስራውን መጠን ግምት በDrainage, በEarthwork እና በStructures ሥራዎች ላይ በትክክል ባለመገመቱ በድጋሚ በተደረገ ልኬት (Remeasurement) ብር 20,005,781.34 ቫሪዬሽን (ጭማሪ) ማስከተሉ ከቫርዬሽን ዶኩመንት ለማወቅ መቻሉ፤
- ለጎሬ-ጋምቤላ ፕሮጀክት የEarthwork አይተም 42.01 a (ii) A Cut to fill/embankment በውለታ መሰረት 314,257 cum የነበረ ሲሆን በክፍያ ሰነድ ላይ እንደሚታየው በሦስት እጥፍ ጨምሮ 946,683.23 cum በመሆኑ ብር 21,970,487.23 ጭማሪ ማሳየቱ፤
- ለሃረር ጅጅጋ ፕሮጀክት የEarth work አይተም በኮንትራት ውል መሠረት ብር 20,192,409.31 የነበረው ከክለሳ በኋላ ወደ ብር 26,013,534.79 ከፍ የተደረገ ሲሆን በመጨረሻም በፔይመንት ሰርተፊኬት 57 (IPC NO. 57) ሰነድ መሠረት ብር 58,125,266.39 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤
- የዲዛይን ኮንሰልታንቱ ለግንባታ ግብዓት የሚውሉ ማቴሪያሎችን አይነትና የሚገኙበትን ቦታ በመለየት የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ለመሆናቸው ፍተሸዎችን (ቴስቶችን) ማድረግ ፕሮጀክቱን በዝቅተኛ ዋጋ በማከናወን አዋጭ እንዲሆን ለማድረግ የሚረዳ ቢሆንም፤

- የጎሬ -ጋምቤላ መንገድ ፕሮጀክት የዲዛይን ኮንሰልታንት በአካባቢው የሚገኙ ማቴሪያሎችን ታሳቢ ያደረገ ዲዛይን ባለመስራቱ (በኪ.ሜ 95-143) የውለታውን እስፔስፊኬሽን የሚያሟላ ሰብቤዝ ማቴሪያል በመታጣቱ የዋጋ ማስተካከያ ስለተደረገ የ153 ቀን የጊዜ መራዘምና ብር 32,603,665.04 ቫሪዬሽን መታየቱ፣
- እንዲሁም ያልተፈቱ ሌሎች (የይገባኛል ጥያቄዎች) ክሌይሞች በመኖራቸው በውለታው ዋጋ ላይ ሌላ ጭማሪ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ መገመቱ፣
- የዋጋ ማስተካከያው የዲዛይን ኮንሰልታንቱ የዲዛይን ዶክመንቱ አካል የሆነውን የማቴሪያል ሪፖርት የጥራት ደረጃን ትክክለኛ ባልሆነ የአካባቢው መረጃመ ሰረት በማዘጋጀቱ እና ባለስልጣኑም የዲዛይን ዶክመንቱን የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን በትክክል ሳያጣራ በመቀበሉ የተከሰተ መሆኑ፤
- በተለያዩ ምክንያቶች የካምፕና ኳዋሪ ሶረስ ቦታዎችን ለተቋራጮች በወቅቱ ሳያስረክብ መቅረቱ በውለታው መሠረትም ተቋራጩ ከጊዜ ጋር የተያያዘ የኦቨርሄድ (over head) ወጪውን ለመሸፈን ኢ.መ.ባ. በየወሩ ብር 3,908,655.00 ለመክፈል በተስማማው መሠረት ለተፈቀደ አጠቃላይ የ16.5 ወር የጊዜ ማራዘሚያ ብር 64,492,807 (ስልሳ አራት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና ሁለት ሺ ስምንት መቶ ሰባት) መከፈሉ፤

➢ ግንደ ወይን -መካነ ሰላም ፕሮጀክት ለፕሮጀክቱ የተለያዩ ክሌምስ (claims) በመኖራቸው ከመጀመሪያው የማጠናቀቂያ ጊዜ (20/8/2009) በ 20 ወራት በመራዘሙ የጨመረ መሆኑ፤

➢ በፕሮጀክቱ የዲዛይን ጥናት ወቅት የቀረጣ ሥራ መጠን ግምት አነስተኛ መሆኑ በነባራዊው የሥራ ሂደት በከፍተኛ መጠን በመጨመሩ፣ያልተጠበቀ የአየር ሁኔታ እና የሲሚንቶ እጥረት በአገር ደረጃ በመከሰቱ እና በዲዛይን ጥናት ወቅት የግምት ሥራው በበቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ ባለመሰራቱ ከፍተኛ የጊዜ መራዘም ያስከተለ መሆኑ፤

- ከመንገድ ወሰን ማስከበር እና ከካሳ ክፍያ ጋር በተያያዘ ለዛሪማ - ማይጸምሪ መንገድ ፕሮጀክት የሚፈለግ መሬት በገማች ኮሚቴ ሳይገመት መሬቱን ለአፈር መድፊያ፣ለማቴሪያል ጥየቃ (ሪኬስት)፣ ለመንገድ ቆረጣ የመጠቀም ሁኔታ መኖሩ፤

- ከአካባቢው ህብረተሰብ የሚቀርቡ የይገመትልን ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ ሳይሰጣቸው ከአንድ ዓመት በላይ የሚቆዩበት ሁኔታ መኖሩ፤

- በገማች ኮሚቴ ከተገመተ በኋላ፣ለፕሮጀክቱ ከተፈቀደ ክልል ውጭ ጨምሮ የመጠቀም፣ ክፍያ በወቅቱ አለመለቀቅ፣ወይም የክፍያ መዘግየት መኖሩ፤

- በፕሮጀክቱ ተሽከርካሪዎች የሚነሳው አቧራ በህብረተሰቡን ለአይን ህመም፣ለጉንፋን በሽታና መሰል ችግሮች ያጋለጠበት ሁኔታ መኖሩ፤

- ለእንዳስላሴ - ደደቢት ፕሮጀክት ለካሳ ክፍያ የተገመተ ገንዘብ ለባለመብቶች በቶሎ አለመላኩ፤

- ለሞጆ - አረርቲ መንገድ ሥራ ፕሮጅክት ባለስልጣኑ የመንገድ ወሰንን (ROW(Rights Of Way) በተፈለገዉ ፍጥነት አስቀድሞ ያለማያስከበር እና የካሳ ክፍያዎች መዘግየት ሁኔታዎች የነበሩ መሆኑ፤

- በመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ሊሳተፉ የሚገባቸው አጋር ድርጅቶች በቅድሚያ ተለይተው ሊታወቁ፤ኃላፊነታቸውም በዝርዝር ተለይቶና በጽሁፍ ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ሊደረግ እና በውይይት ስምምነት ላይ ሊደረስ የሚገባ ቢሆንም፤በኦዲቱ የመስክ ጉብኘት ወቅት፤

    - የጎንደር- ደባርቅ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ከሚያልፍበት የመሬት ወሰኖች ጋር በተያያዘ በተከሰቱ ችግሮች የሥራ ተቋራጩ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ባለው ግንኙነት የፕሮጀክቱ እንቅስቃሴ ለታወክ መቻሉ፤ በአካባቢው መስተዳድርም ችግሩን ለመቅረፍ ጊዜ መውሰዱ፤

    - ፕሮጀክቱ የሚያልፍበት የአርሶ አደሩ መሬትም ሆነ ሌላው ንብረት ከተገመተ በኋላ ክፍያ በመዘግየቱ አርሶ አደሮች ሥራ እናሰራም በማለታቸው ችግሮች የተፈጠሩ መሆኑ፤

- የፕሮጀክቱ የካሳ ጉዳት ገማች ኮሚቴው ምንም ዓይነት ንብረትም ሆነ መሬት ላልተነካባቸው ግለሰቦች ብር 27,391.84 ለአራት ግለሰቦች ያለ አግባብ ካሳ የሰጠ መሆኑ፤
- የካሳ ጉዳት ገማች ኮሚቴው ምንም ዓይነት ንብረትም ሆነ መሬት ላልተነካባቸው ግለሰቦች አለአግባብ መከፈሉ ባለስልጣኑ እና ኮሚቴው ትክክለኛ ባለይዞታዎችን ለመለየት ከአካባቢው መስተዳድር ጋር በመሆን በጥንቃቄ ሳያጣራ ክፍያ እንደሚፈጽም የሚያሳይ መሆኑን፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

➢ ባለሥልጣኑ በማንኛውም የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ላይ የሚሳተፉ የሥራ ተቋራጮችና አማካሪ መሃንዲሶች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑና ተገቢው ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በወቅቱ ስለመመደባቸው ማረጋገጥና ክትትልም ማድረግ ያለባቸው ቢሆንም ፤ ለኦዲት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ፕሮጀክቶች ውስጥ፤

  - ለሞጆ- አረርቲ መንገድ ሥራ ፕሮጅክት የፕሮጀክቱ የሥራ ተቋራጭ ለፕሮጀክት ቁልፍ ሥራዎች (ኃላፊዎች) (ፕ/ማኔጀር; ኮንስትራክሽን ኢንጂነር፣ ኦፊስ ኢንጂነር) በወቅቱ ያልመደበ መሆኑ፣
  - በግንደወይን -መካነሰላም ፕሮጀክት የስራ ተቋራጭ ሥር ያሉ ባለሙያዎች በቂ የሥራ ልምድ የሌላቸው መሆኑ፣
  - ለማይጸምሪ -ዲማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ሥር በአጭር ጊዜ በርካታ ባለሙያዎች ተለውጠው የተገኙ መሆኑ፣
  - ለማይጸምሪ -ሽሬ የመንገድ ሥራ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ የተጠሪ መሃንዲስ (ረዚደንት ኢንጂነር) በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሁለቴ ተቀይሮ፣ አሁን ያለው 3ተኛ ተጠሪ መሃንዲስ መሆኑ፤
  - ለማይጸምሪ ዲማ መንገድ ከተቆጣጣሪ መሃንዲስ አቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ባለሙያዎች መልቀቃቸውን እና የባለሙያ ፍሰት በሚካሄደው የመንገድ ልማት ትግበራ እያጋጠመ ያለ ተግዳሮት መሆኑ ፤

- እንዲሁም ለማይጸምሪ-ሽሬ የረዚደንት ኢንጂነር ለ3 ተኛ ጊዜ የተቀየረው በችሎታ ማነስ በመሆኑ ቅያሪው የግድ አስፈላጊ መሆኑ በሰሜን ሪጅን ዳይሬክተር መገለጹ፤

- የሥራ ተቋራጮችና እና አማካሪ መሃንዲሶች ተገቢ ባለሙያዎችን በወቅቱ አለመመደብና የባለሙያዎቹ ሁኔታ የተረጋጋ አለመሆን የፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም እና ክትትል በተሟላ መንገድ እንዳይከናወን ተጽዕኖ የሚፈጥርና በፕሮጀክቶች ጥራት ላይ የሚደረግ ተከታታይ ቁጥጥር ላይም ክፍተት ሊፈጥር የሚችል መሆኑ፤

➢ ለማንኛውም የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት የተመደበውን ግብዓት (ገንዘብ፣ ማሽነሪ፣ የሰው ኃይልና ማቴሪያል) እና ጊዜ በትክክል ለማስተዳደር (ማኔጅ) እና ለመቆጣጠር የሚስችል ዝርዝር የእቅድ አፈጻጸም መርሃግብር ሊኖረውና በመርሃ- ግብሩ መሠረት በቅደም ተከተል ለመሠራቱ የሚረጋገጥበት የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋለት የሚገባ ቢሆንም፤

- የማይጸምሪ-ሽሬ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት የሥራ ተቋራጭ ሥራዎችን በተቀመጠው ቅደም ተከተል የማያከናወን ሲሆን ሥራዎችም በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው የሚገኙ መሆኑ፣

- ለማይጸምሪ-ሽሬ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት የሥራ ተቋራጩ በቂ መሣሪያዎችን/ማሽነሪዎችን ያለመጠቀሙና አስፈላጊውን የሰው ሃይል በአግባቡ አቅዶና አቀናጅቶ በድሬኔጅ ስትራክቸር ሥራዎች ተግባራዊ አለማድረጉ በተቆጣጣሪ መሃንዲሶች የአፈጻጸም ሪፖርት መገለጹ፤

- እንዲሁም የሥራ ተቋራጩ የበጀት አጠቃቀም ሲታይ፡ ለፕሮጀክቱ በ2003 በጀት ዓመት የተመደበ በጀት ብር 140,000,000.00 ሲሆን ሥራ ላይ የዋለው ብር 127,878,911.52 በመሆኑ ያልተጠቀሙበት (ሥራ ላይ ያልዋለ) ብር 12,878,911.52 መኖሩን ከሥራ ተቋራጩ የተገኘ ማስረጃ የሚያመለክት መሆኑ፤

በፕሮጀክቶች በመጀመሪያ የኮንትራት ዋጋ እና በተከለሰ የኮንትራት ዋጋ የተመለከቱ ልዩነቶች

ሠንጠረዥ 1

	የፕሮጀክት ስም	የመጀመሪያ ኮንትራት ዋጋ	የተከለሰ የኮንትራት ዋጋ	ልዩነት በመብለጥ (በማነስ)	የፕሮጀክቶች ሁኔታ የተጠናቀቀ/ ያልተጠናቀቀ
1	ሐረር-ጂጂጋ	346,262,115.	417,821,728.	71,559,613. ወይም 20.6%	እስከ መስከረም 2004 ያልተጠናቀቀ
2	ሁምቦ - አርባ ምንጭ	380,204,197.	521,783,421.	141,579,224 ወይም 37%	ያልተጠናቀቀ
3	ኮምቦልቻ - ወልዲያ	360,639,363.	932,921,141.	572,281,778. ወይም (158%)	የተጠናቀቀ
4	ጎንደር - ደባርቅ	690,779,965.	743,132,123.	52,352,158.13 ወይም 7.57%	ያልተጠናቀቀ
5	ማይጸምሪ - ዲማ	258,721,412.	462,385,763.87	203,664,351 ወይም 78%	ያልተጠናቀቀ
6	ጎሬ -ጋምቤላ	750,900,145.	1,011,673,832.	260,773,687. ወይም 133%	3 ያልተፈቱ ክሌሞች አሉ፡፡ የመጀመሪያ ርክክብ ተደርጓል፡፡ የመጨረሻ ርክክብ አልተደረገም፡፡

በመንገድ ፕሮጀክቶች ማጠናቀቂያ ጊዜ መካከል የታዩ ልዩነቶች

ሠንጠረዥ 2

ተ.ቁ	የፕሮጀክት ሥም	የተጀመረበት ጊዜ	የመጀመሪያ የማጠናቀቂያ ጊዜ	የተከለሰው የማጠናቀቂያ ጊዜ	ልዩነት
1.	ሐረር-ጂጂጋ	11/01/2006	10/01/2009	10/03/2012	3.2 ዓመት
2.	ሁምቦ-አርባምንጭ	01/01/2008	02/07/2010	08/10/2011	1.3 ዓመት
4.	ኮምቦልቻ-ወልዲያ	01/02/2006	04/02/2009	28/02/2011	2 ዓመት
5.	ጎንደር-ደባርቅ	01/04/2009	31/3/2012	29/07/2012	4 ወር
8.	ማይጸምሪ -ዲማ	15/05/2009	14/05/2012	14/5/2013	12 ወር
9.	መካነሰላም-ግንደወይን	20/02/2006	20/08/2009	12/03/2013	3.7 ዓመት
10.	እንደስላሴ-ደደቢት	22/01/2009	22/01/2012	20/06/2012	5 ወር
12.	ጎሬ-ጋምቤላ	01/03/2007	28/02/2010	15/07/2011	1.4 ዓመት
14.	ሞጆ-አረርቲ	12/02/2008	24/08/2010	24/05/2011	9 ወር
15.	ቡታጅራ--ጉብሬ	11/12/2007	11/06/2011	28/02/2012	8 ወር

- ከላይ በሰንጠረዥ 1 እ ና 2 በዝርዝር እንደተመለከተው ለሐረር - ጅጅጋ በመጀመሪያ ከተያዘለት የኮንትራት ዋጋ በ20.6% ፣ ሁምቦ-አርባ ምንጭ በ37%፣ ጎንደር-ደባርቅ በ7.57% እና ማይጸምሪ - ዲማ በ133% ጭማሪ ያሳዩና ፕሮጀክቶቹም ያልተጠናቀቁ መሆኑ፤
- ኮምቦልቻ - ወልዲያ ፕሮጀክት ከተጠናቀቀ የቆየ ሲሆን ከመጀመሪያው ዋጋ በ158% የጨመረ መሆኑ፣
- ጎሬ - ጋምቤላ ፕሮጀክትም ተጠናቆ የመጀመሪያ ርክክብ የተፈጸመ ቢሆንም 3 ያልተፈቱ ክሌይምች ያሉበት ሲሆን መጀመሪያ ከተያዘለት የኮንትራት ዋጋ 133% ጭማሪ ማሳየቱ፤
- የፕሮጀክቶቹ የማጠናቀቂያ ጊዜም ከ4 ወራት እስከ 3 ዓመት ከ7ወራት እንዲራዘም መደረጉ፤

- ለኮንትራት ዋጋ መጨመር የተለያዩ ምክንያቶች ቢሰጡም መጀመሪያ የፕሮጀክቶች የኮንትራት ዶኩመንት ሲዘጋጅ ደረጃውን ባልጠበቀ እና በደንብ እና በአግባቡ ባልተጠና የዲዛይን ጥናትና ስፔሲፊኬሽን መሰረት የተሰጡ መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ የሚያሳይ መሆኑ፤

<u>በናሙና በተመረጡ የመንገድ ፕሮጀክቶች በእቅድና በአፈጻጸም መካከል የታየ ልዩነት</u>

- የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውላቸው በተመለከተው የጊዜ ገደብ (በታቀደው ጊዜ) እና በኮንትራት ውል በተመለከተው ዋጋ መሠረት (በታቀደላቸው ወጪ) መጠናቀቅ ሲገባቸው እስከ ሰኔ 2011 ድረስ ያለው የፊዚካል እቅድ አፈጻጸም፤ የጎንደር- ደባርቅ በ19.56% ፤ ማይጸምሪ -ሽሬ በ34.24%፣ እንዳስላሴ - ደደቢት በ22.19% ከእቅዱ ያነሰ ሆኖ መገኘቱ፤
- የዛሪማ - ማይጸምሪ እስከ መስከረም 2011 ድረስ ያለው የፊዚካል አፈጻጸም ከእቅዱ በ10.47% ያነሰ ሲሆን፣ የሁምቦ - አርባ ምንጭ 106 ኪ.ሜ መንገድ እስከ ጥቅምት 2004 ዓ.ም. ድረስ ያለው የፊዚካል እቅድ አፈጻጸሙ 55 ኪ.ሜ.(52%) በመሆኑ ከተያዘለት እቅድ በ51 ኪ.ሜ ያነሰ መሆኑ፤
- የእቅድ አፈጻጸሙ ያነሰበት ምክንያቶችንም በተመለከተ፤

<u>ጎንደር- ደባርቅ</u>

- በሰለጠኑ ባለሙያዎች እጥረት ምክንያትና ደካማ የእቅድ ዝግጅት እና ቅንጅት አለመኖር፣
- የሥራ ተቋራጩ ልምድ ያካበቱ እና የሰለጠነ ባለሙያ ባለመኖሩ ምክንያት የተሠሩ ሥራዎችን ጥራት ማረጋገጥ አለመቻል፣
- የአስፋልት JMF ዝግጅት ሥራ መዘግየት፣
- የሥራ ተቋራጩ ከኮንሰልታንቱ የሚተላለፍለትን የሥራ ትዕዛዝ አለመከተል፣
- በምክንያትነት የተጠቀሱ መሆኑን ከወርሃዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ማይጸብሪ - ሽሬ

- የኮንሰልታንት እና የኮንትራክተር ካምፕን ዘግይቶ መጨረስ፣
- ሥራዎችን በተገቢው ቅደም ተከተል ባለማስያዝ፣
- የሰው ኃይሉን እና መሳሪያዎቹን በብቃት አለመጠቀም፣

እንደስላሴ-ደደቢት

- ባልተረጋጋ የነዳጅ አቅርቦት ምክንያት በየጊዜው የሥራ መቋረጥ መታየት፣
- የሥራ ተቋራጩ ለረዢም ጊዜ የተገለገለባቸውን መሳሪያዎች ኪራይ ባለመክፈሉ የዋና ዋና መሳሪያዎች እጥረት ማጋጠሙ፣
- የሥራ ተቋራጩ ባጋጠመው ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ምክንያት የመለዋወጫዎች እና የሲሚንቶ አቅርቦት አለመኖር፣
- በሌሎች መሳሪያዎች እጥረት ምክንያት የዋና ዋና መሣሪያዎች ለረዢም ጊዜ ያለስራ መቆም፣

ዛሪማ-ማይጸምሪ

- የኮንስትራክሽ ሥራን ዘግይቶ መጀመር፣
- ትላልቅ መሣሪያዎችን ወደ ሳይት ዘግይቶ በማንቀሳቀስ፣
- የአካባቢው የመልከዓምድር አቀማመጥ አስቸጋሪ መሆን፣
- የኮንስትራክሽን ማቴሪያልሰ ሲሚንቶ እና ነዳጅ አቅርቦት እጥረት መኖር፣
- በሳይት ያሉ መሣሪያዎችን የክትትል እና የቁጥጥር ደካማ በመሆኑ የመሳሪያዎችን ምርታማነትን ዝቅተኛ መሆን፣
- በፕሮጀክቱ ሳይት እና በቢሮ በቂ እና የካበተ ልምድ ያላቸው የምህንድስና ባለሙያዎች እጥረት መኖር፣

ሐረር-ጂጂጋ

- ከፍተኛ የሆነ የሲሚንቶ እጥረት ማጋጠሙ፣

- የሥራ ተቋራጩ ሐብቶቹን በአግባቡ ባለማቀድ፣ባለማደራጀት እና በሚገባ በሥራ ላይ አለማዋል፣

<u>መካነሰላም- ግንደወይን</u>

- በAbutment No.1 ላይ ባለው መጥፎ የመሬት ሁኔታ የሥራ ተቋራጩ በመጀመሪያው የአሰራር ስልት (piling at the Difarsa Bridge) ላይ በመቀጠሉ በሥራ አፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣
- የመንገድ ኮንስትራክሽን ምርታማነትን ለማሳደግ ተጨማሪ አቅድ እና የመማሪያ ግብዓት በጎርጁ የ MM ክፍል ማስፈለጉ፣
- በዲፋርሳ ወንዝ ላይ የሚከናወነው (Drilling of piles) በአለት መሰንጠቅ ምክንያት መዘግየቱ፣

<u>ሁምቦ - አርባ ምንጭ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት</u>

- መሣሪያዎችን ወደ ሳይት ዘግይቶ በማንቀሳቀስ፣
- ለሥራው የሚያስፈልጉ ማቴሪያል አይነቶችን፣ ምርትን (production) የመሳሪያዎች ተከላን ዘግይቶ መጀመር፣
- ሳይት ላይ የሚከናወኑ ሥራዎች ላይ ደካማ አስተዳደር እና የሐብት አጠቃቀም መኖሩ፣
- የሰለጠነ የሰው ኃይል እንደ ሳይት ኢንጂነር፣ ኮንስትራክሽን ፎርማን በሳይት ላይ እጥረት መኖሩ፣
- የመሳሪያዎች እንደ earth moving machines ገልባጭ መኪናዎች (dump tracks) እጥረት መኖሩ፣
- በፕሮጀክቱ አካባቢ ያልተጠበቀ ጎርፍ መከሰት፣
- በተለይ የፕሮጀክቱ የሥራ አፈጻጸም ከተከለሰው ኮንትራት ጋር ሲነጻጸር በሰኔ ወር 2011 (0.68%) በመሆኑ ለዚህ ደካማ አፈጻጸም፤
- የሥራ ተቋራጩ የተከለሰ የስራ እቅድ (schedule) ስላልነበረው የኮንስትራክሽን ሥራዎችን አፈጻጸም ለመከታተል ባለመቻሉ፣

- የኮንስትራክሽን ማቴሪያሎችን ለምሳሌ ነዳጅ፣ ሲሚንቶ መለዋወጫዎች የተቆራረጠ አቅርቦት መኖር፣
- ለመሳሪያዎች እና ለተሽከርካሪዎች መለዋወጫዎች እንደ ጎማ፣ ፊዩል ፊልተር፣ ኤየር ፊልተር፣ ኦይል ፊልተር በመጋዘን እጥረት መኖር፣
- የዋና እና ቁልፍ የኮንስትራክሽ መሳሪያዎች እና ማሺነሪዎች በተለይ የሎደርስ፣ ገልባጭ መኪናዎች (dump trucks)፣ water trucks፣ motor grader and excavators እጥረት መኖር፣
- በሳይት በሥራ ላይ የነበረው (ያለው) አንድ ሞተር ግሬደርስ (motor graders) ብቻ መሆኑ፣፣
- አራት እሁዶች የፕሮጀክት የሥራ እንቅስቃሴ መቆም ለፕሮጀክቱ ዝቅተኛ አፈጻጸም አስተዋጽኦ ያለው መሆኑ፣
- በተከታታይ ለ3 ቀን ዝናብ መዝነቡ የሥራ አፈጻጸምን ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ መሆኑ፣
- የነዳጅ እና የሲሚንቶ እጥረት መኖር፣

  የሚሉት በምክንያትነት መጠቀሳቸው፤

- አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ሊሆን የቻለው ከኮንትራክተሮች አቅም ማነስ፣ ከማኔጅመንት ብቃት ችግር፣ እቅድን በአግባቡ ካለማዘጋጀት፣ የሰው ኃይልን እና መሳሪያዎችን አቀናጅቶ መጠቀም ባለመቻል፣ መሳሪያዎችን በወቅቱ ሞቢላይዝ ባለማድረግ ፣ደካማ አስተዳደር እና የሃብት አጠቃቀም፤እና ከሥራ ተቋራጮች አሠራር ድክመት የመነጨ መሆኑን ለመረዳት መቻሉ፤
- ፕሮጀክቶች በተጠኑበት፤ የዲዛይን ስራቸው በተሰራበት እና ወደትግበራ በተገባበት ወቅት መካከል ከ 1 እስከ 2 ዓመታት የሚሆን የጊዜ ልዩነት መኖሩ፤
- ለማንኛውም የመንገድ ግንባታ፣ ማሻሻል እና ማጠናከር ሥራ ፕሮጀክት የቴክኒካዊ ደረጃዎችን የሚያሳይ ዝርዝር የኢንጂንሪንግ ዲዛይን ሊዘጋጅለት የሚገባ ቢሆንም ፤

- የቡታጂራ - ጉብሬ፣ ዛሪማ - ማይጸምሪ እና ጎንደር - ደባርቅ መንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች የመጀመሪያው የዲዛይን ጥናት በተካሄደበት እና የትግበራ ስራው በተጀመረበት ጊዜ መካከል የ2 ዓመት ያህል የጊዜ ልዩነት ያለው መሆኑ፤

- ስለቡታጂራ-ጉብሬ የዲዛይን ጥናትና የፕሮጀክቱ ትግበራ የተጀመረበት ጊዜ ፕሮጀክቱ በሚያቋርጣቸውን ዋና ዋና ቦታዎች ምርጫ ጋር በተያያዘ፤ የመሬት አቀማመጡ ተራራማ በመሆኑ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የአፈር ቆረጣ ስራን ለመቀነስ የተጠናቀቀውን ዲዛይን ደግሞ ማየትና መከለስ በማስፈለጉ፤ የተነሱትን ማህበራዊ ጉዳዮች ከቴክኒካል ጥናት ጋር በማጣመር መፍትሄ መስጠት በማስፈለጉ እና ለፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ የተመደበውን በጀት በማየት አጠቃላዩን ፕሮጀክት ለሁለት በመክፈል እና የዝዋይ - ቡታጅራን መንገድ ነጥሎ ጨረታ ማውጣት በማስፈለጉ የቡታጅራ - ጉብሬ መንገድ ሥራ ሊዘገይ መቻሉ በማከላዊ ሪጅን ዳይሬክተር መገለጹ፤

- የጎንደር-ደባርቅ፣ማይጸምሪ - ሽሬ፣ ዛሪማ - ማይጸምሪ እና መካነሰላም-ግንደወይን መነገዶች የዲዛይን ጥናቱና የመንገድ ሥራው በተጀመረበት ጊዜ መካከል ያለው የጊዜ ልዩነት የፋይናንስ ምንጭ መፈለግ፣ ከበጀት ምደባ፣ ከአማካሪ መሐንዲስና ከሥራ ተቋራጭ ግዥ ሂደት (Procurement Process) ጊዜ ወሳጅ ሂደቶች ጋር በተገናኘ የተከሰተ መሆኑ መገለጹ፤

- በዲዛይን ጥናት እና በትግበራ መካከል ይህን ያህል ረዢም ጊዜ በመኖሩ በመሃከል በፕሮጀክቱ አካባቢ የተለያዩ የተፈጥሮ እና የማህበራዊ ለውጦች ሊከሰቱ ስለሚችሉ ወደ ትግበራ ሲገባ የዋጋ ንረትና ሌሎች ተጨማሪ ችግሮችን እንዲከሰቱ በማድርግ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ፤

- ባለስልጣኑ ከሥራ ተቋራጮች ጋር የሚደርጋቸው የውል ማሻሻያዎች የባለስልጣኑን ጥቅም የሚጎዱ እና በጨረታው ከተወዳደሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንጻር ለአቅራቢው የተለየ ጥቅም የሚሰጡ መሆን የሌለባቸውም ቢሆንም ፤

- በኦዲት ወቅት የማይጸብሪ- ዲማ መንገድ ስራ ፕሮጀክት በውለታው መሰረት ሊሠራ የታቀደው ዲዛይኑ (7m gravel wearing coarse) የጠጠር መንገድ ሲሆን፣ በባለስልጣኑ ፍላጎት መሰረት መንገዱን ለማሻሻል ተብሎ የመንገዱ ዲዛይኑ ወደ 10m Double Bitumineous surface treatment (DBST) እንዲለወጥ መደረጉ፤

- በዚህ የዲዛይን ይዘት ለውጥ ምክንያት ብር 183,454,445.13 የሥራ መጠን ወይም የመጀመሪያውን ያህል ተቀራራቢ ዋጋ (71%) ጭማሬ በመታየቱ ለዚህ ተጨማሪ የሥራ መጠን ጨረታ ሳይከናወን በቀጥታ የመጀመሪያውን ሥራ ላሸነፈው የሥራ ተቋራጭ ሥራው የተሰጠ መሆኑ፤

- ስለ ሁኔታው የኢንጂነሪንግ ፕሮኩዩርመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ጨረታ አለመከናወኑን ሆኖም ግን ተጨማሪ ሥራው ለተቋራጩ ከመሰጠቱ በፊት የሥራው አስፈላጊነት እና የቀረበው ዋጋ አዋጪነት ለኢ.መባ ቦርድ ቀርቦ ተቀባይነት እንዳገኘና በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የጸደቀ መሆኑን ይህን ዓይነቱ አካሄድ በመንግስት ግዢ አዋጅ አንቀጽ 51 እንዲሁም መመሪያ ተቀባይነት ያለው መሆኑን መግለጻቸው፤

- የማይጸብሪ- ዲማ ፕሮጀክት ከጠጠር ወደ አስፋልት እንዲቀየር በመወሰኑ በመገንባት ላይ ካለው የስራ ተቋራጭ ጋር ውይይት ተደርጎ የቀረበው ፕሮፖዛል አዋጪ ሆኖ በመገኘቱ ለኢ.መ.ባ. ቦርድ እና ለመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ፍቃድ ተጠይቆ በመፈቀዱ ከተቋራጩ ጋር ተጨማሪ ውል በመግባት የፕሮጀክቱ የሥራ ዓይነት እና ጠቅላላ ዋጋ እንዲስተካከል መደረጉን የሰሜን ሪጂን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር መግለጻቸው፤

- ይሁን እንጂ የግዢ መመሪያው አንቀጽ 4.1.3.2 ላይ የተጠቀሰው ሲታይ፣ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በመከሰታቸው ምክንያት በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ዘርፍ ስራዎችን ማሠራት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና በቴክኒክ ወይም በኢኮኖሚያዊ ጥራት ጠቀሜታ ምክንያቶች እነዚህን ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ከመጀመሪያው ነጥሎ ማሰራት

የማይቻል ከሆነ ያለጨረታ ለመጀመሪያው ተጫራች በመስጠት ማሰራት እንደሚቻል መጠቀሱ፤

- በግዢ መመሪያው ያልታሰቡ ሁኔታዎች በመከሰታቸው ምክንያት ማለት የብር 183,454,445.13 ወይም በመጀመሪው ጨረታ የተሰጠውን ዋጋ ያህል ተቀራራቢ የሆነ የሥራ መጠንን በመጀመሪያ ጥናቶች ሳይታዩ/ሳይታሰቡ የተከሰቱ ናቸው ብሎ ለመቀበል እና ሌሎች ተወዳዳሪዎች ባለመወዳደራቸው የባለስልጣኑ ጥቅም ያልተጎዳና ለአቅራቢውም የተለየ ጥቅም ያልሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ ስላልተቻለ በባለስልጣኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም ፡፡
- የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች ከመነሻ ጥናት ጀምሮ እስከ ትግበራና ፍጻሜው ያለውን ሂደትና ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ ሊዘጋጅ፣ ሊጠናቀርና ለሌሎች ለወደፊት ለሚሠሩ ኘሮጀክቶች ግብዓት ሊሆን በሚችል መልኩ በባለስልጣኑ ሊያዙና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር/ ሊተላለፉ የሚገባ ቢሆንም ፤
- እነዚህ መረጃዎች በባለስልጣኑ የሚጠናቀሩበትና የሚጠበቁበት ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤
- ይህም መሆኑ፤ ጥሩ አፈጻጸም ካለው ፕሮጀክት መልካም ተሞክሮዎችን ለመቅሰም እንዳይቻል ከማድረጉም በላይ መረጃዎቹ ለተለያዩ ተግባራት ሲፈለጉ ለማግኘትና ጥቅም ላይ ለማዋል አስቸጋሪ የሚደርገው መሆኑ፤
- ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አስተዋጽኦ አላቸው ተብለው በተለዩት ፕሮጀክቶች ላይ የድህረ ትግበራ ግምገማ (ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ሥራ ከጀመረ ጥቂት ዓመታት በኋላ ቀደም ብለው በተቀመጡ የፕሮጀክቱ በአካባቢ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉት ተጨማሪ ፋይዳ መሠረት፣ የተገኙ የግብ ስኬቶች እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች) ማካሄድ አሰፈላጊ ቢሆንም፤
- የድህረ ትግበራ ግምገማ ማድረግ ውድ በመሆኑ ለሁሉም ፕሮጀክቶች ማካሄድ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ በመሆኑ በናሙናነት በተመረጡ 4 የመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ የድህረ ትግበራ ግምገማ በመካሄድ ላይ

እንደሚገኝና በተጨማሪ ፕሮጀክቶች ላይም የድህረ ትግበራ ግምገማ ለማድረግ አማካሪ ተመርጦ ወደ ሥራ ለመግባት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ፤

- ይሁን እንጂ በሀገሪቱ ከተጠናቀቁ ቆየት ያሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታቸው ከፍተኛ የሆኑ ትላልቅ ፕሮጀክቶች በመኖራቸው፣ የሚጠበቁት አዎንታዊና አሉታዊ ፋይዳዎች ላይ እስከ አሁን የድህረ ትግበራ ግምገማ አለመሠራቱ ተገቢ ሆኖ አለመሆኑ፤
- በኦዲት ወቅት የታዩ ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንገድ ፕሮጀክቶችን ከጊዜ፤ከወጪ እና ከጥራት አኳያ በብቃት በቅልጥፍናና ኢኮኖሚዊ በሆነ መንገድ ለመፈጸም እንዲቻል በቅድመ ጥናት፤ ዲዛይን ዝግጅት፤ የአፈጻጸም እቅድና ትግበራ፤የካሳ ክፍያና የመንገድ ሳይቶችን ለግንባታ ዝግጁ ማድረግ፤ተለዋጭ ትእዛዞች (Variation Orders) አሰጣጥ፤የአማካሪ መሃንዲሶች እና ሌሎች ባለሙያዎች ቅጥርና አገልግሎት አሰጣጥ ፤ እንዲሁም ድህረ ትግበራ ክትትልና ቁጥጥር ረገድ በታዩ ድክመቶች ላይ የባለስልጣኑ መ/ቤት አግባብ ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

9.1 <u>ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የህንፃና የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ደረጃና ቁጥጥር</u>

- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚመራባቸውና ለመኖሪያ ቤትና ህንፃ ግንባታ ሥራ አፈፃፀም መለኪያ የሚሆን የህንፃ መመሪያ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሊዘጋጅ፣ የሥነዱ ትግበራ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥና የተሟላ እንዲሆን ለማስቻል ሚ/ር መ/ቤቱ ተገቢውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ለሥራ ተቋራጮች፤ ለአማካሪዎች፣ ለባለሙያዎችና ለሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሊሰጥ፣ ሊያሰራጭና አተገባበሩ ላይም የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ሊሰራ የሚገባ ቢሆንም ፤

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በግንቦት ወር 2003 ዓ.ም ተዘጋጅቶ የፀደቀው የህንፃ መመሪያ ቢኖርም በናሙና በታዩት አዳማ፣ ሻሸመኔ፣ ባህር ዳርና ሀዋሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤቶች፣ የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ እና የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ባለሥልጣን ኃላፊዎች በሠነዶቹ ላይ የወሰዱትን የግንዛቤ ማስጨበጫ ከታች በሥራቸው ላሉ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ያላስተላለፉ መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያዘጋጀው የህንፃ መመሪያ በናሙና በታዩት በአዳማ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤትና በይርጋለም ከተማ ማዘጋጃ ቤት ያልደረሰ መሆኑን፣ እንዲሁም በሻሸመኔና በአዳማ ከተማ ማዘጋጃ ቤቶች ሠነዱ ቢደርሳቸውም ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ አለመቅረቡ፤

- ሠነዱ የደረሳቸው የይርጋለም፣ የሀዋሳና የሻሸመኔ ከተማ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች እና የሻሸመኔና አዳማ ከተማ ማዘጋጃ ቤቶች እስከ አሁን ወደ ትግበራ ያልገቡ መሆኑ፤

ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የተዘጋጀው የህንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ በሀርድ እና በሶፍት ኮፒ መላኩን፣ ያልተላኩባቸውም ክልሎች ክፍተታቸው እንዲሞላ የመጠየቅ ኃላፊነት የክልሎች ቢሆንም፣ ክፍተቱን አጥርተው ለመሙላት እንደሚከታተሉ መገለጹ፣

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስትም በትርጉም ሂደት ላይ መሆኑን ማረጋገጣቸውንና በአሁኑ ወቅት ለአማራ፣ ኦሮሚያ እና ትግራይ ክልሎች ለሁሉም አመራሮች ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መሰጠቱን፤ እንዲሁም በቀጥታ ለሚመለከታቸው ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው ሥልጠና በመስጠት የማጠናከር ሥራዎች እንደሚከናወኑ፣ ሥርጭቱ የደረሳቸውም ወደ ትግበራ ያልገቡት የአደረጃጀትና የህንፃ ሹም ምደባ በአፈጻጸም ሥራ ላይ መሆኑንና አፈጻጸሙን እንደሚከታተሉ የገለጹ መሆኑ፤

ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ለሚመለከታቸው ሁሉ ሰነዱን ያሰራጩ መሆኑን ቢገልጹም፣ አንዳንዶቹ ያልደረሳቸውና ከደረሳቸውም አንዳንዶቹ ከክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም መሆኑን የገለጹ ሲሆን፣ የግንዛቤ

ማስጨበጫውም ለሦስት ክልሎች ብቻ የተሰጠ ከመሆኑ እና ግንዛቤውን ያገኙት የአመራር አካላትም ወደ ታች አለማውረዳቸው፤ እንዲሁም በፍጥነት ወደ ትግበራ አለመገባቱ የመረጃ ክፍተት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የህንጻ መመሪያውን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫውን የወሰዱ የአመራር አካላት ወደታች አለማውረዳቸው፣ ሰነዱ በሁሉም ቦታ አለመሰራጨቱና መመሪያው በስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል አለመደረጉ ተገቢ አለመሆኑ፤

- በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚገኙ ሰነዶችን (ኮዶች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች፣ የማስፈፀሚያ ህጎችና ደንቦች...) ተጠቃሚዎች በሙሉ (የመኖሪያ ቤትም ሆነ ህንጻ የሚገነቡ ግለሰቦችና ድርጅቶች) በቀላሉ ሊያውቁና ሊያገኙ የሚችሉበት የመረጃ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም ፤
- በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚገኙትን ሠነዶች ዝርዝር የሚገልጽ መረጃና ሠነዶቹን ማግኘት የሚፈልጉ ተጠቃሚዎች በቀላሉ ሊያገኙ የሚችሉበት የመረጃ ሥርዓት በበቂ ሁኔታ አለመዘርጋቱ፤ በድህረ-ገጽ መጠቀም ለሚችሉ ተጠቃሚዎችም ቢሆን፣ የሁሉም ሰነዶች ዝርዝር በድረ-ገጹ ላይ ተካቶ አለመገኘቱ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙት ሰነዶች ዝርዝር መረጃ በህግ መምሪያ ክትትል እየተደረገ እየወጣ እንደሚገኝ፣ ከዚህ በፊት የወጡትንም ጭምር የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እየከተናወነ መሆኑና በቀጣይ በኤሌክትሮኒክስ ኮፒ በማዘጋጀት በሽያጭ የሚቀርቡትን ልዩ ልዩ ሰነዶች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ የአቅጣጫ ጠቋሚና የቢሮ ቁጥር አድራሻ መግለጫ በቋሚነት መዘጋጀቱን፤
- እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ-ገፅም የተወሰኑ መረጃዎችን እንዲይዝ መደረጉን እና (በክፍያ የሚወሰዱት ካልሆነ በስተቀር) የሚቀሩትንም አከታትለው እንዲጫን እንደሚያደርጉና የዲዛይን ኮዶችን ተደራሽ ለማድረግ ለክልሎች ከክፍያ ነጻ እንዲዳረስ መደረጉን ገልጸዋል፡፡
- ሆኖም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እየተሠራ ያለው ጅምር ሥራ ጥሩ ቢሆንም፣ የተዘጋጁትን ሠነዶች በሙሉ ዝርዝራቸውን የሚገልጽ መረጃ

አለመኖሩና ሠነዶቹን ማግኘት የሚፈልጉ ተጠቃሚዎች ሁሉንም ሠነዶች በቀላሉ ሊያገኙ አለመቻላቸው ተገቢ አለመሆኑ፤

- በክልልና ከተማ መስተዳድር በጀትና ድጋፍ የሚገነቡ መኖሪያ ቤቶች እና ህንፃዎች ከመገንባታቸው በፊት በቂ የመነሻ ጥናት ስለማይደረግ፤

1. በይርጋለም አቦስቶ አካባቢ በ2000 ዓ.ም. የተጀመሩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የሚገዛቸው ባለመገኘቱ 12 ብሎኮች ግንባታው ባለበት ደረጃ እንዲሸጡ መወሰኑ፣
2. በአዳማ ከተማ በ2000 ዓ.ም ግንባታቸው የተጀመሩ ደምበላ ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤት ከግንባታው ጀርባ የከተማው የጎርፍ ውሃ ሲያልፍ የመሬት መንሸራተት በማስከተሉ ምክንያት 4ቱ ቆርቆሮ ተመቶ፣ 3ቱ ቆርቆሮ ሳይመታላቸው 4ቱ ደግሞ G+3 ላይ ደርሰው መቆማቸው፤
3. በባህር ዳር በ1999 የተጀመሩ የሲቪል ሰርቪስ ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሁለት ብሎኮች መሠረት ከወጣ በኋላ ቦታው ላይ ውሃ በመፍለቁ ምክንያት ሥራው መቋረጡ፣

- በህንፃና በመኖሪያ ቤት ግንባታ ወቅት ምን ያህሉቦታ ለአረንጓዴ ሽፋን መዋል እንዳለበት የተዘጋጀ መመሪያ አለመኖሩ፣
- በናሙና በታዩ ከተሞች ውስጥ በመንግስትም ሆነ በግለሰብ ለሚገነቡ ህንፃዎች ወይም መኖሪያ ቤቶች ለግንባታ ከተፈቀደላቸው ቦታ ምን ያህሉን ለአረንጓዴ ሽፋን መጠቀም እንደሚገባቸው የሚገልፅ መመሪያ በማዘጋጀት በስራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ፤
- የመኖሪያ ቤቶች እና ሕንፃዎች በአማካሪ መሀንዲስ ክትትልና ቁጥጥር ሣይደረግባቸው የሚሰሩ መሆኑ፣
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በአዲስ አበባ ከተማ ከጥር 15/2001 ዓ.ም በፊት ያሉ የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታዎች ያለአማካሪ ባለሙያ ተሳትፎ ቀጥታ ከሥራ ተቋራጩ ጋር ባለው ውለታ መሰራታቸውን፣ በሀዋሳ፣ በባህር ዳርና በአዳማ ከተሞች የ1999 ዓ.ም ግንባታዎች ያለአማካሪ ተሳትፎ እንደተሰሩ፣ በሻሸመኔና በይርጋለም ከተሞች ደግሞ የመስክ ጉብኝት እስከ

ተደረገበት ጊዜ ድረስ በግንባታ አማካሪ ባለሙያዎች የታገዘ ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ፣

- የግንባታ ሥራ በሚከናወንበት ቦታ የግንባታ ክትትል የመረጃ መዝገብ (site book) በማዘጋጀት የግንባታ ተቆጣጣሪዎች ክትትል በሚያደርግበት ወቅት ያገኙትን መረጃ መዝገበው መያዝ ሲገባቸው በብዙዎቹ የመንግስትና የግለሰብ ህንጻዎች ላይ የመረጃ መዝገብ የማይቀመጥ መሆኑ፣
- የህንጻ አዋጁን ተከትሎ የግንባታ የመረጃ መዝገብ አደራጃጀት ስርዓት ባለመጠናቀቁ በግንባታ ወቅት የታዩ ችግሮችንና ልዩ ልዩ ትእዛዞችን አማካሪው ለሥራ ተቋራጩ የሚገልጽበትና የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን የሚያረጋግጥበት ግለጽ አሰራር አለመኖሩ፣
- ማንኛውም ግንባታ በግንባታ ሂደት ላይ እያለ በየደረጃው የግብዓት ጥራት የናሙና ፍተሻ ሊደረግና ውጤቱ በፅሁፍ ተዘጋጅቶ ማህተም ሰፍሮበት ሊቀርብ የሚገባ ቢሆንም፣
- ለግንባታ በሚውሉ ግብዓቶችላይ መደረግ ስላለበት የናሙና ምርመራ ዝርዝር መመሪያ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተዘጋጅቶ አለመሰራጨቱ፣
- የጋራ መኖሪያ ቤቶችና የህዝብ መገልገያ ህንፃዎች ሲገነቡ ለአካል ጉዳተኞች እንቅስቃሴ አመቺ መሆናቸው ሊረጋገጥ የሚገባ ቢሆንም፣
- የጋራ መኖሪያ ቤቶችና የህዝብ መገልገያ ህንፃዎች ግንባታ የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ ታሳቢ ያደረጉ አለመሆናቸው፣
- በአዲስ አበባ ይርጋዓለም ሃዋሳ አዳማ ሻሸመኔከተሞች የተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችና የህዝብ መገልገያ ህንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች እንቅስቃሴ ታስቦ የተሰራ ተዳፋት /Ramp/ የሌላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የመስታወት ግድግዳ የሚገጠምላቸው ህንፃዎች መስታወቱ ደረጃ ሊወጣለትና ለተጠቃሚውም ሆነ ለሌሎች አካላት ጉዳት የማያስከትል መሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ የሚገባ ቢሆንም ፣

- በሻሸመኔ፣ በአዳማ፣ በአዋሳና በባህር ዳር ከተሞች በህንፃዎች ላይ የሚገጠሙ መስታወቶች ከውበት አንፃር እንጂ የአካባቢ ብክለት የማያስከትሉ (ሙቀት የማይፈጥሩና አንፀባራቂ) ስለመሆናቸው በማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ አለመሆኑ፤
- በአዲስ አበባ፣ ይርጋለም፣ ሀዋሳ፣ ሻሸመኔ፣ አዳማና ባህር ዳር በሁሉም የግንባታ ሳይቶች የመኖሪያ ቤትና ህንፃ ግንባታ ሰራተኞች ለሥራ ሲሰማሩ የደህንነት መጠበቂያዎችን የማይጠቀሙ መሆኑ፤
- በክልልና ከተማ መስተዳድር በጀትና ድጋፍ የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ብዛት እና ጊዜ በመርሐ ግብር ከተያዘው ጋር የተጣጣመ ሊሆን የሚገባ ቢሆንም፤
- ከ1998 እስከ 2002 በፌዴራልና በክልል ከተሞች 396,000 ቤቶች ለመገንባት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በእቅድ ዘመኑ መገንባት የተቻለው 145,801 ቤቶችን ብቻ በመሆኑ አፈፃፀሙ ከግማሽ በታች መሆኑን ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለመገንዘብ መቻሉ፤
- በሻሸመኔ ግንባታቸው በ2000 ዓ.ም. እንዲጀመር የታቀዱት 26 ብሎኮች ሲሆኑ፣ በመጀመሪያው ፌዝ 4 ብሎኮች፤ በሁለተኛው ፌዝ 9 ብሎኮች ሊጀመሩና ግንባታቸውም በስምንት ወር ውስጥ ሊጠናቀቅ ታቅዶ እስከ ጥቅምት 2004 ዓ.ም. ያልተጠናቀቁ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ፌዝ የተጀመሩት አራት ብሎኮች 82.39% መጠናቀቁና በሁለተኛው ፌዝ የተጀመሩት 9 ብሎኮች ደግሞ 92.91% የስትራክቸር ስራቸው ብቻ መጠናቀቁ፣
- በአዋሳ በ2000 ዓ.ም 97 ብሎክ 92ቱ G+4፣ 5ቱ ደግሞ G+2 እንዲሰሩ የታቀዱ ሲሆን ወደ ክንውን የገቡት 75ቱ G+4ና 5ቱ G+2 እና የቀሩት 17 G+4 አለመጀመራቸው፣
- በአዳማ በ2000 ዓ.ም ሊገነቡ ከታቀዱት 1,506 ቤቶች ውስጥ እየተገነቡ የሚገኙት 1,194 ቤቶች ሲሆኑ፣ ከነዚህም እስከ ጥቅምት 22/2004 ዓ.ም

ድረስ 72.11 በመቶ የደረሱ ሲሆን 312 ቤቶች በደንበላ ሳይት በአርጂን /ጎርጅ/ እና ኮንትራክተር ሥራ ማቋረጥ ምክንያት ግንባታቸው መቆሙ፤

- የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ የቤቶች የማጠናቀቂያ ጊዜ እቅድና አፈጻጸም የተጣጣመ ስለመሆኑ ሲታይ፡- በ2000 በጀት ዓመት ሊገነቡ የታቀዱ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በኦሮሚያ 14,313፣ በአማራ 13,214፣ በደቡብ 6,355፣ በትግራይ 5,548፣ በሐረር 1,540ና በድሬዳዋ 1,877 ሲሆን በቅደም ተከተል አፈፃፀማቸው ግን እስከ ሐምሌ 2003 ዓ.ም. ድረስ 58%፣ 72%፣ 70%፣ 69%፣ 70%ና 79% ብቻ መሆኑ፤

- በአዲስ አበባ፣ በአዋሳ፣ በአዳማ፣ በሻሸመኔና በይርጋለም የሚገኙ የየከተሞቹ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው ከግብዓት እጥረት (ሲሚንቶ፣ ብረት፣ የሳኒተሪና የኤሌክትሪክ እቃዎች)፣ የተቋራጭ የአቅም ውስንነት፣ የመሠረተ ልማት አቅራቢ ድርጅቶች የሥራ መጓተት እና የበጀት እጥረት በማጋጠሙ የተከሰተ መሆኑ፤በሻሸመኔ፡በሀዋሳ፡በአዳማ፡እና በአዲስ አበባ ከተሞች ለሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እንደ መብራት እና ውሃ የመሳሰሉ የመሠረተ ልማት አውታሮች ዝርጋታ ስራ በፍጥነት ስለማይካሄድ ቤቶችን በወቅቱ ለማስተላለፍ ችግር መፍጠሩና ተገልጋዩ ህብረተሰብም የተሟላ የመሠረተ ልማት አገልግሎት እንዳያገኝ በማድረግ ላይ መሆኑ፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም የመኖሪያ ቤቶችና ሕንጻዎች ግንባታ በታያዘለት የጊዜ ሰሌዳ፤ በጀትና የጥራት ደረጃ በማከናወን ለተገልጋዩ ህብረተሰብ በወቅቱ እንዲተላለፉ፤ የተሟላ የመሰረተ ልማት አገልገሎቶችም በፍጥነት እንዲቀርብላቸው፤ የሚገነቡት ህንጻዎችና መኖሪያ ቤቶች የአካል ጉዳተኞችንና ሌሎች ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ከግንዛቤ ያስገቡና ለህብረተሰቡ ምቹ የመኖሪያ አካባቢ እንዲሆኑ ከላይ በተመለከቱት ግኝቶች ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድረሻ አካላት ጋር አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወስድ በሪፖረታችን አሳስበናል፡፡

9.2 <u>በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የመንገድ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ</u>

- ጽ/ቤቱ በአዋጁ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለመንገድ ጥገና ከተጣለ የነዳጅ ታሪፍ የሚሰበስበውን ገቢ በኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት በኩል እየተሰበሰበ በወሩ

መጨረሻ ወደ ፈንዱ ሂሳብ ገቢ መደረግ ሲገባው በወቅቱ ገቢ ስለማይደረግ በአማካኝ ከአንድ ወር እስከ ሁለት ወር ዘገይቶ ገቢ የሚደረግ መሆኑ፤

- በቀድሞው የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በተላለፈ መመሪያ መሰረት ከቅባት እና ዘይት ሽያጭ መሰብሰብ ያለበት ገቢ በነዳጅ ማደያ ድርጅቶች በወቅቱ መሰብሰብና ገቢ መደረግ ሲገባው፤ ነባርም ሆኑ አዲስ የተቋቋሙ የነዳጅ ኩባንያዎች በወቅቱ የማያስገቡ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ መንግሥት ከሱዳን እና ከጅቡቲ መንግስታት ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በውሉ መሰረት በወቅቱ ለመሰብሰብ ጽ/ቤቱ ከኮሜት ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር እና ከወጋገን ባንክ አክስዮን ማህበር ጋር የውል ስምምነት ያደረገ ቢሆንም ገቢው በውሉ መሰረት በወቅቱ ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉ፤
- የኮሜት ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር የሰበሰበው የውጭ ምንዛሪ በትክክለኛው የምንዛሪ ምጣኔ (rate) መሰረት ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ ኩፖኖቹ መቼ እንደተሸጡ የሚያሳይ መረጃ ባለመያያዙ ለማጣራት አለመቻሉ፤
- በሁለቱ ድርጅቶች አማካኝነት እየተሰበሰበ የሚገባው ገቢ በውል ስምምነቱ መሠረት በትክክለኛው የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ እየተሰላ ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ በጽ/ቤቱ በኩል የተከናወነ ኦዲት አለመኖሩ፤
- የወጋገን ባንክ ሚያዝያ 18 ቀን 1998 ዓ.ም.የወሰደውን 300 ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ ገቢ መሰብሰቢያ ባለ 10 ዶላር የኩፖኖች (ቁጥር 0001 እስከ 0300) ሽያጭ እስካሁን ገቢ አለማድረጉ፤
- ጽ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 66/89 መሰረት ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል የገንዘብ ቅጣት ገቢ እንዲሰበስብ ገቢውም የተሽከረካሪ ክብደት መቆጣጠርያ ደንብን ለማስፈጸም ስልጣን በተሰጠው አካል አማካኝነት እየተሰበሰበ እስከ ወሩ መጨረሻ ወደ ፈንዱ ሂሳብ ገቢ እንዲደረግ የተደነገገ ቢሆንም እስከአሁን ምንም ዓይነት ገቢ አለመሰብሰቡ፤

- የክብደት መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ከክብደት በላይ የጫነ ተሽከርካሪ ሲመጣ የቅጣት ወረቀት በመጻፍ ለፍርድ ቤት ሲያስተላልፉም፣ የቅጣቱ መጠን በፍርድ ቤቱ እየተወሰነ አሽከርካሪው የተጣለበትን ቅጣት የሚዛን ጣቢያው ለሚገኝበት ክልል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ገቢ ስለሚደረግ ወደ መንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ሂሳብ በማዘዋወር ገቢውን ሊሰብሰብ አለመቻሉ፣

- ገቢውን ወደ መንገድ ፈንድ ሂሳብ ለማዞር አስቸጋሪ ያደረገውን የአሰራር ሂደት ለመቀየር አዋጁን ለማሻሻል የተጀመረው ሂደት ባለመጠናቀቁ አሁንም ገቢው ወደ መንገድ ፈንድ እየገባ አለመሆኑ፣

- ከክብደት በላይ የጫኑ ተሽከርካሪዎችን ለመለየት የሚያስችል ሚዛን በሁሉም የመግቢያ እና የመውጫ በሮች ባለመኖሩ ተሽከርካሪዎቹ በትርፍነት የጫኑትን ጭነት እንዲያራግፉ በማድረግ በመንገዶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የማድረግ ሥራ አለመሰራቱ፣

- ጽ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 66/1989 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በክብደት ላይ የተመሰረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ እንዲሰበስብ የተፈቀደለት ሲሆን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ አለመደረጉ፣

- በአዋጁ መሠረት በክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችል ደንብና መመሪያ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ለውሳኔ የቀረበ ቢሆንም ውሳኔ ባለማግኘቱ ተግባራዊ ለማድረግ አለመቻሉ፣

- ጽ/ቤቱ ከመንገድ ጠቀሜታ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በውክልና ከሚሰበስቡ ተቋማት ጋር በተደረገው የውል ስምምነት መሠረት ባለመሰብሰቡ የመንገድ ጥገና ወጪን አስተማማኝ በማድረግ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደሩ፣ ለመንገድ ጥገና ከጽ/ቤቱ የሚመደበው በጀት አነስተኛ እንዲሆን እና መንገዶች በወቅቱ ጥገና እንዳይደረግላቸው ማድረጉ፣

- ፈንዱ የገንዘብ እጥረት ያለበት በመሆኑ ሁሉንም ከተሞች የመንገድ ጥገና እና ደህንነት ፈንድ እንዲያገኙ ለማካተት አለመቻሉ፣

- ጽ/ቤቱ ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት ፈንድ ሲሰጥ ገንዘቡ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ስራ ላይ መዋሉን በወሊሶ ማዘጋጃ ቤት፤በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን እና በአማራ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን የተቀጠሩ አማካሪ ድርጅቶችም ሆኑ የውስጥ ኦዲት ክፍል ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የማያደርጉ መሆኑ፤
- ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ብር 39,977,928.20 ለአማካሪ ድርጅቶች ክፍያ ወጪ የተደረገ ቢሆንም፣ የተቀጠሩት አማካሪ ድርጅቶች የማማከር ሥራቸውን በተገቢው መንገድ ለማከናወናቸው የቅርብ ክትትል እና ቁጥጥር ሳይደረግ የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ የሚፈጸም መሆኑ፤
- የውስጥ ኦዲት ክፍሉ ሙያው የሚጠይቀው የቴክኒክ ባለሙያዎች የሌሉት በመሆኑ ተገቢው የፕሮጀክቶች ብቃት ምዘና በአግባቡ እየተከናወነ አለመሆኑ፤
- የውስጥ ኦዲት ክፍሉ የፋይናሻልና ቴክኒካል ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ የያዘ ቢሆንም ኦዲት አለማድረጉ፤
- የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ ዕቅድ ከሚመደበው በጀት ጋር የሚጣጣም ለመሆኑ በባለሙያ አለመታየቱ፤
- ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚፈቀደው በጀት በወቅቱ ባለመጽደቁ፣ የበጀት ዓመቱ ከመግባቱ አንድ ወር አስቀድሞ የጸደቀው አመታዊ ዕቅድ እና በጀት ለመንገድ ኤጀንሲዎች በወቅቱ እንዲደርስ የማይደረግ መሆኑ፤
- በጽ/ቤቱ የአምስት ዓመት (ከ1998 እስከ 2002) ስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት የመንገዶችን ጥራት ደረጃ በማሻሻል የአስፋልት፣ የጠጠር እና የገጠር መንገዶች ሁኔታ እንደቅደም ተከተላቸው አሁን ከሚገኙበት 43%፣ 31% እና 30% ወደ 80%፣ 60% እና 50% በእቅዱ ዓመት መጨረሻ (በ2002 ዓ.ም.) ለማሳደግ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ዕቅዱ የጽ/ቤቱን ድርሻ በግልጽ ስለማያሳይ አፈጻጸሙን ለመገምገም ያልተቻለ መሆኑ፤
- በጽ/ቤቱ የአምስት አመት ስትራተጂክ እቅድ መሰረት (ከ1998 እስከ 2002 በጀት ዓመት) የመንገድ ጥገና አማካይ የኪ.ሜ ወጪን በመቀነስ በኪሎ ሜትር በአስፋልት፤ በጠጠር እና በገጠር መንገድ ላይ እንደ ቅደም ተከተላቸው 20

ሺ.ህ 15 ሺ.ህ እና 5 ሺ.ህ የሚገመተውን የመደበኛ ጥገና ወጪ በ2002 መጨረሻ ወደ 5 ሺ.ህ፣ 5 ሺ.ህ እና 3 ሺ.ህ ዝቅ እንዲል በማድረግ የመንገድ ጥገና ሥራን በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሥራት የተቀመጠው ግብ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተዘጋጀ የመንገድ ጥገና ደረጃ ቢኖርም ደረጃውን ተከትለው የመንገድ ጥገና ሥራዎች ወጥ (standardize) በማድረግ እየተጠገኑ አለመሆኑ፤

- በናሙና ከተመረጡ የመንገድ ኤጀንሲዎች (በኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ መንገዶች ባለሥልጣን፣ እና በአማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እንዲሁም በባህርዳር፣ በጐንደር፣ በሀዋሣ፣ በጅማ፣ በወሊሶ እና በወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት) የመንገድ ጥገና ሂደት መሰረታዊ የጥገና ደረጃ ኖሮት የማይከናወን መሆኑ፤

- ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ጥገናው የሚከናወንበት ደረጃ ባለመኖሩና፣ ለጥገና የሚጠቀሙበት ግብዓት እና ፕሮጀክቱ የሚወስደውን ጊዜ ተወስኖ ተግባራዊ ባለመደረጉ፤ እንዲሁም አማካሪ ድርጅቶችም ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ሳያደርጉ ተሰራ ተብሎ የቀረበውን የክፍያ ሰርተፊኬት ያለገደብ የሚያረጋግጡ በመሆኑ በጊዜ እና በዋጋ ከዕቅድ በላይ የሆኑት ፕሮጀክቶች አፈጻጸሞች የሚያሰዩ መሆኑ፤

- ለዚህም የጫኖ-ጨንቻ መንገድ ጥገና ሥራ በ1997 ዓ.ም. የተጀመረ ቢሆንም በተያዘለት የጊዜ ገደብ እና የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት በመደበለት በጀት ከብር 10,390,999.24 ተጨማሪ ብር 6,787,628.52 (የፕሮጀክቱን 74%) ተጠቅሞም አለመጠናቀቁና እሰከ ጥቅምት 2004 ርክክብ አለመፈጸሙ፤

- ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ በደቡብ መንገዶች ባለስልጣን በሰንዶዴ ድልድይ ግንባታ ላይ የኮንትራት ውል ከመፈጸሙ በፊት በቂ ዲዛይን እና የአፈር ናሙና ጥናት ባለመደረጉ ምክንያት ከተያዘው በጀት በላይ ወጪ ማስወጣቱ፤

- መቀሌ ዩኒቨርሲቲ በትግራይ ክልል ውስጥ በክልሉና በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በአለም ገና ቡታጅራ መንገድ ላይ በተከናወኑ የመንገድ ጥገናዎች ጥናት የጥገናው ሥራ በሚካሄድበት ወቅት የውሃ

ፍሳሽ ማስወገጃ ያልተሠራላቸው፣ መሠረታዊ የዲዛይን ችግር ያለባቸው፣ ለጥገና የሚጠቀሙት ጥሬ ዕቃ ደረጃውን ያልጠበቀ እና የላብላቶሪ ቴስት በሚያስፈልጋቸው የመንገድ ጥገናዎች አልፎ አልፎ አለመሰራቱ ፤

- ፈንዱን የሚያስተዳድረው ጽ/ቤት መንገድ የሚጠገንበትን መሠረታዊ የጥገና ደረጃና ተገቢውን የክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ባለመደረጉ የተፈጠረ ክፍተት መሆኑ፤
- ይሁን እንጂ ከላይ የተመለከቱት ችግሮች የደረሱት የመንገድ ጥገናዎች የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ባወጣው የመንገድ ጥገና ደረጃ መሰረት ደረጃቸውን ጠብቀው መሰራታቸው በጽ/ቤቱ ስለማይረጋገጥ የተከሰቱ መሆኑ፤
- በናሙና ከተመረጡ የመንገድ ኤጀንሲዎች ለመረዳት እንደተቻለው የጥገና ደረጃን ወጥ ከማድረግ አንጻር በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት መመሪያና ስለአፈጻጸሙ ሥርዓት (Guide Lines and Procedures) ያልደረሳቸው መሆኑን መግለጻቸው፤
- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የተዘጋጀ የጥገና መመሪያ ቢኖርም በጽ/ቤቱ የሚመደብላቸው ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ የተነሳ መመሪያውን ተግባራዊ አለማድረጋቸው፤
- በአማራ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን፣ ባህርዳር፣ ጎንደር እና ጅማ ማዘጋጃ ቤት፣ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን እና የደቡብ መንገዶች ባለስልጣን መመሪያው በጽ/ቤቱ በኩል ባይደርሳቸውም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ያወጣው መመሪያ ያላቸው ቢሆንም በመመሪያው መሠረት ለመፈፀም በጽ/ቤቱ ከሚመደብላቸው በጀት አናሳነት የተነሳ በመመሪያው መሰረት ጥራት ያለው መንገድ ጥገና ለማድረግ አለመቻሉን መግለጻቸው፤
- በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ሀዋሳ፣ ወሊሶ፣ እና ወልቂጤ ማዘጋጃ ቤት መመሪያው ከጽ/ቤቱ እንዲደርሳቸው ያልተደረገ እና የመንገድ ጥገና ደረጃን ወጥ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ አለመኖሩ፤
- በመስክ ጉብኝት ወቅት የታዩት የመንገድ ኤጀንሲዎች በሙሉ ከጽ/ቤቱ መመሪያና የአፈጻጸም ሥርዓት እንዳልደረሳቸው የገለፁ ሲሆን ጽ/ቤቱ

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ባዘጋጀው መመሪያ መሠረት መጠቀማቸውን አለማረጋገጡ ተገቢ ሆኖ አለመገኘቱ፤

- የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለመገመገም የተቀጠሩ አማካሪዎች ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- የአማካሪ ባለሙያዎች ቅጥር በወቅቱ የማይፈጸም፣ ከተቀጠሩ በኋላም ከአማካሪ ድርጅት ጋር የተፈረመውን ውል አፈጻጸም ለመከታተል የተዘረጋ የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት አለመኖሩ፤
- አማካሪ ድርጅቶች ኃላፊነታቸውን በትክክል ለመወጣታቸው በቂ ክትትል እና ቁጥጥር የማይደረግ፣ በውላቸው መሰረት ለስራው አስፈላጊ የሆኑትን የሰው ኃይል እና ሎጂስቲክ በማሟላት ስራውን እያከናወኑ አለመሆኑ፤
- ከአማካሪ ድርጅቶች ጋር የተፈረመውን ውል አፈጻጸም ለመከታተል የተዘረጋ የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት ሳይኖር፣ የአማካሪ ድርጅቶቹን ቅጥር ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉት መንግስታዊ ድርጅቶች (የመንገድ ኤጀንሲዎች) መሆናቸው ብቻውን ዋስትና አለመሆኑ፣
- ለመንገድ ጥገና አማካሪ ድርጅቶች ለወጣው ወጪ ተመጣጣኝ አገልግሎት ለመገኘቱ በጽ/ቤቱ በኩል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ ተገቢ አለመሆኑ፤
- የጽ/ቤቱን የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ብቃት እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- ለመንገድ ጥገና ለተከፈለው ወጪ ተመጣጣኝ አገልግሎት መገኘቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት ባለመኖሩ በፕሮግራሞችና በፕሮጀክቶች ላይ ጠንካራ የሆነ ወቅታዊ ክትትል የማይደረግ መሆኑ፤
- የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት በጣም ውስን በሆነ የሰው ኃይል የሚንቀሳቀስ በመሆኑ የአማካሪ ቅጥር ክትትል እና ቁጥጥር በውክልና የመንግስት ተቋም ለሆኑ የመንገድ ኤጀንሲዎች የተሰጠ መሆኑ፤

- የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን ኃላፊ አማካሪ ድርጅቶቹ በተባሉበት ቦታ የማይገኙና ክትትልም በአግባቡ የማይደረግ መሆኑን፣
- የወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አማካሪ ድርጅቶቹ የክትትልና የቁጥጥር ሥራውን በአግባቡ እየሠሩ አለመሆናቸው፤
- የአማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን አማካሪ ድርጅቶቹ ያላቸው የሰው ኃይል ውስን በመሆኑ የቁጥጥሩ ሥራ የሚፈለገውን ያህል እንደማይሠራ መግለጻቸው፤
- የኦዲት ክፍሉ ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት የክትትል እና የቁጥጥር ስራ ለመስራት በዕቅድ የያዘ ቢሆንም አለማከናወኑ፤
- በናሙና በተመረጡ የመንገድ ኤጀንሲዎች በተደረገ ማጣራት በአማካሪ ድርጅቶች ላይ በቂ ክትትልና ቁጥጥር አለመከናወኑ ፤
- ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመታት የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒካል ኦዲት ለማድረግ በእቅድ የያዘ ቢሆንም ኦዲቱን አለማከናወኑ፤
- ጽ/ቤቱ በተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች አይነት፣ ርቀት፣ መቼና በምን ያህል ወጪ እንደተጠገኑ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ የመንገድ ጥገና መረጃ የሌለው መሆኑ፤
- በጽ/ቤቱ ሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች ስለሚያስተዳድሯቸው መንገዶች የሚገልጽ (የመንገዶችን አይነት፣ ርቀት፣ ደረጃ፣ የጥገና ታሪክ፣ በምን ያህል ወጪ እና መቼ እንደተጠገኑ...) ዝርዝር መረጃ አለመገኘቱ፤
- በተመሳሳይ ሁኔታም የጥገና ታሪክ የሚገልጽ መረጃ በመስክ ጉብኝት በታዩት የመንገድ ኤጀንሲዎች ጭምር አለመገኘቱ፤
- በጽ/ቤት ደረጃ በየሁለት አመቱ የመንገድ ኤጀንሲዎች የሚያስተዳድሯቸውን መንገዶችና መንገዶቹ የሚገኙበትን ሁኔታ (Road Condition Servey) ጥናት እንዳለና መረጃ የሚያቀርቡ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ መረጃው ሊቀርብልን አለመቻሉ፤

- ስለሆነም የጥገና ታሪክ መረጃ መያዝ ተገቢውን ስራ እና ውሳኔ እንዲሁም ተጠያቂነትን ለማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ ተጠናቅሮ አለመያዙ ተገቢ አለመሆኑ፤

- በኦዲቱ ወቅት የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው የጫኖ- ጨንቻ እና ከወላይታ በዳውሮ ጅማ መንገዶች ጠመዝማዛና አስቸጋሪ ሆነው ሳለ ምንም ዓይነት የመንገድ ላይ ምልክት የሌላቸው በመሆኑ፤ የመንገድ ኤጀንሲዎች በመንገድ ደህንነት ዙሪያ መሠራት ያለበትን ያህል አለመስራታቸውን የሚያሳይ መሆኑ፤

- በሌሎቹም አውራ መንገዶች ላይ በመንገድ ደህንነት ዙሪያ የተሠራው ሥራ አጥጋቢ አለመሆኑ፤

- ጽ/ቤቱም ለመንገድ ኤጀንሲዎች ስለሥራው ግንዛቤ እንዲኖራቸው አለማደረጉና በጀትም እንዳልያዘ ከወልቂጤ እና ጅማ ማዘጋጃ ቤቶች፣ ከደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልላዊ መንግስት መንገዶች ባለሥልጣን፣ ከአማራ ክልል ገጠር መንገዶች ባለሥልጣንና ከባህርዳር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የተሰበሰበው መረጃ የሚያሳይ መሆኑ፤

- የመንገድ ደህንነት ኘሮግራሞች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተደጋጋሚ የክትትልና የግምገማ ሥራዎች መስራቱንና ከኤጀንሲዎች ጋርም ባለው የጋራ መድረክ ግምገማ እንደሚደረግ ቢገለጽም፤ ተደጋጋሚ የክትትልና የግምገማ ሥራዎች በጽ/ቤቱ በኩል መሠራታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፤

- በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት እና በመንገድ ኤጀንሲዎች፣ በአማካሪ ድርጅቶች፣ እና በባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን የሥራ ግንኙነት ለማጠናከር፣ ያላቸውን የስራ ድርሻ፣ ኃላፊነት እና የተጠያቂነት የሚገልጽ መረጃ በማዘጋጀት እንዲደርሳቸው አለማድረጉ ፤

- በዚህም ምክንያት በሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት፣ በመንገድ ኤጀንሲዎችና በአማካሪ ድርጅቶች በኩል ግልጽ የሆነ እና የተቀናጀ የሥራ ግንኙነት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

- ጽ/ቤቱ ፈንድ ከመሰጠቱ በፊት የመንገድ ኤጀንሲዎች ውል እንዲገቡ እና ክፍያዎችም በተገባው ውል መሰረት እንዲፈጸሙ ለማድረግ የሚያስችል ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- የመስክ ጉብኝት ባደረግንባቸው በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ አዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን አማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን፣ ባህርዳር፣ ፍኖተ ሰላም፣ ወሊሶ፣ ጐንደር፣ ጅማ፣ ወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የመንገድ ኤጀንሲዎች ሁሉ አልፎ አልፎ በሚጠሩ አንዳንድ ስብሰባዎች ላይ ከሚነገራቸው ውጪ መረጃው ተዘጋጅቶ ለመሰራጨቱ የሚገልጽ መስረጃ አለመኖሩ፤

  በመሆኑም ጽ/ቤቱ የመንገድ ፈንድ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ፤ የመንገድ ጥገናና ሌሎች የቁጥጥር ስራዎችንበተመለከተ በተነሱት ድክመቶች ላይ አግባብ ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ እንዲወስደ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

9.3 <u>በውሃና ኢነርጂ ሚ/ር በውጭ ድጋፍ/እርዳታ እና በፌዴራል ደረጃ በማስተባበር የሚሰሩ የመጠጥ ውሃ ኘሮጀክቶች/ኘሮግራሞች አፈፃፀም</u>

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል ውሃ ቢሮዎች እና የከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶች ፈንድ በሚሰጡ ባንኮች የግዥ ስርዕት እና በ LC አከፋፈት ዙሪያ በቂ ስልጠና ያልሰጠ ሲሆን፤በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለተግባሪ አካላት የሚሰጡ ሥልጠናዎች ያስገኙት ጠቀሜታም በየጊዜው የማይለካ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል ውሃ ቢሮዎች እና ለከተማ ውሀ ፍሳሽ አገልግሎቶች ፈንድ በሚሰጡ ባንኮች የግዥ ስርዓት ዙሪያ በቂ ስልጠና አለመስጠቱ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንትራክተሮችን መረጃ አጠናክሮ የማይዝ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2002 እና በ2003 አዘጋጅቶ ለተወካዮች ምክርቤት ባቀረበው የካፒታልና የመደበኛ ስራዎች የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ውስጥ ስለግንባታዎች መዘግየትና የፋይናንስ አጠቃቀም ዝቅተኛ ስለመሆኑ አለማካተቱ፤
- የno objection ጥያቄ በ15 ቀን ዉስጥ ምላሽ ማግኘት ሲገባዉ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው በአንዳንዶቹ ክልሎች ከ 1 ወር እስከ 11 ወር ድረስ የሚዘገዩ መሆኑ፤

- የቡታጅራ እና ሀዋሳ ከተማ ውሀ አገልግሎት ድርጅቶች ለጠየቁት “no objection” ምላሽ ለማግኘት እስከ 4 ወር ድረስ የዘገየባቸው መሆኑ፤
- በአማራክልልበ18 ወር ውስጥ ይጠናቀቃሉ ተብለው ለታሰቡ ፕሮጀክቶች የውሀጉድጓድ ቁፋሮ ለማካሄድ ለጨረታ ዶክመንት ዝግጅት እና ለጨረታ ዶክመንት ምዘና ሪፖርት የ “no objection” ፍቃድ ተጠይቆ ምላሽ የተገኘው ከ11 ወር በኋላ መሆኑ፤
- IDA/DFIDእናADB ድጋፍ ሊሰሩ ከታሳቡ አነስተኛ እና በአንፃራዊ ብዙ ገንዘብ የማይጠይቁ በወረዳ ደረጃ ከሚተገበሩ የመጠጥ ውሃ ስራዎች ውስጥ ከ 2002-2003 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሊተገበሩ ታስበው ከነበሩት 3926 ምንጭ ማጎልበት (spot spring) የውሃ ስራዎች ውስጥ የተሰሩት 2549 (66%) ሲሆን በሁለት አመት ሊተገበሩ ከታሰቡት 3567 የእጅ ጉድጓዶች (Hand dug wells) ውስጥየተሰሩት 2091(58%) ብቻ መሆናቸዉ፤
- ከፍያ ለካፒታል በሚጠይቁ እና ብዙ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ከሚያደርጉ የገጠር የመጠጥ ውሃ ስራዎች ውስጥ ከ 2002-2003 ሊገነቡ ከታሰቡ 2345 ጥልቅ ጉድጓዶች (Shallow Well, Deep Wells) ውስጥ የተሰሩት 1161(49.5%) ሲሆን በነዚህ አመታት ውሰጥ ይገነባሉ ተብለው ከታሰቡት 576 /የገጠር ቧንቧ ዝርጋታ/ rular pipe system (RPS) ውስጥ ተሰርተው የተገኙት 103 (18%) ብቻ መሆናቸው፤
- 2003 ዓ.ም በድሬድዋ እና ሱማሌ ብሄራዊ ክልል በአጠቃላይ በወረዳ ደረጃ በIDA/DFID እና ADB ድጋፍ አማካኝነት ሊተገበሩ ታስበው የነበሩ 24 የመጠጥ ውሃ ስራዎች ቢሆኑም በበጀት አመቱ በሁለቱም ክልሎች ምንም አይነት ግንባታ እና ጥገና አለመካሄዱ፤
- በጎንደር ከተማ እየተገነባ ያለው የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት፤ውሃ የሚወጣበት ቦታ መረጣ ላይ በነበረ ችግር፤በዲዛይን ለውጥ እና በጉድጓድ ቆፋሪ ድርጅቶች /drilling companies/ አለመኖር ስራው በመዘግየቱ መጀመሪያ ስራውን ለመጨረስ በዕቅድ ከተያዘው በላይ ተጨማሪ በጀት እስከ ብር 200,000,000. እንደጠየቀና ከፍተኛ የበጀት እጥረት ያጋጠመው መሆኑ፤

- የውሃ ልማት ፈንድ ፅ/ቤት በአጠቃላይ ከሚያገኘው ፈንድ ውስጥ እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ ከ30% በላይ ተጠቅሞ የማውያቅ ሲሆን፣ በ2003 በጀት አመት የተጠቀመው 51% ብቻ መሆኑ፤
- ፅ/ቤቱ ከሚያስተባብራቸው የከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ውስጥ የሚዛን ተፈሪ፣ የወልቂጤ፣ የሃዋሳ እና አክሱም ከተማ ፕሮጀክቶች እያንዳዳቸው ከአንድ አመት በላይ ዘግይተው የተጠናቀቁ መሆኑ፤
- ፅ/ቤቱ የሚያስተባብረው የሀረሪ እና የክብረመንግስት ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ስራቸው እስከ መስከረም 2004 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ያልተጠናቀቀ ሲሆን መጠናቀቅ ከነበረባቸው ጊዜ በላይ 6 እና 4 አመት እንደየቅደምተከተላቸው መዘግየታቸው፤
- የሀረር ከተማ ፕሮጀክት ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ መስጠት ከነበረበት የመጠጥ ውሀ ውስጥ የሚሰጠው ከ 50-60% ብቻ የነበር መሆኑ፤
- በአለም ባንክ ድጋፍ በሃዋሳ ከተማ በ 23,299,981. ብር ወጪ የተገነባው እና የካቲት 2003 ላይ የተጠናቀቀው ፕሮጀክት (በሰከንድ 55 ሊትር ውሀ ለመስጠት እናለ 24 ሰዓት አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ የነበረ ቢሆንም) በኦሮሚያ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰብ እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስቶች መካከል በተፈጠረው አለመግባባት እስከ 30/03/04 ድረስ በጥቅም ላይ አለመዋሉ፤
- ፕሮጀክቱ ተጠናቆ አገልግሎት ላይ ባለመዋሉ እስከ 30/03/04 ድረስ ሊሰጥ ይችል የነበረውን 1,283,040,000 ሊትር ውሀ ሳይሰጥ እንዲቀር እና የከተማው የመጠጥ ውሀ ሽፋን ከ55 % በላይ እንዳይዘል ማድረጉ፤
- የምንዛሪ ጭማሪን አካቶ በጠቅላላለ IDA/DFID ከተያዘው 3,402,568,612. ብር ውስጥ ፕሮግራሙ ከተጀመረ ከ 6 አመት ተኩል በኃላ እና ለመጠናቀቅ አንድ አመት ተኩል /19%/ ሲቀረው ስራ ላይ የዋለው ብር 1,177,620,534.(34.6%) ብቻ መሆኑ፤
- በ 2003 በጀት አመት በአጠቃላይ ከ 2002 የተላለፈ እና የምንዛሬ ጭማሪን አካቶ ለክልሎች ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ እና መከታተያ እንዲውል በIDA/DFID ከተለቀቀ 1,199,216,827 ብር ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው 372,460,910 (31%) ብቻ መሆኑ፤

- በ ADB የሚደገፈው የንፁህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት መጀመሪያ እንዲጠናቀቅ ታሰቦ የነበረው በ 4 አመት ውስጥ ቢሆንም በዋጋ ንረት እና በተለየዩ ምክንያቶች ወደ 6 አመት መራዘሙ፤
- ለፕሮጀክቱ በምንዛሬ ጭማሪ የተገኘውን አካቶ ካለው አጠቃላይ ብር 1,013,452,115 በጀት ውስጥ ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ከ 4 አመት ተኩል በኃላ (ለፕሮጀክቱ ከተያዘው ጊዜ ውስጥ 25% የቀረው) ጥቅም ላይ የዋለው ገንዘብ ብር 213,412,588 (21%) ብቻ መሆኑ፤
- የADB ፕሮግራም ከተያዘለት 6 አመት ውስጥ አንድ አመት ተኩል እየቀረው የትግራይ አማራ፣ ኦሮሚያ፣እናደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ክልሎች እንደቅደምተከተላቸው በአጠቃላይ ለፕሮግራሙ ከተያዘላቸው ብር 73,499,591፣ 231,868,151,፣ 333,140,774 እና 193,488,402 በጀት ውስጥ የተጠቀሙት ብር 20,596,575 (28)%፣ 38,308,867 (16%)፣ 82,748,267 (25%) እና 39,257,826 (20%) ብቻ ሲሆን፤ከአራቱ ልዩ ድጋፍ ከሚሹ ክልሎች ውስጥ የአፋር እና የሱማሌ ክልሎች እንደየቅደምተከተላቸው ካላቸው 35,584,736 እና 78,164,185 ብር በጀት ውስጥ ጥቅም ላይ ያዋሉት ብር 4,857,091 (14%) እና 5,307,726 (7%) ብቻ መሆኑ፤
- በኦዲቱ ወቅት በታዩት የኦሮሚያ፣ የደቡብ፣ የሶማሌ፣የሀረር እና የአማራ ብሄራዊ ክልሎች በየክልላቸው ከሚገኙ ቀበሌ፣ወረዳ እና ዞኖች በሚመጣ ሪፖርት ከ2001-2003 ዓ.ም ተገንብተው ያለቁ እና አገልግሎት የማይሰጡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶችን አገልግሎት ያቆሙበትን ምክንያት፣ አገልግሎት ያቆሙበትን ጊዜ፣ለምን ያህል ግዜ አገልግሎት እንደሰጡ፣ በየክልላቸው ውስጥ ምን ያህል የመጠጥ ውሀ ጉድጓድ እንደተቆፈረ እና ምን ያህሉ እንደመከነ የሚያሳይ የተሟላ መረጃአለመኖሩ፤

  በመሆኑም የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያስተባብራቸው የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች አፈጻጸም ዙሪያ በታዩ ጉድለቶች ላይ አግባብ ካላቸው ባለድረሻ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወስድ በላክነው የኦዲት ሪፖረት አሳስበናል፡፡

9.4 <u>*የፌዴራ ልህብረት ስራኤጀንሲ ለህብረት ሥራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የተዘረጋው የአሰራር ስርዓት አፈፃፀምና ውጤታማነት*</u>

- የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ 2003 ዓ.ም የህብረት ስራ ፖሊሲን ለማስፀደቅ በዕቅድ ከመያዝ ባለፈ በአገር አቀፍ ደረጃ የህብረት ስራ ፖሊሲ እንዲቀረፅ አለመደረጉ፤
- ኤጀንሲው ከ2000-2002 ዓ.ም እና ከ2003-2007 ዓ.ም ባዘጋጃቸው ስትራቴጂክ ዕቅዶች ውስጥ 2204 መጋዘኖች ተገንብተው ለህብረት ስራ ማህበራት ለመስጠት፣ 3 የህብረት ስራ ባንኮችንና 2 ኢንሹራንሶችን ለማቋቋም፣ የግብይት መረጃ ልውውጥ ስርዐትና ትስስር ለመዘርጋት፤ እንዲሁም የስልጠና ፍላጎት ጥናት በ2001 ዓ.ም እና በ2003 ዓ.ም ለማጥናት ዕቅድ ቢይዝም ተግባራዊ አለማድረጉ፤
- ከ2001-2003 ዓ.ም ባሉት የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች ላይ በአለምአቀፍ የስራ ድርጅት (ILO) በየጊዜው የሚወጡ ውሳኔዎችንና ስምምነቶችን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተግባራዊ ለማድረግ፣ የህብረት ስራማህበራትን እንቅስቃሴ ሊያግዙ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ለማዘጋጀት እና በፌዴራል ደረጃ ህብረት ስራ ማህበራትን ለማደራጀት (በመሰረታዊ፣ በዩኒየን እና በፌደሬሽን) በየአመቱ እቅድ ቢይዝም አለማከናወኑ፤
- ክልሎች ህብረት ስራማህበራትን በብዛት የሚያደራጁ ቢሆንም፤አደራጅ ባለሙያዎችን የአዋጭነት ጥናት እንዲያጠኑ በ2001 ዓ.ም እና በ2002 ዓ.ም በተግባር በማሳየት እገዛ ያላደረገ መሆኑ፤
- የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የቤኒሻንጉልና የደቡብ ክልል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች የሶሽዩ ኢኮኖሚ ጥናት እንዲያጠኑ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እገዛ አለማግኘታቸው፤
- በክልል ወረዳዎችና ዞኖች የሚገኙ ህብረትስራማህበራት አደራጆች በመሰላቸው መንገድ የሚያደራጁ መሆኑና፤ የተዘጋጀ መመሪያ አለመኖሩ፤
- በክልሎች የሚሰራው የአዋጭነት ጥናት ወጥነት የሌለው መሆኑ (በቅጽ፣ከሌላ ጥናት ጋር አንድ ላይ በማድረግ፣ የንግድ ዕቅድን እንደአዋጭነት በመውሰድ መሰራቱ)፤

- ባሕላዊና ሀገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት (እድር፣መረዳጃ ማህበር ወዘተ) ወደ ዘመናዊ የህብረት ስራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናት እና ምርምር አለመድረጉ፤
- እስከ ግንቦት 2003 ዓ.ም ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች (ቤኒሻንጉል፣ጋምቤላ፣ሶማሌና አፋር) ከተደራጁት 1539 ኀብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከ2001-2002 ዓ.ም 3 ህብረት ስራ ማህበራትን ብቻ ያደራጀ ሲሆን፣ በ2003 ስለማደራጀቱ መረጃ አለመገኘቱ፤
- የፌዴራል ኀብረት ሥራ ኤጀንሲ በ2002 ዓ.ም አንድ ጊዜ የስልጠና ፍላጎት ጥናት ቢያጠናም በኦዲት ወቅት ከታዩት 8 የወረዳ ኀብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤቶች መካከል ከ2001-2003 ዓ.ም 3 የወረዳ ኀብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤቶች ብቻ ስልጠና ያገኙ መሆኑ፤
- በፌዴራልኀብረትሥራኤጀንሲ ከ2001-2003 ዓ.ምስልጠና የተሰጣቸው ሶስቱ ማህበራት የስልጠና ፍላጎት ያልተጠየቁ ሲሆን 1 ህብረት ስራ ማህበር ደግሞ የስልጠና ፍላጎት ቢጠየቅም የተሰጠው ስልጠና ግን ፍላጎትን መሠረት ያደረገ አለመሆኑ፤
- በሰርቬይ እና በአካል ከታዩ 37 ሕብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 20 (54.05%) የሚሆኑት ከ2001-2003 ዓ.ም ከፌዴራሉም ሆነ ከክልል ኀብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ስልጠና አለማግኘታቸው፤
- እንዲሁም በኦዲት ወቅት ከታዩት 8 የወረዳ ኀብረት ሥራ ማስፋፊያ ጽ/ቤቶች ውስጥ 4ቱ ከ2001-2003 ዓ.ም ከፌዴራል ኀብረት ሥራ ኤጀንሲ ስልጠና ያላገኙ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል የታዩ 2 የወረዳ ኀብረት ሥራ ማስፋፊያ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ከ2001-2003 ዓ.ም ከአንድ ጊዜ በስተቀር በፌዴራል ኀብረትሥራ ኤጀንሲ ስልጠና አለማግኘታቸው፤
- ከወረዳዎች በተገኘው ዓመታዊ ሪፖርት መሰረት በጊምቢና በጎማ ወረዳ ከተደራጁ 112 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 96ቱ (86%) ከ2001- 2003 ዓ.ምስልጠና ያላገኙ መሆኑ፤

- ከዚህ በተጨማሪም በፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የሚሰጡ ስልጠናዎች ንድፈሃሣብ /theory/ ላይ ብቻ በመመስረታቸውና ከተግባር ሥራ ጋር የተቆራኙ ባለመሆናቸው፣ የሰልጣኙን ፍላጎት ለማሟላት አለመቻሉ፤
- የፌዴራል ኅብረት ሥራአጀንሲ ለኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ባለሙያዎችና ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጣቸው ስልጠናዎች ያስገኙትን ውጤት የሚለካበት ስርዓት ባለመዘርጋቱ የተገኘውን ውጤት ለመገምገም አለመቻሉ፤
- ኤጀንሲው ለክልል ኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት የአሠልጣኞች ስልጠና ቢሰጥም አሠልጣኞች በሄዱበት ቦታ ስልጠናውን ተግባራዊ ማድረጋቸውን አለመከታተሉ፤
- በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት 4 ክልሎች መካከል በ4ቱም የክልልኅብረትሥራ ማስፋፊያ አካላት የተሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ውጤት አለመለካቱ፤
- በአማራ፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ክልሎችና መስተዳድሮች በስራ መመሪያ ዝግጅትና አተገባበር ዙሪያ በኤጀንሲው በተጠናው ጥናት በአማካይ 78% መመሪያ አተገባበራቸው ደካማ መሆኑ፤
- በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና በክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት በእርጅና፣ በጡረታና በህመም ምክንያት ከአባሎቻቸው ጋር እኩል መሳተፍ ያልቻሉ አባላትን በተመለከተ ግልፅ የሆነ መመሪያ አለመዘጋጀቱ፤
- የህብረት ስራ ማህበራት የመስሪያ ቦታ ስለሚያገኙበት ሁኔታ ግልፅ የሆነ መመሪያ ባለመኖሩ በአማራ 2፣ በኦሮሚያ 9፣በደቡብ 2፣ በአዲስአበባ 2 እና በቤንሻንጉል 1 ህብረት ስራ ማህበራት ለጠየቁት የቦታ ጥያቄ ከ1 ወር እስከ 6 ወር መልስ ሳያገኙ መቅረታቸው፣
- በኦሮሚያ ክልል የንጋት ኮከብ የእጅ ባለሙያ ህብረት ስራ ማህበር ቦታ በሊዝ እንዲገዛ መደረጉ እና 3 ማህበራት (የበዳዲናረቢ የማዕድን አምራቾች ህብረት ስራ ዩኒየን፣ መልካ አዋሽ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየንና የጊቤ ዴዴሳ የገበሬዎች ሁለገብ ህብረት ስራዩኒየን) ለመስሪያ ቦታና ለመጋዘን ኪራይብር 232,100 በማውጣት ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸው፤

- በአጠቃላይ በአማራ ክልል ፤ እንዲሁም በኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል፣ በአዲስአበባና በደቡብ ክልሎች አንዳንድ ህብረት ስራ ማህበራት ላለባቸው የቦታ ችግር መፍትሔ ማግኘት አለመቻላቸው፤
- የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ህብረት ስራ ማህበራት ስለሚያወጡት ፈቃድ እና የሚከፍሉትን ቀረጥ በተመለከተ የአፈፃፀም መመሪያ አለማዘጋጀቱ፤
- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከ2000-2002 ዓ.ም እና ከ2003-2007 ዓ.ም ባዘጋጃቸው ስትራቴጂክ ዕቅዶች በኅብረት ሥራ ማህበራት የሴቶችንና ወጣቶችን ተሳትፎ/ቁጥር/ እንደሚጨምር ቢገለጽም፤ ባዘጋጃቸው መመሪያዎች ውስጥ የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎና አመራር ሰጭነት በሚያበረታታ መልኩ አለማስቀመጡ፤
- በዚህ ምክንያት በአገሪቱ እስከ መጋቢት 2003 ዓ.ም በህብረት ሥራ ከተደራጁ 6,781,223 አባላት ውስጥ የሴቶች ብዛት 1,322,299 (19.49%) ብቻ መሆኑ፤
- የፌዴራል ኅብረት ሥራኤጀንሲ በመላ አገሪቱ ለሚገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት አንድ ወጥ የሆነ የሂሣብ ምርመራ /ኦዲት/ ማድረጊያ ጊዜ አለመዘርጋቱ፤
- ከ2001-2003 ዓ.ም በኤጀንሲው አማካኝነት ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎችና በሀረሪ ክልል ኦዲት ከተደረጉ 32 ኀብረት ሥራ ማህበራት መካከል የ5 ኀብረት ሥራ ማህበራት የ4 ዓመት ሂሣብ የ6 ኀብረትስራ ማህበራት ደግሞ የ3 ዓመት ሂሣብ በአንድ ጊዜ ኦዲት የተደረገ መሆኑ፤
- በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና በሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት (በአማራ፣ በአዲስአበባ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ) ከተደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በአጠቃላይ በአማካይ በ2001ዓ.ም 25,155 (80.8%)፣ በ2002 ዓ.ም 26,837(77.7%)፣ በ2003 ዓ.ም 31,267(84.2%) ኀብረት ሥራ ማህበራት ኦዲት አለመደረጋቸው፤
- የፌዴራል ኀብረት ሥራ ኤጀንሲ በራሱ ባለሙያዎች የሰራውን የኦዲት ሪፖርት ለሕብረት ስራ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ አለማስፀደቁ፣ በኦዲት ሪፖርት የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነትንም አለመከታተሉ፣

- በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት 4 የክልል ኅብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት 3ቱ /75%/ለኅብረት ሥራ ማኅበራት የሂሣብ ምርመራ ውጤታቸውን መሠረት በማድረግ ያሉበትን ደረጃ የሚያሣይ ሠርተፊኬት አለመሰጠቱ፤
- በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና በክልል ሕብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት (በአማራ፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል እና በደቡብ) የተደራጁ ህብረት ስራ ማህበራት በአጠቃላይ በ2001 ዓ.ም 22,225 (71.4%)፣በ2002 ዓ.ም 20,734(60%)፣ በ2003 ዓ.ም 26,912 (72.5%) በአደረጃጀታቸው፣ በስራ አመራራቸው፣ በስራ አፈፃፀማቸው ወዘተ የኢንስፔክሽን አገልግሎት አለማግኘታቸው፤
- እንዲሁም በወረዳና በዞን ደረጃ የሚገኙ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ኢንስፔክት ላደረጓቸው የህብረት ስራ ማህበራት የኢንስፔክሽን ግብረ መልስ የማይልኩ መሆኑ፤
- የፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲና የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት ስለሕብረት ስራ ጠቀሜታ፣ እንቅስቃሴ እና እድገት ለተደራጅዎችና ለባለድርሻ አካላት በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ባለመፍጠራቸው በኦዲቱ ወቅት በአካል ከታዩት 30 ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ በፌዴራል፣ በኦሮሚያ፣ በአዲስአበባና በቤኒሻንጉል 10 ህብረት ስራማህበራት፤ እንዲሁም በሶማሌ እና በአፋር የተደራጁ ህብረት ስራማህበራት ቀድመው ስለህብረት ስራማህበር ምንነት እና ጠቀሜታ በቂ ግንዛቤ ያልነበራቸው መሆኑ፤
- የፌዴራል ህብረት ስራኤጀንሲ የኅብረት ሥራማኅበራት ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሙያዊ ድጋፍ የመስጠት፣ በሀገር ውስጥ ሸማችና አምራች በቀጥታ የሚገናኙበትን ሁኔታ የማመቻቸ ትስልጣን በአዋጅ የተሰጠው ቢሆንም፤ከህዳር 1/2001 ዓ.ም ጀምሮ ማንኛውንም ግብይትን የተመለከተ አገልግሎት ለኅብረትሥራማህበራት መስጠት ማቋረጡ፤
- በአካል ከታዩና የሰርቬይ መጠይቅ ተልኮላቸው ከመለሱት 37 ህብረት ስራማህበራት ውስጥ በኦሮሚያ፣በአማራ፣ በደቡብ፣ በቤኒሻንጉልና በፌዴራል 13ቱ (35%) ከ2001-2003 ዓ.ም የምርትና የገበያ የልምድ ልውውጥ አግኝተው የማያውቁ ሲሆን፤ 19ኙ (51.3%) ህብረት ስራማህበራት ደግሞ በፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እና በክልሎች በሚዘጋጀው የህብረት ስራ ቀን

በዓል ላይ እስከ 2003 ዓ.ም አንድ ጊዜ የተሳተፉ ቢሆንም ምርታቸውን ከማስተዋወቅ ውጭ የምርትና የገበያ የልምድ ልውውጥ አለማድረጋቸው፤

- ኤጀንሲው እና በየደረጃው የሚገኙ የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት በጋራ በመሆን የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት/ዋጋ/ እንዲኖራቸው እና በሚፈለገው ቁጥር ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት እንዲለወጡ አለማድረጋቸው፤
- በኦዲቱ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተደራጁት 6,781,223 አባላትን የያዙና 3,884,299,411 ካፒታል ያሏቸው 38,699 መሰረታዊና ዩኒየን የህብረት ስራማህበራት ውስጥ እስከ 2003 ዓ.ም መጨረሻ ወደ አግሮ ኢንዱስትሪነት የተቀየሩ 29 (ከ1% ያነሱ) ህብረት ስራማህበራት ብቻ መሆናቸው፤
- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ 2002 ዓ.ም መጨረሻ ከተደራጁት ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ 70 በመቶ ያህሉን የብድር ተጠቃሚ ለማድረግ እቅድ ቢይዝም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት መካከል 17 ህብረት ስራማህበራት የብድር አገልግሎት ለማግኘት የክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላትን ድጋፍ ቢጠይቁም 8ቱ(47በመቶ) ከ2001-2003 ዓ.ም የብድር ተጠቃሚ አለመሆናቸው፤
- የፌዴራል ሕብረት ስራ ኤጀንሲ አገር አቀፍ የህብረት ስራ መረጃ ስብሰባ፣ትንተና እና ስርጭት የአሰራር ስርዓት ሲያዘጋጅ ከፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ወደ ክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች/ ቢሮዎች/ጽ/ቤቶች፣ ከክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ ወደዞን፣ ከዞን ወደ ወረዳ፣ ከወረዳ ወደ ህብረት ስራ ማህበራት መረጃ የሚደርስበትን ቀን ባዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ ባለማስቀመጡ በፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የተዘጋጁ ሪፖርቶች፣ ጥናቶች፣ ህትመቶችና መመሪያዎች ወደ ክልሎች ሲላኩ እስከ 3 ወር የሚዘገዩ መሆኑ፤
- እንዲሁም ከክልል ህብረት ስራ ማስፋፊያ አካላት መረጃዎች በየሩብ ዓመቱ የመጨረሻ ቀን ለኤጀንሲውና ለባለድርሻ አካላት መሰራጨት እንዳለባቸው በጊዜ ሰሌዳው የተጠቀሰ ቢሆንም፤ የዕቅድና ክንውን ሪፖርቶች ለፌዴራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ እስከ 34 ቀናት ዘግይተው የሚላኩ መሆኑ፤

- የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ ከህብረት ስራማስፋፊያ አካላት ጋር በድጋፍ አሰጣጥ ዙሪያ የመግባቢያ ሰነድ (MoU) የሌለው መሆኑ፤
  በመሆኑም የፌደራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ በፌደራል እና በክልል ደረጃ ለሚገኙ የህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጠውን ድጋፍ ቀልጣፋና ውጥታማ ለማድረግ እንዲችል በኦዲቱ ውቅት በታዩ ጉድለቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ አሳስበናል፡፡

10.11 <u>የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድን ሥራ አፈጻጸም በተመለከተ</u>

- ባለአደራ ቦርዱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን ውስጥ ያሉ ስራዎች (ከልዩ ፈንዱ የሚፈፀም ማንኛውም ክፍያ) በስራ አመራር ቦርዱ የሚያፀድቅ ሲሆን ከዚህ ውጭ ያሉ ስራዎች እንደ ጨረታ መነሻ ዋጋ መወሰን፣ የጨረታ ኮሚቴው በሚያቀርባቸው አማራጮች መሰረት ሽያጮች በሙሉ የማፅደቅ ስራዎች በማን እንደሚፀድቁ እና በምን መልኩ እንደሚከናወኑ፤ በዋና ዳይሬክተርና በስራ አመራር ቦርድ በመለየት ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያልተዘጋጀ እና ሁሉም ሥራዎች ለውሳኔ ወደ ስራ አመራር ቦርድ የሚሄዱ መሆናቸው፤

- ወደ ባለአደራ ቦርዱ የተላለፉ ቋሚ ንብረቶች ሥራ አመራር ቦርድ ሳይፈቅድና ዋጋቸው ሳይከለስ ከ1997 እስከ 2004 ዓ.ም እየተከራዩ መገኘታቸው፣

- በናሙና ከታዩት 13 የተለያዩ መጋዘኖች፣ ሱቆችና ቢሮዎች ውስጥ 12ቱ (92%) በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሰረት ዋጋቸው ያልተከለሰ መሆኑ፤

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ውስጥ ድሬደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ንብረቱን ሳይረከቡ ብር 4,394.32፣ ደብረብርሃን ብርድ ልብስ ፋብሪካ ብር 223,129.98 እና አዲስ ጎማ ፋብሪካ ብር 1,327,635.24 የሚያወጡ ንብረቶች ለፋብሪካዎቹ ከመመሪያው ውጭ ያለጨረታ በመዝገብ ዋጋ መሸጣቸው፤

- እንዲሁም የቡና ግዥና ሽያጪ ድርጅት ንብረት የሆነ አንድ ሞተር ሳይክል ቀደም ሲል በጨረታ የተሸጡ ሞተር ሳይክሎችን እንደመነሻ ዋጋ በመውሰድ ያለጨረታ የተሸጠ መሆኑ፤

- በኦዲቱ ወቅት ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እና ባለአደራ ቦርድ በቅንጅት የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ ባለአደራ ቦርዱ ያልተዘጋ ሂሳብ የሚረከብ መሆኑ (አደይ አበባ ድርና ማግ ፋብሪካ የ8 ዓመት ሂሳብ ሳይዘጋ)፣ ሰነዶች የሚጠፉ መሆኑ (በርክክብ ላይ የሚገኘው የቀድሞው ውሃ ጉድጓድ ስራዎች ድርጅት የጥቃቅን ወጪዎች መክፈያ ቫውቸር በቁጥር 30፣ የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቫውቸር በቁጥር 13 እና የቼክ መክፈያ ቫውቸር በቁጥር 12 ባጠቃላይ 55 ቅጠሎች በርክክብ ወቅት አለመገኘታቸው) እና በርክክቡ ወቅት ያልተገኙ ሰነዶችን በተመለከተ ተጠያቂ የተደረገ አካል አለመኖሩ፤

- ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ለባለአደራ ቦርድ ንብረቶችን እንዲረከቡ ካሳወቃቸው ድርጅቶች በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ አዲስ ጎማ ፋብሪካ፣ ደብረብርሃን ብርድልብስ ፋብሪካ እና የአዲስ የመለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበር የእያንዳንዱ ንብረት ዓይነትና የዋጋ ዝርዝር አለመላኩ እና በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጅ በ(restructuring) ጥናቱ መሰረት ከካፒታል ውጭ የሆነ ብር 57,053,479 የሚያወጣ ንብረት በጥቅል ወደ ባለአደራ ቦርድ እንዲተላለፍ መደረጉ፤

- እንዲሁም ድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ 18 ሺህ ላይን አይተም እና ከብር 24 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ንብረት ያለርክክብ ሠነድ ለቦርዱ መተላለፉ፤

- ባለአደራ ቦርድ የተረከባቸውን ንብረቶች መቆጣጠሪያ መዛግብት የመያዝ፣ ንብረቶችን የመረከብና ወጪ የማድረግ ሥራን አንድ ሰው እየሰራ የሚገኝ መሆኑ፣

- የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአክሲዮን ማህበርነት ሲደራጁ ከተፈቀደላቸው ካፒታል ውጪ የሆኑ ንብረቶችን እንዲያስወግዱለት ከአክሲዮን ማህበራቱ ጋር የውክልና ሽያጪ ውል የተፈራረመ ቢሆንም ከ1997 ዓ.ም እስከ 2003 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ስለሽያጩ እና ንብረቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ክትትል ያላደረገ መሆኑ፤

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ባለአደራ ቦርዱ ከተረከባቸው የተለያዩ ንብረቶች ውስጥ በአዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አክሲዮን ማህበር እና የቀድሞው የኢትዮጵያ ችርቻሮ ንግድ ኮርፖሬሽን የድርጅቶቹ ንብረቶች እና ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸው ንብረቶች በአንድ መጋዘን ውስጥ ንብረቶቹን በከፊል በቦታ በመለየት ጥበቃው በሌላ አካል ስር ሆኖ ከላይ ክፍት በሆነ ቦታ መቀመጣቸው፤

- እንዲሁም ባለአደራ ቦርዱ ንብረቶቹን ከተረከበ ጊዜ ጀምሮ ንብረቶች ለመኖራቸው (Existance) የማረጋገጥ ስራ ተሰርቶ የማያውቅ መሆኑ፤

- በኦዲት ከታዩት ድርጅቶች ውስጥ አቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ብር 35,145,548.17 የመነሻ ዋጋ ሲሰላ፤ባለው እዳ እና ወደፊት ስራዎችን ለማከናወን ሊወጡ የሚችሉ ወጪዎችን ታሳቢ በማድረግ የተሰጠ እንጂ የድርጅቱ ንብረት በባለሞያ ተጠንቶ የጨረታ መነሻ ዋጋ ያልተሰጠ መሆኑ፤ ጨረታ ሲወጣም የነዳጅ ማደያና ዲፖ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ እና ዋጋ ያልተሰጠበት መሆኑ፤

- የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት ለጨረታ የቀረቡ 13 የቡና ማበጠሪያዎች፣ ጽ/ቤቶች እና መጋዘን የዋጋ ግመታ በባለሞያ አለመታየቱ፣

- ጽ/ቤቶችና የቡና ማበጠሪያዎች በውስጣቸው የያዙት የማበጠሪያ ማሽን፤ የቋሚ ንብረት ብዛት እና አይነት ሳይገለፅ የመነሻ ዋጋ የተሰጣቸው መሆኑ፣

- የዲላ ጽ/ቤት ኤ(A) ሽያጭ ተፈፅሞ ለገዥው ርክክብ ሲደረግ ወደገዥው መተላለፍ ከነበረበት ንብረት ውስጥ 52 አይነት ቋሚ ንብረት ያልተላለፈ መሆኑ፤

- እንዲሁም የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት የጌምቤ ጽ/ቤትና መጋዘን በብር 555,000 ጨረታውን ካሸነፉ በኋላ ዋጋ የተሰጠው በስህተት ነው በማለት አሸናፊው ለዋስትና ባስያዘው ብር 55,000 ከመነሻ ዋጋ አንሶ የተሸጠ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

- የባለአደራ ቦርዱ መቋቋሚያ አዋጅ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሰረታዊ ዓላማ በመከተል የባለአደራ ቦርድ ሰራተኞች የሚተዳደሩበት መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል ቢልም መመሪያውን ያላዘጋጀ መሆኑ ነገር ግን በሐምሌ 1/2003 ዓ.ም የሊኩዴሽን ቨርቹዋል ቲም ስራና የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር የፀደቀ መሆኑ፣

- በዚህም መመሪያ የተካተተው የሊኩዴሽን ቡድን የአበል ክፍያ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስን መሰረታዊ አላማ ያልተከተለና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ ለሊኩዴሽን ቡድን አስተባባሪ የነዳጅ ፍጆታ መጠን ያልተቀመጠ መሆኑ፤

- የሊኩዴሽን ወጪዎችን በተመለከተ የስራ አመራር ቦርድ እንደማያየውና እንደማያፀድቀው፣ ለሊኩዴሽን ስራ ማስኬጃ እንዲወጣ በሊኩዴሽንና የድርጅቶች ንብረት አስተዳደር መምሪያ ሥራ አስኪያጅ መፈቀዱ፣ በተፈቀደው መሰረት ለጥቃቅን ወጪ በየወሩ እንዳለቀ የሚተካ ለቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት ብር 3,000 እና ለአቃቂ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር ብር 2,500 እየተከፈለ እና ከ2001-2003 በጀት ዓመት ለጥቃቅን ወጪዎች ተብሎ በድምሩ ብር 172,037.56 ወጪ መደረጉ፣ ክፍያውም በዋናነት ለመስተንግዶ፣ ለነዳጅና ለመሳሰሉት የሚውል መሆኑ፤

- ባለአደራ ቦርዱ ከአቃቂ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር ከተረከበው ነዳጅ እንዲጠቀም በስራ አመራር ቦርድ ሳይፈቀድ ተጠቅሞ መገኘቱ፣ በርክክብ ወቅት 7,410 ሊትር ቤንዚን እና 5,725 ሊትር ናፍጣ በህዳር 2001 ዓ.ም የተረከቡ ቢሆንም በካርድ ባላንስ መሰረት "oct 17/2011" 192 (2.59%) ሊትር ቤንዚን እና "May /2011" 1257 (22%) ሊትር ናፍጣ የቀረ እና 7,218 ሊትር ቤንዚን ና 4,468 ሊትር ናፍጣ የተጠቀሙበት መሆኑ፤

- ባለአደራ ቦርዱ ውስጥ ይዞታቸው የተቀየሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ስራ ተረክቦ ለማከናወን በየበጀት ዓመቱ ዕቅድ የሚያዘጋጅ ቢሆንም ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ክንውኑ ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡

- በናሙና ከታዩት በባለአደራ ቦርድ ሂሳብ ማጣራት ስራ ከተከናወነባቸው ድርጅቶች ውስጥ የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት እና የአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ

አክሲዮን ማህበር ስራውን ለመስራት በቅድሚያ የተዘጋጀ ዕቅድ እና የድርጊት መርሃ ግብር አለመኖሩ፤

- የቡና ግዥና ሽያጭ ድርጅት ከፈረሰ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም ለ10 ዓመታት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን እንዲሁም ከ 2001 እስከ ህዳር 2004 ዓ.ም ለአራት ዓመታት የሂሳብ ማጣራት ስራ በባለአደራ ቦርድ እየተሰራ ቢሆንም ስራው ያልተጠናቀቀ መሆኑ፤
- በናሙና ከታዩት የሂሳብ ማጣራት ስራዎች የቡና ግዥና ሽያጪ ድርጅትና የአቃቂ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት የሚዘጋጅ ቢሆንም፤ ሂሳቡ በውስጥም ሆነ በውጪ ኦዲተር ተመርምሮ የማያውቅ መሆኑ፤

  በመሆኑም የባለአደራ ቦረዱ በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

10.12 <u>በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የእርዳታ ቁሳቁሶች አጠባበቅ</u>

- የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚገለገልባቸው የምድር ሚዛኖች በትክክል ስለመሰራታቸው በመንግስት ኃላፊነት በተሰጠው አካል የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ሊኖራቸው እና የምድር ሚዛኖቹም በትክክል ስለመሰራታቸው በሚዛን ኦፕሬተሮች ቁጥጥር ሊደረግባቸው ሲገባ፤
  - በሻሸመኔ ቅርንጫፍ የሚገኘው ማኑዋል የምድር ሚዛን ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት ማቋረጡ ዲጂታል ሚዛኑም አልፎ አልፎ ችግር የሚያጋጥመውና የተወሰነ ደረጃ ከመዘነ በኋላ የማተም (print) ችግር ያለበት መሆኑ፣
  - በአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የሚኘው የምድር ሚዛን በሌላ ግቢ የሚገኝ መሆኑ፣

- የሁለቱም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የምድር ሚዛኖቹ ባለቤትነታቸው የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በመሆናቸው በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ባለሙያዎች ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግባቸው መሆኑ፣

- አስተዳደሩ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች እህል እየተመዘነ ገቢና ወጪ መደረግ ሲኖርበት በወላይታ ሶዶ፣ በሸነሌና በወረታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እህል ወደ መጋዘን ገቢና ወጪ ሲደረግ በምድር ሚዛን የማይመዘን መሆኑ፣

- የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር በስሩ የሚገኙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መጋዘኖች በክምችት የሚይዟቸውን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በተገቢው መንገድ ለመጠበቅ እንዲቻል ጥገና ለሚያስፈልገው መጋዘኖች በወቅቱ ጥገና ሊደረግላቸው ሲገባ፤ በወላይታ ሶዶና የመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የመጋዘን ጥገና ባለሙያዎች ባለመኖራቸው በዝናብ ወቅት የሚያፈሱ መጋዘኖች ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ወቅታዊ ጥገና ለማድረግ አለመቻሉ፣

- በአስተዳደሩ ስር የሚገኙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የእህል ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቴክኒሻኖች በስራቸው በሚገኙ መጋዘኖች ላይ አስተዳደሩ ባወጣው መመሪያ መሠረት በወር አንድ ጊዜ ፍተሻ የማያከናውኑ መሆኑ እና የጥራት ፍተሻውም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ በተለያየ የጊዜ ርቀት የሚደረግ መሆኑ፤

- የአስተዳደሩ ማዕከላዊ ላብራቶሪ አገልግሎት እና የምግብ ጥራትና ተባይ ቁጥጥር ቡድን ባለሙያዎች በቅንጅት በየሩብ ዓመቱ በሁሉም የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መጋዘኖች የሚካሄደው የእህል ክምችት ደህንነት የጥራት ፍተሻ ስራው በአግባቡ ስለመካሄዱ ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ ክትትል አለማድረጋቸው፣

- በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች የሚገኘው የእህል ክምችት መጠን ኦዲት የተደረገው እና ያልተደረገው ተለይቶ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ ላይ ተሞልቶ በየሦስት ወሩ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣

- አስተዳደሩ በስሩ የሚገኙ የእህል ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች እንዳይኖሩ እና መጋዘኖቹም በንጽህና እንዲጠበቁ ማድረግ ሲገባ፤ እህል መጋዘኖች ውስጥ ሌሎች ቁሳቁሶች የሚቀመጡ መሆኑ፣

- በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚገኙ መጋዘኖች የሚሰሩ የመጋዘን ሃላፊዎችና ሠራተኞች ሥራቸውን የሚያካሂዱበት ከመጋዘኑ የተለየ ቢሮ የሌላቸው በመሆኑ ሥራቸውን የሚያከናውኑት በመጋዘኖቹ ውስጥ መሆኑ፣
- አስተዳደሩ በስሩ በሚገኙ የእህል እና እህል ነክ ያልሆኑ መጋዘኖች በር ላይ በያንዳንዱ መጋዘን ቢያንስ ሁለት የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪዎች ሊኖሩና መሣሪያዎቹም በትክክል ስለመስራታቸው ወቅታዊ ክትትል ሊደረግ፤እና መሣሪያዎቹንም በትክክል መጠቀም የሚችሉ ባለሙያዎች ሊሟሉ ሲገባ፤ መጋዘኖቹ በቂ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች ያልተሟላላቸው እና ወቅታዊ ጥገናና ፍተሻም የማይደረግላቸው መሆኑ፣
- አስተዳደሩ አስቸኳይ የምግብ እጥረትን ለመቋቋም ይቻል ዘንድ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ቦርድ በሚያዘው መሠረት ለተለያዩ ድርጅቶች ከክምችቱ በብድር እህል ሊሰጥና የተሰጠውንም ብድር በወቅቱ እንዲመለስ ማድረግ ሲጠበቅበት፤ አስተዳደሩ ከክምችቱ ለተለያዩ ድርጅቶች በብድር የሚሰጠው እህል አልፎ አልፎ በወቅቱ የማይመለስ መሆኑ፣
- የመጠባበቂያ የምግብ ክምችት አስተዳደር የውስጥ አሠራሩን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችለው በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተጠናከረና የተደራጀ የመረጃ ስርዓት አለመኖሩ፤
- አስተዳደሩ ለስራው አስፈላጊ ሆነው በግዥና በእርዳታ ያገኛቸውን የእህል ሚዛኖች በአግባቡ ስራ ላይ ሊያውል፣ ሲበላሹም በወቅቱ ሊያስጠግን እና መጠገን ካልቻሉም የሚወገዱበትን መንገድ ማመቻቸት ሲኖርበት፤ አስተዳደሩ በእርዳታ ያገኛቸው አገልግሎት የማይሰጡ ተንቀሳቃሽ የእህል ሚዛኖች በወቅቱ እንዲጠገኑ ወይም መወገድ የሚገባቸውን እንዲወገዱ አለማድረጉ፣

- በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የሚገኙት የአስተዳደሩ የእህል እና እህል ነክ ያልሆኑ መጋዘኖች በአደጋ ጊዜ እርዳታን ለመጠየቅ የሚያስችሉ የስልክ ቁጥሮች ግልፅ በሆነና በቀላሉ ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ አለመቀመጡ፣
- በአስተዳደሩ ስር በሚገኙ የእህል መጋዘኖች የእህል ህክምና ከተደረገ በኋላ የሚቀሩ የተለያዩ መድኃኒት የመጣባቸው ቆርቆሮዎችና አመድ በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ በተገቢው ሁኔታ እንዲቀበሩና እንዲወገዱ አለመደረጉ፣
- በአስተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች ለእህል ጤንነት መጠበቂያ የሚጠቀሙባቸው መድኃኒቶች ተገቢውን ደረጃ የጠበቁና የመጠቀሚያ ጊዜያቸውም ያላለፈባቸው ሊሆኑ ሲገባ፤ በሸነሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት መድኃኒት የሚጠቀም መሆኑ፣
- አስተዳደሩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሰቁሶች ለሚፈለጉበት ተግባር በብድርና በትውስት ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ክምችቱን በአግባቡ እንዲጠበቅና ለጉዳት እንዳይጋለጥ መጠበቅ ሲኖርበት በአስተዳደሩ የአዳማ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች መጋዘን ውስጥ ለረዥም ጊዜ ያለአገልግሎት የተከማቹ እና ለጉዳት የተጋለጡ ቁሰቁሶችና መኖራቸው፣
- አስተዳደሩ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስር በሚገኙ መጋዘኖች መብራት ሲቋረጥ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ጄኔረተሮች የሌሉት መሆኑ፣

በመሆኑም የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር በህግ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነቶች በብቃትና በቅልጥፍና ለመወጣት እንዲችል በኦዲቱ ወቅት በታዩ የአሰራር ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እረምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል፡፡

10.13 በትምህርት ሚኒስቴር በቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የውጤት ተኮር ስልጠና እና የቴክኖሎጂ ሽግግርና ክምችት ስርአት ውጤታማነት

- በናሙና ተመርጠው በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳደር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስልጠና ፍላጎት ጥናት በማድረግ ለየክልላቸው የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮዎች በየአመቱ ሪፖርት የማያደርጉ መሆኑ፣
- በትምህርት ሚኒስቴር በቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ፣ በክልል ቢሮዎች፤ እንዲሁም በማሰልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች የሥራ ገበያ ፍላጐት ጥናት በማጥናት ስልጠናውን በጥናቱ መሠረት ማካሄድ ሲኖርበት የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት በፌዴራል ደረጃ በአገር አቀፍ ጥናት ሲካሄድ በክልል ደረጃ ደግሞ ክልል አቀፍ ጥናት የሚካሄድ መሆኑ፤
- በአማራ እና ኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ የቴክኒክና ሙ.ያ ተቋማት የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት ቢያካሄዱም፤ በጥናቱ መሠረት ሥልጠና የማይሰጡ መሆኑ እና በአዲስ አበባ መስተደደር ሥር የሚገኙ የቴክኒክና ሙ.ያ ተቋማት ደግሞ የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት አለማካሄዳቸው፣
- የክልል ቴክኒክና ሙ.ያ ቢሮዎች የአገር አቀፍ ሙ.ያ ደረጃን የሚያሟላ ስልጠና ለመስጠት በየተቋማቱ የተሟላ የስልጠና መስጫ መሳሪያዎች መኖሩን ማረጋገጥ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም፤ በናሙና ተመርጠው በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሙ.ያ ደረጃው በሚያዘው መሠረት በቂ የስልጠና መሣሪያዎች አለመሟላታቸው፣
- የክልል የቴክኒክና ሙ.ያ ቢሮዎች በስራቸው ለሚገኙ ተቋማት የስራ ትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርዓት በመዘርጋት ተቋማት እርስ በርሳቸው በቅንጅት የሚሰሩበት የስምምነት ሰነድ እንዲኖራቸው ማድረግና መከታተል ሲጠበቅበት፤ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስራ ትብብር እና ግንኙነት (clustering) ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም፤ የስራ አፈፃፀሙ ያልተጠናከረና

ተቋሚቱ እርስ በርሳቸው በቅንጅት የሚሰሩበት የስምምነት ሰነድ የሌላቸው መሆኑ፣

- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍና የክልል ቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች የልህቀት ማእከል center of competency (coc) ውጤትን መሰረት በማድረግ የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጃ መገምገም ሲጠበቅበት በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የአዲስ አበባ መስተዳድር እና ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ የልህቀትን ማዕከል (coc) ውጤትን መሰረት በማድረግ የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጃ አለመገምገሙ፤
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጠነው የተመረቁ ሰልጣኞች ከስልጠና በኋላ የትና በምን ሥራ ላይ እንዳሉ አብዛኛዎቹ የማሰልጠኛ ተቋማት የድህረ ገበያ ጥናት የማያከናውኑ መሆኑ፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጣኞች ከስልጠና ጊዜያቸው 70% በተግባር ልምምድ 30% ደግሞ በንድፈ ሃሣብ ስልጠና መዋሉ ክትትል ሊደረግበት ሲገባ በአማራ፣ በኦሮሚያና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጣኞች የተግባር ልምምድ ማድረጊያ ኢንዱስትሪዎች እጥረትና የግንዛቤ ችግር በመኖሩ ስራው በተሟላ መልኩ አለመተግበሩ፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና የቴክኒክ እና ሙያ ቢሮዎች በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በተጠናከረ መልኩ አለመደገፉ፣
- በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎት በመለየት እና በመምረጥ ቴክኖሎጂዎች እንዲሸጋገሩ ለማድረግ መረጃውን ወደ ተቋማትና ኮሌጆች በመላክ አፈጻጸሙን ሊከታተልና ድጋፍ ሊያደርግ ሲገባ የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየት፣ የመምረጥ፣ እና ቴክኖሎጂዎች እንዲሸጋገሩ መረጃውን ወደ ተቋማትና ኮሌጆች የመላኩ ስራ ከፌዴራል እስከ ተቋማት ድረስ በመቀናጀት በተጠናከረ መልኩ አለመሰራቱ እና በፌዴራል እና በክልል የቴክኒክ እና ሙያ ባለሙያዎች በሁሉም ተቋማት በቂ ክትትልና ድጋፍ አለመደረጉ፣

- በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና የክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮዎች ለማሰልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር አሰራር ላይ ከጫፍ እስከ ጫፍ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመስራት፣ እና ስራውን በባለቤትነት እንዲሰሩ ለሁሉም ተቋማት እና ኮሌጆች በዘርፉ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ አለመሰጠቱ፣
- በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የማሰልጠኛ ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት እያገለገሉ አለመሆኑና በክልሎች የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች የሚደረገው ክትትል እና ድጋፍም አናሳ መሆኑ፣
- በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ የሚሰሩ ስራዎች ላይ የአካባቢውን የትኩረት ኢንደስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና እየሰሩ አለመሆኑ፣
- በናሙና ተመርጠው ከታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ለቴክኖሎጅ ክምችትና ሽግግር የሚያገለግሉ መረጃዎችን በአግባቡ የሚይዙበት እና ስራ ላይ የሚያውሉበት የመረጃ አያያዝ ስርአት ያልዘረጉና ስራ ላይ ያልዋሉ መሆኑ፣
- በናሙና ተመርጠው ከታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ የማሰልጠኛ ተቋማት እና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ማምረት ሂደት ወቅት የወጡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች ውጤታማና ኢኮኖሚያዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መዝግበውና ተንትነው አለመያዛቸው፣
- በናሙና ተመርጠው ከታዩት የአማራ፣ የኦሮሚያና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ የሚሰሩዋቸውን ስራዎች ከአሰልጣኞች፣ ከሰልጣኞችና ከአካባቢው ኢንደስትሪ ጋር በጋራ ለመስራት ቅንጅታዊ አሰራር የሌላቸው መሆኑ፣
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራ የሚረዱ ማንዋሎችና መመሪያዎች በናሙና ተመርጠው ከታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር ለሚገኙ ተቋማትና ኮሌጆች

እንዲደርሳቸው የተደረገ ቢሆንም፤ መመሪያዎቹ በትክክል ስለመፈጸማቸው በፌደራልም ሆነ በክልል የቴክኒክና ሙያ ቢሮ ኃላፊዎች የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ አናሳ መሆኑ፣

- በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት አብዛኞቹ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚሰሩ ስራዎች ከሀገሪቱ እና ከአካባቢው የልማት አቅጣጫ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንዲካሄድ የተጠናከረ የቴክኖሎጂ ፋይዳ የዳሰሳ ጥናት እያደረጉ አለመሆኑ፣

በመሆኑም በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የውጤት ተኮር ስልጠና እና የቴክኖሎጂ ሽግግርና ክምችት ስርአትን ውጤታማ ለማድረግ በኦዲቱ ወቅት በታዩት ድክመቶች ላይ አግባብ ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊው እርምጃ እንዲወስድ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

10.14 <u>በምግብ፣ በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን የመድኃኒት ጥራት ደህንነት ፤አጠቃቀም ቁጥጥርና አወጋገድ ስርዓትን በተመለከተ</u>

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊውን የጥራት መመርመሪያ መሣሪያዎችን እንዲሁም በመግቢያና መውጫ ኬላዎች ላይ የሚኒ እና የተንቀሳቃሽ (mobile) ላብራቶሪዎችን በማደራጀት በተሟላ ሁኔታ ስራ ላይ አለማዋሉ፤
- ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የላብራቶሪና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ማሟላት ያለባቸውን አጠቃላይ መረጃ (labelling requirement) ሳያሟሉ መግባታቸው፣
- የኬላ መልቀቂያ ደረሰኝ በህጋዊ ድርጅት የታተመ፡ ቅደም ተከተል ያለው ስለዕቃው ምንነት የሚገልፅ ባለ ሶስት ኮፒ ሊሆን ሲገባ፤በአንዳንድ ኬላዎችና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በህጋዊ ድርጅት የታተመ፣ቅደም ተከትል ያለውና ስለ እቃው ምንነት የሚገልፅ የመልቀቂያ ደረሰኝ በተሟላ ሁኔታ አለመኖሩ፣
- በኬላዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ መድሐኒቶች እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ላይ በሚካሄድ ኢንስፔክሽን እቃውን የፈተሸው ኢንስፔክተር

እቃውን ስለመልቀቁ የሚገልጽ በፎርማ የተረጋገጠ መረጃ ቀሪ ሊያዝና መረጃውም በየኬላዎች ባግባቡ ሊጠበቅ ሲገባ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የመድሐኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ማሟላት ያለባቸውን መረጃዎች ስለማሟላታቸው በኢንስፔክተሩ የተረጋገጠበት መረጃ በአግባቡ አለመያዙ፣

- በኢንስፔክሽን ውጤት መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ ደንብን በተላለፉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ተመጣጣኝ እና ወጥነት ያለው እርምጃ መውሰድ የሚያስችል ደንብ አለማውጣቱ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀትና የመግባቢያ ሰነድ በማዘጋጀት በቅርንጫፍ የምግብ፣መድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ቢሮዎች እና በኬላዎች ለሚገኙ ባለሙያዎች አስፈላጊውን ስልጠናና የማቴሪያል ድጋፍ አለመደረጉ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም አስመጭና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ያስመጣቸውን፤ ያከፋፈላቸውን፤ በክምችት የያዛቸውን እና ያሰወገዳቸውን መድሀኒቶችና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በአመቱ መጨረሻ ሪፖርት ማድረጉን በመከታተል መረጃውን በአግባቡ አጠናቅሮ አለመያዙ፤
- አብዛኞቹ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች አስመጭና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ስለአስመጧቸው፣ ስለ አከፋፈሏቸውና በክምችት ስለያዟቸው መድሐኒቶችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ለባለስልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት የማያደርጉ መሆኑ፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የመድኃኒት አጠቃቀም ቁጥጥር መመሪያ በማዘጋጀት በሥራ ላይ አለማዋሉ፣
- የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን የሚያስመጡና የሚያከፋፍሉ ድርጅቶች መድሐኒቶቹን ከብረት ካቤኔት ውጭ እንደማንኛውም መድሐኒት በመደርደሪያ ላይ የሚያስቀምጡ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የባህል መድኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ለማረጋገጥ የሚያስችል የመቆጣጠሪያ ስርዓት ሊዘረጋ፣ ምዝገባ በማካሄድ የምስክር ወረቀት ሊሰጥና ባህላዊ ሕክምና አገልግሎት ከዘመናዊው ህክምና

ጋር ተቀናጅቶ ሊሠራ የሚችልበትን ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ፤

- የባለስልጣን መ/ቤቱ ለመድሀኒት ምዝገባ አገልግሎት የሚውል ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ (guideline) የሌለው መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው አስመጭና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የሚፈልገው መድሀኒት ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ብሔራዊ የመድሀኒት መዘርዝር ውስጥ የተካተተ መሆኑን ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ያዘጋጀው የብሔራዊ የመድሐኒት መዘርዝር ቢኖርም፤ መረጃው ወቅታዊ ሲደረግ ለየኬላዎች በወቅቱ የማይደርሣቸው መሆኑ፣
- የባለስልጣን መ/ቤቱ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የመድሀኒት ፋብሪካዎችላይ የመልካም አመራረት ቁጥጥር በማከናወን ደረጃዎችን ያለፉ፣ በማስጠንቀቂያ የታለፉ እና ያላለፉ በማለት የመለየት ስራን በማከናወን በውጭ ሀገራት የመድሐኒት ፋብሪካዎች ላይ ይደረግ የነበረውን የመልካም አመራረት ቁጥጥር ከግንቦት 2010 በኋላ ያቋረጠ መሆኑ፣
- የባለስልጣን መ/ቤቱ የመድሀኒቶች የሰነድ ግምገማ በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት (BPR) ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ ማለትም ከ30 ቀናት በላይ ረጅም ጊዜ የሚወስድና ሰነዶችም በጥንቃቄ ስለማይያዙ የሚጠፉ መሆኑ፣
- የባለስልጣን መ/ቤቱ የላብራቶሪና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ መሳሪያውን ያመረተው ፋብሪካ ባስቀመጠው ውጤት ደረጃ መሰረት እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ፣
- አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ መድሐኒቶችን ጎጂ ባህርያት በተመለከተ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የመድሐኒት ጎጂ ባህሪያትን ለባለስልጣኑ ሪፖርት እንዲያደርግ፤ ባለስልጣኑም በሪፖርቱ መሠረት ጥናትና ክትትል በማድረግ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችለው የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም፤ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ባለመሠራቱ ሪፖርት የሚያደርገው ህብረተሰብ አነስተኛ መሆኑ፣

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ከመድኃኒት አምራቾች፣ ከመድሐኒት አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች እና ከመድኃኒት ጋር ተያያዥነት ካላቸው ማህበራት ጋር መደበኛ የሆነ የውይይት መድረክ የሌለው መሆኑ፤
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የመድህኒት ቁጥጥር አገልግሎት ያመጣው/ያስገኘውን ፋይዳ በተመለከተ ዳሰሳ ጥናት በየዓመቱ የማያከናውን መሆኑ፣
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሐኒቶችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች የሚወገዱበት መመሪያ የፀደቀ ቢሆንም፤ባለሥልጣኑ በሥራ ላይ አለማዋሉ፣
- በተለያዩ አካላት የሚወገዱ ጊዜያቸው ያለፈባቸው፣ በኮንትሮባንድ የተያዙና ለህዝብ ጥቅም መዋል የሌለባቸው መድሐኒቶች ከመወገዳቸው በፊት በያዙት ንጥረ ነገር(sorted by active ingredient) እና የመድሐኒቱ ይዘት(solid, semi-solid, and powders;liquids; and aerosol canisters) መለየታቸውን፤ እንዲሁም መድሐኒቶቹ ከሌሎች ቁሳቁሶች ተለይተው መቀመጣቸውን ባለስልጣኑ የማያረጋግጥ መሆኑ ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ መድሃኒቶችን ለማስወገድ ሃላፊነት የሚሰጣቸው ባለሙያዎች ቡድን በዓለም የጤና ድርጅት (WHO disposal guideline) ወይም በባለስልጣን መ/ቤቱ የአወጋገድ መመሪያ መሰረት ተገቢውን የባለሙያ ስብጥር የማያሟሉ መሆኑ፣
- ባለስልጣኑ ከተለያዩ አካላት ጋር በመተባበር የመድሐኒት አስወጋጅ አባላት መድሐኒቶችን በሚያስወግበት ወቅት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት መድሃኒቶችን ለማስወገድ በቡድኑ የተካተቱት አባላት ራሳቸውን ከአደጋ ለመከላከል (ለጥንቃቄ) የሚያስፈልጉ አልባሳት ማለትም (ቱታ፣ ቦት ጫማ፣ ጓንት እና ማስክ) እንዲሟላላቸው እና እንዲጠቀሙ የማይድረግ መሆኑ፤
- የባለስልጣን መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ መድኃኒቶችን ለማስወገድ የሚያስችል ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የተዘጋጀ ኢንሲነሬተርና የማስወገጃ ቦታ የሌለው መሆኑ፤

በመሆኑም በምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ ረገድ የሚደረገው ቁጥጥር በአገርውስጥ የሚመረቱትም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ምግብ መድሃኒቶች እና

የህክምና መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን የሚያሟሉ መሆናቸውን፣ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውም በተገቢው መንገድ የሚወገዱበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በኦዲቱ ወቅት በታዩት ድክመቶች ላይ አግባብ ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊው እርምጃ እንዲወስድ ለባለስልጣን መ/ቤቱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

10.15 <u>በብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት የብዝሀ ሕይወት ሀብት አጠባበቅ እና አጠቃቀም</u>

- ወቅታዊ የሆነ እና የሀገሪቱን የተፈጥሮ ደን ሽፋን እና በየጊዜው የሚታየውን ለውጥ የሚያሳይ ካርታ ባለመዘጋጀቱ፣ የሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን ስርጭት እና መጠን በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለመረዳት እና በብዝሐ ህይወት ሀብት ላይ እየደረሰ ያለውን ጥፋት መጠን ለመከታተል አለመቻሉ፣
- ሀገር በቀል የሆኑ በተለይም ዝርያቸው በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የብዝሀ ህይወት ሀብቶች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊጠበቁ እና ሊስፋፉ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲመቻች አለመደረጉ፣
- የነዚህ የነባር ዝርያዎች ልዩ ጠቀሜታን በተመለከተ በኅብረተሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆን እና በከፍተኛ ሁኔታ እየተመናመኑ እና እየቀነሱ፣ እንዲሁም የአካባቢው ባልሆኑ ሌሎች ዝርያዎች እየተተኩ መሆኑ፣
- ሀገሪቱን ሥርዓተ ምህዳሮች ወካይ በሆነ ደረጃ ሀገር በቀል የሆኑ የብዝሀ ሕይወት ዝርያዎችን ኅብረተሰቡን በሚያሳተፍ ሁኔታ በአሉበት የተፈጥሮ አካባቢ ለመጠበቅ ተገቢ ትኩረት አለመሰጠቱ፣ በሀገሪቱ ብዝሀ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሊፈጥር የሚችል እና በተለይም በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ ዝርያዎች እንዲጠፉ ሊያደርግ የሚችል መሆኑ፣
- በኢዘቦታ (exsitue) ወይም ከተፈጥሮ የአኗኗር ሁኔታ ውጪ በናሙና ተይዘው በማቀዝቀዣ ክፍል ውስጥ በመጠበቅ ላይ የሚገኙ ዕጽዋቶች ከአቅም በላይ በሆኑ ድንገተኛ አደጋዎች (እሳት አደጋ፣ ጎርፍ፣ ወዘተ) እንዳይጎዱና እንዳይጠፉ ለመጠበቅ እንዲቻል ተመሳሳይ ናሙናዎች በሌላ ቦታ (duplicate gene bank) በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲቃቋም አለመደረጉ፣

- በዘቦታ የብዝሀ ሕይወት ሀብትን የመጠበቁ ሁኔታ የጎላ ድክምት የሚታይበት ከመሆኑ አንፃር በኢንስቲትዩቱ ሥር በኢዘቦታ (ጅን ባንክ) የብዝሀ ህይወትን መጠበቂያ ስፍራ አንድ ብቻ መሆኑ፤ ባልተጠበቀ ሁኔታ አደጋ ቢደርስ ኪሳራው ሊካካስ የማይችል እና ከፍተኛ ጥፋት ሊያደርስ የሚችል መሆኑ፤
- የሀገሪቱን የብዝሃ ሕይወት ሀብት ለመጠበቅ እና ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ የመጠቀም ልምድ መዳበርን ለመከታተል የሚችል የብዝሀ ሕይወት ግብረ ኃይል (biodiversity task force) በፌደራልም ሆነ በክልሎች ደረጃ አለመቋቋሙ፤
- በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፀውን የብዝሀ ሕይወት ስትራቴጂክ ዕቅድ ለማስፈጸምና ለማስተባበር የመሪነት ሚና የሚጫወት አካል አለመኖር፤ እንዲሁም የብዝሀ ሕይወት ግብረ ኃይል (biodiversity task force) በፌዴራል እና በክልል ደረጃ አለመቋቋም ብዝሀ ሕይወትን በተመለከተ ሊከናወኑ የታቀዱ ሥራዎችን በአግባቡ ለማስተባበር እንዳይቻል እና ተገቢው የመረጃ ልውውጥ እንዳይኖር በማድረጉ የተቀናጀ አሠራርን በመዘርጋት በሀገሪቷ የብዝሀ ህይወት ሀብት ላይ እየደረሰ ያለውን ውድመት ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት ውጤት እንዳያመጣ እያደረገው የሚገኝ መሆኑ፤
- በፌዴራልም ሆነ በክልሎች የሚተገበሩ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ለብዝሀ ሕይወት ትኩረት የሰጠ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ በቅድሚያ ብቃት ባለው የባለሙያ ቡድን ተጠንቶ ሊቀርብ እና በሚመለከተው አካል አግባብነቱ ታይቶ እና ጸድቆ በአግባቡ ተግባራዊ ስለመሆኑ ክትትል ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም ለተፈጥሮ ሀብትና ለደኖች መጥፋት አስተዋፅኦ ያላቸው የልማት ፕሮጀክቶች መኖራቸውን እና የተጽዕኖ ግምገማ በአግባቡ ሳይደረግ፣ እየተተገበሩ እንደሚገኙ ለመገንዘብ መቻሉ፤
- የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የተካሄደባቸው የልማት ተግባራትም ቢሆኑ በአካባቢ ላይ በተለይም በሀገሪቱ የብዝሀ ሕይወት ሀብት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉት ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ እንዲቻል በቀረበው የተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ላይ የተቀመጡት የመከላከያ ስልቶች በአግባቡ መተግበራቸውን በተመለከተ ክትትልና ቁጥጥር የማይካሄድባቸው መሆኑ፤

- በፌዴራልም ሆነ በክልሎች ላይ የሚተገበሩ የልማት ፕሮጀክቶች በብዝሀ ሕይወት ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት በተመለከተ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ደረጃውን ጠብቆ በብቃት አለመከናወኑ፤
- የተጽዕኖ ግምገማ ለተደረገላቸውም ቢሆን በሰነዱ ላይ የተመለከቱ ሊከሰቱ የሚችሉት ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የተቀመጡት የመከላከያ ስልቶች በአግባቡ መተግበራቸውን በተመለከተ ክትትልና ቁጥጥር የማይካሄድ በመሆኑ፤በብዝሀ ሕይወትና በአካባቢው ተፈጥሮ ሀብት ላይ ሊካካስ የማይችል እና አሁን ያለውንም ሆነ ተተኪውን ትውልድ ተጎጂ የሚያደርጉ ሁኔታዎች እየደረሱ መሆኑ፤
- ቀደም ብለው ገብተው የሚገኙ ወይም አዲስ ከውጭ ሀገር የሚገቡ መጤ ወራሪ ዝርያዎች በብዝሀ ሕይወት ሀብት ላይ የሚያደርሱት ተጽዕኖ በጥናት ለማወቅ አጥጋቢ ጥረት አለመደረጉ፣ ችግሩን ሊያቃልል የሚችል የመፍትሔ እርምጃም አለመወሰዱ፤
- በተለይ ፓርቲኒየም (በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል) እና ፕሮሶፒስ (በምስራቁ የሀገሪቱ ክፍል) የተባሉት ወራሪ ዝርያዎች በከፍተኛ ፍጥነት በመስፋት የግጦሽ እና እርሻ መሬቶችን በመውረር በግጦሽ መሬቶች ላይ ያለውን የብዝሀ ሕይወት እስከ 90 በመቶ እንዲጠፋ፣ የእርሻ መሬቶችም ምርታማነት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ እያደረጉ መሆኑ፤
- የውጭ ሀገር ተመራማሪዎች ወይም ተቋማት የዘረመል ሀብት አርከቦት ጥያቄ አቅርበው ሲፈቀድላቸው ወደ ሥራ በሚገቡበት ወቅት ህጋዊነትን ያልተከተለ ተግባር እንዳይፈጽሙ ለመከላከል የሚያግዝ የአሠራር ሥርዓት ሊኖር እና ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም፤የውጭ ተመራማሪዎች ፈቃድ አግኝተው በብዝሀ ሕይወት ሀብት ዙሪያ ጥናት በሚያደርጉበት እና መረጃ በሚሰበስቡበት ወቅት ከማስተባበር ውጪ ኢትዮጵያዊያን ባለሞያዎችን አብሮ በመሳተፍ የቅርብ ክትትል የማድረግ ተግባር ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው በመሆኑ የጄኔቲክ ሀብት ስርቆት ሊደርስ የሚችልበት ዕድል ሰፊ መሆኑ፤
- በመሆኑም ሀብቱ ለስርቆት ሊጋለጥ የሚችልበት ሰፊ ክፍተት የሚታይ በመሆኑ ሀገሪቷ ሊኖሩአት የሚችሉትን ጠቃሚ የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች አቅምን

በማጠናከር፣ በመለየት እና በማወቅ ተጠቃሚ የምትሆንበትን ዕድል በጎላ ሁኔታ እንዲጠብ የሚያደርገው መሆኑ፤

- ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በተለያየ መንገድ ወደ ውጪ የተወሰዱ የብዝሀ ህይወት ሀብቶች ጥቅምን የመጋራት ወይም የማስመለስ ተግባራትን የሚመለከቱ የሕግ ጉዳዮችን በመከታተል ሀገሪቱ ከብዝሀ ሕይወት ሀብቷ የተሻለ ተጠቃሚ እንድትሆን ጥረት ለማደግ በኢንስቲትዩቱ ብዝሀ ሕይወትን የሚመለከቱ የሕግ ጉዳዮችን የሚከታተል አካል አለመኖሩ፤
- የሀገሪቱን የብዝሀ ህይወት ሀብት ይዘው በሚገኙት ክልሎች የሚገኙ እና ብዝሀ ሕይወትን በመጠበቁ ረገድ የጎላ ሚና ባላቸው መንግስታዊ መ/ቤቶች የብዝሀ ህይወት ሀብትን ለመጠበቅና ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ የመጠቀም ልምድ ለማዳበር የሚያግዝ ተግባር ሊያከናውን የሚችል መደበኛ የሆነ አደረጃጀት በእነዚህ አካላት እንዲኖር ትኩረት አለመሰጠቱ፤
- ብዝሀ ሕይወትን የሚመለከቱ ተግባራትን የሚያከናውን አካል በሚመለከታቸው የክልል ባለድርሻ አካላት ውስጥ አለመደራጀት፤ ከኢንስቲትዩቱ ጋር የመረጃ ልውውጥ እና የሥራ ትብብር በተፈለገው ደረጃ እንዳይከናወን ማድረጉ፤
- ይህም ሁኔታ የዓለም አቀፍ የብዝሀ ሕይወት ስምምነትን መሠረት በማድረግ ከፍተኛ ገንዘብ ፈሶበት የተዘጋጀውን ሀገር አቀፍ የብዝሀ ሕይወት ስትራቴጂክ ዕቅድ እንዳይሳካ እንቅፋት በመሆን፤ የሀብቱ ጥበቃ ሥራ በተሻለ ሁኔታ እንዳይይከናወን እያደረገ የሚገኝ መሆኑ፤
- የሀገሪቱን የብዝሀ ሕይወት ሀብት ጠቀሜታ እና ዋጋ ለመለካት፣ ለመተመን እና ለማወቅ የሚያስችል ግልጽ የአሠራር ሥርዓት አለመኖሩ፤
- የሀገሪቱ የብዝሀ ሕይወት ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ የብዝሀ ሕይወት ሀብትን ጠቀሜታ እና ዋጋ ለማወቅ የሚያስችል መለኪያ መኖር እንዳለበት ያስቀመጠ ቢሆንም ሥራው አለመሰራቱ፤
- የሀገሪቱ ብዝሀ ሕይወት ሀብትን ጠቀሜታ በዋጋ መተመን ሌሎች የልማት ተግባራት ከመከናወናቸው በፊት ከብዝሀ ህይወቱ ከሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የተሻለ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ መሆን አለመሆኑን

በመገንዘብ ውሳኔ ለመስጠት የጎላ አስተዋጽኦ እንዳለው የሚታመን ቢሆንም፣ ለመለካት የሚያስችል አሠራር ባለመኖሩ የብዝሀ ህይወት ሀብቱ የሚኖረው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካላት ግምት ውስጥ ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ እንዳይፈጠር በማድረግ በብዝሀ ሕይወት ሀብት ላይ የጎላ ውድመት እንዲደርስ መንገድ እየከፈተ የሚገኝ መሆኑ፤

- ሀገራችን ተግባራዊ ለማድረግ በፈረመችው ዓለም አቀፍ የብዝሀ ሕይወት ስምምነት መሠረት የተቀረጸው እና በከፍተኛ ወጪ የተጠናው ሀገር አቀፍ የብዝሀ ሕይወት ስትራቴጂክ ዕቅድ ተግባራዊ አለመደረጉ፤
- ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚያስተባብር ስትሪንግ ኮሚቴ፣ በፌደራልና በክልል የብዝሀ ሕይወት ግብረ ኃይል እንዲቋቋሙ እና ተጠናክረው የተቀመጠላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ አለመደረጉ፤

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም የሀገሪቱን የተፈጥሮ ደን ሀብት ሽፋን የሚያሳይ ካርታ እንዲዘጋጅ፤ሀገር በቀል የሆኑ ዝርያዎች ልዩ ትኩረት በማግኘት፤የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎን በማጎልበት ዘላቂነት ባለው መልኩ ለሀገሪቷ ህዝቦች ብሎም ለዓለም ኅብረተሰብ ሕልውና ወሳኝ የሆነውን የሀገሪቱ የብዝሀ ሕይወት ሀብትን በተገቢ ሁኔታ ለመጠበቅ እንዲቻል በዓለምአቀፍ ስምምነቶች መሰረት ተግባራዊ እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

10.16 በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር የጥናትና ምርምር ስራዎች እና ኢንደስትሪ ትስስር

- የዩኒቨርስቲዎች፣ የመንግስት የምርምር ተቋማትና የኢንደስትሪ ትስስርን እንደ አንድ ወሳኝ ጉዳይ ያካተተው የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ረቂቅ ፖሊሲ እና የዚህ ፖሊሲ የማስፈፀሚያ ህጋዊ ማዕቀፍ እና ማስፈፀሚያ ደንብ ማዘጋጀትና ማስፀደቅ በ2001 እና በ2002 በጀት ዓመታት ቢታቀድም ተግባራዊ አለመሆኑ፤
- አንዳንድ የጥናትና ምርምር ተቋማት በሀገሪቱ በሚገኙ ኢንደስትሪዎች ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችን በራሳቸው ጥረት በመመርመርና በመለየት ጥናት በማድረግ የደረሱባቸውን የተለያዩ የጥናትና ምርምር ሥራ ውጤቶችን ለኢንደስትሪዎቹ ለማቅረብ የሚሞክሩ ቢሆንም፤ እነዚህን የጥናት እና ምርምር

ውጤቶች የተቀበሉ ኢንደስትሪዎች ግን ተግባራዊ አድርገው የደረሱበትን ሁኔታ ለጥናት እና ምርምር ተቋማቱ የሚያሳውቁበት ሁኔታ አለመኖሩ፤

- በተመለከትናቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሶስት በጀት ዓመታት ማለትም 2001፣ 2002 እና 2003 ሥራዎች እና ዕቅዶች ውስጥ በጥናት እና ምርምር ተቋማት የሚካሄዱ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የኢንደስትሪውን ችግሮች ከግምት ውስጥ ያስገቡ ስለመሆናቸው፤ የምርምር ሥራ ውጤቶች ለኢንደስትሪው ድጋፍ ለማድረግ ስለመቻላቸው ወዘተ… በተመለከተ የሚገመገምበት ሥርዓት እንደሌለ እና ይህንን በተመለከተ የሚሠራ ሥራ በእቅድም አለመያዙ፤
- የተሻለ የፈጠራ ሥራ ለሚሠሩ ባለሙያዎች የማበረታቻ ሽልማት የሚሰጥበት ሁኔታ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደሌለ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶች ማቋቋም እንዳለበት በሚኒስቴር መ/ቤቱ መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 603/2001 ላይ የተደነገገ ቢሆንም፤ እነዚህ ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ አለመደረጉ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርምር ሥራዎች ከኢንደስትሪው ጋር ያላቸውን ትስስር የሚያግዙ የምርምር ሥራ መረጃዎችን ለማጠናቀር የሚረዳ የተደራጀ የመረጃ ቋት አለመኖሩ፤
- በተመራማሪዎች እና ተመራማሪዎቹ በሚሠሩባቸው ድርጅቶች መካከል የፈጠራ ሥራዎችን በማስመዝገብ ረገድ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን መፍትሄ ለመስጠት አስቸጋሪ ሁኔታ የሚፈጠር መሆኑን እና የምርምር ሥራዎችን ማስመዝገብን በተመለከተ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ገና ባለመፅደቁ ቀጣይ ሥራዎችን መሥራት እንዳልተቻለ፤
- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፖሊሲ የኦዲት ሪፖርቱ ወጪ እስከተደረገበት ጥር 2004 ድረስ አለመፅደቁ፤ የባለድርሻ አካላት ኃላፊነት በዝርዝር እንዲዘጋጅ አለመደረጉ፤ በሥራ ላይ የዋሉት የምርምር ሥራዎች ያስገኙት ውጤት የሚገመገምበትና በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች የሚመደበው በጀት በትክክል ለምርምር ሥራ ስለመዋሉ ክትትል የሚደረግበት የአሠራር ሥርዓት አለመኖሩ እና የሳይንስና ቴክኖሎጂ የመረጃ ማዕከል አለመደራጀቱ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዱ በረቂቅ ደረጃ

የተዘጋጁ ስትራቴጂዎች እንዳይተገበሩ፤ ባለድርሻ አካላትን በብቃት ለማሳተፍ እንዳይቻል እና የተሻለ የመረጃ ልውውጥ እንዳይከናወን የሚያደርግ መሆኑ፤ ይህም በሀገሪቱ የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች በተሻለ ብቃት እንዳይከናወኑ፤ ለምርምር ሥራ የሚመደበው ገንዘብ በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ እንዲሁም የተፈተሹ ወቅታዊነትና ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ የጥናት እና ምርምር ሥራ ውጤቶች ለኢንደስትሪው መሻሻል የተሻለ አስተዋጽኦ እንዳያበረክቱ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሊሆን እንደሚችል በመግለጽ ግድፈቶቹን ለማቃለል ይረዳሉ ያልናቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች ለኦዲት ተደራጊው አቅርበናል፡፡

10.17 <u>በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገዶች አጠባበቅ እና ጥገና</u>

- በባለስልጣኑ ሥር የሚተዳደሩ መንገዶች ከመጀመሪያ ግንባታቸው ጀምሮ በየጊዜው የተደረገላቸውን የጥገና ሂደት ታሪክ (Road History) ለአጠቃቀም በሚያመች እና ግልጽ በሆነ ሁኔታ በመረጃ ቋት ሊያዝ የሚገባ ቢሆንም፤ በናሙና በተመረጡ ዲስትሪክቶች በተደረገ የመስክ ጉብኝት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ባለሥልጣኑ ለሚያስተዳድራቸው መንገዶች ከመጀመሪያ ግንባታቸው ጀምሮ አጠቃላይ ታሪካቸውን የሚያሳይ የመረጃ ቋት (Road History) የማይያዝላቸው መሆኑ፤

- መንገዶች ከተገነቡበት ወቅት ጀምሮ ስለመንገዶቹ አጠቃላይ ታሪክና (Road History) ተዛማጅ መረጃዎችን የሚያሳይ የመረጃ ቋት አለመደራጀት በቀጣይ መንገዶቹን በሚመለከት ለሚከናወኑ ተግባራት አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ለማግኘት ስለማያስችል መንገዶቹን ለመጠገንም ሆነ አጠቃላይ ጥበቃ በማድረጉ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ፤

- የመንገድ ጥገና ከመከናወኑ አስቀድሞ የጥገና ዕቅድ ሊዘጋጅ፤ የመንገድ ጥገና እቅድ በሚዘጋጅበት ወቅትም የመንገዱን የመጀመሪያ ፕላን፣ ከዚህ ቀደም በመንገዱ ላይ የተካሄዱ የጥገና ሥራዎች እና በእነዚህ ጥገናዎች ወቅት የተገኙ ግኝቶች ወዘተ… ታሳቢ ማድረግ ያለበት ቢሆንም፤ ለጥገና ከሚመደበው በጀት ዝቅተኛነት የተነሳ የሚከናወነው የጥገና ሥራ በዕቅዱ መሠረት እንዳልሆነና

በሚመደበው በጀት መጠን ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ መንገዶች ብቻ ጥገና እንደሚደረግላቸው መሆኑ፤

- ወቅቱን የጠበቀ ጥገና ለሁሉም ባለሥልጣኑ ለሚያስተዳድራቸው መንገዶች መደረግ አለመቻሉ፤ በአነስተኛ ወጪ ጥገና ማድረግ የሚቻልበትን ዕድል በማሳጣት ለመንገድ ጥገና የሚያስፈልገው ወጪ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ እንዲሆን እና ተጠቃሚው ኅብረተሰብም ለእንግልት እንዲዳረግ የሚያደርግ መሆኑ፤

- የመንገድ ጥገና ከመከናወኑ በፊት የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ሊከናወን፤ በተጠናው ጥናት መሠረት የጥገና ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ለመሆኑ ክትትል ሊደረግ እና የጥገናፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የፕሮጀክቱ ክንውን እና መንገዱም አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጎጂ ተጽዕኖ ለመቀነስ የተቀመጡ ስልቶች እና አማራጮች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ሊቀርብ የሚገባ ቢሆንም፤ የመንገድ ጥገና ሥራዎች በሚከናወኑበት ወቅት በአካባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶች ትኩረት እንዳልተሰጣቸው እና በዚህም ምክንያት በመንገዶች እና በመንገድ ዳርቻዎች ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑ፤

- በአካባቢና ማኅበረሰቡ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ግምት ገብቶ ለመንገድ ጥገና ተግባራት የአካባቢ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አለመከናወኑ እና ይህን ጥናት መሠረት በማድረግ የአካባቢ ጥበቃ እቅድ (Enviromental Management plan) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ፤ በመንገድ ጥገና እና ከጥገና በኃላ መንገዶቹ አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት በአካባቢ ላይ ጉዳት በማድረስ በኅብረተሰቡ ሕይወት እና ጤና ላይ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ መሆኑ፤

- የመንገዶች ግንባታ እንደተጠናቀቀ ለመንገዶቹ አስፈላጊው ወጥነት እና ተከታታይነት ያለው ጥበቃ እና ጥገና ሊደረግላቸው የሚቻልበት ሁኔታ ሊመቻች የሚገባ ቢሆንም፤ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ የሆኑት ዲስትሪክቶች የሚያስተዳሩት የመንገድ አውታር ሽፋን ካላቸው የሠራተኛ ብዛት እና

ከሚመደበው በጀት ጋር የማይጣጣም መሆኑና ከአካባቢው መስተዳደር ጋር ተቀናጅቶ የሚሠራበት ሁኔታ አጥጋቢ አለመሆኑን እና በተለይም፤

- ለመንገድ ጥገና የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ከአካባቢው ለማግኘት፤ እንዲሁም ዋና መንገዶችን እና የመንገድ ዳር ይዞታዎችን ለማስጠበቅ በሚደረጉ ሂደቶች ላይ የጎላ ችግር መታየቱ፤
- በመንገድ ዳር ሀብቶች (ምልክቶች) ላይ ስርቆት እየተፈጸመ መሆኑን፤
- ለመንገድ ዳር ቦዮች እና ፍሳሽ ማስተላለፊያዎች ወቅታዊ እንንክብካቤ አለመደረጉ፤

- በባለሙያ እጥረት በመንገዶች ላይ ጉዳት ሲደርስ በፍጥነት ጥገና ለማድረግ እንዳይቻል፤ በአካባቢው እና በመንገድ ተጠቃሚው ህብረተሰብ ዘንድ ስለ መንገድ አጠቃቀም እና አጠባበቅ ያለው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ፤ ተቀናጅቶ ለመሥራት እንዳይቻል እና ለመንገዶች የሚደረገው ጥገና በተሻለ ብቃት እና ደረጃ በወቅቱ እንዳይከናወን እያደረገ የሚገኝ መሆኑ፤

- የመንገድ ጥገና ሥራዎች አዋጭነቱ እና ጠቀሜታው ተገናዝቦ በሰው ኃይል እና በአነስተኛ የእጅ መሣሪያዎች ብቻ በየአካባቢው የሚጠገኑበት አሠራር ሊኖር የሚገባ ቢሆንም፤ ተጠናክሮ በስፋት የተሄደበት ሁኔታ አይታይም፡፡ በተጨማሪም ይህን ሥራ እንዲያከናውኑ በጨረታ የተመረጡ ተቋራጮች ሥራቸውን በጨረታ መዘግየት የተነሳ በጊዜ እና በወቅቱ የማይጀምሩበት ሁኔታ መኖሩ፤

- መንገዶቹ ወቅቱን ጠብቀው ባለመጠገናቸው ቦዮች ተቦርቡረው፣ ተሸርሽረው እና ተደፍነው ፍሳሽ ባግባቡ ማስተላለፍ ባለመቻላቸው መንገዱ የተሰራበትን አፈር በመሸርሸር ለከፍተኛ ጉዳት የተጋለጡ መሆኑ፤

- የተወሰኑ ተግባራቶች በጅምር ደረጃ የሚታዩ መሆኑ የሚያበረታታ ቢሆንም በዚህ መልኩ በየአካባቢው የሚጠገኑበት አሠራር በበቂ እና በተጠናከረ ሁኔታ እየተከናወነ ባለመሆኑ በመንገዶች ላይ የከፋ ጉዳት ሳይደርስ በአነስተኛ ወጪ ሊጠገኑ እና የተሻለ አገልግሎት እንዳይሰጡ ማድረጉ፤

- የመንገድ ጠርዞች (road shoulders) እንዳይጎዱ እና የዋናው የመንገድ ደህንነት ለመጠበቅ እንዲቻል ከፍተኛ ክብደት የጫኑ ተሽከርካሪዎች የማቆሚያ ቦታ እንደአስፈላጊነቱ በየተወሰነ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ (ROAD SIDE STATION) ሊዘጋጅላቸው የሚገባ ቢሆንም፣ ከሚሰጡት ጥቅም እና ከአስፈላጊነታቸው አንጻር የመንገድ ዳር ማረፊያ ቦታዎች በቂ አለመሆናቸው፣

- ይህም ውስን የሆነውን የመንገድ ስፋት በማጣበብ ለትራፊክ መጨናነቅ እና ለአደጋዎች መባባስ ዋነኛ ምክንያት ይሆናል፡፡ እንዲሁም ማረፊያ ቦታዎች ለማግኘት በማይቻልባቸው መሰመሮች ላይ አሽከርካሪዎች ለረጅም ሰዓታት ስለሚያሽከረክሩ በመዳከም ለአደጋ የሚጋለጡበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡

- በመንገድ ጥገና ሥራዎች ላይ ወጥነትና ተከታታይነት ያለው የጥራት ቁጥጥር ኦዲት ገለልተኛ በሆነ አካል የሚደረግበት ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም፣ መንገዶች ጥገና ከተደረገላቸው በኋላ የጥራት ቁጥጥር ኦዲት ገለልተኛ በሆነ አካል የማይደረግ መሆኑና የሚታዩ ጉድለቶችን በማጣራት በሚመለከተው አካል የማስተካከያ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የማይቻልመሆኑ፣

- ከተፈቀደው ክብደት በላይ ጭነው ለሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች በተጓዙባቸው መንገዶቹ ላይ ከመነሻ እስከ መድረሻቸው ላደረሱት ጉዳት ተገቢውን ቅጣት ሊከፍሉ የሚችሉበት ሥርዓት ሊኖር እና ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም፣ ይህን ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ ተመሳሳይ ለሆኑ ጥፋቶች የተለያየ የቅጣት ውሳኔ የሚሰጥበት፣ የሚጣለው ቅጣትና በመንገዱ ላይ የሚደርሰው ጉዳት የማይመጣጠን እና አጥፊዎቹን ከጥፋታቸው እንዲታረሙ የማያደርግ መሆኑ፣

- ከዚህም በተጨማሪ በሀገሪቱ መግቢያ ድንበሮች ላይ የሚዛን ጣቢያዎች ባለመኖራቸው ቁጥጥር የሚደረገው እነዚህ ትርፍ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ከድንበር ጀምሮ ረጅም መንገድ ከተጓዙ በኋላ በመሆኑ መንገዶችን ከጉዳት ለመከላከል እንዳልተቻለ እና በመንገዶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ መሆኑ፣

- መንገዶች ከሚሸከሙት አቅም በላይ በከባድ ተሽከርካሪዎች ላይ ጭነው የሚያሽከረክሩ ሹፌሮች የተቀጡበት መረጃ የሚያሳይ የመረጃ ቋት ሊዘጋጅ የሚገባ ቢሆንም፤ መረጃዎችን በተፈለጉ ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት አለመኖሩ፤

- ከተፈቀደው ልክ በላይ ጭነው የሚያሽከረክሩ ሹፌሮች ካደረሱት ጉዳት አንፃር ተመጣጣኝና አስተማሪ ሊሆን የሚችል ቅጣት እንዲቀጡ ለማድረግ እና የቅጣት አወሳሰን ሂደቱን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ስልት አለመዘርጋቱ፤ እንዲሁም በድንበር መግቢያ ቦታዎች ላይ የሚዛን ጣቢያዎች አለመተከል ከተፈቀደው በላይ ጭነት የጫኑ ተሽከርካሪዎች በከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የተሠሩትን መንገዶች በእጅጉ በመጉዳት ያገለግላሉ ተብሎ ከተቀመጠላቸው ጊዜ ቀድመው እንዲበላሹ በማድረግ በሀገሪቷ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ የጎላ ተጽዕኖ ማሳደሩ፤

- በተጨማሪም የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎቹ በተለያየ ጊዜ በተደጋጋሚ ከልክ በላይ ጭነት ጭነው የተቀጡ ሹፌሮችን በቀላሉ ለመለየት የሚያስችል መረጃ በአግባቡ ያለመያዙ ጥፋተኞች የሚያደርጉትን የጥፋት ድግግሞሹን ግምት ውስጥ በማስገባት ተመጣጣኝ እና አስተማሪ ቅጣት እንዳይጣልባቸው እና በዚህ ረገድ በመንገድ ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ የማያስችል ከመሆኑ በላይ በመቆጣጠሩ ሂደት ላይ ብልሹ አሠራር እንዲከሰት በር የሚከፍት መሆኑ፤

በኦዲቱ የተገኙ ዋናዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንገዶች ባለስልጣን መ/ቤት የመንገዶች አጠባበቅ እና ጥገናን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል በኦዲቱ ወቅት በታዩት ጉድለቶች ላይ አግባብ ካላቸው ባለድረሻ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን የእርምት እረምጃዎች እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

10. ሌሎች ሥራዎች

10.1 የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትን በተመለከተ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለግል ኦዲተሮች እና ለሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ የማደስና የመሠረዝ ሥልጣን፤ እንዲሁም በማናቸውም የፌዴራል መ/ቤትና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊ የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

በዚህም መሠረት በበጀት ዓመት ውስጥ፣

- በተለይም የኦዲት ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅቶች ላይ ትኩረት በማድረግ፤በመስከረም /2004 ያሉበትን ያላቸውን የሰው ኃይልና በኦዲቱ ሥራ ያሰማሯቸው የኦዲት ባለሙያዎች ብዛት፤እንዲሁም የኦዲቱ ሙያ የሚጠይቃቸውን የኦዲት ደረጃዎች መከተላቸውን፤ በአጠቃላይ ድርጅታዊ ሁኔታቸውን በመገምገም ለ 52 የኦዲት ድርጅቶች አዲስ ደረጃ በመስጠት በመ/ቤታችን ድረ-ገጽ እንዲታወቅ ተደርጓል፡፡

- 2 የተፈቀደላቸው ኦዲተሮች የኦዲተርነት እና 88 የተፈቀደላቸው የሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

- 69የተፈቀደላቸውኦዲተሮችና 324 የሂሣብ አዋቂዎች በተፈቀደላቸው የጊዜ ገደብ የሙያ ብቃት ሰርተፊኬታቸውን በ2003 ያሣደሱ ሲሆን የስም ዝርዝራቸውን በመ/ቤቱ ዌብ ሣይትናእንዲገባ ተደርጓል፡፡

- የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በጠየቁት መሠረት በየደረጃው ለሚገኙ 13 የውስጥ ኦዲተሮች የሙያ ደረጃ ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡

- በመ/ቤታችን በተዘጋጀው የሙያ ስነምግባር እና አዲስ በጸደቀው በግል ለሚሰሩ ኦዲተሮችና የሂሳብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምሰክር ወረቀት አሰጣጥ ደንብን በሚመለከት ለኦዲትና የሂሳብ ባለሙያዎች የማስተዋወቂያ ውይይት ተካሂዷል፡፡

- የአገር አቀፍ ሠርቲፊኬሽን ኮሚቴ በተለያዩ ጊዜያት ባደረገው ስብሰባ ልዩ ልዩ የዲስፕሊን ጉድለት በታየባቸው ባለሙያዎች ላይ ውሣኔ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡

10.2 የመ/ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና ሥልጠና

- በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት በሙሉና ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፤ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች አስፈጻሚ አካላት በተገኙበት መድረክ በተደጋጋሚ ስለሚታዩ የኦዲት ግኝቶች ፤እርምጃ አወሳሰድ፤ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትዔ እርምጃዎች እና በአስፈጸሚው አካላት ለኦዲቱ መደረግ ስለሚገበው ትብብር የግማሽ ቀን ገለጻና ውይይት ተደረጓል፡፡

- ከእንግልዝ ሀገር የናሽናል ኦዲት ኦፊስ (NAO) በመጡ ባለሙያ በፓርላማና በዋና ኦዲተር መ/ቤቶች መኖር ስለሚገባው ግንኙነት ፤የ PAC አሰራርና ሪፖርት አቀራረብ በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ ለመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላትና ለመ/ቤታችን የኦዲት ባለሙያዎች የግማሽ ቀን ገለጻና ውይይት ተደርጓል፡፡

- አንድ የሰው ሀብት ባለሙያ በደቡብ አፍሪካ የ AFROSAI-E Human Managers Experts በሚል በተዘጋጀ Work Shop ላይ ተሣትፏል፡፡

- ለ24 የክዋኔ ኦዲት ባለሙያዎች ከመስከረም 22-26 AFROSAI-E ያዘጋጀውን performance Audit 3 module ስልጠና ተሰጥቷል፣

- 2 የክዋኔ ኦዲት ባለሙያዎች ወደ ደቡብ አፍሪካ ሄደው AFROSAI-E ያዘጋጀውን ስልጠና ወስደዋል፣

- የህንድ መንግሥት Auditing in IT Environment በሚል የሰጠው ስልጠና ሁለት ኦዲተሮች ተሣትፈው ተመልሰዋል፡፡

- የፌዴራል ስቪል ሰርቪስ ሚ/ር በጠየቀው መሠረት የመ/ቤቱ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መረጃዎች ተልኮለታል፣

- አዲስ ለተቀጠሩና ለነባር ከድጋፍ ዘርፍ ወደ ኦዲተርነት የተዛወሩ ሠራተኞች የማስተዋወቂያ ስልጠና (Induction Course) ተሰጥቷል፣

- የመ/ቤቱ መጽሔት ልሳነ-ኦዲተር የተለያዩ ዜናዎችና ትምህርታዊ ርዕሶችን በማካተት የ2003 ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

- ለመገናኛ ብዙሃንና ሌሎች አካላት የሚፈልጉትን መረጃዎች እንዲያገኙና ከመገናኛ ብዙሃን ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

- ለሥራ ጉዳይ ለሚመጡ የውጭ ሀገር ዜጎችና ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር ለሚሄዱ የመ/ቤቱ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ጉዞ የማመቻቸት ሥራዎች ተከነውኗል፡፡

10.3 ለክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የተሰጠ የስልጠና ድጋፍ

- የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በሥልጠና ረገድ የድጋፍ ጥያቄ ሲያቀርቡ መ/ቤታችን አስፈላጊውን እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡
- የፌዴራልና የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በዲሞክራሲ አቅም ግንባታ ኘሮግራም (DIP) አማካኝነት በ2003 እና በ2004 ለማከናወን የሚፈልጓቸውን በመለየት እቅድ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በማድረግ የእቅዱ አተገባበርና ያገጠሙ ችግሮች ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡
- በፌዴራልን የክልል ዋና ኦዲተሮች ዓመታዊ የምክክር መድረክ በመቀሌ 17ኛው ጉባዔ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ተካሄዶ ሰለመንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝና የኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ አወሳሰድ በተመለከተ የተለያዩ የጋራ ውሳኔዎች አሰተላልፏል፡፡

10.4 በኢንፎርሜሽን ሰርቪስ የተሠሩ ዋና ዋና ሥራዎች

ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱን በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ የማደራጀት፣ የኮምፒውተር ስልጠናና ድጋፍ መስጠት፣ ኮምፒውተርና የኮምፒውተር

ተዛማጅ እቃዎች ግዥ ሂደት ላይ ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፣ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ዳታ ቤዝ ማዘጋጀት፣ በኦዲት ሶፍት ዌር ላይ ስልጠና መስጠትና የኢንተርኔት አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ የሚከተሉትን ተግባራት አከናዉኗል፡፡

- በTeammate Audit Management ሶፍት ዌር በመጠቀም የፖይለት ሥራ ላይ ለሚሣተፉ የሥራ ክፍሎች ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል፣
- ሁለተኛው ዙር የTeam mate ሥልጠና ከመ/ቤታችንና ከትግራይ ክልል ለተውጣጡ 14 ኦዲተሮች እንዲሰጥ ተደርጓል፡
- በዓለም ባንክ በኩል የተፈፀሙ የመረጃ ቴክኖሎጂ እቃዎች ግዥ ላይ ክትትል ተደርጎ ርክክበ ተፈጽሟል፣ የኮንፊግሬሽን ሥራም ተሠርቷል፡፡
- ከDIP በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የLAPTOP እና የFirewall ግዥ በጨረታ ተከናውኗል፣
- የVPN (ቨርቹዋል ኘራይቤት ኔትወርክ) ሥራ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የPublic IP ግዥ እንዲፈፀም ተደርጓል፡፡
- የመ/ቤታችን ድረ ገጽ ለማሻሻል በጨረታው መሠረት አሸናፊው ተለይቶ ሥራው ተጀምሯል፡፡
- ከየዳይሬክቶሬቱ ለተውጣጡ 46 ኦዲተሮች የACL ስልጠና ተሰጥቷል፣
- የVPN ኮንፊግሬሽን ሥራ ተጠናቆ የሙከራ ሥራው በተለያዩ ቦታዎች እንዲፈተሽ ተደርጓል፡፡
- በየዳይሬክቶሬቱ ውስጥ ለሚገኙ ባለሙያዎች የWindow 2008 server ላይ የመጀመሪያ ዙር ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

10.5 የእቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ

- የመ/ቤቱን የ5 ዓመት የስትራቴጂክ እቅድ ረቂቅ ሰነድ ላይ ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ጋር (ከመ/ቤቱ ሠራተኞች፣ከመ/ቤቱ የሥራአመራርና ከክልል ዋና ኦዲተሮች ጋር) ውይይት በማድረግ የተሰባሰቡ የማሻሻያ ሃሣቦችን በማካተት የመጨረሻ ቅርፅና ይዘት በመስጠት ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡

- በስትራቴክጂ እቅድ ላይ የተመለከቱትን ተግባራት ለማስፈጸም የሚያስፈልገው የአምስት ዓመት የበጀት ፍላጐት የመጀመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡
- ለመ/ቤቱ ለ2004 በጀት ዓመት ፀድቆ የመጣውን በጀት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በኩል ቅናሽ የተደረገባቸወን ርዕስ እና የተቀነሰውን መጠን በመለየት እንደገና በየዳይሬክቶሬቱ የመደልደል ሥራ ተከናውኗል፡፡
- የመ/ቤቱ የድጋፍ ሰጪ ክፍሎች የ2004 እቅድ የማጠናቀር ሥራና የ2003/04 በጀት ዓመት ኦዲት ዘርፍ የሁለተኛ እና የሦስተኛ ሩብ ዓመት የድጋፍ ሰጪው የ2003 በጀት ዓመት አፈጻፀም እና የ2004 በጀት ዓመት የአንደኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት በማጠናቀር ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተልኳል፡፡
- ወርሀዊ የእቅድ አፈጻፀም ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡
- የመ/ቤቱን የ2004 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተልኳል፡፡
- የ DIP አማካኝነት ፌዴራል እና የክልል ኦዲት መ/ቤቶችን አቅም ለመገንባት ለሚሠሩ ሥራዎች የበጀት እጥረት ለታየባቸው ተግባራት ከDIP እና MoFED ጋር በመነጋገር የበጀት ዝውውር ተፈጽሟል፡፡

10.6 <u>የሰው ሀብት ሥራ አመራር</u>

ዳይሬክቶሬቱ መ/ቤቱ በልዩ ልዩ ህጐች ደንቦች እና መመሪያዎች የተሰጡትን የሥራ ኃላፊነትና ግዴታ በሚገባ ለመወጣት የሚያስችለው ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማንኛውም ጊዜ እንዲኖረው ለማስቻል ክፍት መደቦችን በቅጥር፣ በደረጃ እደገትና በዝውውር ለመሙላት፣ የሙያ ክህሎትና እውቀት የሚያስፈልጋቸው ሠራተኞች በስልጠና እና መደበኛ ትምህርት እንዲሣተፉ በማድረግ ለማብቃት፣ አዳዲስ የአሠራር ሥርአቶችን እና አስተሣሰቦችን ለማስረፅ የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን አቅዶ በግማሽ ዓመቱ ውስጥ፣

- የ25 ኦዲተሮችና የ2 ሾፌሮች ቅጥር ሲሆን፤ የ4 ሾፌሮች ቅጥር ለማካሄድ በምርታማነት ማሻሻያ ማዕከል የተግባር ፈተና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡
- የመጀመሪያ ዲግሪና የACCA ትምህርት በመከታተል ላይ ለሚገኙ የመ/ቤቱ ሠራተኞች የትምህርት ክፍያ ተከፍሎላቸዋል፣
- መ/ቤታችን ከኢትዩጵያ ሥራ አመራር ኢንስትቲዩት ጋር በመተባበር ሊሰጥ ያሰባቸውን የሥልጠና ፍላጐት ኘሮግራም በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡
- የመ/ቤቱን የሥራ መደቦች እና ደረጃን ለማሻሻል ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴራል ሲቨል ሰርቪስ ሚ/ር ጋር በመመካከር ተሻሽሎ እንዲቀረፅ ተደርጓል፡፡
- በመ/ቤታችን የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነትን አስመልክቶ በመ/ቤቱ ቢሮዎችና ግቢ ውስጥ ጥናት ተካሂዶ በጥናቱ መሠረት ለሥራ አካባቢ ጠንቆችና ጉጂዎች የሆኑትን በመለየት የማስወገድ ሥራ ተከናውኗል፡፡
- የመ/ቤቱ ቤተመጻህፍት ለተጠቃሚዎች የንባብ፣ የውሰትና የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጥቷል፣
- ለ24 የክዋኔ ኦዲት ባለሙያዎች ከመስከረም 22-26 AFROSAI-E ያዘጋጀውን performance Audit 3 module ስልጠና ተሰጥቷል፣
- 2 የክዋኔ ኦዲት ባለሙያዎች ወደ ደቡብ አፍሪካ ሄደው AFROSAI-E ያዘጋጀውን ስልጠና ወስደዋል፣
- የህንድ መንግሥት Auditing in IT Environment በሚል የሰጠው ስልጠና ሁለት ኦዲተሮች ተሣትፈው ተመልሰዋል፡፡
- ለአንድ የመ/ቤቱ ሾፌር የመካኒክነት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- የፌዴራል ስቪል ሰርቪስ ሚ/ር በጠየቀው መሠረት የመ/ቤቱ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መረጃዎች ተልከለታል፣
- አዲስ ለተቀጠሩና ለነባር ከድጋፍ ዘርፍ ወደ ኦዲተርነት የተዛወሩ ሠራተኞች የማስተዋወቂያ ስልጠና (Induction Course) ተሰጥቷል፡፡

11. ያጋጠሙ ችግሮች

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የታዩ ችግሮች፣

- ሥራውን በተጠናው የመሰረታዊ አሰራር ለውጥ (BPR) መሠረት በጥራትና በብዛት ተግባራዊ ለማድረግ ልምድ ያለው የሰው ኃይል በሚፈለገው መጠን እና የብቃት ደረጃ ለማግኘት አለመቻል፤
- ልምድ ያላቸው ሠራተኞች ከደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ማነስ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች መ/ቤቱን መልቀቅ፣
- የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ለልዩ ልዩ ማብራሪያዎችና ጉዳዮች ሲፈለጉ በወቅቱ አለመገኘትና፤በሥራ አመራር ሪፖርት ላይ በወቅቱ ምላሽ አለመስጠት እና ለኦዲተሮች ሥራ የሚያስፈልግ ቢሮ በወቅቱ ያለመስጠት፣ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ናቸዉ፡፡

12. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ያለውን የሰው ኃይል በማሰልጠን የማብቃት ሥራዎችን በማከናወን፣ በየወቅቱ ክትትል በማድረግና ከገበያም የተገኘውን ያህል በመቅጠር ክፍተቱን፤ከውስጥም ያለውን በደረጃ እድገት ለመሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡
- በመ/ቤቱ መዋቅር ላይም ከሥራው ባህሪ ጋር በሚጣጣም መልኩ እንዲስተካከሉ የተጠየቁ ጉዳዮች ተስተካክለው ስራ ላይ እንዲውሉ እየተደረገ ነው፡፡
- በም/ቤቱ አስተባባርነት በተዘጋጀው የፓርላማውና አስፈጻሚ አካላት መድረክ በኦዲቱ ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮች ላይ ውይይት በማድረግ፤ለወደፊት የመፍትዔ አቅጣጫ ተቀምጦ በም/ቤቱ የተለያዩ ቀሚ ኮሚቴ አባላትም በጉዳዩ ላይ ክትትል እንደሚደረግ ቃል ተገብቷል፡፡

13. ማጠቃለያ

በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው የኦዲት ሽፋን በሂሳብ ምርመራ ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የተያዙትን ጨምሮ 92.07% ደርሷል፡፡የኦዲት ዕቅድ ክንውናችንም የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት 100% እና የክዋኔ ኦዲቱም 17የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዶ 15ቱን

በተያዘለቸው የጊዜ ሰሌዳ ሲጠናቀቁ 2 ደግሞ በ1 ወር ዘግተው ወጪ ተደርጓል፡፡ 5 የዳሰሳና ቅኝት ደረጃ የሚገኙ ኦዲቶችበዕቅዱ መሰረት ወደ ቀጣዩ ዓመት ቢተላለፉም፤ውዝፍ የኦዲት ሥራ ባለመኖሩ ወቅታዊ የኦዲት መረጃን ማመንጨት ተችሏል፡፡

በዚህ ረገድ የተገኘው ውጤት የሀገራችንን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት የተሻለ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመለክት ቢሆንም፤ በኦዲቱ ሂደት በየመ/ቤቱ በተደጋጋሚ የሚታዩት ዋና ዋና ግድፈቶች በአፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ ዝርዝር ሪፖርቱ በሁለት ጥራዝ ተዘጋጅቶ፤የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት ለአፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት የተላከ በመሆኑ፤ ም/ቤቱ በመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል በጥልቀት መርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በተጨማሪም እርምጃ ሳይወሰድባቸው ከዓመት ወደ ዓመት የሚተላለፉ የሠነድ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተመሳሳይ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች፤ እንደዚሁም ከመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮችና በሚቀርቡት የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የማይወስዱ አካላትን በተመለከተ ያሉት ጉዳዮች ትኩረት አግኝተው መርሀ-ግብር ወጥቶላቸው ክትትል በማድረግ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በመጨረሻም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የቀረፃቸውን የአሠራር ማሻሻያዎችና ስትራቴጂዎችን በሚገባ በመተግበር ይበልጥ እንዲጠናከርና የምክር ቤቱን የክትትልና የቁጥጥር ተግባር በተሻለ ደረጃ እንዲያግዝ ሁሉን አቀፍ ድጋፍና ክትትል እንዲደረግልን እንጠይቃለን፡፡

የ2003 በጀት ዓመት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች

ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና ግኝቶች

1. መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሥት በጀት እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በውጭ ሀገር መንግሥት ድጋፍ የሚከናወኑትን ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የዕርዳታ ሂሳቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በመ/ቤቱ የአቅም ውስንነት የተነሳ ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሰቦች በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና ከመ/ቤቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርት መነሻነት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊው ድርጅት፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ የበላይ መ/ቤቶች በደብዳቤ አስፈላጊውን ማሳሰቢያ በመስጠት ውጤቱን ከሌሎች ኦዲት ጋር ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀርባል፡፡

በዚሁ መሠረት የ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በተከናወነውኦዲት የተገኙ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

2. የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2003 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት

2.1 የኮርፖሬሽኑ ዓላማ

የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የተቋቋመው በአዋጅ ቁጥር 126/1969 ሲሆንየመንግሥት የሆኑ ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዘ የማምረቻና

የማከፋፈያ እና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሂሣብ ኦዲት ማድረግና የኦዲት ሙያን ማዳበር ሲሆን፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው በአዋጅ ቁጥር 25/1984 እንዲተዳደሩ ከተወሰነ ወዲህ ግን፣ የኦዲት ሥራውን በጨረታ ካሸነፈ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንም ሆነ የግል ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት በማድረግ ላይ ይገኛል።

2.2 የኦዲት ሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት

የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ኦዲት ሪፖርቶችን ለድርጅቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ወይም ለሥራ አመራር ቦርድ ሲልክ በግልባጭ ለተመርማሪው ድርጅት ያሳውቃል።

በተጨማሪም ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርቱን ተመልክተው አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙና ክትትል እንዲያደርጉ በግልባጭ እንዲያውቁት ይደረጋል።

አንድ የፋይናንስ ኦዲት ከተከናወነ በኋላ የሚዘጋጁት ሪፖርቶች ሁለት ዓይነት ሲሆኑ እነርሱም አጭርና ረዥም /ዝርዝር/ ሪፖርት በመባል ይታወቃሉ።

በአጭር ሪፖርት የሚሰጡ አስተያየቶች ዋና ዓላማ በአንድ ድርጅት ተዘጋጅተው የቀረቡ የሂሣብ መግለጫዎች በአለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን የኦዲት ደረጃዎች መሠረት በማድረግ በቂ በሆነ ናሙና /በአልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴ/ በመጠቀም ኦዲት ከተደረጉ በኋላ መግለጫዎቹ ትክክለኛውን የፋይናንስ ሁኔታ ማሣየት ወይም አለማሳየታቸውን በመግለፅ ኦዲተሩ አስተያየት የሚሰጥባቸው ናቸው።

በረጅም ሪፖርት ላይ የሚሰጡ አስተያየቶች በኦዲቱ ወቅት የተደረሰባቸውን የገንዘብና የንብረት ጉድለቶች፣ የቁጥጥርና የአሠራር ድክመቶች በመጠቆም እነዚህን ጉድለቶችና ድክመቶች ለማስወገድ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በመግለጽ የማሻሻያ ሃሣብ የሚሰጥበት ነው።

2.3 የሥራ ዕቅድና ክንውን

ኮርፖሬሽኑ በ2003 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዛቸውና ያከናወናቸዉ የሂሣብ ምርመራ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ተራ ቁ.	መግለጫ	የ2003 በጀት ዓመት		የ2002 በጀት ዓመት
		ዕቅድ	ክንውን	ክንውን
1	የአምራች ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ	169	177	154
2	የአገልግሎት ሰጪና የማከፋፈያ ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ	66	75	68
	ድምር	235	252	222

ከላይ እንደተመለከተው የ2003 ክንውን በሪፖርት ብዛት ከዕቅዱ ጋር ሲነፃር በ17 ሪፖርቶች ከፍያለና ከ2002 በጀት ዓመት ክንውን ጋርም ሲነፃር በ30 ሪፖርት ወይም በ14% ብልጫ አሳይቷል።/ይህ የሂሳቦች ኦዲት በአንድ ጊዜ የአንድ ድርጅት የሁለትና ከዚያ በላይ በጀት ሂሳብኦዲት የተደረገውን ሁሉ ይጨምራል/

ከዚህም በተጨማሪ ኮርፖሬሽኑ በመንግስት ጥያቄ የሁለት የፈረሱ ድርጅቶችን ሂሳብ ማጣራት ሥራ እያገባደደ ሲሆን፤ከዚህም በበጀት ዓመቱ ብር 559,211 ገቢ አግኝቷል።

2.4 <u>የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ የሠራተኛው ብዛት 112 የነበረ ሲሆን፣በ2003 በጀት ዓመት ውስጥ የተቀጠሩ 14፣ ከምድብ ሥራቸው ላይ የጠፉ 6፤ በጡረታ የተገለለ 1፤በሞት የተለየ 1 እና በፈቃዳቸው የተሰናበቱ 2 በመሆኑ ፤ በ2003 በጀት ዓመት መጨረሻ 116 ሠራተኞች እንደነበሩ ታውቋል።

በ2003 በጀት ዓመት መጨረሻ የነበረው የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ፕሮፌሽናል ኦዲተሮች 77 ፣ የአስተዳደር 38 እና አንድ የትምህርትና ስልጠና ሠራተኞች እንደሆኑ ታውቋል።

2.5 <u>የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ</u>

ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዓላማ አንደኛው የኦዲት ሙያ በይበልጥ የሚዳብርበትንና አገሪቷ በዚህ ሙያ ረገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሷን እንድትችል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል።

በዚህም መሠረት በእንግሊዝ አገር ከሚገኘው አሶስዬሽንስ ኦፍ ሠርቲፋይድ አካውንታንትስ (ACCA) የሚሰጠውን የተልዕኮ የሙያ ትምህርት የድርጅቱ ኦዲተሮች እንዲከታተሉ በገንዘብና በጊዜ እንዲሁም በመጻሕፍት እየረዳ 22 ሠራተኞችን በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በአገር ውስጥ ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን በትርፍ ጊዜአቸው ለሚማሩ ሰራተኞች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተገቢውን ድጋፍ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

የኦዲት ሙያ ያለ ቀጣይና ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ሊከናወን እንደማይችል በዓለም አቀፍ ደረጃ የታመነበት በመሆኑ ኮርፖሬሽኑ በዚህ ረገድ ለሠራተኛ የሚሠጠው ሥልጠና ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

2.6 የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

የኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ ሲሆን፤በተጨማርም ከሂሳብ ማጣራትና ከሕንጻ ቢሮዎች በሚገኝ ኪራይ ነው፡፡ በ2003 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዘውና አገልግሎቱን አከናውኖ ያገኘው ገቢ ፤እንዲሁም ሥራውን ለማከናወን ያቀደው ወጪና በአግባቡ ወጪ ያደረገው ሂሣብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ2003 የፋይናንስ ዕቅድና ክንውን

መግለጫ	ገቢ ብር	ወጪ ብር	ትርፍ ብር
ዕቅድ	9,942,283	7,484,017	2,458,266
ክንውን	11,555,444	7,816,982	3,738,462
ክንውን በመብለጥ /በማነስ/	1,613,161	332,965	1,280,196

የ2003 የዕቅድ ክንውን ከ2002 ጋር ሲነፃፀር እንደሚከተለው ነው፡፡

የበጀት ዘመን	ገቢ ብር	ወጪ ብር	የተጣራ ትርፍ ብር
2003	11,555,444	7,816,982	3,738,462
2002	8,529,102	6,155,299	2,373,803
ልዩነት በመብለጥ	3,026,342	1,661,683	1,364,659

በሰንጠረዡ እንደተመለከተው የ2003 የገቢና ወጪ ክንውን እና የተጣራ ትርፍ ከ2002 ጋር ሲነፃፀር ከፍ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡

3. <u>በ2003 በጀት ዓመት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች የተሰጠ የኦዲት አስተያየት</u>

በ2003 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረገት የመንግስት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 99 ሲሆኑ በኢትዮጵያ መንግስትና በውጭ መንግሲታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ደግሞ 146 በድምሩ 245 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ ሂሳቦቻቸው ኦዲት የተደረገውን ማቤት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርቡ እንደአንድ ብቻ በመቁጠር የተወሰደ ነው) ናቸው፡፡

በእነዚህ ሪፖርቶች የተሰጠው በኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፣ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Unqualified opinion) የቀረበበት 93፣ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት (Qualified opinion) የቀረበበት 144 ፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት (Disclaimer opinion) የቀረበበት 7 እናተቀባይነትየሚያሳጣየኦዲትአስተያየትየቀረበበት2 በድምሩ 245 ነቸው፡፡

4. <u>የኦዲት ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

በ2003 በጀት ዓመት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች ሂሣባቸው ኦዲት ተደረጎ ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን ከደረሱን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጉልህ የሆኑ የየድርጅቶቹ ድክመትና የሂሣብ አያያዝ ጉድለቶች የተነሳ የኦዲት ሪፖርቱ ውጤት አቋም ለመውሰድ የማይቻልና ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት ሪፖርት እንዲያሰጥ ያደረሱናቸው ተብሎ በኦዲተሮች አስተያየት የተሠጠባቸው

ድርጅቶች ሁኔታና ከሁለት ዓመት በላይ ሂሳባቸውን ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1 አቋም ሊወሰድበት የማይቻል የኦዲት አስተያየት የቀረበባቸው

አቋም ሊወሰድበት የማይቻል (Disclaimer opinion) የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና አስተያየቱን ሊያሰጡ የቻሉ ዋና ዋና ድክመቶችና የሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

4.1.1 የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ድርጅት

ሰኔ 30/2001 የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሳብ በሙሉብርሃን መረሣ እና ጓዶቿ ኦዲት ተደርጐ የቀረበው የኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ነው፡፡

- ሰኔ 30/2000 እና 2001 የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሳብ ኦዲት የተደረገ ሲሆን፤ ከኦዲቱ በኂላ የቋሚ ንብረት (የተጣራ) ብር (54,080)፤ የሚሰበሰብ ምርት ብር (66,204)፤ ክምችት ብር (17,519)፤የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ በብር (10,416) ተስተካክለው ወይም የሂሳብ ሚዛናቸው ላይ ለመድረስ (እንድጨማሩ)ና እንድቀነሱ ተደርጎ በድርጅቱ ሂሳብ ውስጥ በመካተታቸው፤
- በክምችት ዕቃዎች ሂሳብ ከተያዘው ወስጥ ብር 1.41 ሚሊዮን አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ የመለዋወጫ ዕቃዎች መኖራቸውና ምንም መጠባበቂያ ሂሳብ ያልታዘዘላቸው በመሆኑ፣
- በተሰብሳቢነት ከሚታየው ሂሳብ ውስጥ ከሠራተኞችና ከተለያዩ ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳብ በጠቅላላ ብር 3,193,484 እና በተከፋይ ከተያዘው ሂሳብ ውስጥ ብር 3,811,479 ለተለያዩ ባለገንዘቦች የሚካፈል ተብሎ ላለፉት ዓመታት የዞረና ምንም እንቅስቃሴ የሌለው ሲሆን፤ የስራ አመራሩ ከመዝገብ እንዲሠረዙ ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ቢያሳውቅም እስከኦዲቱ መጠናቀቂያ ጊዜ ድረስ ፈቃድ ያላገኘ በመሆኑ፣
- በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በኩል በተደረገ የብድር ስምምነት መሰረት ለጊቤ የጥጥ ምርት ልማት ከIDF ብድር የተገኘ ሲሆን፤ የመጀመሪያው የብድር ክፍያ ሰኔ 30 /2001 መከናወን ቢኖርበትም እስካሁን ያልተከፈለ መሆኑና ፤
- ኦዲት የተደረገውን በጀት ዓመት ሂሳብ ጨምሮ የድርጅቱ የተጠራቀመ ኪሣራ ሚዛን ብር 11,517,626 መድረሱን ያሳያል፡፡ ይህን አስመልክቶ የመንግሥት

ልማት ድርጅቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁ.25/1984 አንቀጽ 39/4/ የአንድ ድርጅት የተጠራቀመ ኪሣራ የተከፈለውን ካፒታል 75% ያህል በድርጅቱ ከደረሰ ለድርጅቱ መፍረስ ምክንያት እንደሆነ ይደነገጋል፡፡ ስለዚህ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች የድርጅቱን የቀጣይነት ሕልውና (Going concern) መሠረት አድርገው ስለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ ማግኘት ያልተቻለ በመሆኑ ፤ የድርጅቱ በሥራ የመቀጠል ሕልውና አጠራጣሪ ሆኖ በመገኘቱ፡

ኦዲተሮቹ በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥቧል፡፡ ድርጅቱ ባለፉት ዓመታትም ተመሳሳይ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን ይህንን በተመለከተ መ/ቤታችን ለድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ በኦዲት ተደራጊዉ በኩል በቀረበው የኦዲት ሪፖርት ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልፅልን ጠይቀን የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡ ሆኖም ነሐሴ 5 ቀን 2002 ከኘራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በተገኘው መረጃ መሠረት ድርጅቱ በሽያጭ ሂደት ላይ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

4.1.2 <u>የውሃ ጉድጓድ ሥራ ድርጅት</u>

ሰኔ 30 ቀን 2001 የተጠናቀቀው የድርጅቱ ሂሣብ በደገፋ ለሜሳና ኩባንያው ኦዲት ተደርጎ የቀረበው ኦዲት አስተያየት ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

- በሰኔ 30/2001 የቋሚ ንብረት ቆጠራ ቢደረግም ውጤቱ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር አልተደረገም፡፡በተጨማሪም በርካታ ጉዳት የደረሰባቸውና ሊያገለግሉ የማይችሉ ቋሚ ዕቃዎች በሂሣብ መዝገብ ውስጥ ተካቷል፤
- በተሰብሳቢ ሂሣብ ከሚታየው ውስጥ ብር 27.3 ሚሊዮን ለረዥም ጊዜ ሳይሰበሰብ መጠባበቂያ ብር 2,912,874.43 የተያዘለት ሲሆን ይህም ለበርካታ ዓመታት ሳይለወጥ የቆየ ነው፤
- ከሠራተኞች የሚሰበሰብ 1.8 ሚሊዮን ሂሣብ ውስጥ ብር 327,940 ድርጅቱን ከለቀቁ ሠራተኞች የሚፈለግና ሊሰበሰብ ስለመቻሉ አጠራጣሪ መሆኑ፤
- ትክክለኛ ያልሆነው የተሰብሳቢ ሂሣብ (abnormal balance) ብር 3,076,023 ትክክለኛነት ያልተረጋገጠና በቂ ምክንያት አለመኖሩ፤
- የጥቃቅን ወጪዎች ገንዘብና የግዥ ፈንድ ሂሣብ ብር 755,149 ስለመኖሩ በቆጠራ አለመረጋገጡ፤

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተካፋይ ሂሣብ መዝገብና ለፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን እንደሚከፈል ከተገለፀው ሂሣብ መካከል የብር 1,659,069 ልዩነት መኖሩ፤
- በተከፋይ ሂሣብ ከተመለከተው ሂሣብ ብር 2.61 ሚሊዮን ለረዥም ጊዜ ሳይከፈል የቆየና ብር 975,111 ትክክለኛ ያልሆነ ባላንስ (Debit) የሚያሳይ መሆኑ፤
- በሌሎች ተከፋይ ሂሣቦች ውስጥ ከተያዘው ሂሣብ የቀረጥተከፋይ ሂሣብ ብር 714,478.16 በበቂ ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ፤

በድርጅቱ ተዘጋጅተው በቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት ለመስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት የድርጅቱ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ተመሳሳይ አስተያየት የቀረበበት መሆኑንና ማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱን በመጥቀስ በድጋሚ የማስተካከያ እርምጃ ተወስዶ እንዲገለጽልን፤ ብንጠይቅም ከድርጅቱም ሆነ ከስራ አመራር ቦርዱ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

4.1.3 <u>የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ</u>

ሰኔ 30/1999 የተጠናቀቀው የኤጀንሲዉ ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ የቀረበው ኦዲት አስተያየት ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ተሰብሳቢ ብር 6.5 ሚሊዮን ለተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች የተከፈለ ሲሆን ሊሰበሰብ ስለመቻሉ በቂና አስተማማኝ መረጃ ያልቀረበለት በመሆኑ፣

- በጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ላይ የተመለከተው ያልተለመደ ሚዛን (Negative balance) ብር 6.3 ሚሊዮን እንዴት ሊከሰት እንደቻለና በሀብትና ዕዳ መግለጫው ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሚዛን ላይ ለምን እንደተቀነሰ እንዲሁም ብር 374,578 በባንክ ገቢ የተመለከተው ከዓመት በላይ ለምን በእንጥልጥል እንደቆየ በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠው በመሆኑና ባጠቃላይ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቡ ትክክለኛነት አስተማማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ፣

- በባንክ ሂሰብ ማስታወቂያዎች ላይ የተመለከቱት የተለያዩ ወጪዎች በጠቅላላ ብር 4.2 ሚሊዮን እና በጠቅላላ ብር 2.41 ሚሊዮን ገቢ በኤጀንሲው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ ለምን እንዳልተመለከተ በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠበት በመሆኑ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የባለዕዳዎች ሂሳብ ውስጥ ብር 25.65 ሚሊዮን ለረዥም ዓመታት ሳይከፈል ለምን እንደቆየና የኤጀንሲው ትክክለኛ ዕዳ ስለመሆናቸው በቂና አሳማኝ ማብራሪያ ባለመሰጠቱ፣
- ከተጠራቀመው ሀብት ላይ ብር 168 ሚሊዮን በወጪ እንዲቀነስ (writer off) የተደረገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 72.6 ሚሊዮን ቀደም ሲል በኤጀንሲው ሥር የነበሩ ቋሚ ንብረት በመንግሥት ትእዛዝ ወደ ክልል መንግሥታት ይዞታ ሥር እንዲሆኑ የተላለፈና ቀሪው ብር 73.1 ሚሊዮን ለቀድሞ የቤት ባለቤቶች ክፍያ መጠባበቂያ የተያዘና ብር 22.43 ሚሊዮን ያለፉት ዓመታት ወጪ በስህተት በተሰብሳቢ የተያዘ እንደሆነ ያሳያል፡፡ እነዚህ ንብረቶች ለክልል መንግስታት የተላለፉበት የርክክብ ማስረጃ ባልቀረበበትና የመጠባበቂያ ሂሳቡ እንዲሰረዝ ሥልጣን የተሰጠው አካል ትእዛዝ ባልቀረበበት ሁኔታ ስለሂሳቡ ከመዝገብ መሠረዝ ትክክለኛነት ማጣራት ባለመቻሉ፡
- ኤጀንሲው የኪራይ ታክስ ሊከፍል የሚገባው ቢሆንም ለዚህ የያዘው መጠባበቂያ የለም፡፡ ቀደም ባሉት ዓመታት የተከፋይ ታክስ ሂሳብ በሀብትና ዕዳ መግለጫው እንደተሰብሳቢ የተመለከተ ቢሆንም በጠቅላላው ብር 283.9 ሚሊዮን ተከፋይ ሂሳብ ከመጠባበቂያ ሀብት (reserve account) እንዲቀነስ /እንዲሰረዝ/ ተደርጓል፡፡ ቀሪው ተከፋይ ብር 3.3 ሚሊዮን አሁንም በሀብት ዕዳ መግለጫው ላይ በሰኔ 30/1999 ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ተመልክቷል፡፡ ይህም ሆኖ ኤጀንሲው ከ1992-1995 ብር 85 ሚሊዮን የኪራይ ታክስ የከፈለ ሲሆን እዚህ ሂሳብ ላይ እንዴት ሊደረስ እንደቻለ፤ ከመጠባበቂያ ሀብቱ ላይ ከላይ የተመለከተው ሂሳብ ለምን እንደተቀነሰ እና የተከፈለውም የኪራይ ታክስ ዕዳ ይህ ብቻ ስለሆኑ በቂ ማስረጃና ማብራሪያ ሊቀርብ ባለመቻሉ፣

- ኤጀንሲው በሚሰበስበው የኪራይ ገቢ ላይ የዘረጋው የውስጥ የቁጥጥር ሥርዓት ባመኖሩ የተመዘገበው ከኪራይ የተሰበሰበ ገቢ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- የቀድሞ የቤት ባለቤቶችን በመወከል በመንግሥት ለተወረሰባቸው ቤቶች የባንክ ዕዳ ተብሎ ለባንክ የተከፈለው የረዥም ጊዜ የባንክ ዕዳ ክፍያ ብር 20.63 ሚሊዮን የመሰብሰብ ዕድሉ በጣም ዝቅተኛ በሆኑ በሙሉ በወጪ ሊመዘገብ የሚገባ መሆኑ፣
- በሀብት ዕዳ መግለጫው በተሰብሳቢነት የተመለከተው ብር 59.52 ሚሊዮን ለተለያየ ኮንትራክተሮች ቅድሚያ ክፍያ ለበርካታ ዓመታት የቆየና ወደ ሕንፃ ሂሳብ ያልተካተተ ወይም በግንባታ ሂደት ላይ ወዳለ ሂሳብ ያልዞረ በመሆኑ፤ ወደ ሕንፃ ሂሳብ ገብቶ የእርጅና ተቀናሽ ሊሰላለት የሚገባው ምን ያህሉ እንደሆነ ባለመታወቁ የተጣራ ትርፉን ለወሰን አዳጋች በመሆኑ፣
- እስከ ሰኔ 30/1985 ተገኘ የተጣራ የተጠራቀመ ትርፍ ስለመካፈሉ ወይም ስለመኖሩ ያልተገለፀ ሲሆን ከ1986 እስከ 1999 ድረስ ለገ/ኢ/ል/ሚ ብር 355 ሚሊዮን ተከፍሏል፡፡ነገር ግን ኤጀንሲው ሂሳቡ በትክክለኛ ዕዳውና ይህ ብቻ ስለመሆኑና እንዴት እንደተሰላ ወይም እንደተወሰነና የተጣራ ትርፍ አጠቃቀምን የሚያሳይ ማስረጃና በቂ ማብራሪያ ባለመቅረቡ በሰኔ 30/1999 ሂሳብ ውስጥ የተመለከተው ዕዳ የተጠራውን ሀብት በትክክል የሚያመለክት መሆኑን ለማረጋገጥ አዳጋች የሚያደርገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በተጨማሪም በርካታ የሂሳብና የንብረት አያያዝ ድክመቶች ሪፖርት የተደረጉ ሲሆን፣ በተለይ ኤጀንሲው ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ገቢ የሚያገኝ ቢሆንም እንደቋሚ ንብረት በሂሳብ መዝገብ መዝግቦ የእርጅና ተቀናሽ እየታሰላለት በሂሳብ መግለጫዎች እንዲካተቱ ባለመደረጉ የተጠራቀመ ትርፉ የተጋነነ እንዲሆን ስለሚያደርገው አስፈላጊው ማስተካከያ ያልተደረገለት በመሆኑ፤

በኤጀንሲው ተዘጋጅተው የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች የዓለም አቀፍ የሂሳብ አሠራር ደረጃዎች ተከትሎ ያልተዘጋጁና በተጠቀሱት ምክንያቶች በቂና አሳማኝ መረጃ ባለማግኘታቸው አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡

በዚሁ መሠረት እነዚህና ሌሎች በሪፖርቱ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ እንዲገለጽልን በመ/ቤታችን ተጠይቆ በተሰጠው ምላሽ ኤጀንሲው ችግሮቹን በየደረጃው ለመፍታት ጥረት እያደረገ እንደሆነና እስከአሁን፣

- ከውዝፍ የኪራይ ተሰብሳቢዎች ሊሰበሰቡ የሚችሉትንና የማይችሉትን በመለየት ከግለሰብ ተከራዮች፤ ከኤንባሲዎችና አለም አቀፍ ድርጅቶች ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር ጋር በመተባበር በርካታ የመንግሥት ገንዘብ ለመሰብሰብ መቻሉንና ቀሪ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን እንዲያጣራ ኮሚቴ ተቋቁሞ በማጣራት ላይ መሆኑን፣
- ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጋር በመተባበር የተለያዩ የረዥም ጊዜ ብድር ዕዳዎች መፍትሔ ያገኙ መሆኑን፣
- ኤጀንሲው የተወረሱ ቤቶችን በአዋጅ እንዲያስተዳድር ከመደረጉ በስተቀር በትርፍነት መወረሳቸውን የሚያረጋግጥ ቅጽ 003 እና የይዞታ ማረጋገጫ ማግኘት አለመቻልና የተወረሱት ቤቶች የተሰሩበት ዋጋ ፤የተሰሩበት ዘመንና ከነዝሁ ጋር ተያይዞ የመጣ ዕዳ በትክክል ተመዝግቦ ባለመገኘቱ በርካታ ችግሮች የነበሩ በመሆኑ ይህንን ለማስተካከል እንቅስቃሴ እየተደረገ እንደሆነና ኤጀንሲው የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች ዘመናዊ በሆነ መልክ የማደራጀትና የባለቤትነት ማረጋገጫ እንዲኖራቸው በማድረግ የቤቶች ቆጠራ ፕሮጀክት ቀርጾ ቆጠራው የተጠናቀቀ ሲሆን፤ የቤቶቹ የይዞታ ማረጋገጫ በተመለከተ ከአዲስ አበባ መስተዳድር ጋር በመተባበር የቤቶቹ ካርታ እየተዘጋጀ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡

4.1.4 <u>አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ዋና መ/ቤት</u>

ሰኔ 30/1998 የተጠናቀቀው የዩንቨርሲቲው ዋና መ/ቤት የ4 በጀት ዓመታት ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በሰኔ 30/1998 የሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የነዳጅና የቅባት ሂሳብ ብር 1.68 ሚሊዮን በቂ የቆጠራ መረጃ ሳይቀርብለት በሂሳብ መግለጫው በመካተቱ ለዚህ ማስተካከያ ማድረግ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ ከፍተኛ ለውጥ የሚያስከትል በመሆኑ፣
- የጽሕፈት መሣሪያዎችና የጽዳት እቃዎች ክምችት ላይ ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (credit balance) ብር 1.05 ሚሊዮን እንዴት እንደተከሰተና በሂሳብ መግለጫው የተመለከተው የክምችት ሂሳብ ብር 3.34 ሚሊዮን ላይ ለመድረስ አስቀድሞ ለምን እንደተቀነሰ በቂ ማብራሪያ ያልሰጠ መሆኑ፣
- በተሰብሳቢ ሂሳብ የተመለከተው በግምት ብር 52 ሚሊዮን ለበርካታ ዓመታት ሳይሰበሰብ የቆየና ከዚህ ውስጥ ሳይሰበሰቡ ሊቀሩ ለሚችል ሂሳብ ምንም መጠባበቂያ ያልተያዘለት፤ እንዲሁም ዩንቨርሲቲው በሕግ በማስገደድ ሊሰበስባቸው ለመቻሉ ምንም እርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ ላይ መሆኑ፣
- በጥሬ ገንዘብና በባንክ ሂሳብ የተመለከተው ብር 16.00 ሚሊዮን ስለመኖሩ በቂ ማስረጃ ያልቀረበና በኦዲት ለማረጋገጥ የሚያስችልሌላ አሰራር ለመከተል አስቸጋሪ መሆኑ፤
- የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ብር 1.15 ሚሊዮን ያልተለመደ ሚዛን (credit balance) እንዴት ሊከሰት እንደቻለና ከላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብና በባንክ ሂሳብ ላይ ከመደረሱ በፊት ለምን እንደተቀነሰ በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠ በመሆኑ፣
- ከባንክ ወጪ የሆኑ የተለያዩ ክፍያዎች በጠቅላላ ብር 51.45 ሚሊዮን እና የተለያዩ ገቢዎች (deposits) በጠቅላላ ብር 58 ሚሊዮን በባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ (Bank statements) የተመለከቱት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ለምን እንዳልተንፀባረቁና የተመለከቱም ከሆነ በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሆነ ለማጣራትና ማብራሪያ መገኘት አለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ብር 13.73 ሚሊዮን በባንክ ገቢ የሆነ ሂሳብ ጨምሮ ሲሆን፤ ይህ ሂሳብ ከ1 ዓመት በላይ የቆየና ስለትክክለኛነቱ በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠበት በመሆኑ

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ሚዛኑ ትክክለኛነትና አስተማመኝነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤ ፣

- በተከፋይ ሂሰብ የተመለከተው ብር 38.16 ሚሊዮን ለበርካታ ዓመታት ሳይከፈል የቆየና ለምን እንዳልተከፈለ ወይም ትክክለኛ የዩንቨርሲቲው ዕዳ ስለመሆኑ በቂ ማብራሪያ መገኘት ያልተቻለ በመሆኑ፣
- በዩንቨርሲቲውና በተባባሪ ድርጅቶች መካከል ምንም የሪፖርት ወይም የሂሳብ መግለጫዎች ልውውጥ ባለመኖሩ የተመዘገቡትን ሂሳቦች ዝውውርና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ባለመቻሉ፣
- ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተገኘው ማረጋገጫ መሠረት በሰኔ 30/1998 ከመንግሥት ለዩንቨርሲቲው ከተላለፈ በጀት ውስጥ ብር 5.96 ሚሊዮን የዩንቨርስቲው ምዝገባ በማነስ የሚያሳይ በመሆኑ፣
- በዩንቨርሲቲው የውስጥ ገንዘብ ዝውውር (Inter-fund balance) በተሰበሳቢና በተከፋይ የተመዘገቡ ሂሳቦችን በማዋወጥ (off-set) በሰኔ 30/1998 የሀብትና ዕዳ መግለጫው የተጣራ ብር 9.23 ሚሊዮን ተሰብሳቢ ያሳያል፡፡በተጨማሪም ብር 39,816 ተሰብሳቢ ከካፒታል ፈንድ የሚፈለግ ተብሎ የተመለከተ ሲሆን በዩንቨርሲቲው ምዝገባ ላይ ለመገኘት ያልተቻለ፤ በመሆኑም ለዚህ ሁሉ በቂ ማብራሪያ መገኘት ባለመቻሉ፣
- በግምት ዋጋው ብር 1.5 ሚሊዮን የሚያወጣ በብሔራዊ ባንክ ጥበቃ ሥር የሚገኝ የዩንቨርሲቲው ወርቅ የሂሳብ መግላጫዎች ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ፤

ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች በዩንቨርሲቲው ተዘጋጅተው የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች በሰኔ 30 1998 ዩንቨርሲቲውን የፋይናንስ አቋም፣ የሥራ ውጤት፤ እንዲሁም የሀብት ምንጭና አጠቃቀም በትክክል ያሳያሉ ብሎ አስተያየት ለመስጠት ያላስቻሏቸው መሆኑን ኦዲተሮቹ ገልፀዋል፡፡

መ/ቤታችንም ሪፖርቱ እንደደረሰው በሪፖርቱ በተዘረዘሩት የሂሳብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ ችግሮች ላይ የተወሰደው እርምጃ እንዲገለጽልን፤ ወደ ኂላ የቀሩት በጀት ዓመታት ሂሳብም ኦዲት ተደርገው ሪፖርት እንዲቀርብ እንዲደረግ ለትምህርት ሚኒስትር በአድራሻና አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲን በግልባጭ ለጠየቅነው ጥያቄ

የትምህርት ሚኒስቴር ለዩንቨርሲቲው እርምጃ በመውሰድ እንዲያሳውቀን ማሳሰቢያ ቢሰጠውም ከዩንቨርሲቲው የተሰጠን ምላሽ የለም፡፡

4.1.5 አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የቢዝነስናኢኮኖሚክስ ፋኩልቲ

ሰኔ 30/1998 የተጠናቀቀው የፋኩልቲው የ4 በጀት ዓመታት ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ የቀረበው አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ ፋኩልቲው ተቀጽላ ሌጀር(Subsidiary ledger) ባለመያዙ ምክንያት በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከቱት ሂሳቦች ሚዛን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሰኔ 30/1998 መጨረሻ በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ እና በባንክ ሂሳቡ የተመለከተው በቆጠራ ከተገኘው በብር 89,656 በማነስ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ ሚዛን ብር 2.56 ሚሊዮን ላይ ለመድረስ ብር 8,540 ለምን እንደተቀነሰ በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠበት በመሆኑ፣
- በፋኩልቲው የውስጥ ገንዘብ ዝውውር (inter-fund balance) በተሰብሳቢና በተከፋይነት የተመዘገቡ ሂሳቦችን በማዋወጥ (off-set) ውጤቱ ዜሮ ሚዛን እንዲያሳይ ቢደረግም የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 289,731 እና ተከፋይ ሂሳብ ብር 16,701 የሚያሳይ በመሆኑ ለዚህም በቂ ማብራሪያ መገኘት አለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ከተመለከተው ተሰብሳቢ ብር 373,102 በርካታ ዓመታት የቆዩና ለዚህም ምንም መጠባበቂያ ሂሳብ ያልተያዘለት ሲሆን በኦዲተሮቹ አስተያየት ይህ ሂሳብ ሊሰበሰብ የመቻል ዕድሉ በጣም አጠራጣሪ በመሆኑ በሙሉ ከሂሳቡ መሰረዝና የሌሎች ዓመት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግ የሚገባው በመሆኑ፣
- ምክንያት የተነሳ በሂሳቡ ላይ አስተያየት ለመስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልጸዋል፡፡

- ይህንን በማስመልከት መ/ቤታችን ለአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ፕሬዝዳንት በአድራሻና ለፋኩልቲውበግልባጭ በእነዚህ ግኝቶች ላይ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግና የሂሳቡም ኦዲት በወቅቱ በ4 ዓመታት ወደኋላ የቀረ መሆኑን በመግለጽ ወደኋላ የቀሩት ሂሳቦችም ኦዲት ተደርገው ሪፖርቱ እንዲቀርብ ማሳሰቢያ ቢሰጥም፤ ከሁለቱም አካላት የተሰጠን ምላሽ የለም፡፡

4.1.6 አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የሕክምና ፋኩልቲ

ሰኔ 30/1998 ዓ.ም የጠናቀቀው የሕክምና ፋኩሊቲው የ4በጀት ዓመት ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የፋኩልቲው ሂሳቦች በትክክል ስለመመዝገባቸው በኦዲት ለማረጋገጥ አንዳንድ የሂሳብ ዶክመንቶችና መረጃዎች ለኦዲት ያልቀረቡና በቂ ማብራሪያ ማግኘት ባለመቻሉ፣
- በሀብት ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 685,424 ሳይሰበሰብ ለበርካታ ዓመታት የቆየ በመሆኑ ፋኩልቲው ሊያስገድድና ሊሰበስብ ስለመቻሉና በቂ ማብራሪያ ባለመቅረቡ ፤
- በተከፋይ ሂሳብ የተመለከተው ብር 397,145 ለበርካታ ዓመታት ሳይከፈል ለምን እንደቆየና የፋኩልቲው ትክክለኛ ዕዳ ለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ ማግኘት ባለመቻሉ፣
- ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተገኘው ማረጋገጫ መሠረት በሰኔ 30/1998 ከመንግሥት ለፋኩልቲው ከተላለፈ በጀት ውስጥ በብር 2,004,361 የሕክምና ፋኩልቲው ምዝገባ በማነስ የሚያሳይ መሆኑ፣
- በደመወዝ መክፈያ (payroll) ዝግጅትና የደመወዝ ክፍያዎች ላይ ፋኩልቲው ተገቢ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ፤ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሌላ አመቺ የኦዲት ዘዴ መከተል አለመቻሉ፣
- በፋኩልቲው የውስጥ ገንዘብ ዝውወር (Inter-fund balance) በተሰብሳቢና ተከፋይ የተመዘገቡ ሂሳቦችን በማዋወጥ (off-seting) የተጣራ ብር 17,428 የሚታይ ሲሆን ለዚህም በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠ በመሆኑ፣

በሕክምና ፋኩልቲው ተዘጋጅተው ለኦዲት የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች የፋኩልቲውን የፋይናንስ አቋም፣ የሥራ ውጤት እንዲሁም የሀብት ምንጭና አጠቃቀም በትክክል ያሳያሉ ብሎ አስተያየት ለመስጠት ያላስቻሏቸው መሆኑን ኦዲተሮቹ ገልፀዋል፡፡

በዚሁም መሠረት መ/ቤታችን በኦዲት ሪፖርቱ በተዘረዘሩት የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ ችግሮች ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገለጽልንና ወደኋላ የቀሩት በጀት ዓመታት ሂሳብም ኦዲት ተደርገው ሪፖርት እንዲቀርብ እንዲደረግ በአድረሻ ለአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲና ለፋኩልቲው በግልባጭ ማሳሰቢያ ቢሰጥም ከሁለቱም አካላት የተሰጠን ምላሽ የለም፡፡

4.1.7 <u>አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ፋኩልቲ-ሰሜን ካምፓስ</u>

ሰኔ 30/1998 ዓ.ም የተጠናቀቀው የፋኩልቲው የ4 በጀት ዓመታት ሂሳብ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጐ ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 584,920 ለበርካታ ዓመታት ሳይሰበሰብ የቆየና ሊሰበሰብ ላለመቻሉ ሥጋት ምንም መጠባበቂያ ያልተያዘለት በመሆኑ፤ይህም ሂሳብ ሊሰበሰብ ለመቻሉና ፋኩልቲው በሕግ ሊያስገድድ እንደሚችል እርግጠኛ ለመሆኑ ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣
- በፋኩልቲው የውስጥ ገንዘብ ዝውውር (Interfund balance) በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን በማወወጥ (off-seting) የተደረሰበት ሂሳብ የተጣራ ተሰብሳቢ ብር 28,311 የሚያሳይና ይህም እንዲታረቅ ባለመደረጉ የውስጥ ዝውውሩን ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ባለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው ተከፋይ ሂሳብ ብር 969,353 ፋኩልቲው ዝርዝር ተቀጽላ ሌጀር (subsidiary ledger) ባለመያዙ ለባለዕዳዎች ለይቶ ለመክፈል አስቸጋሪ የሚያደርግ በመሆኑ፣

- ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተገኘው ማረጋገጫ መሠረት በሰኔ 30/1998 ዓ.ም ከመንግሥት ለፋኩልቲው ከተላለፈው በጀት ውስጥ በብር 217,571 የፋኩልቲው ምዝገባ ልዩነት በማነስ የሚያስይ በመሆኑ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ብር 2,043,896 ላይ ለመድረስ ያልተለመደ ሚዛን (credit balance) ብር 169,936 በመቀነስ /በማጣጣት/ ሲሆን ይህም ለምን እንደተደረገ በቂ ማብራሪያ ባለመገኘቱ የተመለከተው ሂሳብ ትክክል ስለመሆኑ ለማጣራት ባለመቻሉ፣
- በባንክ የሚገኝ ብር 473,123 ለSIDA/SAREC የምርምር ሥራ የተያዘ ገንዘብ በሰኔ 30/1998 የፋኩልቲው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ ባለመካተቱ የበጀት ዓመቱን የፋኩልቲውን የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሀሳብ በዚሁ ያህል ዝቅ የሚያደርገው በመሆኑ፣

በፋኩልቲው ተዘጋጅተው የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች ከላይ በተጠቀሱት መረጃዎች ዕጥረት በመገደባቸው የፋይናንስ አቋም ፣ገቢና ወጪ በትክክል ያሳያሉ ብሎ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ገልፀዋል፡፡

ይህንን መሠረት በማድረግ መ/ቤታችን በኦዲት ሪፖርቱ በተዘረዘሩት የሂሳብ አያያዝ ችግሮች ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጽልንና ወደኋላ የቀሩት በጀት ዓመታት ሂሳብም ኦዲት የተደረገው ሪፖርት እንዲቀርብ እንዲደረግ በአድራሻ ለአ.አ ዩንቨርሲቲ ፕሬዝዳንትና ለፋኩልቲው በግልባጭ ማሳሰቢያ ቢሰጥም ከሁለቱም የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

4.2 ቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት የሰጠባቸው

ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት ሪፖርት እንዲያሰጥ የደረሱ ጉልህ የሆኑ የየድርጅቶቹ ድክመትና የሂሣብ አያያዝ ጉድለቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.2.1 የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት ኢ.ማ.

ሰኔ 30 ቀን1999 ዓ.ም. የተጠናቀቀው የአክስዮን ማህበሩ ሂሣብ በአማ.ኃይ የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጐ የቀረበው ኦዲት አስተያየት ቀጥሎ የተመለከተው ነው፡፡

- አክስዮን ማህበሩ በጥር 1/1992 ዓ.ም. ሲመሠረት የተጣራ ሀብት በግምት ብር 135,150,000 ሲሆን፤በወቅቱ የነበረው የዕቃ ክምችት (stock)፣ የተሰብሳቢ፣ የተከፋይና የተጣራ ሀብት ሂሳቦች በሂሳቡ ያልተንጸባረቁ በመሆኑ በሰኔ 30/1999 መጨረሻ በሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ የሚታየው በትክክል የማያሳይ መሆኑ፤
- በዓመቱ መጨረሻ የክምችት ዕቃ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም በቆጠራውና በመዝገብ መካከል የብር 1,610,852 ልዩነት እየታየ በሂሳብ መግለጫው በመካተቱ፤በክምችት ዕቃዎች ላይ ስለሚደረገው የውስጥ ቁጥጥር አስተማማኝነትና የሂሣቡ ትክክለኛነት ለማመን አልተቻለም፤
- ለረጅም ጊዜ የቆዩ የተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 48,379,840 እና ተከፋይ ሂሣብ ብር 25,917,657 ከመዝገብ እንዲሰረዙ (write-off) ማኔጅሜንቱ ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ደብዳቤ የፃፈ ቢሆንም፤ ለተሰብሳቢ ሂሣቦቹ መጠባበቂያ ያልተያዘና ስለተከፋይ ዕዳው እውነተኛነት ለማመን አዳጋች በመሆኑ፤

በድርጅቱ ተዘጋጅታው ለኦዲት የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች የአ.ማህበሩን የስራ እንቅሰቃሴ፤ የገንዘብ ምንጭና አጠቃቀም፤በአለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ መርሖዎች መሰረት እንደማያሳዩ ኦዲተሮቹ ገልጸው፤በዚሁ ምክንያት ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ሳይስተካከሉ የሂሳብ መግለጫቹ እንዳይጸድቁ በማስጠንቀቅ አስተያያታቸውን ሰጥተዋል ።

በዚሁ መሰረት መ/ቤታችን በኦዲት ሪፖርቱ መሰረት የተወሰደ እርምጃ እንዲገለጽልንና የተቀሩት በጀት ዓመታት ሂሳቦች ኦዲት ተደርገው ሪፖርት እንዲቀርብ እንዲደረግ ለስራ አመራር ቦርዱ ባሳሰበው መሰረት የ2000 እና 2001 ዓ.ም ሂሳቦች እስከ ጥር 2003 ድረስ ለውጭ ኦዲት እንደሚቀርቡና በሪፖርቱ የተጠቀሱት ችግሮች አንዳንዶቹ እንደተሰተካከሉ ገልጸው ሌሎች ማስተካከያዎችም ለማድረግ የተዘጋጀውን መርዓ-ግብር አያይዘው ልከዋል።

4.2.2 <u>አዶላ ወርቅ ማዕድን ልማት ኢንተርፕራይዝ</u>

በሰኔ 30/1999-2001 የተጠናቀቀው የኢንተርፕራይዙ የ3 ዓመት ሂሣብ በአማ.ኃይ የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ኦዲት ተደረጐ የተሰጠው አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በመግለጫዎቹ ስለተካተተው የክምችት ዕቃዎች ዋጋ ብር 8,617,893 ትክክለኛነት ማረጋገጥ በሚከተሉት ድክመቶች ምክንያት አልተቻለም፡፡
- በሀብትና እዳ መግለጫው የተመለከተ የክምችት ዕቃዎች ከወጪ ቀሪ ሚዛን ብር 8,617,893 ክሬዲት ባላንስ ከተቀነሰለት(net balnnce) በኂላ መሆኑ፤
- እንዲሁም የክምችት ዕቃዎች ክሬዲት "ለማስተካከያ" ብር 2,801,8992 እና "ያልተለየ ወይም ያልተወቀ ልዩነት" ተብሎ ብር 257,249 የተያዘን ሂሣብ በተመለከተ በቂ ማብራሪያ መስጠት አለመቻሉ፤
- በጉዞ ላይ ያሉ ዕቃዎች ሂሣብ ውስጥ ብር 32,314,789 ለረጅም ጊዜ የቆየና የሂሣቡንም ሁኔታ መለየት አለመቻሉ፤
- ለረጅም ጊዜ እየተንከባለለ የሚገኘው ተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 193,187,058 ውስጥ ላይሰበሰብ ይችላል ተብሎ መጠባበቂያ 57,270,933 ብቻ የተያዘለት ነው፡፡ ከዚሁ ተሰብሳቢ ሂሣብ ሊሰበሰብ የመቻል ዕድሉ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በተጨማሪ መጠባበቂያ ብር 135,916,125 መያዝ የነበረበት በመሆኑ፤
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የጥሬ ገንዘብና ባንክ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ ብር 35,949,298 ትክክለኛነት በሚከተሉት ምክንያቶች በመገደቡ ማረጋገጥ አልተቻለም፤
- የተለያዩ 3 የባንክ ሂሣቦች ከወጭ ቀሪያቸው ትክክለኛ ያልሆነ ባላንስ ብር1,137,091 (credit balance) የሚያሳይና የባንክ ሂሣብ ማስታወቂያ መግለጫ ባለመቅረቡ ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- የተለያዩ 8 የባንክ ሂሣቦች ከወጭ ቀሪያቸውን የሚያሳይ የባንክ ሂሣብ ማስታወቂያ መግለጫና የተዘጋጀ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ መግለጫ ባለመቅረቡ ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

- በተለያዩ 3 የባንክ ሒሣቦች ላይ በባንክ ሒሣብ ማስታወቂያና የሒሣብ መዝገቦች የተመለከተው መካከል በድምሩ ብር 25,057,945 ልዩነቱ ስለሚያሳይና ይህም የባንክ ሚዛኑን ትክክለኛነት የሚያጠራጥር ከመሆኑም በላይ ለባንኮች ማረጋገጫ እንዲልኩልን ጠይቀን ምንም ምላሽ ባለማግኘታችን ፤
- በተካፋይ ሂሣብ ከተያዘው ውስጥ ብር 23,677,261 ለረጅም ጊዜ ሳይከፈል የቆየ በመሆኑ፤ ትክክለኛ እዳ /ተካፋይ/ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በሚከተሉት ምክንያቶች በሂሣቡ የተመለከቱትን ስለረጅም ጊዜ ብድሮች ብር 46,020,575 ሙሉነትና ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም (ሁሉም የክፍያ ጊዜያቸው አልፏል)
  - በረጅም ጊዜ ተይዘው ካሉ ብድሮች አንዳንዶቹ በቀጥታ ወይም በተዛዋዋሪ ከውጭ አበዳሪዎች የተገኙ ሲሆን አከፋፈላቸው በውጭ ምንዛሪ መሆኑ ወይም አለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ አለመቅረቡ፤
  - እስከ ሰኔ 30/1999 ዓ.ም በእነዚህ ብድሮች ላይ ሊከፈል የሚገባ ወለድ አለመያዙ፤

  ናቸው፡፡

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ምክንያት በኢንተርፕራይዙ ተዘጋጅተው ለኦዲት የቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች የአ.ማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ፤ የገንዘብ ምንጭና አጠቃቀም፤በአለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ መርሖዎች መሰረት እንደማያሳዩ ኦዲተሮቹ ገልጸዋ፡፡

መ/ቤታችንም በኦዲት በሪፖርቱ ላይ የተወሰዱትን እርምጃ እንዲገለጽልንና የተቀሩት በጀት ዓመታት ሂሳቦች ኦዲት ተደርገው ሪፖርት እንዲቀርብ እንዲደረግ፤ ለሥራ አመራር ቦርዱ በአድራሻ ና ለኢንተርፕራይዙ በግልባጭ ቢያሳውቅም፤ ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ምንም ምላሽ አልተሰጠም፡፡

5. ስለድርጅቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ

የድርጅቶች አጠቃላይ የሂሳብ አያያዝ ንብረት አጠባበቅና የፋይናንስ አስተዳደርን በተመለከተ በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ችግሮችና መፍትሔያቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

5.1 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ የሌላቸው፤ ያላቸውም ቢኖሩ ምዝገባቸው ያልተሟላ አንዳንዶች ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን አንድ ላይ መዝግበው መገኘታቸው ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መዝገብ ቢይዙም የግዥ፤ ሽያጭንና ዝውውርን በተመለከተ የተሟላ መረጃ ካለመመዝገባቸው የተነሳ መዝገብ ውስጥ ያለው የዋጋና የአገልግሎት ቅናሽ ሂሳብ በዋናው መዝገብ ጋር በየወቅቱ ባለመመሳከሩ በሁለቱ መዝገቦች መካከል ልዩነቶች እንደሚያጋጥሙ፣
- በመዝገብ የተዘረዘሩት ንብረቶች በእውን መኖራቸውንና ተገቢው እንክብካቤ የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የቋሚ ንብረት ቆጠራ እንደማይደረግና የተደረገም ከሆነ ከመዝገቡ ጋር የማይገናዘብና ልዩነት ከተገኘም እንዲታረቅ የማይደረግ መሆኑ፣
- በውርስና በተለያዩ መንገድ ቋሚ ንብረቶች ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ሲዛወሩ በተገቢው መንገድ ርክክብ የማይካሄድና በሰነድ ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ንብረቶች በተረካቢውም ሆነ በአስረካቢው ድርጅት የሂሳብ መዝገብ ውስጥ በትክክል የማይመዘገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ለቋሚ ንብረቶቻቸው የገዙት የመድን ዋስትና በቂ ያልሆነና በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን ሌሎች ደግሞ ለንብረቶቻቸው የመድን ዋስትና ያልገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የንብረት መጥፋት የተከሰተ መሆኑ ለመረዳት ቢቻልም ንብረቱ የጠፋበት ምክንያት ተጣርቶ እንዲተካ እንደማይደረግ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በንብረት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርጉና የንብረት ሂሳባቸው ትክክለኛውን ሂሳብ ለማንጸባረቅ እንዲቻል አስፈላጊውን ሁሉ እንዲደረግ በየኦዲት ሪፖርቱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

5.2 <u>በመጋዘን ያሉ እቃዎች</u>

- በመጋዘን ያሉ እቃዎች (stock) በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ቆጠራ የማያደርጉ ወይም ከፊል ቆጠራ ብቻ ማድረጋቸውና ሌሎች ደግሞ ቆጠራ ቢያካሂዱም የቆጠራውን ውጤት ከሂሳብ መዝገቡ ጋር ተገናዝቦ ልዩነት ካለ አስፈላጊውን ማስተካከያ የማያደርጉ መሆኑ፤
- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን ያሉ እቃዎች እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት መቆጣጠሪያ መዛግብት (stock card) እንደማይዙ፤ ሌሎች ደግሞ አሟልተው የማይመዘግቡና የምዝባ ስህተቶች ልዩነት ሲያጋጥሟቸው ጉዳዩን ሳያጣሩ በተሰብሳቢ ወይም ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ የሚይዙ መሆኑ፣
- በብዙ ድርጅቶች ውስጥ በብልሽትና በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ሳይውሉ ለረዥም ጊዜ ተከማችተው የቆዩ እቃዎች መኖራቸውና በአንዳንድ ድርጅቶችም እነዚህ እቃዎች በዝርዝር ተመዝግበው ባለመያዛቸው ለእቃዎች መጠባበቂያ ተብሎ በመዝገብ የሚታየው ሂሳብ ትክክለኛነት ለመገመት የማይቻል መሆኑ፣
- ከሀገር ውጭ በሚገዙ እቃዎች እስከሚደርሱ ድረስ በጉዞ ላይ ያሉ እቃዎች በሚል ሂሳብ ውስጥ እስከ 6 ወር ያህል ጊዜ ብቻ መዝግቦ መቆየት የሚቻል ቢሆንም በበርካታ ድርጅቶች በጉዞ ላይ የሚገኙ እቃዎች ተብሎ ከሁለትና ከዚያ በላይ ዓመት የሚቆዩና አንዳንዶቹም በሰነድ ያልተደገፉ ሂሳቦች፤ የጠፉ ወይም የተበላሹ እቃዎች ከሆኑም በወቅቱ የመድን ካሳ ያልተጠየቀባቸው መሆኑ፣
- በእቃ ግመጃ ቤት ውስጥ ከረዥም ጊዜ በፊት አንዳንዱም ከውርስ ጊዜያቸው ጀምሮ በምርት ዕደት የነበሩ ወይም ለሌላ አገልግሎት ያልዋሉና በየጊዜው ምንም እንቅስቃሴ የማያሳዩ ለረዥም ጊዜ በመቆየታቸው የተነሳ ጥቅም ላይ ወይም በምርት ተግባር ስለማይውሉ እነዚህ ዓይነት ንብረቶች የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያዝላቸው ወይም ከሂሳብ መዝገብ ውስጥ እንዲቀነሱ የማይዳረግ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ የተገኙ ናቸው፡፡ በመሆኑም ድርጅቶቹ በክምችት እቃዎች ላይ የሚያደርጉት ቁጥጥር እንዲጠናከርና የታዩት ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ በየኦዲቱ ሪፖርት ማስገንዘቢያ ተሰጥቷል፡፡

5.3 <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- አብዛኞቹ ድርጅቶች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ሳይሰበስቡ ከዓመት ዓመት ስለሚያሸጋገሩ ተሰብሳቢው እየበዛና ጊዜው እየረዘመ በሄደ ቁጥር ባለእዳዎችን በውዴታ ወይም በሕጋዊ መንገድ ለማስከፈል ችግር መፍጠሩና ድርጅታቸው በውዝፍ ያሉትን ሂሳቦች ገቢ እንዲደረጉለት ተገቢውን ጥረት የማያደርጉ መሆኑ፣

- አንዳንድ ድርጅቶች ተሰብሳቢ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ከማን መሰብሰብ እንዳለባቸው የማይታወቁ መኖራቸው፤እንዲሁም ድርጅቶቹ የሂሳብ ግንኙነት ካላቸው መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የተሟላ አድራሻ ባለመያዛቸዉ በኦዲት ወቅት የተመረጡ ድርጅቶችን በዓመቱ መጨረሻ የነበረው ሂሳብ በቀጥታ ከድርጅቶች ለማጣራት /ማረጋገጫ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት አልተሳካም፣
- በብዙ ድርጅቶች ለሠራተኞች ብድርና የቅድሚያ ደመወዝ ብድር መስጠት የተለመደ ቢሆንም አንዳንድ ድርጅቶች ስለአወሳሰዱ፤ አፈቃቀዱና አሰባሰቡ መመሪያ የሌላቸው መመሪያ ያላቸውም ቢሆኑ በትክክል ስለማይተገበሩ ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ በሠራተኞች ስም በተሰብሳቢ ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ ብድር ያለባቸው ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ ወይም ወደሌላ ድርጅት ሲዛወሩ ያለባቸውን እዳ እንዲከፍሉ ወይም እንዲጣራ ስለማይደረግ ለረዥም ጊዜ የቆዩ የብድር ሂሳቦች ሲንከባለሉ የሚታዩ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለአንድ ባለእዳ ሁለትና ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሂሳብ ቋት ስለሚከፈት የሂሳቦች መመሰቃቀልና አለመስማማትን የሚያስከትል ሆኖ ይታያል፡፡

በመሆኑም በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ቁጥጥር እንዲጠናከር፣ ሊሰበሰቡ የሚችሉ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲሰበሰቡ ይህም ካልተቻለ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመመካከር ሂሳቡ እንዲሰረዝ በማድረግ ሂሳቦቹ ትክክለኛው የድርጅቱን የተሰብሳቢ ሂሳብ ገጽታ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ በኦዲቱ ሪፖርት አስተያየተ ተሰጥቷል፡፡

5.4 <u>በባንክና በካዝና ያለ ገንዘብ</u>

- አንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበስቡትን ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማያደርጉና ከዚህም ገንዘብ ላይ ክፍያዎች እንደሚፈጽሙ፤ በርካታ ድርጅቶች በባንክ ያላቸውን ሂሳብ በየወሩ ከባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ጋር በወቅቱ በማገናዘብ እንደማያስታርቁ ፤የባንክ መዝገባቸውና የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መካከል ልዩነት ቢያጋጥም እንኳ የልዩነቱን መንስኤ እንደማያጣሩና አንዳንዶችም ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው የባንክ ሂሳቦች ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ መኖሩ፣

- በርካታ ድርጅቶች በሂሳብ ዘመኑ መጨረሻ በካዝና የነበረውን ጥሬ ገንዘብ እንደማይቆጥሩ ቢቆጥሩም በዓመቱ መጨረሻ የሚደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከመዛግብቱ ጋር በማመሳከር ልዩነቱ ካለ እንደማያጣሩ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች በባንክ ያለውን ሂሳብ በትክክል ለመቆጣጠር ከባንክ የሚላከውን ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያና ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ከሂሳብ መዝገብ ጋር ማስታረቅና ልዩነቶችና ስሕተቶችን እንዲሁም አላግባብ ወጪ የሆኑ ሂሳቦች ሲኖሩ ወዲያውኑ ተከታትሎ አስፈላጊውን እርምጃ እንደወስድ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ተገልጾላቸዋል፡፡

5.5 ተከፋይ ሂሳቦች

- በርካታ ድርጅቶች ለመንግሥት መከፈል የሚገባቸውን ግዴታዎች ማለትም ከሰራተኞች ደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ ማዋጮ እንዲሁም የሽያጭና የንግድ ትርፍ የታክስ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው እንደማይከፍሉ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተካፋይ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩና ለማን መክፈል እንዳለባቸው የማይታወቁና ለረዥም ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩ የረዥም ጊዜ ብድሮች እንዳለባቸውና ከአበዳሪዎች ጋርም በየጊዜው የሂሳብ መግለጫዎች ስለማይለዋወጡ በኦዲት ወቅት ከአበዳሪዎች /ተከፋይ ድርጅቶች/ ማረጋገጫ በሚጠየቅበት ጊዜ መልስ የማይሰጡ ቢሰጡም ድርጅቶቹ አለን ከሚሉት ሂሳብ ጋር ከፍተኛ ልዩነት የሚታይ መሆኑ የሂሳቦቹን ትክክለኛነት አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች የተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ በየወቅቱ እንዲከፍሉ ትክክለኛነቱንም እንዲያጣሩ በተላከላቸው ሪፖርት ተገልጿል፡፡

5.6 ስለሂሳብና የሰነድ አያያዝ

- አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ቫውቸሮች በሂሣብ ሠራተኞች ከተዘጋጁ በኋላ ተገቢው የሥራ ኃላፊ ተመልክቶት ትክክለኛነታቸውን መርምሮ ሳያፀድቅ በሂሣብ መዝገብ እንደሚመዘገቡ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለሂሣብ ሠነዶች የሚያደርጉ ቁጥጥር እናሳ መሆኑና በማተሚያ ቤት ቁጥር ተሰጥቶአቸው የሚወጡ ሰነዶች እንቅስቃሴ እየተመዘገበ ቁጥጥር እንደማይደረግ፤ ከክፍያ ሠነዶች ጋር የተያያዙ የወጪ ደጋፊ ደረሰኞች

የተወራረዱ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ምልክት እንደማይደረግባቸውና በአንዳንድ ሒሣቦችም የአርዕሰት አመዘጋገብ ስህተት እንደሚታይ ታውቋል፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር የድርጅቶችን ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ፤ የሒሣብ ሠነዶችን በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት ስለማይቻል ፤ሠነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙና ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደማገባ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ሪፖርት ተልኳል፡፡

6. የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሄያቸው

6.1 የችግሮቹ ምክንያቶች

በሂሣብ አያያዝና ቁጥጥር ረገድ በሚታዩት ችግሮች ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከቱሉት ናቸው፡፡

- በብዙዎቹ ድርጅቶች ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋትና ካለም ተግባራዊ አለማድረግ፤
- አንዳንድ ድርጅቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት የማያስደርጉ መሆኑ/ዝርዝራቸው በአባሪ-34 ተመልክቷል/
- የድርጅቶች የበላይ ኃላፊዎችና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በውጭ ኦዲተሮች የሚሰጡ የእርምትና የማሻሻያ ሃሣቦች ላይ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ ናቸው፡፡

6.2 ችግሮቹን ለማቃለል ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃች

- የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በማንኛውም ድርጅት መዋቅርና የአሠራር ፕላን ውስጥ መዘርጋት ያለበት ሲሆን፣ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውንም የምዝበራና ብኩንነት ሁኔታ ከምንጩ በመከልከል፣
  - የድርጅቶች የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶችና መረጃዎች አስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥና የሥራ ቅልጥፍናና የውስጥ ጥራት እንዲኖር ለማድረግ፣
  - ማኔጅመንቱ የሚያውቃቸውና ከበላይ አካል የሚወጡ መመሪያዎች ሁሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ተበቢ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
  - በውስጥም ሆነ፤ ከውጪ ኦዲተሮች የሚሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦችን ተግባራዊ ማድረግና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችም አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡